ቅሌት

ከአንዳርጌ መስፍን

ነሐሴ 1986
አዲስ አበባ::

ስታሰር ጠያቂዬ፣ ስታመም አስታማሚዬ በመሆን ምንጊዜም ከጎኔ ለማትለየኝ እህቴ ለወይዘሪት ዐሀይቱ እማኙ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው::

ደራሲው

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው::
All Rights Reserved.

ነሐሴ 1986
አዲስ አበባ::

መግቢያ

ስለ ደርግ የሰቆቃ አገዛዝ አንድ መፅሃፍ መፃፍ እንዳለብኝ የተገነዘብኩት ለአራት አመታት በተለያዩ እስር ቤቶች አማቅቅ በነበረበት ወቅት ነው:: ጉግማንጉግ በሚል ርእስም እረቂቁን የነደፍኩት ከዚያው እስር ቤት እንዳለሁ ነበር:: ይሁን እንጂ ከእስር ቤት ከወጣሁ በኋላ ደርግ በህይወት እያለ እንደዚህ አይነት መፅሃፍ ማሳተም ስለማይቻል የደርግ ውድቀት እስከሚደርስ ድረስ ለአይኔ ትኩረትን፣ ለአእምሮዩ ጭንቀትን የሚፈጥሩትን እየመዘገብኩ ማስቀመጥ ያዝኩኝ::

ደርግ የፈለገውን ያህል ቢፎክርም በህዝቡ ዘንድ ከመወደድ ይልቅ መጣላትን፣ ከመከበር ይልቅ መዋረድንና መናቀን እያተረፈ መጣ:: የህዝብ ድጋፍና ፍቅር በማጣቱም ተንፈራጦ መቆየት አልቻለም:: እንዳንበሳ ባገሳባት አገር እንደ ውሻ ሙሆ በየአቅጣጫው ፈረጠጠ:: ከዚህ በኋላ ሁኔታዎች ሁሉ ግልብጥብጥ አሉ:: ጦሩም ፍርክስክሱ ወጣ:: ኢህአዴግም ባሸናፊነት አዲስ አበባ ገባ:: እኔም ለመፃፍ ያቀድኩትን መፅሃፍ ከደርግ አስከሬን ላይ ለመቋጨት ወሰንኩ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከም/መ/አ እስከ ኮሎኔል ማእረግ ድረስ ያላችሁ ጃንሜዳ ከቀድሞው 1ኛ/ጦር መምሪያ እንድትከቱ ተብሎ በሬዲዮ ጥሪ በመተላለፉ እኔም "የደርግ ማእረግተኛ" ስለነበርኩ አብሬ ከተትኩኝ:: ይህ አጋጣሚ አዳዲስ ክስተቶችን እንዳይ አረዳኝ:: ከጃንሜዳ ወደ ሆለታ መጋዛችን ደግሞ የበለጠ እድሉን አሰፋልኝ::

ገነት ጦር ት/ቤት ለወር ያህል ስንቆይ የብዙዎቹ መኮንኖች መዝረክረክና ክብር ማጣት "ለካ እንደዚህ ኖረናል?" ብዬ እራሴን እንድጠይቅ አስገደደኝ:: የሚኒስትሮቹና የጀኔራሎቹ እጅ አሰጣጥም ሀሊናዬን አቁስሎት ስለነበር በፊት እየፃፍኩ ካስቀመጥኩት ጋር እያይዤ ለመፃፍ ሳስብ የሚንዛዛብኝ መሰሉ ታየኝና የበፊቱን አዘግይቼና እራሱን አስችየ ወቅታዊ የሆነ መጽሀፍ ለመፃፍ ወሰንኩኝ:: የበለጠ ያነሳሳኝ ደግሞ ከሆለታ ወደ ጦላይ ተጋፈን መወሰዳችን ነበር::

ለሶስት ቀናት ለተሃድሶ ሴሚናር ተብለን ሆለታ ገብተን፣ ከዚያ ደግሞ ወደ ጦላይ ጠራርገው ከወሰዱን በኋላ የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር የተሃድሶ ትምህርቱን ያጓትቱት ጀመር:: በዚህ ጊዜ ውስጥ ግን በቋንቋ፣ በጎሳ፣ በጥቅም በመከፋፈል አንድነታችንን አሳጥተው ውሻ እንደገባበት የዝንጀሮ መንጋ በታተኑን:: ከዚህ በኋላ በያዳራሾቹ ይታዩ የነበሩት ትርኢቶች እጅግ አሳፋሪዎች ነበሩ:: ለዚህም ነው እያሌ ቅሌቶችን በማየቴ የመፅሃፌን ርእስ ቅሌት ብዬ የሰየምኩት::

በወቅቱ የፕሬስ ነፃነት ስላልነበር ይህን ሁሉ ካጠናቀኩ በኋላ አስተይቤ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ለቅድመ ምርመራ /ሳንሱር/ አቅርቤ ባጭር ጊዜ ውስጥ እንዲታተም ተፈቅዶልኝ ሳለ ማተሚያ ቤት ሳላስገባው በጠና በመታመሜ ምክንያት ስራው በመጓተቱ ስበሳጭ በሌሊት ከመኖሪያ ቤቴ ባፋኞች ታፈንኩኝ::

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ለረጅም ጊዜ እየፃፍኩ ያጠራቀምኳቸው አንድ ሳይቀሩ ተለቃቅመው፣ ይኸው ቅሌት እራሱ ከኔው ጋር ለእስር ተዳረጉ::

ከእስር ቤት እስር ቤት ስዘዋወር ቆይቼ ከ10 ወራት በኋላ እኔ ስፈታ ፅሁፎቼ ግን ከኔ የከፉ ወንጀለኞች ሆነውም እንደሆን አላውቅም

በዚያው ሰጥመው ቀሩ:: በተለይም ደም በደም የተሰኘው አረጅም ታሪካዊ ልብ ወለድ ፅሁፌ ምን ጊዜም ቢሆን የጎን ውጋት ሆኖብኝ ይኖራል:: ቀሪ ስለሌለኝ መልሽ ለመሻፍ አልቻልኩም:: የተወለደን ህፃን መልሶ እንደመፀነስ ይቆጠራል:: ይህን ችግር ደራሲዎች ብቻ ናቸው ሊፈርዱኝ የሚችሉ::

ለአሳሪዎቼ ከመፈታቴ በፊትም ሆነ ከተፈታሁ በኋላ ፅሁፎቼን እንዲመልሱልኝ በፅሁፍም፣ በቃልም በተደጋጋሚ አመልክቼ ሳይሳካልኝ ቀርቷል::

ቅሌትን ግን ከስር ቤት እንደወጣሁ ያለና የጠፋ ንብረቴን ሳፈላልግ አረቂቅ የነደፍኩበትን ካልባሌ ቦታ ተወሽቆ በማግኘቴ እንደገና ጀምሬ እነሆ ከግብ ላደርሰው ችያለሁ::

እንግዲህ ዋና ዓላማዬ አንዱን ከቤ ሌላውን ለማዋረድ ወይንም የሌለ ታሪክ ፅፌ ስም ለማጥፋት አይደለም:: ከኛ ውድቀት የነገው ትውልድ ትምህርት እንዲያገኝበት ማድረግ ነው:: በተለይም በወያኒዎች እጅ ላይ ከወደቅን በኋላ ለጥቂት ጊዜ እራሳችንን መቆጣጠር አቅቶን እጅግ አሳፋሪ ድርጊቶችን ሰርተናል:: በእርግጥ ቆፍጣና መኮንኖች የነበሩም ቢሆን አብዛኞቹ ተበሻቅጠው አበሻቅጠውናል:: አገሪቱም የሞተችው ግና ከማስዳው ሀላፊነት በጎደላቸው ወመኔዎች እጅ የወደቀች እለት ነበር::

በወያኔዎች ጸዝ ባይነት አጋላጭና ተጋላጭ ጠላይ ሲተናነቁ ማየት የሚያሳፍርም፣ የሚያሳዝንም፣ የሚያስቅም ነበር:: የበደለና የተበደለ ቢተናነቅ ባልከፋ ነበር:: የሚገርመው ግን ትንሹ ዘራፊና ትልቁ ዘራፊ ርስበርሳቸው ሲናከሱ ማየታችን ነው::

ታዲያ ትውልድ ከዚህ ውርደት ምን ይማራል?

እንግዲህ ወጣቱ ትውልድ ከዚህ ውርደት ምን ይማራል? መዘጋጀት አለበት:: በራሱ ተማምኖና ኮርቶ እንዲኖር ካሁኑ መዘጋጀት አለበት:: ኢትዮጵያንም እንደ ጥንቷ የከራችና የታፈረች አገር ልናደርጋት የምንችለው ኩሩ ወጣቶችን ማፍራት ስንችል ብቻ ነው:: ስለበለዚያ ሁልጊዜም ጦርነት፣ ሁልጊዜም የጎሳ ሆያ ሆዬ የትም አያደርሰንም:: ይህን ሆያሆዬ የሚሹት ከታሪካዊ ጠላቶቻችን የቤት ስራ ረሃብ ነው:: ይህን ሴራ ማምከን ያለበት ወጣቱ የተቀበሉ ብቻ መሆን አለባቸው:: ይህን ሴራ ማምከን ያለበት ወጣቱ ነው:: የዛሬውን ሳይሆን ነገና ከነገ ወዲያ የሚከተለውን መዘዝ በመረዳት በሆደ ሰፊነት መቋቋም አለበት:: አለበለዚያ ጎሰኞች ኢትዮጵያን ከማፈራረስ ወደኋላ አይሉም:: ተልእኳቸው ነውና!

በህይወት ቆይቼ ዛሬ በተረፈ በፈለኩበት ጊዜ ባይደርስልኝም በህይወት ቆይቼ ዛሬ ይህን ዘገባ በማድረሴ ከፍተኛ እፎይታ አግኝቻለሁ:: እንግዲህ ወደ ዋናው ፅሁፍ የምታደርስ ግጥም ጣል አድርጌ ልሰናበት::

> ግብሩንም፣ታክሱንም ሁሉን ሲምሩት
> አስራትን ብቻ ነው አንተውም ያሉት::
> ደራሲው

ምዕራፍ አንድ

> «ባህያ ቁርበት የተሰራ ቤት
> ብትንትን ያላል ጅብ የጮኸለት!»

1

አዲስ አበባና ዙሪያዋ በጭጋግ ተሸፍናለች:: የሰውም ፊት ጨፍግጓል:: መሽቶ የማነጋ፣ነግቶ በሰላም የሚውል፣ ተውሎ የሚታደር አይመስልም:: ሁሉም በደመነፍስ ወደየእለት ከስቡ ይንቀሳቀሳል:: ሰላምታ በቅጡ የሚለዋወጥ የለም:: ሁሉም በስጋት ተወጥሯል:: የድል አጥቢያ አርበኞች፣የቀበሌ ጀግኖች፣የኢሰፓ ጀሌዎች የት እንደገቡ አይታወቅም:: እምቦ ከተያዘች ወዲህ...

እለቱ ማክሰኞ ግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም. ነው:: በስድስት ሰአቱ ዜና ቆራጡና ብልሁ መሪያችን፣ ጓድ ፕሬዚዳንት መንግስቱ ሀይለማርያም:-«ለኢትዮጵያ ደህንነት ሲባል ከስልጣን ወርደው ወደ ውጭ አገር ሄደዋል::» ባንድ የመንግስት ቃል አቀባይ ተገለፀ::

አብዮታዊ መሪያችን:- «ከመሳሪያና ከሰው አንድ እስከሚቀረኝ ድረስ እዋጋለሁኝ!» እንዳላሉ ሁሉ ዛሬ ፈረጠጡ!!

ይህን ዜና ስሰማ አንድ ነገር ትዝ አለኝና ወዘ የሌለው ሳቅ ሳኩኝ:: ከሶስት አመት በፊት ዘመዶቼን ለመጠየቅ ወደ ትውልድ ቀበሌዬ ሄጄ ነበር:: ታዲያ ኑሮ ከመረራቸው አዛውንት እንደ ዘበት እንዲት ግጥም ሰምቼ ነበር:: ዛሬ እውን ሲሆን በጣም ገረመኝ:-

> «ፈረሱም ጓመረ፣ በሬውም አገሳ
> ሊሮጥ ነው መሰለኝ ይኸ አህያ ፈሳ!»

በማግስቱ ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩት ሌ/ጀኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ሆነው እንደሚሰሩ ተነገረ:: እርሳቸውም ከምሽቱ ሁለት ሰአት ለኢትዮጵያ ህዝብ የመማፀን ጥሪ አስተላለፉ:: እንዳልካቸው መኮንን፣ "ፋታ!" ብሎ እንደነበረ ሁሉ እኚህም በሰፈሩት ቁና የመሰፈር አይነት «...ታሪክ በትናንትናው እለት ሀላፊነት ስለጣለብኝ እንጅ ስልጣን ፈላጊ ሆኘ አይደለም:: ጊዜ ለመሻማትም አይደለም...» በማለት ወተወቱ:: በዚሁ እለት የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ማሰልጠኛ ጣቢያ እንዳሉ ላምስቱ ሀያላን መንግሥታት የመማፀን ጥሪ አስተላለፉ:: በእጅጉ አሳዘኑኝ:: ቆራጥ መሪ አለን ብለው ትምህርታቸውን አቋርጠው አገርን ካደጋ ለማዳን ፈጥነው ለመድረስ ነበር ጥሪታቸው :: ታዲያ ምን ይሆናል አብዮታዊ መሪያችን የውሃ ላይ ኩበት አድርገዋቸው ሄዱ:: ደግሞኮ እነሱን ላነጋግር ብለው ነው የሄዱት!

ግንቦት 15 ቀን ሀሙስ የሌኒን ሀውልት ተገነደሰ! በዚሁ እለት ባዲስ አበባ አናት ካራት ሰአት ጀምሮ ቀስተ ዳመና ቀለበት ሰርቶ ታየ::

ብዙ አባውንቶች የየግል ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል:: አንዳንዶቹ "ቀለበት ሰርቶ በባንዲራችን ተመስሎ የታየን አምላካችን ሲታረቀን ነው" ሲሉ ሌሎች ደግሞ "የጦርነት ምልክት ነው:: ባንዲራ ቀዳጅ ወራሪ መምጣቱን ማሳየቱ ነው" በማለት ተንበየዋል:: ይህ ሁሉ ሲሆን ሞት ባዲስ አበባ አናት ላይ ክንፉን ዘርግቶ ያነጋል! ዋጥ ስልቅጥ ለማድረግ:: የሲኦል በሮችም ተከፍተዋል:: በሀጢአት የጎደፉ ነፍሳትን ለማስተናገድ!

አርብ፣ ግንቦት 16 ቀን አዲስ አበባ እርሀብ በጎዳቸው፣ ውሃ ጥም ባቃጠላቸው፣ መሪ ባጡ ቅጠልያ ለባሾች ተጥለቀለቀች:: ወታደሮቹ አዲስ አበባ እንደ ገቡ ዘረፋ አላካሄዱም:: በስርአት አንዱ በሄደበት ሌላው በመከተል መስመር ይዘው ነው የሚጓዙት፣ የጦር ትጥቃቸውን ክርችም አድርገው እንደ ታጠቁ ናቸው:: መሪ ግን የላቸውም:: እስበሳቸው እየተማሩ ወደ ምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያና ወደ ማስተናገጃ ዋና ክፍል ይተማሉ፣ ምግብና ማረፊያ እንዲሰጣቸው ለመጠየቅ:: ተቀባይ ግን አላገኙም:: እነ ጓድ ጀኔራል የሉም:: በየሸርንቁላው አድፍጠዋል:: ለካም አገሬን እወዳለሁ ማለት በቀን ላይ ኖሯል:: ከዚያ ሁሉ የደርግ ጀኔራል አንድ እንኳን ቆራጥ አስተባባሪ ጠፋ:: ከዚህ በኋላ ወታደሮቹ የትም ተበተኑ::

ሰራዊቱ ፊታጅ አጥቶ የትም ሲባዝን ለከፋ ችግር እየተጋለጠ መጣ:: ሌላ ምርጫ አልነበረውም፣ የጦር መሳሪያውን ቸበቸበው:: ቢኬኤም ሙትረየሶች እስከነ እንግታቸው በቀላል ገንዘብ በነጋዴዎች እጅ ገቡ:: ክላሽ ጠመንጃዎች ባሮጌ ልብሶችና በእለት እንጀራ ተለወጡ:: ፕላስቲክ በምቦች እንደ ከረሚላ በህፃናት እጅ ተበተኑ::

ግንቦት 19 ቀን ሰኞ የክተት ጥሪው ተነሳ:: ይህ ሁሉ ሲሆን አዲስ አበባ ከተማ የሞት ጥላ እንደጣለባት ነበረች::

2

"አብዮታዊ" መሪያችን ወደ ውጭ አገር ከፈረጠጡበት እለት ጀምሮ አዲስ አበባ የመረጋጋት ሁኔታ አይታይባትም:: በተለይም ካስራ ሁለት ሰአት በኋላ አውራ ጎዳናዎች ጭር ይላሉ:: ተባራሪ እግረኞች ብቻ እየተገላመጡ ወደ ላይ ወደ ታች ይጣደፋሉ::

ከሀሙስ ወዲህ ተኩስ እንደ ቀለጠ ያድራል:: መትረየስ እንዳጓራ፣ የክላሽ ጥይት እንደ ፈንድሻ እንደተንጣጣ ይነጋል:: የሚገርመው ግን ጧት ሁሉም ያገኘውን ቀምሶ ወደየእለት ተግባሩ ይሰማራል:: ከነጋ በኋላ የተኩስ ድምፅ ሳይሰማ እረጭ ብሎ ይውላል:: ተኳሾቹ እነማን እንደ ሆኑ በውል ባይታወቅም ሁለት አይነት ግምቶች አሉ::

1ኛ. የጦሩ መሳሪያ በግለሰቦች እጅ ስለገባ ለመሞከር ነው የሚሉ ነበሩ::

2ኛ. ወያኔዎች ከጦሩ ጋር ተቀላቅለው በመግባት ሽብር ለመፍጠር ነው የሚሉም አልጠፉም::

በውጭው አለም ደግሞ አዲስ አበባ ዘጀም ባህር ልትዋጥ ነው እየተባለ ይሟረትባታል:: እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱትም ሞቃዲሾና ሞኖሮቢያ ናቸው:: ያዲስ አበባ ህዝብ ግን ሲነጋ ቁርሱን በልቶ ወደ መደበኛ ስራው ደፋ ቀና ይላል::

ሰኞን በምጥ ውለን ማታ በሁለት ሰአት ሌ/ጀኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን ጦሩ ትጥቁን እንዲፈታ ጥሪ ካስተላለፉ በኋላ ሌ/ጀኔራል ሀዲስ ተድላን፣ኮሎኔል ብርሃኑ ባይህንና አቶ ሀይሉ ይመኑን አስከትለው ጣሊያን ኤምባሲ የሙጥኝ አሉ:: ጦሩ ግን አመራር አጥቶ እረኛ እንደ ሌለው መንጋ የትም ተበትኖ ቀረ::

ምእራፍ ሁለት

«እንኳን አሁንና ሙሉ ትጥቅ እያለን፣
በጦር በጎራዴ ታንክ እንማርካለን!»

3

ሰኞ ሌሊት እንደ መሰንበቻው ሁሉ አዲስ አበባ በተኩስ ስትናወጥ ነው ያደረችው:: እንዳይነጋ የለም ጨለማው ተገፎ በብርሃን ተተካ:: እለቱም ማክሰኞ ቀኑ ግንቦት 20 ነው:: የማማ ልኬ ድምፅ እንደ ተኛሁ ይሰማኛል:: ከቤት እደጅ ወጣ ገባ እያሉ ነው የሚነጋገሩት::

"ኧረ እባክህ አምላኬ ሰላሙን ላክልን" እያሉ ይማፀናሉ:: የሰሞኑ ፀሎታቸው ይኸው ነው:: ከግንቦት 13 ቀን ወዲህ ክፉኛ ተሸብረዋል:: በርግጥ እሳቸው ብቻ አይደሉም፤ ጠቅላላ ያዲስ አበባ ህዝብ በሽብር ተውጧል::

እማማ ልኬ እኔ ተጠግቼ የምኖርባቸው አባውንት ናቸው:: ከርሳቸው ቤት ተከራይቼ ጣሊያን ሰፈር መኖር ከጀመርኩ ድፍን አራት አመታት አስቆጥሬአለሁ:: ተግባብተን እናትና ልጅ ሆነን እንኖራለን::

ከመኝታዬ ሳልነሳ ከራስጌዬ ያለውን ሬዲዮ ስከፍተው መደበኛ ፕሮግራሙን በማስተላለፍ ላይ ነው:: ከዜና በኋላም ከፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ ማስተላለፍ ቀጠለ:: ተረጋጋሁኝ:: ወያኔዎች ገብተው ያድራሉ የሚል ግምት ነበረኝ:: አቃቂ፣ ሰበታ፣ ሰንዳፋ፣ ጫንጮ፣ ሆለታ በአጠቃላይ ባዲስ አበባ ዙሪያ ባሉት ትንንሽ ከተሞች መግባታቸውን ገና በግዜ ሰምቼ ነበር:: ታዲያ እንዴት ዘገዩ? የሚያደናቅፋቸው ነገር እንኳን የለም:: ሁሉም ነገር ተመቻችቶላቸዋል:: ጦሩም ትጥቁን ፈቷል:: በዚህ ሀሳብ ላይ እየዋለልኩ እንዳለሁ:-

«የዘመናት ህዝባችን ብሶት የወለደው ጀግናው የኢህአዴግ ሰራዊት ደርግ ሲጠቀምበት የነበረውን ያዲስ አበባን ሬዲዮ ጣቢያ ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ተቆጣጥሮታል! ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም.» እየደጋገመ አስተጋባ:: በመገረም አይነት እንደ ተጋደምኩ ፈገግ አልኩኝ!

ልብሴን ለባብሼ ከመኝታ ቤቴ ብቅ ስል:- "የት ትሄድ ጎርፉ? ኧረ እርፈህ ተቀመጥ ልጅ" አሉኝ እማማ ልኬ:: ቀይ ድርፍዋማ ፊታቸው ተከፍቶ::

"ወጣ ብዬ አካባቢውን ልቃኘው እንጅ፤ መቸስ ተኘቼ አልውል" አልኳቸው::

"ምን የሚቃኝ ነገር አለ? ወያኔዎች ገብተዋል:: ሬዲዮ ጣቢያውን ሁሉ ይዘውታል" አሉኝ:: መልስ ሳልሰጣቸው ፊቴን ተጣጥቦ፣ ፀጉሬን እንደ ነገሩ አበጣጥሬ ከቤት ወጣ ስል ፀሀይዋ ሞቅ ብላለች:: እማማ ልኬ ከቤታቸው በር ቆመው እግድም ወደ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ሳልፍ አትኩረው ያዩኝ ነበር::

ወደ ዋናው ጎዳና የሚያዘልቀውን መንገድ ይዤ ብቅ ስል ከታች በኩል ህፃናት፣ወጣቶች፣ ሴቶች ሸትብ ወደ ሬዲዮ ጣቢያው ይጎርፋሉ:: ቤተመንግስት አካባቢ የቀለጠ ተኩስ ይሰማኛል እንጅ በተረፈ አዲስ አበባ በመጠኑ እረጭ ብላለች::

አቡነ ጴጥሮስ ሀውልት አካባቢ፣ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ያጥሩ ዙሪያና ማዘጋጃ ቤት በህዝብ ተከቧል:: ይኸ ሁሉ ግርግርና ትርምስ ወያኔዎችን ለማየት ነው:: እንዳንዶቹ በትግርኛ ያነጋግሯቸዋል:: የቀረው ደግሞ ከበ ለጉድ ያያቸዋል:: እነሱ ያለምንም ስጋት ግማሾቹ ቁጭ ብለዋል:: ግማሾቹ ደግሞ ጋደም ብለው በኩራት በአይኖቻቸው ወዲህና ወዲያ ይማትራሉ:: እየተዘዋወርኩ ደህና አድርጌ አጤንኳቸው:: መቅረፀ ድምፅና ፎቶ ማንሻ አለመያዜ እንጅ ጉብኝቴስ ልክ እንደ አንድ ጋዜጠኛ ነበር::

ፊታቸው በፀሀይና በቁር ተፍረግርጓል:: እንደ ማንኛውም የሰሜን ህዝብ መጣጣ ናቸው:: አብዛኞቹ ከሰውነታቸው ጥብቅ ያለች ቁምጣ ሱሪ ነው የታጠቁት:: ጎፈሪያቸው እውነትም ፋኖ አስመስሏቸዋል:: ጫማቸው በዘልማድ ኮንጎ ወይንም ሰንደል ጫማ እያልን የምንጠራው ነው:: ፎጣ ከራሳቸው ጠምጥመዋል:: ሌላ ቅራቅንቦ የላቸውም:: የነፍስ ወከፍ ቦምቦች በወገባቸው በኩረጆ ነገር ከተው ታጥቀዋል:: ካንዳንዶቹ በስተቀር ጉርድ ክላሽ ጠመንጃ ነው የያዙት::

የሴት ወታደሮችም አሉ:: መልክ የሚባል የላቸውም:: የወንድን ልጅ ቀልብ አይስቡም:: የሴት ወታደሮቹን ላይ ግን አንድ አይነት እልህ ተናነቀኝ:: አንደኛዋንማ ለጉድ ነበር አትኩሬ ያየኋት:: ብቻዋን ፈንጠር ብላ ተቀምጣለች:: እንደኔው ከበው በመቆም የሚያይዋት ብዙ ናቸው:: የድካም ምልክት ይታይባታል:: ክላሿን ትራስ አድርጋ በጀርባዋ ተጋደመች:: ከዚያ አገርግሬን የቆምነው ሳቅን::

"ምነው?" አለችን ፈገግ ብላ::

"ምንም" አልናት:: ከዚህ በኋላ ከዚያ ግድም አልተገኘሁም:: ወደ ቤቴ ተመለስኩ:: ሁኔታዎችን ሁሉ መለስ ብዬ ሳስባቸው ያንዘበዝቡኝ ጀመር:: ብቻየን እየተንከተከትኩ እስቃለሁ::

ሴቷ እንኳን ቆጭቷት ቀሚሷን አውልቃ ሱሪ ስትታጠቅ፣
የደርግ ጀኔራሎች ሱሪያቸውን ጥለው አደፈጡ እንደ ቆቅ!

እንጀቱ እርር ሲል የቋጨሁት ግጥም ነበር::
«በመራራው ትግላችን እናሸንፋለን!!» እንዲህ አድርጎም መራራ ትግል የለ!
አሁን በቅርቡ በኑዛዜ ቃላቸው «ህዝቡ ሲደማ እደማለሁ፤ ህዝቡ ሲቆስል እቆስላለሁ፤...» ብለው ነበር! ምን አይነት አታላይ ኖረዋል?

ላመል ያህል በሩን እንኳኩቼ ሹክክ ብዬ ስገባ እማማ ልኬ ከድብዳባቸው ላይ ቁጭ ብለው አቦል ቡና ብቻቸውን ይጠጣሉ:: ይኸው ናቸው:: ቡና ከጎረቤት ሴቶች ጋር መጠጣት አይወዱም:: «ትርፉ ሰው ማማት ነው» ይላሉ::

"የት ደርሰህ መጣህ?" አሉኝ:- ቡናቸውን ፉት እያሉ::

"ወያኔዎቹን አይቻቸው መጣሁ" አልኳቸው::

"ምን ይመስላሉ?" አሉኝ:-ወደኔ አንጋጠው እያዩ::

"ለነገሩማ የኛው ሰዎች ናቸው" ስላቸው:-

"እሰይ! እስቲ የኛው ሰዎች ያድርጋቸው" አሉ::

ወደ መኝታ ክፍሌ ገባሁና ጫማዬን አውልቄ ካልጋዬ ላይ በጀርባዬ ተንጋለልኩኝ:: በቃ ወደ ደጅ ሳልወጣ እንደ ተጋደምኩ ዋልኩ::

ሌሊት ደግሞ ያን እሮጌ ቤት ነፋሱ ያንቋቋው ጀመር:: የግንቦት ነፋስ ይኸው ነው:: እማማ ልኬ ግን የነፋሱ ብርታት ከፉኛ አስፈርቷቸዋል:: መብራቱን አስርዬ እያበሩ:-

"ኧረ ምንድን ነው መቶ አለቃ ጎርፉ?"

"ነፋስ ነው እማማ ልኬ! እርፈው ይተኙ::"

"የምን ነፋስ? ጣራ የሚደረምስ! ኧረ የሰው ኮቴ ይሰማኛል!"

"አይዞዎት ነፋስ ነው::"

"አይዞዎት ትለኛለህ እንዴ!" አጉተመተሙ:: ወዲያው ደግሞ ድመቶች በጣራው ላይ ድድድ...! ብለው እየተዛለሉ ሮጡ:: ተኩሱም ልክ እንደመሰንበቻው ይቀደዳል::

"ኧረው!" አሉ::

"ምነካዎ! እማማ ልኬ? ድመቶችኮ ናቸው!"

"ምነው ልኬ! 'ድመቶች' ትለኛለህ እንዴ! " ተቆጡ:: ድመቶቹ እንደገና በጣራው ላይ እየተሯሯጡ መጥተው 'ሚያው!' ብለው ድምፃቸውን ባያሰሙ ኖሮ እማማ ልኬ ኡኡታቸውን ይለቁት ነበር:: ዝም ብለው አዳመጧቸውና:-

"ቀልብ ገፋፊዎች!" አሉአቸው::

ለትንሽ ጊዜ ዝም ብለው ቆይተው፣ "መቶ አለቃ ጎርፉ! እንቅልፍ ወሰደህ እንዴ?" አሉኝ:: ደግሞኮ እስከ ዛሬ ድረስ በማእረጌ ጠርተውኝ አያውቁም:: በጭራሽ ሊያስተኙኝ አልቻሉም::

"ኧረ አልወሰደኝም" አልኳቸው::

"ተኩሱ ይሰማሀል?"

"ይሰማኛል::"

"ተገቡ በኋላ ደግሞ ምን አድርጉ ነው የሚሉን?" አሉኝ:: ዝም አልኳቸው:: እንቅልፍ ሳይወስዳቸው እንዲሁ አነጉ::

4

"አንተ ጎርፉ፤ምንድን ነው የቤቱን ጣሪያ ሲነቀንቀው ያደረው?" አሉኝ ጧት ከመኝታ ቤቴ ስወጣ::

"ነፋስ ነው እማማ ልኬ::"

"ነፋስ እንኳን አይደለም:: ደግሞስ ተገቡ በኋላ የምን ተኩስ ነው? እንደ ዶፍከ ነው ሲወርድ ያደረው::"

ቁርሴን በልቼ እንዳበቃሁ አክስቴን ለመጠየቅ ተነሳሁ:: አይናን ካየሁት ሰንበት ብያለሁ:: ደግሞ ዘመድም የሚጠየቀው በእንዲህ ያለ ወቅት ነው::

"ወዴት ልትሄድ ነው ልጄ አርፋችሁ ተቀመጡ እየተባለ::"

"በቅሎ ቤት ሄጄ አክስቴን እስቲ ልጠይቃት::"

"ወዳክስትህ ከሆነስ ደግ" አሉኝ::

ከሰፈሬ ወጥቼ ወደ ዋናው መንገድ ስገሰግስ አክስቴ ባለፈው "አብዮታዊ መሪያችን" የፈረጠጡ እለት ስልክ ደውላ እየሳቀች ያነጋገረችኝ ትዝ አለኝ::

"ሀሎ! አንተ፣ ጎርፉ..." እኔ መልስ እስከምሰጣት ድረስ እንኳን አልጠበቀችም:: እየተጣደፈች፣ "ሳልሳዊ ቴዎድሮስ ጉድ አድርጎን ፈረጠጠ አይደል!" የቁጭት ሳቅ ሳቀች::

"ምን ታደርጊዋለሽ:: እኔን ያሳዘኑኝ አሽቃባጮቹ ናቸው:: 'ብልሁ፣ አስተዋዩ፣ ቆራጡ መሪያችን!' እያሉ ሲወሸክቱ የነበሩት" አልኳት::

"ማሽቃበጥማ በዘመነ ደርግ ማን ያላሽቃበጠ አለ ብለህ ነው:: ሌላው ቢቀር ህይወትን ለማቆየት ሲባል፤ እንዲያው ግን አይገርምህም? እነጎሹን፣ እነዳዊትን ...ኧረ ስንቶቹን 'ከሀዲዎች! የኢፔሪያሊዝም ቅጥረኞች!' እያለ እንዳልወሸከተ ሁሉ ዛሬ እንዳህያ ውርንጭላ ጭራውን ሰቅሎ ይፈርጥጥ! ቅሌት! " ስትለኝ አንድ ተረት ትዝ አለኝና፡-

"እትየ ሰናይት፤ አንድ ተረት ልንገርሽ:: ይቅርታ ግን በስልክ ብዙ ቆየን" አልኳት ተረቱን መፈለግ አለመፈለጓን ለማረጋገጥ::

"ቁም ነገርም አይደል የምናወራው? በል ንገረኝ::"

"እይውልሽ፤ እንስሳት ሁሉ ተሰብስበው አለቃ እንምረጥ አሉና በድምፀ ማማር ተማርከው አህያን 'አንተ አለቃ ሁነን' ብለው መረጡት" ስላት፡-

"እሽ" አለችኝ ለመስማት በመጓጓት::

"ቡላ ሆዬ ባለቅነቱ እየተኩራራ ለጥቂት ጊዜ ደህና የሚያገለግል ሲመስልልሽ ጊዜ እንዴት እንዴት ያለው ኮርማ በሬ ያሽረግድለት ጀመር:: በይህ ጊዜ ቡላ የልብ ልብ ተሰማውና ኮርማውንም፣

ወይፈኑንም፣ ጥጃውንም፣ ጊደሩንም... እንዲያው ያገኘውን ሁሉ ትንሽ ትልቅ ሳይለይ በርግጫ እያፈረጠ ይጥለው ጀመር:: እንስሳቱ ሁሉ የሚያደርጉት ቢያጡ ከርግጫው ለመሸሽ ወደ ጫካ ገቡ:: ግማሾቹ ደግሞ እየተሰባበሩ ወደቁ:: የዚህ ጡር የተራበ ጅብ ከጫካ ብቅ ይልልሻል::"

"እሰይ! በዘረገፈው!" አለች::

"ቡላ ሆዬ የጅቡን ድምፅ ሲሰማ ፈሱን እንዛርጦ እግሬ አውጭኝ ይላል!" ስላት ሳታቋርጥ ሳቅ ፍንቅል አደረጋት:: ፀጥ ብዬ ሳቋን እስክትጨርስ ድረስ የስልኩን እጀታ ከጆሮየ ለግቼ ጠበኳት::

"ሀሎ! አንተ! ይዝጋህና! ምነው ይህን የመሰለ ተረት አስከዛሬ ሳታጫውተኝ?" አለችኝ::

"በምን እስታውሽ ልንገርሽ? መንስኤ መኖር አለበት:: 'ቴዎድሮስ ነኝ፤ ያንበሳው ክፍለ ጦር አባል ነኝ' እያለ ይደነፋል! አሽቃባጮች ተቀብለው 'ቆራጡ መሪያችን' እያሉ ሰማይ ላይ ሲሰቅሉት ልቡ በእብሪት አብጦ፡- 'አድሃሪያንን ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮንም በቁጥጥራችን ስር እናደርጋለን!' እያለ ሌት ከቀን ደነፋ:: ተፈጥሮም በድርቅ እንገርግባ በቁጥጥሯ ስር አደረገችን:: አድሃሪያን የሚላቸውም ይዘውና አስፈረጠጡት!"

"አፈር ይብላና! ምናለ ጀኔራሎቹን ይዞ አልሆንለት ቢል እንኳን እንደ ቲያድባሬ ባገሩ ጫካ ገብቶ ትንሽ ቢያደፍጥ? ወይንም እንደ ሳሙኤል ዶ ከታማኝ ወታደሮቹ ጋር ሆኖ የክብር ሞት ቢሞት:: ብስብስ!" አለችው::

"ይህን ሁሉ ማድረግ የሚቻለው አእምሮ ሲኖር ነው:: ደርጎች ደግሞ ለዚህ የታደሉ አይደሉም:: እንሳሳቸው አስገራሚ እንደ ሆነ ሁሉ አወዳደቃቸውም አስቂኝ ነው:: 'ጀኔራሎቹን ይዞ' ብትይኝ አንድ ነገር ትዝ አለኝ:: እየውልሽ፤ እኔ ምክትል መቶ አለቃ ሳለሁ አስር አለቃ የነበሩ ሁለት የደርግ አባላት ዛሬ ለጀኔራልነት ማእረግ በቅተዋል:: የሚገርምሽ ደግሞ ሁለቱም በአዋሳ በኩል ሲፈረጥጡ አንዱ ተገደለ፤ ሁለተኛው በፀና ቆስሎ ተያዘ:: ታዲያ ከነዚህ ጋር ቢሸፍት ምን ሊፈይድ? ያው የገበሬ ቤት ያቃጥሉና ይዘርፉ እንደሆን እንጅ::"

"እሱስ እውነትክን ነው፤ የገበሬ ቤት ከመዝረፍ አያልፉም:: ለነገሩማ ከትግራይ ተነስተው ከዚህ እስከሚደርሱ ድረስ እሱ ሚኒስትሮቹን ይዞ በምእራብ ኢትዮጵያ ወርቅ ይሰበስብ አልነበረም?"

"በይ እትዬ ሰናይት! ሲመቸኝ ብቅ እላለሁ" ብያት ነበር በስልክ የተለያየነው::

አክስቴ ያኔ በስልክ ያለችኝን እያሰላሰልኩ ቸርችል ጎዳና በመግባት ቁልቁል ተዳፋሁ:: መኪና የሚባል ነገር ጨርሶ የለም:: ለካም አዲስ አበባን የሚያደምቃት መኪና ኖሯል:: ጎዳናው ጭር ብሏል:: እግረኞች ብቻ ወደላይ ወደታች በርጋታ ይንቀሳቀሳሉ::

ቴዎድሮስ አደባባይ ስደርስ ከኋላዬ መንጋ በቅሎ እየተንጋጋ ደረሰብኝ:: ህፃናት፣ ወጣቶች ከኋላ እየተከተሉ እንደ ብርቅና ድንቅ ያዩዋቸዋል:: ወደ ዳር ወጣ ብዬ አስቀደምኳቸው:: ባልቆጥራቸውም ወደ ሰባና ሰማኒያ ይጠጋሉ::

"ወይ ቸርችል ጎዳና! ዲኤክስና ማርቸዲስ መኪና እንዳልተርመሰመሰብሽ ሁሉ ዛሬ በቅሎ ፋንድያውን እያንጠባጠበ ይንጋጋብሽ ጀመር" አልኩኝ በመገረም::

ልጆቹ እየተንጫጩ ይከተሏቸዋል:: ሁለት የኢህአዲግ ወታደሮች ይነዷቸዋል:: እነሱም መሳሪያ በመያዛቸው እንጂ እረኞች ናቸው:: በመንገድና በጭንት ስለተንገላቱ የብዙዎቹ ጀርባ ተገጥጧል:: ግራና ቀኝ በጎዳናው ዳር ዳር ያለው ህዝብ እነሱን እያየ ይስቃል:: ያንዳንዶቹ ሳቅ ግን «ማሽላ ሲያር ይስቃል» የሚባለው አይነት ነው:: አንድ አዛውንት ያሉት ግን ምንጊዜም አይረሳኝም:-

"እነዚህ ናቸው የመንግሥቱ ሀይለማርያምን ታንክና መድፍ አንጋግተው ካገር ያሰፈረጠጡት? ትፍ! " ብለው በቁጣ እየተፈናጠሩ አቆልቁለው ሄዱ:: እኔም እየተወራጨሁ ተከተልኳቸው::

ለካም ጨዋታም የሚጥመው አገር ሰላም ሲሆን ነው:: ካክስቴ ጋር ይህን ያህል የጣመ ጨዋታ አልተጫወትንም:: ብናነሳው፣ ብንጥለው ያው ስለ ጦሩ መፈረካከስና ስለ "አብዮታዊ መሪያችን" መፈርጠጥ ነው::

"ይገርምሀል! ለካ ደርግ ውስጡ ባዶ ኖሯል? ያለነገር ምላስ አላበዛም" አለችኝ::

"ለባዶነቱማ ምን አንድና ሁለት አለው:: እውቅ ጀኔራሎችን አርዶ ጨርሶ ጦሩን ያለመሪ አስቀርቶ የንቧይ ካብ ሲክብ ኖሮ ባንድ ጊዜ ሲናድ እግሬ አውጭኝ አለ::"

"ኧረ አንዳንድ ጊዜስ እነዚህ ወያኔዎች ደግ አደረጉ:: ይህ ቅርንጢጥ! ጥግብ ብሎብን ነበር::"

"እረስቼ ሳልነግርሽ፤ ቅድም ወዳንቾ ስመጣ መንጋ በቅሎዎች አይቼ ስስቅ ነበር::"

"የምን በቅሎዎች ናቸው?"

"የወያኔ በቅሎዎች ናቸው:: ስንቃቸውንና መሳሪያቸውን ጭነው ያመጡባቸው::"

"እንተ ሆየ፤ ታንኩን፣ መድፉን፣ ጀቱን ይዛችሁ በበቅሎ በተጫነ መሳሪያ ነው የተሸነፋችሁት? ወታደሮቹንም አየኋቸው፤ ከዚህ ታች ከባንኩ ሲጠብቁ:: ጭብጥ ያሉና ርሃብ የጎዳቸው ናቸው:: ፀጉራቸው ብቻ የተንጨፈረረ:: እንዲያው ያ-ዘብጣጣ ዘብጣጣ የደርግ ወታደር ሁሉ የት ደረሰ?" ስትል በመገረም ጠየቀችኝ::

"አሁንኮ ተናግረሽዋል እትዬ ሰናይት:: ደርግ ባዶ ጉራ ወናፍ ነው! ጦሩን ማን ይምራው? ሰውኮ የለም:: ስዎቹን ቀደም አድርገው ጨርሰዋቸዋል::"

"አዎን ልጄ፤ አርደው ጨርሰዋቸዋል" አለችኝ:- አንገቷን በሀዘን ዘንበል አድርጋ::"

የሚጥመን ባናገኝም ካክስቴ ጋር ስንጫወት ውለን ወደ ማታ ቤቴ ተመለስኩ:: አሁንም መኪና አልነበረም:: ጥሩ እስፖርት ነው:: ከበቅሎ ቤት ጣሊያን ሰፈር ድረስ በግር ደርሶ መልስ፤ እቀበቱን ተጋተርኩት...

5

«ግርም ያደርገኛል የኢትዮጵያ ሁኔታ፣
አሳሪ ሲታሰር ታሳሪው ሲፈታ፣
ከትከት ብላ ሳቀች አለም ጥርስ አውጥታ!»

ብሎ ነበር አንድ አቅራሪ በ66 ዓ.ም. የሀይለስላሴ ባለስልጣኖች ተጋፊው ሲታሰሩና ያላግባብ የታሰሩት ደግሞ ሲፈቱ:: ባስራ ሰባተኛ አመቷ ደግሞ ታሪክ እራሷን ደገመች:: የደርግ ባለስልጣኖችም እየተለቀሙ ይታሰሩ ጀመር::

የኢሰፓ የፖሊት ቢሮ አባልና የትግራይ እራስ ገዝ አስተዳዳሪ የነበረው ጓድ ሻምበል ለገሰ አስፋው ለሁለተኛ ጊዜ ተያዘ:: ሻምበል ለገሰ አስፋው ለብዙ ንፁህን ደም መፍሰስና ለበርካታ ምሁራን መሰደድ ምክንያት የሆነ ግለሰብ ነበር:: ለኢትዮጵያ ውድቀትም አንዱና ዋናው ተጠያቂ ሰው ነው:: ሌላው ቢቀር እንኳን ትግራይን ባይሾምና ፈርጥጦ ባይመጣ ኖሮ የዛሬው መፈረካከስ ባልደረሰ ነበር:: የውሻ ደም የማያስቀረው እምላክ ወገቡን እንደ ተመታ እባብ አጥመልምሎ አጥመልምሎ ከወያኔዎች እጅ ላይ ጣለው::

«ጓድ ሻምበል ለገሰ አስፋው» በመጀመሪያ ኢህአዲግ አዲስ አበባ ከመግባቱ በፊት በሰበታ በኩል ሊሾልክ ሲል የ14ኛ ክፍለ ጦር ባልደረቦች ናቸው የያዙት:: ከዚያ ወደ ማእከላዊ እስር ቤት ተወስዶ ይታጎራል:: ኢህአዲግ አዲስ አበባ ሲገባ ደግሞ እንደማንኛውም እስረኛ ይለቀቃል:: ለጌ ሆዬ ወደ ዮሃንስ አካባቢ እንደ ሰባራ እህያ ሲጥመለመል ከወያኔዎች እጅ ይገባል:: እያጣደፉ በመውሰድ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ከበሩ ላይ ገትረውት ዋሉ፤ ህዝቡ እንዲያየው:: በርግጥም መሳለቂያ ሆኖ ዋለ:: 'የሞተ ሰው ምንፈቀደኝ!' ያሰኛል:: በፍዋለለባት አገር፣በፈነጨባት ከተማ እንደዝንጀሮ ቡጫሌ ተቆጥሮ የህፃናት መጫወቻ፣ያዛውንቶች መዘባበቻ ሆነ::

ጓድ ለገሰ አስፋው ትግራይን የተሾመ እለት ህዝቡ ጉድ ብሎ ስለነበር እኔም አንዱ ጉድ ባይ ነበርኩና በወቅቱ አንዲት ግጥም ቋጥሬለት ነበር:-

ቢፈለግ ቢፈለግ ሰው ጠፍቶ ካገር፣
ለገሰ ተሾመ በትግራይ ምድር፣
አየ ትህትና አየ ቁምነገር፣
እስረክቦ መጣ ሳይውል ሳያድር::
ምን ጊዜ አርጦ ምን ጊዜ ደረሰ?
ለጌ ባይሆን ኖሮ ልቡ በፈረሰ::

ማታ ደግሞ በሬዲዮ ጀኔራሎችና ሚኒስትሮች ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ድረስ እየሄዱ እጃቸውን እንዲሰጡ ጥሪ ተላለፈ:: ጧት ቁርሴን በልቸ እየገሰገስኩ የሄድኩት ወደ ተጠቀሰው ቦታ ነበር:: እጃቸውን እንዴት እንደሚሰጡ ለማየት::

አምባሳደር ቲያትር ግንቡን ተደግፌ በመቆም ትኩረቴን ወደ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ግቢ አደረኩኝ:: ያ ሁሉ ጀኔራል ከያደፈጠበት በመውጣት እጁን ይሰጥ ጀመር:: ደግሞኮ ፈገግ ለማለት ይሞክራሉ::

ኧረ አንዳንዶቹስ ይስቃሉ:: ኢህአዲጎቹን ለማግባባት ይሁን ወይንም ጠላትን ደስ አይበለው፣ ወዳጅን አይከፋው ብለው ከቶ አልገባኝም::

ዝግባ ዝግባ የሚያክል ጀኔራል፣ እንደ ጠጅ በርሚል የተንዘረጠጠ የሲቪል ሚኒስቴር ቂጥ ለቂጥ ተጋፋ:: ህዝቡ ከቦ እያየ ይስቃል:: እኔም በዋናው በር በኩል ጠጋ ብዬ እያቸው ጀመር:: እንደ ገለባ ቀለሉብኝ:: ጨርሰው ላይኔ ሚዛን አልሞላ አሉ:: ኢህአዲጎቹም በንቀት ነበር የሚያዩዋቸው::

በ66 ዓ.ም. አብዮቱ የፈነዳ ጊዜ:-

«ጥይት ሳይተኮስ ቦምብ ሳይፈነዳ፣
ያ ሁሉ መኳንንት እንደ በግ ተነዳ!»

ተብሎ ነበር:: ዛሬ ያ ቁና ተደገመ:-

ኢህአዲግ ቢመጣ ባምቦ በኩል ቆርጦ፣
መንግስቱ እሮጠ በኬንያ አቋርጦ::
የደርግ ጀኔራሎች እነ አውሎ ነፋሱ፣
እጅ ስጡ ሲባል ከያደፈጡበት ተንጋግተው ደረሱ::
ለካ ለዚህ ኖሯል ያ ሁሉ ድንፋታ ያ ሁሉ ጨኸት፣
እንዲህ ሆኖ ቀረ የደርግ ወንድነት::
ደህና ደህናው ሱሪ የትም ተጣለና፣
ገመናችን ታየ ቀዳዳው ቀረና::

ከዚያ ቁሜ እነሱን መመልከቱ ሲያስጠላኝ ጊዜ ሽቅብ በፖስታ ቤት ሳቀና ከኋላዬ:-

"መቶ አለቃ ጎርፉ" የሚል የጥሪ ድምፅ ሰማሁና ዘወር ብዬ ሳይ የመስሪያ ቤቴ ባልደረባ አምሳ አለቃ እንዳለው ነው:: የፖለቲካ ሰራተኛ ነበር:: ዛሬን አያድርገውና መሬቷን ለመርገጥ ይጠየፋት ነበር:: ቆም ብዬ ጠበኩት::

"ታዲያስ፤ ደህና ነህ" አልኩት ካጠገቤ ደርሶ እጅ ለጅ ስንጨባበጥ::

"ምን ደህንነት አለ በቁማችን ሙተን:: አየሃቸው አይደል የኛን ጀኔራሎች?" አለኝ:- እንደ መብሸቅ ብሎ::

"አየኋቸው:: እድሜ ለናንተ" አልኩት ኮስተር ብዬ::

"እንዴት ማለት? እኛ እነማነን?" ሲል ጠየቀኝ::

"ኢሰፓዎች ናችኋ! ምድረ ዱማ ተሰብስባችሁ ለሽንፈት ያበቃችሁን! ያለ ሆድ ተዝካር በስተቀር ሌላ ነገር አታውቁ! በየቀኑ ስብሰባ እያላችሁ እጃችንን አስጨበጣችሁን!" አልኩት::

"ታዲያ ይህንን ሀሳብህን ለምን ቀደም ብለህ አታቀርብም ነበር?" አለኝ፣ እንደመየቀም ብሎ::

"ያኔማ ባቀርብ ቆራርጣችሁ ትበሉኝ ነበር:: ያቀረቡትስ የታሉና:: እኔም ብሆን የስርን ፅዋ ቀምሽ ነው የወጣሁት:: ለመሆኑ ዛሬን አያድርገውና ደርጎችና ኢሰፖዎች የሰው ምክር ትቀበሉ ነበር? በእብሪት ተወጥራችሁ!" የጀኔራሎቹን ቁጭት ተወጣሁበት::

"ለመሆኑ በምን እንደ ተሸነፍን አውቀሀል?" አለኝ::

"ደግሞ በምን ተሸነፍን ልትሉ ይሆን?"

"ባስማት ነው:: ከሱዳን በመጣ አስማት ነው የተሸነፍነው" ሲለኝ ከት ብዬ ሳኩኝ:: የብሽቀት ሳቅ::

"ምን ያስቅሀል? ህዝቡ እያወራ ያለው ነው::"

ለምን የሊቢያ አስማት ሳይጨመር ቀረ ብዬኮ ነው የሳኩተ:: ወናፎች! ደግሞ ብላችሁ በሱዳን አስማት አመካኛችሁ? ሱዳን እንደዚህ ያለ ጥበብ ካላት ለምን የራሷን ችግር አልፈታችም ነበር?"

"እሽ ተወው:: እውነቱን ማወቅ ከፈለክ ግን ሄደህ ማየት ትችላለህ" አለኝ ቀዝቀዝ ብሎ::

"ምኑን ነው የማየው?"

"አስማት የተደረገባቸውን"

"ምንድን ናቸው እነሱ?"

"አንዲት ነጭ ቀበሮና አንዲት ነጭ ድመት ናቸው:: መዘጋጃ ቤት አስቀምጠዋቸው እየተጠበቁ ህዝቡ ለጉድ ያያቸዋል" ሲለኝ ምራቁን በብሽቀት ተፋሁና:-

"ይልቅ ቀበሮዎቹና ድመቶቹ እኛ ነን ብትለኝ አምንህ ነበር!" አልኩትና እንደ እልህ ስለተናነቀኝ፣ "በል ያየኸውን ውሰድና አሳየኝ" ስለው:-

"በቻህንም ቢሆን ማየት ትችላለህ:: እኔ ከዚህ ተረት ሰፈር ከጓደኛየ ጋ ቀጠሮ ስላለብኝ አቸኩላለሁ" አለኝ:- ቆም ብሎ ሰአቱን እያየ:: በዚህ ወቅት ቴዎድሮስ አደባባይ ከፌርማታው አጠገብ ደርሰን ነበር::

"ከጓደኛህ ቀጠሮ ስትመለስ ትደርስበታለህ:: ሳታሳየኝ አትሄድም:: አለበለዚያ ለኢህአዲጎች ነው ጠቋሚ የማሲዝህ" ስል አስቦካሁት:: ካደባባዩ አጠገብ ዙ23 አየር መቃወሚያ አጥምደው ይጠብቃሉ:: ከመቅዐቡት ላብ በግንባሩ ችፍፍ አለ::

"እንዴ! ምን ማለትህ ነው መቶ አለቃ ጎርፉ፤ ምን አደረኩህ? ከምርህ ነው እንዴ?" አለኝ:- እንደ መማፀን እያለ::

"ከምሬ ነው:: ዛሬ ዋሽተህብኝ አትሄድም! እስከ ዛሬ የተቀደዳችሁት ይበቃል!" አልኩት አሁንም ኮስተር ብዬ::

"ዳግመኛ አይለመደኝም:: የዛሬን አውጣኝ" አለኝ ወደ እግሬ ስር እየጎነበሰ:: እንዲህ ሲሆን ደግሞ አሳዘነኝ::

"አስኮናኝ:: ሁለተኛ ውሸትን ፈጥሮ ማውራት እንዳይለምድህ:: በል ሂድ" ስለው ፈትለክ አለ::

ከአምሳ አለቃ እንዳለው እንደ ተለየሁ በቀጥታ የሄድኩት ወደ ማዘጋጃ ቤት ነበር:: በዋናው በር በኩል ስደርስ ህዝቡ ከቦ ወደ ውስጥ ያያል:: ኢህአዲጎቹ በግቢው ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ:: በታች በኩል ደግሞ ካትክልቱ ስር ሁለት ኢህአዲጎች ገልበው ይፀዳዳሉ:: ንቀት ይሁን አውቀት ማነስ እንጃ:: የሚያያቸው ሰው ሁሉ ይስቃል::

ሰው ወደ ውስጥ እንዳይገባ ከበሩ ሁለት ኢህአዲጎች ቁመው ይከላከላሉ:: ነጭዋን ቀበሮና ድመት ለማየት ወደ ውስጥ ባተኩር ከኢህአዲጎቹ በስተቀር የሚታየኝ ነገር የለም:: ምናልባት ነጭ ቀበሮና ድመት ያለኝ አምሳ አለቃ እንዳለው ኢህአዲጎቹን ይሆን እንዴ? እውነትም ሰው ከቦ የሚያየው እነሱኑ ነው:: እየሳኩኝ ወደ ቤቴ ሄድኩ::

አየ ቀበሮና ድመት! የደርግን ሰራዊት ብትንትን አደረጉት!

6

በማግስቱ ግንቦት 23 ቀን ነበር፤ ያን እለት የሄድኩት ወደ መርካቶ አቅጣጫ ነበር። "አብዮታዊ ጦራችን" በየመንገዱ ዳር ፈሶ ይለምናል። እጃቸውን፣እግራቸውን የተቆረጡ ሁሉ አሉ። በተለይ አውቶቢስ መናኸሪያ የግር መንቀሳቀሻ የለም። ደክሟቸው የወደቁ፣ ርሃብ የረታቸው በየጥጋጥጉ ወድቀዋል።ትኩስ ቁስለኞች ተዘርግተው ያቃስታሉ። መናገር ያቃታቸው አፋቸውን ገጥመው አይኖቻቸው ብቻ ይቅበዘበዛሉ። ሳንቲም በመሻት። አንዳንዶቹ ደግሞ ቅራቅንቧቸውን ይዘው እየተማሩ የሚሄዱበትን ሳያውቁት ወደ አገኙበት አቅጣጫ ይንከላወሳሉ። ሁሉም ግን ደክመዋል። ጨርሶ ተስፋ የላቸውም። ሞራላቸው ሙቷል።

"ላገራችን መግቢያ" ልመናቸው ይኸው ነው። ህዝቡ የተቻለውን ያህል ይሰጣቸዋል። ደረታቸውን የሚደቁ ብዙዎች ናቸው። የሚያለቅሱ ሁሉ አሉ። «ነፃ አውጪው ሰራዊታችን...» እየተባለ ሲነገርለት የነበረው ሰራዊት እራሱን እንኳን ነፃ ሳያወጣ ለልመና ተዳረገ። እንዲህ ሆኖ ሳየው አእምሮየን ጭንቅ ጭንቅ አለኝ። ያለኝ ምርጫ ከዚያ ግድም መጥፋት ነው።

በባንኩ በኩል አድርጌ ቁልቁል ባመዴ ገበያ ተዳፋሁ። እንደ መናኸሪያው አይትረፍረፉ እንጂ በዚያም ተልከስክሰዋል። ወጭ ወራጁን ደፈር ያሉት "ላገራችን መግቢያ" ይላሉ። ጥግ ይዘው በመቀመጥ የሚለምኑም አሉ። እኔምኮ የሚጠብቀኝ የነሱው እድል ነው። አንጀቴን በሉኝ። ግን ምን ላድርጋቸው?

ላገር መግቢያ እያለ ሲለምን እያየሁ፣
ዝም ብየው አለፍኩኝ አይቼ እንዳላየሁ፣
እኔምኮ እንደሱ እጃጠር ሁኛለሁ።

ወዴት እንደምሄድ ባላውቅም ስራመድ እየተጣደፍኩ ነው። በምሄድበት ሁሉ ሰራዊት አላጣም። የትም ተረጭተዋል። በራስ ቲያትር አድርጌ ቁልቁል ወደ ሰንጋ ተራ የሚያዘልቀውን ጎዳና ይዤ እፈናጠር ጀመር።

ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ስደርስ ወደ ግራዬ አጠፍ ብዬ ቁልቁል ወደ ዋናው ጎዳና የሚያዘልቀውን መንገድ ያዝኩኝ። አሁንም ስራመድ ልክ ቀጠሮው እንዳለፈበት ሰው ሆኘ ነው። ወደ ትግላችን ሀውልት ገሰገስኩ። ህዝቡ ከቦ ያያል። እረማመዴ ግርምድምድ አድርጌ የማፈርሰው እመስላለሁ። ፊቴ ተኮሳትሯል። ደረጃዎቹን ጡብ ጡብ እያልኩ ወጥቼ አይኖቼ በመጀመሪያ ያረፉት 24 ሰአት ከሚነደው እሳት ላይ ነበር። ጠፍቷል። እንኳንም እልም አለ! አብሪተኞቹም እልም ብለዋል! በንዴት የተቀጣጠለ ሰውነቴ በረድ ሲልልኝ ታወቀኝ። ቀዝቀዝ አልኩ። "ሰደድ" ነበር። እርጥብ ከደረቅ የማይለይ የኢሰፓዎች ምድጃ!

ወደ ሀውልቱ ብዙም ሳልጠጋ ልክ ከዚያ በፊት እንደ ማላውቀው ሁሉ ከቂጡ እስከራሱ ማስተዋል ጀመርኩኝ። በርግጥም

ከዚያ በፊት መኖሩን እንጂ አስተውየ አይቸው አላውቅም ነበር። ያዲስ አበባ ህዝብ ባንድ ወቅት ያለው ትዝ አለኝ።

"የደርግ ጀላ!" እያለ ነበር የሚጠራው። እውነትም "አብዮታዊ መሪያችን" እንደዚት ያለ ስራ ሰርተው ሄዱ!!

"እርግጠኛ ነኝ፤ ይህን ሀውልት ያለዛሬ አይተኸው አታውቅም" የሚል የሴት ድምፅ ሰማሁ። መለስ ስል የኔነሽ አሰፋ ነች። ፈገግታዋ አስቀድሞ ሰላምታ ሰጠኝ። እኔም ልክ ከደመና ውስጥ ድንገት ብቅ እንደምትል ፀሀይ ፈገግ አልኩኝ።

"ልክ ነሽ፤ አልተሳሳትሽም" ብያት ለመሳሳም ተቃቀፍን። የሽቶዋ መአዛ እውድ አደረገኝ። ባንድ ወቅት የኔነሽ የኔ ነበረች። በፍቅር አክንፋኛለች።

"ከዚህ ጎላ ሚካኤል አክስቴን ጠይቄ በዚህ ሳልፍ ህዝቡ ተሰብስቦ ሳይ ጊዜ እንደ ሌኒን ሀውልት እየናደው መስሎኝ ቀና ስል አንተን አየሁህ። የኔ ጎርፍ ለመሆኑ ደህና ነህ?" አለችኝ ተሳስመን ስናበቃ።

"ደህና ነኝ። እኔማ ምን እሆን ብለሽኝ" አልኳት ልክ የናቱን ሞት የተረዳ ያህል ሆኜ።ፈገግታዬ ጭልም እያለ።

"እረ እንኳን ደህና ሆንክቴ። እኔስ አስቤልህ ነበር።"

"እውነት?" አልኳት፣ አታስቢልኝም በሚል አይነት ጥያቄ።

"እንዴት? አታስቢልኝም ማለትህ ነው?"

"ከተያየን ብዙ ጊዜያችን ስለሆነ አታስታውሽኝም ብዬ እንጅ እንደምታስቢልኝ እንኳን አውቃለሁ።"

"ምንስ ቢሆን የጨረቃ ጉዞው ይረሳል" ስትል የሩቅ ጊዜ ትዝታ ቀሰቀሰችብኝ።

"ምላጭ!" አልኳት እኔም ፈገግ ብዬ።

"ምን ትሰራለህ? እንሂድ፤ ይህን ሀውልት ተገትረህ ብታየው መንግስቱን አይወልድልህ" አለችኝ።

"ያውስ በጀግንነቱ የሚፈለግ ሰው አይደል።"

"ኤዲያ! 'አብዮታዊ መሪያችን! ቆራጡ! ብልሁ!' ስትሉ የነበራችሁት እናንተው መለዮ ለባሾቹ ነበራችሁ!"

"ልክ ነሽ! ይህን የሚክድ የለም። እውነተኛ ባህሪውን ግን እራሱ አስመሰከረ። ሳይሞት ሀውልቱን ተሸምቶ ያሰራው የቁም ሙት መሆኑን አውቆ ኖሯል።"

"ኤዲያ! ተወኝ እባክህ" ብላኝ ተያይዘን ወረድን።

አምሳ ኪሎ ጤፍ የሚቋጥር አፍና ቂጡ በቀይ ቆዳ የተለጎመ ዘንቢል መሰል ቦርሳ አንግታለች። ከውስጡ ምን እንዳለበት እንጃ ከብዷት ነው መሰል አስር ጊዜ ወደ ትከሻዋ ከፍ ታደርገዋለች። ራንግለር ጃኬትና ሱሪ ነው የለበሰችው። ከስር ደግሞ ነጭ ሸሚዝ ለብሳለች፤ የላይኞቹን ሁለቱን ቁልፎች አልቆለፈቻቸውም። እርግጠኛ ነኝ ሆን ብላ ነው። ከጡቶቿ መሀል ያንገቷ ሀብል ተዘለግልጎ ይታያል። እቅል እልም ነው የምታደርገው። ስትራመድ ነጠር ነጠር ስለምትል ሽንጧ ያረግዳል። ፀጉሯን ምንጊዜም ቢሆን ከልክ በላይ ማሳደግ አትወድም። አጠር አድርጋ ነው የምታበጥረው። ውሽት ምን ያደርጋል

ነፍሴ እስክምትወጣ ድረስ እወዳት ነበር:: ታዲያ ምን ይሆናል:: አጥማጇ በዛ፤ እሷም ቅንዝንዝ ሆነች:: ስለዚህ በቅናት ከማር ብዬ ከሷ መራቅን መረጥኩኝ:: ሲበዛ ጭልፊት ነች:: የፈቀደችውን ወንድ የማጥመድ ችሎታዋ የተለየ ነው:: ጥሩ ጥርሶች አሏት:: በፈገግታዋ ነው ጠብ የምታደርገው:: እኔንም ጠብ ያደረገችኝ በጥርሶቿ ነበር:: ትዝ ይለኛል፤ከየኔነሽ እሰፋ ጋር የተዋወቅነው ድሬደዋ ነው:: እኔ ያንየ ዘጠነኛ ክፍል ጦር፤ የ25ኛ አየር መቃወሚያ ባትሪ ባልደረባ ነበርኩኝ:: የሰፈሩ ስም "ነምበር ዋን" ይባላል:: የጦሩ ካምፕ ከሰፈሩ አጠገብ ስለሆነ ሶስት መኮንኖች ሆነን ከወይዘሮ ዘውድነሽ ምግብ ቤት ኮንትራት ይዘን እንመገብ ነበር:: ያኔ ድሬደዋ ገና ከጦርነት በማገገም ላይ ነበረች:: እኔም ከመሃል ኢትዮጵያ ወደዚያው የሄድኩት በዚሁ በጦርነቱ ወቅት ነበር::

የኔነሽ እሰፋ ተወልዳ ያደገችው አዲስ አበባ ነው:: ወይዘሮ ዘውድነሽ ያባቷ ትንሽ እህት ስለሆኑ የረፍት ጊዜዋን የምታሳልፈው ድሬዳዋ አክስቷ ዘንዳ ነበር:: እንደ ነገረችኝ ከሆነ አባቷ የሞቱባት በልጅነቷ ነው:: አክስቷ ናቸው በከፊል ያሳደጓት:: በዚህ የተነሳም ወደ ድሬዳዋ ትመጣለች:: ያን ጊዜ ደግሞ 12ኛ ክፍል ጨርሳ ስራ ፈላጊ ነበረች::

ካክስቷ ቤት ወጣ ገባ ስንል ባይናቿ ትቃኘን ነበር:: አንዳንድ ጊዜም ምግብ ታቀርብልናለች:: ሁለቱ ጓደኞቼ ውስጥ ውስጡን አብስለዋት ኖሯል:: እኔ ግን ያን ጊዜ ለፍቅር ግድ አልነበረኝም:: "እንዴት ሶማሊያ ትደፍረናለች" ብዬ ትኩረቴ ሁሉ ወደ ጦርነቱ ነበር:: ምንላድርግ:- «ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር!» እየተባለ ጧት ማታ በዜና ማሰራጫ ይስተጋባል:: አእምሮየ ተሰልቧል፤ የፍቅር ስሜቴ ሞቷል ማለት እችላለሁ:: በዚህ ላይ ደግሞ አይነ አፋር ነኝ:: ጓደኞቼ ግን መቀራረቡ ጠበቅ ሲል ከሷ ጋር ሜት አብረው መቃም ጀምረው ኖሯል:: የየኔነሽ ምርጫ ግን ወደኔ ይሆናል:: ታዲያ ምን ይሆናል እኔ ዳፍንት ሆንኩባት:: ሰረቅ አድርጌ ካልሆነ በስተቀር ባይናቼ ሞልቼ አላያትም ነበር:: ሴትን ልጅ ትክ ብሎ ማየት እፈራለሁ:: ዛሬም ቢሆን ይኸው ነኝ:: ቅልስልስ::

አንድ ቀን ምሳየን በልቼ ካበቃሁ በኋላ ከሰአት እረፍት ስለነበርኩ ዝም ብዬ ተቀመጥኩ:: በዚህ ጊዜ ወይዘሮ ዘውድነሽ ብቸኛ መሆኔ ተሰማቸውና:-

"ጓደኞችህ ጓዳ ውስጥ አሉ:: ግባና ተጫወት:: አንተ ጫት አትቅም" አሉኝ:: ተነስቼ ስገባ የኔነሽን ከጎናቸው አድርገው ይህን ለምለም ጫት ይሉታል:: የሰንደሉ ጭስ ይተናል:: ፊታቸው ሁሉ በላብ ወርዝቶ ይብለጨለጫል:: ጓደኞቼ ቀና ብለው አፈጠጡብኝ:: "ምን ልታደርግ መጣህ?" በሚል አይነት:: እኔም በመጠኑ ደነገጥኩ:: የኔነሽንም በማየቴ እንደ ማፈር አልኩኝ:: ልመለስ ስል:-

"የት ትሄዳ? ና ተቀመጥ" ስትል ቀልጠፍ ብላ ከሷ ጎን እንድቀመጥ አመቻቸችልኝ:: በምንተፍረት ሄጄ ከጎኗ ተቀመጥኩ:: ድሪያ ነበር የለበሰችው:: ሰረቅ አድርጌ ሳያት ደረቷ ልትጠልቅ ያለች ፀሀይ ይመስላል::

"ሜት እንካ" ብላ የገዛችን ሜት ዘረጋችልኝ::

"አይ" ብዬ በመ[illegible] ራሴን ነቀነኩ::

"አትወድም?" አለችኝ::

"አልወድም" አልኳት::

"ካልቃምክ ውጣልን:: አትደብረን" አሉኝ ጓደኞቼ::

"እሽ ብዬ ብድግ ስል":-

"ለምን? እማየ ትሙት ልክ አይደላችሁም" ብላ ሸሚዜን ጨምድዳ በመያዝ አስቀረችኝ:: ከዚያ ኮካላ ከፍታ ሰጠችኝ::

ለስላሳየን እየጠጣሁ ከመቅለስለስ ወደ መጫወት ተሸጋገርኩ:: አይነ ሞራየ ከተገፈፈ በኋላ ደግሞ ጨዋታየ ከማር ይጣፍጣል:: አፍነክንካት ጀመር:: እነእጅሬ ግን ፈገግም አላሉ::

ያንለት እንዲሁ በተራ ጨዋታ ተለያየንና ከሶስት ቀናት በኋላ ጨረቃ ጉዞ ሆቴል በፍቅር አበድነው::

"ለምን ከጓደኞችህ መካከል አንተን እንደ መረጥኩህ ታውቃለህ?" ነበር ያለችኝ የመጀመሪያው ቀን::

"አላውቅም" አልኳት::

"ቅልስልስ ስለሆንክ ነው:: እማየ ትሙት፤ ለምን እንደሆነ እንጃ ቅልስልስ ወንዶች ደስ ይሉኛል::" ገና ፍቅርን ያልጠገበች አሳት ነበረች:: ዛሬም ያው ናት:: ቋያ! ጨረቃ ጉዞ ሆቴል ዛሬም ትዝ ይለኛል::

"አሁን ወደ ቤትሽ ነው የምትሄጅው ወይንስ ወደ ሌላ" አልኳት ከቀድሞ ትዝታችን ስመለስ:: ሽቶዋ አሁንም አትልቀቃት እያለኝ ነው::

"ወደ ቤቴ ነው የምሄደው:: አንተስ ወዴት ነው የምትሄደው?" አለችኝ:- ቦርሳዋን ወደ ትከሻዋ ከፍ እያደረገች::

"እኔ እንኳን ለጊዜው ወዴት እንደምሄድ አልወሰንኩም::"

"ከቤትህ ስትነሳ ምንም ፕሮግራም አልነበረህም?"

"አልነበረኝም:: ዝም ብዬ ነው በመርካቶ ዙሬ ከሀውልቱ የደረስኩት:: ወደ ቤትሽ ከሆነ ትደርሻለሽ፤ ምሳ ልጋብዝሽ?"

"በቀር ይህን ያህል ጊዜ ሳንተያይ ቆይተን ሳትጋብዝ ልትሰደኝ ኖሯል?" ስትል ቀለደችኝ:: ተያይዘን ወደ ቋራ ምግብ ቤት ሄድን::

"አሁን ቋራ ምግብ ቤት ይዘኸኝ የመጣኸው ቴዎድሮስን አታገኘው" አለችኝ:: ዝም አልኳት:: ምን መልስ ልስጣት? እንዳለችው ቋረኛው ካሳ እንደ ገና አይወለድ::

ሁሉም በየቤቱ መሽጎ ነው መሰል የምግብ አዳራሹም ሆነ ውጭ መናፈሻው ጭር ብሏል:: እንደኛው ተባራሪ ሰዎች ናቸው አልፎው አልፎው የተቀመጡት::

ምሳችንን በልተን ለስላሳ ይዘን ረጋ ያለ ጨዋታ ያዝን:: ጧት ለማኝ ጦር አየሁ ብዬ እንደ ትኩስ እብድ ወፈፍ ወፈፍ እንዳላልኩ ሁሉ አሁን በፈገግታ ተውጬ ከየኔነሽ ጋር በመሆን እኔን አታለልኩት::

ከምግብ ቤቱ ለቀን ወደታች ስንወርድ እንደ ዋዛ አድርጌ ልክ በፊት እንደ ምጠራት፤ "የኔ የተረሳ ፍቅር ማደስ አይቻልም እንዴ? ለምን የዛሬን እንኳን አብረን አናሳልፍም?" አልኳት በተለሳለሰ አንደበት::

"ወጭው ካልከበደህ" አለችኝ::

"ኧረ ለወጭውስ ግዴለሽም" አልኳት ቀልጠፍ ብዬ:: ከሁሉ ደስ የምትለኝ ለፍቅር ደጅ አለማስጠናቷ ነው:: አይጣል ግን ወዷት ለጠላቻው:: ዞራክ አታየውም::

"በል እንግዲያው ለማየ ስልክ ልደውልላት" አለችኝና የህዝብ ስልክ ወዳለበት ስንሄድ:-

"ከሆነ አይቀር ለሶስት ቀናት የምትቆዪ መሆንሽን ንገሪያቸው" ስላት:-

"እማየ ትሙት ከኔ ጉያ ተደብቀህ መቆየት ትፈልጋለህ መሰል?" ቆም ብላ በሽሙጥ ፈገግታ አየችኝ::

"ብስጭት ብስጭት ስላለኝ ካንች ጋር ስሆን እረሳዋለሁ:: ለዚያውም የቀድሞዋ የኒነሽ ከሆንሽ ነው::"

"ድንቄም ብስጭት:: ምን ለመሆን?" ብላ የስልክ እጀታውን አንስታ ወደ ጆሮዋ ካስጠጋች በኋላ ሳንቲሞች ጨመረችና ቁጥሮች ታሽከረክር ጀመር:: እኔ ካጠገቧ ቁሜአለሁ:: ወዲያው ሳንቲሙን ስልቅጥ ሲያደርገው:-

"ሀሎ! እማየ ነሽ?... እንደምን ዋልሽ... እየውልሽ ለሶስት ቀናት ያህል እንዲት ጓደኛዬ ታማ ከሷ ቤት ነኝ:: ብቻዋን ስለሆነች አነጋገሪኝ ስላለችኝ ነው:: እንዳታስቢ ብዬ ነው የደወልኩልሽ..." አለቻቸው:: ወዲያው ደግሞ ምን እንዳሏት እንጃ ፊቷን ከስክሳ፣ "የራሱ ጉዳይ ነው! ጓደኛዋ ታማ ሄዳለች በይው!" ብላ በቁጣ ስልኩን ዘጋችው:: "የምን ሰው ነው? " ብዬ ልጠይቃት አልኩና መልሽ ተውኩት::

እኔም እማማ ልኬ እንዳያስቡ ለሶስት ቀናት ከከስቴጋ የምቆይ መሆኔን በጎረቤት ስልክ ገልጨላቸው ጎን ለጎን ሆነን ወደታች ወረድን:: የትኛው ሆቴል እንደሚሻል ማማረጥ ያዘን:: ለፀጥታውም ሆነ ለማንኛውም ነገር የተሻለ ሆቴል መምረጥ ነበረብን:: ለሶስት ቀናትም ቢሆን ሰላማችን መደፍረስ የለበትም::

ከየኒነሽ እሰፋ ጋር እርብለት የመሸግን ለኛለት ተለያየን:: ቁሜ መሄዶ ብርቱ ነኝ:: እራሴ ሁሉ በፍቅር ዞሯል:: አይኖቼም ቀልተዋል:: ሰውነቴ በጠቅላላው ደቋል:: የኒነሽ መቼም እያደር ጥንቅሽ ነው የምትሆነው:: የተረሳ ፍቅርን እንደ ገና መቀስቀስ ደግሞ አይጣል ነው:: የተዳፈነው እየተጫረ ይቀጣጠልና መላ አካላት መጋየት ነው:: ሁሉን ነገር አስረሳችኝ:: ከሷ ጉያ ተሸጉጨ ዋልኩ፤ አደርኩ፤ ተረጋጋሁ::

ከሷ እንደተለየሁ ወደ ቤቴ ነበር የሄድኩት:: ታክሲዎች ስራቸውን ጀምረው ስለነበር በታክሲ ነበር የሄድኩት:: በግሬ ቢሆን ኖሮ እርግጠኛ ነኝ ከመንገድ አዙሮኝ እወድቅ ነበር::

ከቤቴ እንደደረስኩ ካልጋዬ ላይ ተዘረርኩኝ:: ሙሉ ቀን ድብን ያለ እንቅልፍ ተኛቼ ዋልኩኝ:: የሶስት ቀናቱን እንቅልፍ ተወጣሁት:: የኒነሽ እንዴት ሆና ይሆን? አጅሪት ወይ ይሄኔ አንዱን ጠምዳው ይሆናል:: ፍቅር የማትጠግብ ፍጥረት::

እራቴን በልቼ እንደገና ተጠቅልየ ተኛሁ:: እስከ ሌሊቱ አስር ሰአት ድረስ ከንቅልፌ አልነቃሁም ነበር:: አስደንጋጩ ፍንዳታ ነው ከንቅልፌ ያባነነኝ::

ምእራፍ ሶስት

የዘር መፈጠሪያው ዋዜማው ግንቦት፣
ምነው እሳት ሆነ ዛሬና ትናንት::

7

እለቱ ማክሰኞ ግንቦት 27 ቀን 1983 ዓ.ም. ነው:: ይህ እለትና ወር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሲታሰብ የሚኖር ይመስላል:: ብዙ ክንዋኔዎች በተከታታይ ተከናውነውበታል::

ግንቦት 8 ቀን 1981 እለቱ ማክሰኞ በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር መፈንቅለ መንግሥት ተሞክሮ በመክሸፉ ሜ/ጀነራል መርእድ ንጉሴ የጦር ሀይሎች ኢታማጆር ሹም፣ ሜ/ጀኔራል እምሀ ደስታ፣ ያየር ሀይል አዛዥ በእለቱ ራሳቸውን ገደሉ::

ግንቦት 10 ቀን 1981 የሰሜኑ የጦር አዛዥ ሜ/ጀኔራል ደምሴ ቡልቱና ጥቂት ጀኔራሎችና በርካታ ኮለኔሎች በ102 አየር ወለድ ክፍለ ጦር ተገደሉ:: እሳዛኝ ውድቀት:: ኢትዮጵያ በየቀኑ ጀግና እያጣችና እየተራቆተች መጣች፤ ባንፃሩ ምንቸቶች ጋን ሆኑ::

ግንቦት 13 ቀን 1982 ዓ.ም. "አብዮታዊ መሪያችን" 12 ጀኔራሎችን ረሸኑ፤ በእንፃሩ ቱልቱላዎች ብቻ ቀሩ::

ግንቦት 11 ቀን 1983 መፈንቅለ መንግስቱ የከሸፈበትን ሁለተኛ አመት ምክንያት በማድረግ ቤተ መንግስት፣ "ካብዮታዊ መሪያችን" ቤት ቅልጥ ያለ ግብዣ ነበር:: በውስጥ ግን "ቆራጡ መሪያችን" የወጭ ያደረጉት ግብዣ ነበር:: በዚህ እለት ደሴ ተያዘች::

ግንቦት 13 ቀን 1983 እለተ ማክሰኞ፤ "ቆራጡና ብልሁ መሪያችን፣ ውድ ጓድ መንግስቱ ሀይለማርያም፣ የኢሰፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ዋና ፀሀፊ፣ የኢህድሪ ፕሬዚዳንት፣ያብዮታዊ ጦር ጠቅላይ አዛዥ" በዳሽ ፋይፍ አይሮፕላን ወደ ዝምባብዌ ፈረጠጡ!!

ግንቦት 20 ቀን 1983 አዲስ አበባ በኢህአዲግ ተያዘች::

ግንቦት 27 ቀን እለተ ማክሰኞ በሳምንቱ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት ጀምሮ አዲስ አበባ በከባድ ፍንዳታና ቃጠሎ ተናወጠች::

ቃጠሎው የተነሳው ወደ ነፋስ ስልክ አቅጣጫ፣ ጎተራ አጠገብ፣ በቅሎ ቤት እየተባለ ከሚጠራው አካባቢ ያለው የጦር ሰራዊት የመሳሪያ ዲፖ በእሳት በመያያዙ ነው:: ከእንቅልፌ የባነንኩት በከባድ ፍንዳታው ሳቢያ ካልጋየ ላይ ስናጥ ነበር:: እማማ ልኬ ቀድመው በመነሳት:-

"እግዚኦ! እግዚኦ! ምኑን ማት አመጣህብን ጌታዬ!" እያሉ ይብረከረካሉ:: ልብሴን ለባብሼ ፈጥኘ ከቤት ስወጣ የሰፈሩ ሰው ሁሉ በየቤቱ በር አገርግሮ በመቆም ይንጫጫል:: ደቡብ አዲስ አበባ እየጋየች ነው:: የከባድ መሳሪያ ፍንዳታ ከተማዋን በሞላ ያናውጣታል:: የሁላችንም ግምት አድፍጦ የነበረ ጦር ገብቶ ከኢህአዲግ ጋር ውጊያ ገጥሟል የሚል ነበር:: ንጋት ቀደደና ሁሉም ነገር ሲታይ ያደፈጠ ጀግና ጦር ሳይሆን እሳት ነው:: የግንቦት ወር እሳት::

ጥቀርሻ የመሰለ ጭስ በመጠኑ ወደ መናገሻ ጋራ ረገብ ብሎ ሰማዩን ደግፎት የቆመ ይመስላል:: ከሰማዩ ላይ ሌሊቱን ወጥቶ የተከመረው ጭስ ጥቀርሻ መስሎ ሊዘንብ የተቃረበ ይመስላል:: ከስር ደግሞ ነበልባል ሽቅብ ሽቅብ ይተፋል:: ከባድ ፍንዳታ በፈነዳ ቁጥር ብራማ መልክ ያለው፣ የተድቦለቦለ ነገር እንደተወርዋሪ ኮከብ በጭሱ መሀል ሰንጥቆ ለረጅም ጊዜ ላይን ሳይጠፋ ይቆይና ያርጋል:: ሌላ ብርቱካንማ መልክ ከስር ይነሳና ተብለጭልጮ ይሄዳል:: መካከለኛ ተኩስ ደግሞ እንደ በረዶ ይንዷዷል:: ቃጠሎው ደግሞ ካንዱ ህንፃ ወደ ሌላው ህንፃ ባፋጣኝ እየተሸጋገረ አዲስ አበባን ብርክ ውስጥ አስገባት:: የእግዚአብሄር ቁጣ፣ ያላህ ሰይፍ የተሰነዘረባት አደረጋት::

ንጋት ከቀደደ በኋላ ህዝቡ ከያለበት በመውጣት ወደ ቃጠሎው መጉረፍ ያዘ:: ወገኑን፣ ዘመዱን፣ ወዳጁን... ከመቅሰፍት ለማዳን:: እኔም ወዳክስቴ ቤት እሩጫየን ቀጠልኩ:: ደግሞ ቤቷ ከዚያው ከቃጠሎው አካባቢ ነው::

ቸርችል ጎዳና ብቅ ስል ከወደታች በኩል ሽቅብ የሚያቀናው ህዝብ ለጉድ ነው:: ቢጠይቁት መልስ አይሰጥም:: ወዴት እንደሚሄድ አያውቅም:: በፍርሃትና በጭንቀት ብቻ ይቃትታል:: አብዛኞቹ አሮጊቶችና ህፃናት ናቸው:: ውስጥ ልብስ ብቻ የለበሱ አሉ:: ብርድ ልብስ ጠቅልለው የያዙ ብዙዎች ናቸው:: እጅና እግራቸውን ብቻ ይዘው የሚቅበዘበዙት ደግሞ ከሁሉም ይበልጣሉ:: ሁሉም ግን አሳዳጅ የተከተላቸው ይመስል እየዞሩ እያዩ በዚያ አቀበት ይቧችቻሉ::

እናቶቻቸው የጠፍዋቸው ህፃናት «እናቴ» እያሉ ይጮሀሉ:: ልጆቻቸው የጠእፍዋቸው እናቶች «ልጆቼ» እያሉ ይንጦዠጦዦሉ:: ምስቅልቅል ያለ ሁኔታ ነው:: ጋራው ከመጣው ቁጣ የሚያድን ይመስል ሁሉም ወደ እንጦጦ አቅጣጫ ነፍሴ አውጭኝ ይላል... ቃጠሎውም የጥፋት አድማሱን በማስፋት ደቡብ አዲስ አበባን ሙሉ በሙሉ በጭስ ጋርዷታል:: ጥቀርሻ መስሎ ይጥመለመላል:: ነበልባሉም ብጫ መልክ አንዳንድ ጊዜም ቀይ ላንቃ እየመሰለ ሽቅብ ሽቅብ ይጎናል::

ሶስት አራቱ በአንድ ጊዜ ሲፈነዳ ምድሯ ትናወጣለች:: በነውጡ ምክንያት ያዲስ እበባ ረጃጅም ፎቆች መስተዋታቸው እንዳለ ወርዶ መሬት ላይ እንደ በረዶ ሆጭ ብሎ ተከምሯል::

ቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤት ስደርስ ከላይ የመጣውን ህዝብ እንዳያልፍ ኢህአዲጎች አጥር ሰርተው አግደውታል:: ሕዝቡ ጥቅልል ብሎ አግድም ወደ መስቀል አደባባይ አለፈ:: እኔም ተቀላቅየ ነጎድኩ...

የቦሌን መስመር እንደ ያዝን ሁሉም አቋራጭ መንገድ እየፈለገ ወደ ቃጠሎው ለመድረስ በያቅጣጫው ተሰራጨ:: እኔም ተሹለክልኬ ካክስቴ ቤት ደረስኩ:: በሌሊት ልብሷ ብቻ ደንብራ እንደ ወጣች አገኘኋት:: ተነፈስኩ::

"ይህ የእግዚአብሔር ቁጣ ነው" አለችኝ፡- ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ::

"ለምን ልብስ አለበስሽም?" አልኳት::

"ምኑን እለብሰዋለሁ? የቤቱ በር በፍንዳታው ምክንያት በራፉ ተቆልፎ አልከፈትም አለ" አለችኝ:: እውነትም ተከርችሟል:: ቤቷም ባላንድ ፎቅ ስለነበረ ባንድ በኩል መስተዋቱ በመጠኑ አረግፍዋል::

ወዲያው ተሯሩጠን አናፂዎች አምጥተን ከፈቱልን:: እግዜር ይስጣቸው::

አሁንም አካባቢው በጭስ ደመና እንደ ጨለመ ነው:: በርግጥ የጧቷ ፀሀይ ፈንጥቃለች:: ያዲስ አበባ ህዝብ ግና ገና ተስፋ አልፈነጠቀበትም:: ፍንዳታው አሁን በመጠኑ ተግ ብሏል:: የቀላል መሳሪያ ተኩስ ግን እንደ ዶፍ ይወርዳል:: የቃጠሎው ድምፅ ልክ እንደ ወገቦ ሲንጃጃ ይሰማል::

አክስቴን ካረጋጋኋት በኋላ እልቂቱን ለማየት ወጣሁ:: ከታች ከጎዳናው ልደርስ ግን ለማለፍ አልቻልኩም:: አሁንም ኢህአዲጎቹ በየቦታው ግድግዳ ሆነው አላሳለፉም:: ከቃጠሎው ቦታ ደርሸ የጠፋውን ጥፋት የማየት እድል ሳይገጥመኝ ቀረ:: ያው ማታ እንደ ማንኛውም ሰው በሬዲዮ ሰማሁት:: እሱም ቢሆን ቁጥብ ነበር:: "... ወደ ፊት የወደመውን ንብረትና የሞተውን የሰው ብዛት እንደ ተረጋገጠ እንገልፃለን" የሚል ነበር:: ሁለት የውጭ ጋዜጠኞች ግን አንደኛው ወዲያው ሲሞት ሁለተኛው ደግሞ በፀና መቁሰሉ ተገልፅዋል::

ማታ በሬዲዮ እንደ ተገለፀው ከሆነ የቃጠሎው መንስኤ የተሳበበው በደርግ ሰራዊትና በኢሰፓዎች ነው:: ይኸ ሰበብ በጣም አስገረመኝ:: ደርግም ይኸው ነበር:: አንድ ነገር የተፈጠረ እንደ ሆነ «የኢምፔሪያሊዝም ቅጥረኞች ደባ! አድሃሪያን አሻጥር ሰርተው...» እያለ ይለፈልፍ ነበር:: ከጥቂት አመታት ወዲህ ደግሞ የጦር ሜዳው ድል እየከዳው ሲመጣ እራሱ በፈጠረው ጭፍን አመራር ኢኮኖሚው ሲንኮታኮት «ያረብ ቅጥረኞች ሴራ! የወያኔዎች ደባ!...» በማለት ይወተውት ነበር:: የሚገርመው ግን አንዳንዶቹንማ ድርጊቶች እራሱ ይፈፅማቸውና ለመቀስቀሻነት ይጠቀምባቸዋል:: የነዚህም አዝማሚያ አላማረኝም:: ካንድ ወንዝ የተቀዱ አስመሰሏቸዋል::

ጀኔራሎቹ በጦር ሜዳ ማዋጋት አቅቷቸው ጦሩን እየመሩ አዲስ አበባ ገብተው፣ አዲስ አበባ የቆዩትም በየሽርንቁላው እንደ ጥንቸል አድፍጠው ቆይተው እጅ ስጡ ሲባል እጃቸውን ለመስጠት ሲሽቀዳደሙ እያየናቸው፡- «የደርግ ሰራዊት ሴራ ነው» መባሉ መልሶ የኢህአዲግ ሴራ ነው ያሰኛል::

ጦሩም የትም ተበትኖ የሚበላው አጥቶ ልመና ተሰማርቷል:: ለዚያውስ የትኛው አመራር ሰጭ ተገኝቶ ነው እንዲህ ያለው ስውር ደባ የሚፈፀመው? በርግጥ ለተንኮል ስራ ደርጎችና ከነሱ የተጠጉ ሁሉ ይሰንፋሉ አይባልም:: ጥያቄው በዚህን ወቅት አሞቱ አላቸወይ? የሚስዩቻቸውን ቀሚስ አጥልቀው በማድፈጥ፡- «ምን ይመጣ ይሆን?» እያሉ እየባነኑ እንዲህ ያለ ሙያ ሊሰሩ! ድንቄም!

በዚህ ቃጠሎ ሌሎቹ ታሚተኞች ኢሰፓዎች ናቸው:: እነሱም ቢሆን እንደዚህ ያለ ተግባር ይፈፅማሉ ብዬ አላስብም:: ሰውን ያለስራው ማማት ሀጢአት ነው:: ለነገሩስ ቀላል ነው:: ህፃን ልጅም ቢሆን ካሳዩት ያደርገዋል:: ክብሪት ጭሮ መለኮስ ነው:: ከዚያ በኋላ ቀስቃሹ አይልም:: በራሱ ይቀጣጠላል:: አቀጣጣይ ከቤንዚን የበለጠ ባሩድ አለ:: ቁምነገሩ ከበር ያሉትን ዘቦች ሰብሮ ከመግባቱ ላይ ነው:: አጥፍቼ ልጥፋ የሚል የኢሰፓ አባል ደግሞ ካሳለፍናቸው የትንቅንቅ አመታት ውስጥ አላጋጠመንም:: ኢሰፓዎችን እናውቃቸዋለን፣ሁሉም ናቸው ባይባልም አብዛኞቹ የድል አጥቢያ አርበኞች ናቸው:: ወይንም

ደግሞ የሰላም ጊዜ ጀግኖች ናቸው:: ባይሆን በግልፅ የሚነገርላቸው ውስኪ ለመጠጣት፣ ጮማ ለመጮምጮም የማይቀደሙ፣ የሴት ዳሌ የማያማርጡ መሆናቸውን ነው፤ በተረፈ ግን ቁርጥማታሞች ናቸው::

የናት አገር ጥሪ በመጣ ቁጥር በተግባር አይተናቸዋል:: የበሽታቸው ብዛት ተነግሮ አያልቅም:: ጉበት፣ ሳንባ፣ ጨጓራ፣ ኩላሊት፣ ጣፊያ፣ ትርፍ አንጀት፣ ስኳር፣ ደም ብዛት፣ ደም ማነስ... ኧረ ምኑ ቅጡ? በሽታቸው ጠቅላላ የሆድ እቃ በሽታ ነው:: ያን ሰሞን ሆስፒታሎች በኢሰፓዎች ይጣበባሉ:: ሚስቶች ይደግፋሉ፣ ልጆች ጃንጥላ ይዘው ይከተላሉ፤ እነሱ ያቃስታሉ፤ በዚህ በዚያ ብለው ቅርት ያሏታል:: ሀኪሞቹም በነሱ ላይ አይጨክኑም:: መከረኛ ዘበኞች ከየድርጅቱ ይለቀሙና ወደ ጦርነት ይላካሉ:: ያልገባኝ ግን የደርጎችና የኢሰፓዎች በሽታ ለምን የሆድ እቃ ብቻ እንደሆነ ነው? የድሉት በሽታ ይሆን እንዴ? ደግሞኮ የሚነሳው ጦርነት ሲቀሰቀስ ነው:: ቁንጮ የደርግ አባላትም በሆድ እቃ በሽታ ጡረታ ወጥተዋል:: ኧረ ስለ ኢሰፓዎች ብዙ የተባለ አለ:: አሁን በቅርቡ እንኳን ኢህአዴግ ከጎንደር እያሳደደ ወደ ጎጃም ሲያሻግራቸው ሩጫቸው የገረመው የጎንደር ህዝብ:-

«እነ እንቁላል ቁርሱ እነ ብር ትራሱ፣
ሀሙሲት ቢተኮስ ባህርዳርን አልፈው ዳንግላ ደረሱ::
ደህንነት ባህያ ኢሰፓ በፈረስ፣
አሽቅድድም ያዙ ማርቆስ ለመድረስ!» ብሏቸዋል::

ከማርቆስ ደግሞ ፈርጥጠው አዲስ አበባ ሲገቡ የጎጃም ህዝብ:-

«የወያኔ ጥይት ጨሞጋ ቢያንራ፣
ማርቆስ ላይ ቀረ ድሃና ባንዲራ!» ብሏቸዋል::

እኛ ደርጎችንና ኢሰፓዎችን የምናውቃቸው ከሞላ ጎደል በዚህ ተግባራቸው ነው::

አሁን በመጨረሻው በሚያዝያው የክተት ጥሪ ደርግ «ራሳችሁን ተከላከሉ» ብሎ መሳሪያ አስታጥቋቸው ነበር:: ጥቂቶችም ስንዳፋ ገብተው ለጥቂት ቀናት ለመሰልጠን ሞክረዋል:: «አዙጥ» በሚል መጠሪያ ስምም ተሰባስበው ነበር:: «አዲስ አበባ ዙሪያ ጥበቃ» ማለት ነው:: ዞሮ ዞሮ ግን የተፈየደ ነገር የለም:: ያው ዙጥ ብለው ቀሩ እንጂ:: እና የተሰነዘረው ምክንያት አጥጋቢ አይደለም ባይ ነኝ:: «ሲበሏት የፈለጓትን አሞራ ጅግራ ናት ይሏታል» እንደ ሚባለው እንዳይሆን:: ይልቅየ በቃጠሎው የተጎዱት ህዝቦች በጅጉ ያሳዝናሉ::

እኔም በየኔነሽ ፍቅር ተቃጥያለሁ:: ማታ ስልክ ደውየላት ነበር:: እናቷ "የለችም" አሉኝ:: የት ሄዳ ይሆን? እየቆየሁ ቅናት ሰረሰረኝ:: ይህን ጊዜ ካንዱ ጋር በፍቅር እየተምነሸነሸች ይሆናል:: ቅጥል አልኩ::ያለፉት ሶስት ሌሊቶች ትዝ አሉኝ:: እንደ እንዝርትኮ ነው ሹራ የምታሽረው:: ተስማ አትጠገብ፤ ሁለመናዋ የማር ወለላ:: ታዲያ ምን ይሆናል! እሷን የብቻው አድርጎ ያስቀረ ወንድ የለ:: አይናቿ፣ ጥርሶቿ! እርምጃዋ ሁሉ ወንድ ይጠራሉ:: አሁን ምን ነበር ድምፅዋን ብሰማው:: እንቅልፍ ወስዶኝ ያድር ነበር:: ከማን ጋር እየከነፈችው ይሆን? እሷ

መቼም በፍቅር ልግመት አታውቅም:: እኔን እንዳበጠረችኝ ሁሉ አንዱን የታደለ እያበጠረችው ይሆናል:: ያለኝ ምርጫ ተጠቅልየ መተኛት ነው:: ተኛሁ:: እንቅልፍ ግን ሊወስደኝ አልቻለም::

ቀደም ሲል ያልሰማሁት ጥሪ፣ «በድጋሚ ጥሪ» ብሎ በሬዲዮ "ከነገ ጀምሮ በ48 ሰአት ውስጥ ከም/መቶ አለቃ እስከ ኮሎኔል ማእረግ ድረስ ያላችሁ መኮንኖች ጃንሜዳ በሚገኘው የቀድሞው 1ኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ::"

"ይቺ ጥሪ የዚህ ቃጠሎ መንስኤ ነች" አልኩኝ:: ይህንኑ ሳሰላስል ለጊዜው የኔነሽን እረሳኋት::

8

በልማዱ የግንቦት ወር የበልግ ወቅት ነበር:: በዚህ አመት ግን ደርቋል:: ነፋስ ብቻ፤ አቀጣጣይ ነፋስ...

ማታ በሬዲዮ በተላለፈው ጥሪ መሰረት በጧት ቁርሴን በልቼ ደፋ ደፋ እያልኩኝ በጊዮርጊስ አቅንቼ ወደ ጃንሜዳ ገሰገስኩ:: ሲቪሉ ህዝብ ኪራ ስለጀመረ በያቅጣጫው ይጣደፋል:: ሰውም ከያደፈጠበት ወጥቶ መተረማመስ ይዟል:: በመጠኑ የመረጋጋት ሁኔታ ይታያል::

እየገሰገስኩ ከቀድሞው 1ኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ስደርስ ከበሩ ውጭ መኮንኖች ፈሰዋል:: ሁሉም አፍ ላፍ ገጥመው ያንሾካሹካሉ:: ወደ ውስጥ ስገባ ደግሞ የእግር መቋሚያ የለም:: ሁሉም የጦር መኮንን የሲቪል ልብስ ነው የለበሰው:: ሽማግሌ ኮሎኔሎች ሳይቀሩ የዘመኑን ራንግለር ጃኬትና ሱሪ ነው የለበሱት:: ያንዳንዶቹ ነተብ ብሏል:: ሁሉም ማለት ይቻላል ከራሳቸው የሌኒን ቆብ አይነት ደፍተዋል:: የፀሐይ መነፅርም የሰኩ በርካታ ናቸው:: ብቻ ሁሉም ተዋናይ መስሏል::

ለመመዝገብ፣ «ተሰለፉ» ተባልንና መሰለፍ ስንጀምር መቆሚያ የት ተገኝቶ:: ደግሞ ቀድሞ ለመሰለፍ መስገብገብ የጀመርነው ከዚህ በኋላ ነበር:: የት ለመድረስ እንደ ተጣደፍን አልገባኝም:: ግብግቡ የዋዛ አልነበረም:: ይህም ሆኖ አልተሳካልንም:: ቦታው በመጥበቡ:-«ወደ ጃንሜዳ ውጡ» ተባልን:: ቀድሞ ሰልፍ ለመያዝ እንደ ግሪሳ ወፍ ግርር አልን:: ወላ ኮሎኔል ወላ ሻለቃ ትናንት ከተመረቀው ምክትል መቶ አለቃ ጋር እኩል እግርን ነቅሎ መፈትለክ ሆነ::

አንድ ቁመቱ የስልክ ምሰሶ የሚያክል ሰውነቱ ጭርንቅ ያለ መኮንን ሲሮጥ ጥቅልል ብሎ ወደቀና እንደግንዲላ ተንከባለለ:: ሁለት ጊዜ እቃሰተና ተነስቶ አቧራውን እንኳን ሳያራግፈው እሩጫውን ቀጠለ:: ፈንደስ ፈንደስ እያለ:: ነፍሴ እስከምትወጣ ድረስ ሳኩኝ::

ምዝገባ ከመጀመሩ በፊት:- «ተሰብሰቡ» ተባልንና ሰላማው በድምፅ ማጉሊያ ተገለፀልን:: ቀደም ሲል የፖሊስ መኮንን ነበሩ አሉ:: ጥቁር ናቸው:: የማእረግ ምልክት ባያደርጉም ሌ/ኮለኔል እንደ ነበሩ የሚያውቋቸው ነግረውኛል:: ወደ ጦሩ ተዛውረው ያንድ ብርጌድ የጦር አዛዥ ነበሩ:: ሲቀናቸው ትግራይ ላይ ተማረኩ:: ፊጣጣ ከፊታቸው

አይለይም። ተፈጥሮአቸው ይሆን ወይንም በድል አድራጊነታቸው ኮርተውና ተደስተው አይታወቅም ሲናገሩም ፈንደቅደቅ እያሉ ነው። ብቻ እንደ ጥቁረታቸው ፈገግታቸው ባይኖር ኖሮ ያስደነግጡን ነበር።

"ምዝገባውን እንደ ጨረሳችሁ ለተሃድሶ፣ ደርጋዊ አመለካከታችሁ በመጠኑ እንዲለወጥ፣ ለሶስት ቀናት ካዲስ አበባ ወጣ ትላላችሁ። ደግሞ አስሯቸው እንዳታስችን ለቤተሰቦቻችሁ አስረዷቸው" ሲሉ በመግባቢያ እነጋገር ተናገሩ። እኛ በመጠራጠር ተተራመስን።

"የሌሊት ልብስ አልያዝንም" ሲል አንድ መኮንን ጠየቀ።

"ችግር የለም፤ ልብስም፣ ምግብም ዝግጁ ነው። አታስቡ። ባይሆን እንደ ደርግ ጮማ አናቀርብላችሁም" በማለት ሁላችንንም አሳቁን። ከዚህ በኋላ ማንም ቅር አልተሰኘም። ሁላችንም የሶስቱን ቀን የተሃድሶ ሴሚናር ተካፍለን ለመምጣትና የግንቦትን ወር ደመወዝ ለመውሰድ ቸኩልን። ከዚያ ደግሞ እንዳቅማችን ስራ መያዝ... ወዲያው ስድስት አይፋ መኪናዎች ቀረቡና የተመዘገቡትን ማሳፈር ያዙ። እኔ እሳፈር እኔ እሳፈር ጦርነት ሆነ።

«የደርጉ መኪና ሸራ የለበሰው፣
ያን ሁሉ መኳንንት ወዴት አደረሰው?»

እንዳልተባለ ሁሉ ዛሬ ያ-ፅዋ ሞልቶ በመፍሰሱ በራሽን መጫኛ ባሮጌ አይፋ እንደ ሰርዲን እየታጨቅን እንጫን ጀመር። ንጉሱም ባሮጌ ቮልስዋጎን ነበር ወደ እስር የተወሰዱት። ያ-ሁሉ በጥራን ኮለኔል ቂጡ እየተገፋ ይሳፈር ጀመር። ማእረግና ስልጣንም የምትከብደው ለካ በጊዜ ላይ ኖሯል። እንደ ጌሾ ቀለነው አረፍነ። ግፊያው፣ ትርምሱ፣ ጩኸቱ እራሱን የቻለ ትርኢት ነው።

ያን እለት ፈፅሞ ወረፋ ሳይደርሰኝ በመቅረቱ ወደ ቤቴ ተመለስኩ። እርም የለኝም፤ ማታ ለየኔነሽ ስልክ ደወልኩላት:- «የለችም» ተባልኩ። ንድድ እንዳልኩ ተጠቅልየ ተኛሁ።

9

በማግስቱ ቀደም ብዬ በመነሳት ቁረሴን እንደ ነገሩ ቀማምሼ ቀድሜ ስልፍ ለመ‥ንዝ እየገሰገስኩ ስደርስ ሌሊቱን ሲጓዙ ይደሩ ወይንም እንደኔው ይማልዱ ጃንሜዳ ጠጠር ቢጣል መሬት ላይ አታርፍም። አብዛኞቹ ግን ከዚያው ጃንሜዳ ተኝተው ያደሩ ናቸው። እኔ ስደርስ እንኳን ውርጭ ያገረራቸው ገና አልተነሱም ነበር። ልክ እንደ ስደተኛ ተኮራምተዋል።

የዛሬውማ ለጉድ ነው። ሚስቶች፣ ልጆች፣ ጎረቤቶች፣ ወዳጆች አልቀሩም። ተነቅንቀው መጥተዋል። «ሴሚናር ሊሄዱ ነው» ስለተባለ ለመሸኘት ነው። ብርድ ልብስ፣ አንሶላ፣ ጠቅልለው በፌስታል፣ በትንሽ ቦርሳ አንጠልጥለው የያዙ ጥቂቶች አይደሉም። ከዚህ ላይስ እኔም ብልጥ ሆኛለሁ። ለክፉም ለደጉም ብዬ አንድ ፎጣ፣ አንድ ጋቢ፣ ካናቴራና መለወጫ የውስጥ ሱሪ በቦርሳ ከትቼ አንጠልጥዬ ይዣለሁ።

በኪሴ ደግሞ አምሳ ብር ብቻ አለችኝ። ለምናልባት እንጅ ምግብም ተዘጋጅቶ ይጠብቀናል ተብሏል።

እኩለ ቀን ላይ ከኛው መካከል መንጃ ፈቃድ ያላቸው ሹፌሮችም ተመርጠው ተመደቡ። ምዝገባውም ከዚያው እንዲሆን ተወስኖ ቆመ። ከዚህ በኋላ የትንቅንቁ ነገር አይነሳ። ለካም ከዚህ በፊት ትንቅንቁ መጠነኛ የነበረው ግማሹ ስለሚመዘገብ ኖሯል። አሁንማ አንድ አይፋ እንደ አፈር ገልባጭ ገልብጦ በመጣ ቁጥር ሺ መኮንን ይሰፍርበታል። ኋላማ ኢህአዲጎቹም ማስተባበሩን ተውት። ሹፌሮቹ እኛ፤ ተሟጋሞቹ እኛ፤ ምን ችግር አለው?

ሚስቱ ከኋላው ቂጡን እየገፋችው የሚሳፈር አለ። እንሳፈራለን ሲሉ እንደ ኑግ ጆንያ ተንደባለው የሚወድቁ አሉ። አውቅተን እንስቃለን። ከወደቁበት ተነስተው ተፍገምግመው ለመሳፈር ይታገላሉ። ደግነቱ የሞተ ሰው የለም።

"ኧረ ኅበዝ፤ ኧረ ተዋረድን፤ ኧረ ይኸ ቀን ያልፍና ያስተዛዝበናል። ኧረ እረጋ በሉ። የት ለመድረስ ነው?" አሉ አንድ በድሜ ጠና ያሉ መኮንን። ሌላው ቀበል አድርገው:-

"ለካ እንደዚህ ኖረናል? እኛን ያላሸነፉስ ማንን ሊያሸንፉ ኖሯል! የጀኔራሎቹ እጅ አሰጣጥ ሲያስቀን የኛው ብሶ ቁጭ አለ" አሉ ክፉኛ አዝነው።

አይፋዎቹ አንዱ ሲሄድ ሌላው ይመጣል። መኮንኑ ግን ጉደልም አላለ። ደርግ በየወሩ ያስመረቀው ቢዝቁት ቢዝቁት ንቅንቅ አልል አለ። እኔም ወረፋ ሳይደርሰኝ የምሳ ሰአት ደረሰ።

ባካባቢው ካሉት ምግብ ቤቶች በልቼ ለመምጣት በታችኛው በር በኩል ወጣ ስል ከውጭ በግንቡ አጥር ዙሪያ ጥቁር ጥቁር መነፅራቸውን ደንቅረው ተኮልኩለው የቆሙ መኮንኖችን አየሁ። ከወደ ውስጥ የሚወጡትን ጠቀስ እያደረጉ ስለሁኔታው ይጠይቃሉ። ሳያቸው ከትናንት ጀምረው ወደ ውስጥ አልገቡም። የፍርሃትና የጥርጣሬ ሁኔታ ይታይባቸዋል። አብዛኞቹን አውቃቸዋለሁ። ከዚሁ አዲስ አበባ በተለያዩ ክፍሎች ተመድበው ገንዘብ ሲመዘብሩ የነበሩ ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ በቀይ ሽብር ጊዜ የህዝብ ልጅ እንደ ጎመን የቀረደዱ ናቸው። በዚህም ስምና ማእረግ አግኝተውበታል። ከተራ ወታደርነት ባንድ ጊዜ ሻለቃ የደረሱ አሉ። የደርግ ማእረግኮ አንዳንድ ጊዜ የቃቃ ማእረግ ነው። መፈክር ሲያሰማ ድምፀ መረዋ ነው ተብሎ ምክትል አስር አለቃ የተሾመ ወታደር አውቃለሁ። ከዚህ በኋላ ጉረሯቸው እስኪነቃ መፈክር የሚያሰሙ ወታደሮች ነበሩ። ማእረግ ለማግኘት።

ባንድ ወቅት «አብዮታዊ መሪያችን» በምስራቅ ጦር ግንባር ጉብኝት ሲያደርጉ አገራችን በሶማሌ ጦር በተወረረችበት ወቅት ሞፈር ቀንበሩን ሰቅሎ የመጣ ሚሊሺያ መመለሻ አጥቶ ስጥሞ በመቅረቱ የቀድሞ ስራው ትዝ ስላለው በሬዎችን ጠምዶ ሲያርስ ቢያገኙት ባንድ ጊዜ የሻምበልነት ማእረግ አሸከሙት። ዶሮዎችን ሲያረባ የተገኘ ሙቶ አለቃም የሻለቃነት ማእረግ አግኝቷል። እነዚህ ሁሉ «መኮንኖች» ናቸው።

ከውጭ ቁመው ወሬ የሚያነፈንፉትን ላፍታ ያህል ገልመጥ ብዬ አይቻቸው አለፍኩና ካንድ ቀበሌ ምግብ ቤት በመግባት ከያዝኳት አምሳ

ብር ሶስት ብር እንደልኩላት:: ቶሎ ደመወዝ ካልተከፈለን በስተቀር ከችግር ላይ መውደቃችን የማይቀር ነው::

ምሳየን በልቼ እንዳበቃሁ ወጣ ብዬ የህዝብ ስልክ ፈልጌ ለየኔነሽ ደወልኩላት:: ልሰናበታት ፈልጌ ነበር:: ግን «የለችም» አሉኝ::

"ሀሎ! ማታም ደውዬ ነበር:: ላገኛት አልቻልኩም:: በጤናዋ አይደለችም እንዴ?... ታዲያ በጤናዋ ከሆነች ወዴት ደረሰች?... 'ከጓደኛዋ ቤት?' ... እም ...! እሺ::" ብዬ ስልኩን ዘጋሁት:: ከኔም ጋር ለሶስት ቀናት የተፍነሸነሸችው "ጓደኛዬን እሚቷል" ብላ አመካኝታ ነው:: አንዱ የታደለ ለሳምንት ይዟት መሽጓል ማለት ነው:: ሁሉ የሚቀጥፋት::

ተመልሽ ወደ ግቢው ስገባ አሁንም መኪና ላይ ለመውጣት የሚደረገው እርኩቻ እንደ ቀጠለ ነው:: ማየቱ እንኳ ያስጠላል:: መኮንኑ ሁሉ ቂጡን ጥሎ አብዷል:: እይፋ በመጣ ቁጥር ግርር ብሎ መስፈር ነው:: ወዲህ ወዲያ የሚቅበዘበዙ መኮንኖችም አሉ:: ኢህአዲጎቹን ለማማከርም ይቃጣቸዋል:: ቶሎ ለመለጠፍ::

አንድ የብርጌድ የፖለቲካ ሀላፊ የነበረ ሻምበል በኔ አጠገብ ያልፍ የነበረ የኢህአዲግ አባልን እሮጥ ብሎ አስቆመና:-

"ጓድ" አለው ሊያማክረው በመፈለግ::

"ይቅርታ ጓድ አይደለሁም" አለው ኮስተር ብሎ::

"እሺ፤ ጓድ ታጋይ" አለው እንደ ማፈርም እንደ መደንገጥም ብሎ:: ሁለት ማእረግ ባንድ ጊዜ ስላስታቀፈው ነው መሰል ኢህአዲጉ አሁን ፈገግ ብሎ ነበር:: ፈገግታው ግን የንቀት ነበር::

"እንደዚህ እየተንጋጉ መኪና ላይ ሲወጡ ሊጎዱ ይችላሉ:: ተሰልፈው በስርአት ቢሳፈሩ አይሻልም?" ሲለው:-

"ጥሩ ሀሳብ ነው:: በል ሂድና አንተ አሰልፋቸው" ብሎት አብስ:: ጓድ የብርጌድ የፖለቲካ ሀላፊ እንደ ቆመ ቀረ...

እንዲሁ እይን እይን በማየት ብቻ የጉዞ ወረፋ ሳይደርሰኝ ከ12 ሰአት ደረስኩ:: ሰአት እላፊ አንድ ሰአት ላይ ስለሆነ አንዳንድ መኮንኖች እየተጣደፉ ወደየቤታቸው መሄድ ይዘዋል:: እኔም እየተጣደፍኩ ከግቢው ስወጣ ከበሩ ላይ የክፍሌን ባልደረባ ሻምበል አዱኛ ደቻሳን አገኘሁት:: ከወደ ውጭ ሊገባ ሲል ነው ግጥምጥም ያልነው::

"እንዴ! ጎርፉ!" አለኝና ተቃቀፍን:: ከግንቦት 19 ቀን ወዲህ ስንገናኝ የመጀመሪያችን ነው::

"አንተ ደህና ነህ? ተጠፋፋን አይደል" አለኝ ትከሻ ለትከሻ ከተሳሳምን በኋላ:-

"ደህና ነኝ:: አሁን ነው እንዴ የምትመጣው?" አልኩት::

"ኧረ ከዚሁ ነው የዋልኩት:: ለባለቤቴ ስልክ ለመደወል አሁን ነው የወጣሁት::"

"ምን አደዋወለህ:: መሽቷል እንሂድ እንጅ" ስለው:-

"መኪና ላይ ለመሳፈር ያለውን ስቃይ አይተኸዋል? ስለዚህ አንተም ተመለስና ከዚሁ አምሽተን ቅልል ሲልልን መሳፈር ነው:: አለበለዚያ በሳምንትም አይደርሰን" አለኝ::

"ልቅር ብለህ?" አልኩት እንደ ማመንታት እያልኩ::

"ቅር አባክህ" ብሎ ጎተት አደረገኝና ወደ ግቢ ተመለስን:: ጎን ለጎን ሆነን ስንሄድ የሱ ሰውነት ጭርንቅ ብሎ ኮቴው ሳይቀር ይከብደኛል:: በቁመትም ከኔ ዘለግ ብሎ ይታያል::

እኔና ሻምበል አዱኛ እንዳሰብነው በቶሎ ሳንሳፈር ቀረን:: ለካም ሁሉም እንደኛ ልባም ኖሯል:: የተነቃነቀም የለ:: ሄዱ ያልኳቸውም እራታቸውን እየበሉ ተመለሱ:: ምን አይነት ስነስርአት አክባሪ ኖረናል?

ግማሽ ሌሊት የጃንሜዳ ውርጭ መጥቶ ፈሰሰ:: ቆዳ ያኮማትራል፤ አጥንት ይቆረጥማል፤ ጆሮየ ሳይቀር የተነቀለ መስሎኝ ነበር:: ከስር መሬቱ ሲወረዛ ከላይ ያየሩ ቅዝቃዜ እንደ በረዶ ይጠብሳል:: መኪናዎቹ አሁንም ያንጉዛሉ:: ወሰል ያለች ጨረቃ ነበረች:: ልክ እንደ ቀኑ ሁሉ ሌሊትም መኪና ላይ ለመውጣት ግብግብ ነበር:: እኔ እንኳን መኪና ላይ ታግየ ልወጣ ይቅርና ጋደም ካልኩበትም መንቀሳቀስ አልቻልኩም:: እጆቼም፣ እግሮቼም ኩርትምትም ብለው ደንዝዘዋል:: እግዚኦ ነው! እኔ እሳት ብቻ መስሎኝ ነበር የሚጠብሰው፤ ለካም ውርጭም ይሞሽልቃል:: እንዳይነጋ የለም ባይናችን እንቅልፍ ሳይዞር ነጋ::

"እግዚአብሄር ይይልህ አዱኛ! እንዲህ አድርገህ ትጫወትብኝ!" አልኩት::

"ካሁኑ ችግሩን መላመድ አለብህ:: ሄደህኮ ሜዳ ላይ ነው የምትወድቀው" አለኝ::

"ለምን ሜዳ ላይ እወድቃለሁ?"

"ታዲያ ይህን ሁሉ መኮንን የሚችል ቤት ይገኛል ብለህ ታስባለህ?" ሲለኝ ትንሽ ድንጋጤ ተሰማኝና:-

"ለሶስት ቀናት መቼስ የሆነውን ሁሉ መቀበል ነው እንጅ" አልኩት::

"አካና! 'ለሶስት ቀናት?' እንዲህ ከሆነማ ትናንት የሄዱት ነገ ሊመለሱ ነዋ!" በማለት የምፀት ፈገግታ አሳየኝ::

"ታዲያ ለስንት ቀናት ልንቆይ ነው? እራሳቸው ናቸው 'ለሶስት ቀናት ነው የምትቆዩት' ያሉን" ስለው:-

"ጅል! ታዲያ ለወር ለሁለት ወር ወይንም ላመት ሊሉን ኖሯል?" ሲለኝ ቆጣ ብዬ:-

"ምንድን ነው የምታወራው? የሰማኸው ነገር ካለ ንገረኝ::"

"ምንም የሰማሁት ነገር የለም:: ሁኔታውን ስገመግመው ግን ለበጎ ነገር አይመስለኝም:: ቀና ነገር ቢያስቡ ኖሮ እኛን ለሶስት ቀናት ሴሚናር ብለው ካዲስ አበባ ውጭ ማጓጓዝ ባላስፈለጋቸው ነበር" የገዛ ጭንቅላቴ ኮብዶኝ አንገቴን አቀርቅሬ ፀጥ አልኩኝ::

ሻምበል አዱኛ ደቻሳ በሰራዊቱ ውስጥ የረጅም ጊዜ አገልግሎት አለው:: የቀድሞ የክብር ዘበኛ አባል ነበር:: ከረጅም ጊዜ አገልግሎት ካገኘው ልምድ የተነሳ ምን ጊዜም ተጠራጣሪ ነው:: ጥሩ ተጠራጥሯል::

ወጣ ብለን ቁርሳችንን በልተን ተመለስን:: ዛሬ ደግሞ የመጨረሻ እለት ስለሆነ እድፍጦ የነበረው ሁሉ በመምጣቱ ጃንሜዳ ተጨነቀች:: ከረፋዱ ላይ እንደምንም ታግለን ተሳፈርን:: ለሶስት ቀናት የተሃድሶ ሴሚናር ወደ ሆለታ ተወሰድን::

ምእራፍ አራት

ደርግ ሲያቃጥለኝ ሲያንገበግበኝ፣
ልፀድቅ ነው መሰል በኢህአዴግ ጊዜ ገነት ገባሁኝ።

10

ለስራ ጉዳይ ወደ ወለጋ ክፍለ ሀገር ወይንም ወደ አምቦ የሚሄድ ሰው ካዲስ አበባ ሲነሳ የምእራብን አቅጣጫ መያዝ አለበት። ገፈርሳን አልፎ ከመናገሻ ጋራ ጎን ያሉትን የወልመራን ኮረብታዎች ሲዳፋ መንገዱ ወገብ ለወገብ ሆኖ ጠመዝማዛና በደን የተሸፈነ ነው። ቢሆንም ከታች ከረባዳው ላይ የተንጣለለውን ሜዳ ተንተርሳ የከተመችውን የሆለታ ከተማን ከማየት አያግድም።

የወልመራን ጠመዝማዛ መንገድ እያሽቆለቆሉ ሄዶ ከዙበጡ እንደ ደረሱ በሽንጣም አውቶቢስ አለዚያም ባነስተኛ መኪና ፍጥሎ ሆለታ መግባት ነው።

ለመዝናኛ የሚሆኑ አውቅ ሆቴሎች ባይኖሩም ካሉት መጠነኛ ሆቴሎች ውስጥ ካንዱ አረፍ ብሎ በተለይም በረንዳ ላይ ወንበር ይዞ በመቀመጥ ንፁህ አየር እየተመገቡ በርቀትም፣ በቅርበትም ሲታዩት ስሜትን ይማርካል። አፄ ምኒልክ ተሳስተዋል፤ ዋና ከተማቸውን ከዚህ ነበር መመስረት የነበረባቸው ያሰኛል።

በስተምስራቅ የመናገሻ ጋራ እንደ ጋሻ ጃግሬ ተገትሮ ከዱጋ የሚጠብቃት ይመስላል። ከንጣጠ ጀምረው እንደ ሰንሰለት ተቆጣጥረው የሰሜንን አቅጣጫ በመያዝ ወደ ሙገር የሚያልፉት የወልመራ ኮረብታዎች ጎርፍ ገድበው የሚያስቀሩላት ይመስላሉ። በደን ተጀቡነው በመኮፈስ።

ወደ ምእራብ አቅጣጫ ደግሞ ከትንንሽ ጉብታዎችና ሸለቆዎች በስተቀር በቆ ድረስ ያለው መሬት ለጥ ያለ እረባዳ ነው። ወደ ደቡብ በኩል ግን አይን እስኪታክት ድረስ መመልከት ይቻላል።

ገነት ጦር ትምህርት ቤት የሚገኘው ከከተማዋ በስተደቡብ በኩል ከዳር ላይ ነው። ገነት ጦር ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት የጦር ትምህርት ቤቶች ባንጋፋነቱ ቀደምትነትን ይይዛል። ካምሳ አመት በላይ እድሜ አለው። የመጀመሪያዎቹን እጩ መኮንኖች ለማይጨው ጦርነት አውጧል።

ከትምህርት ቤቱ ግቢ እንደ ተገባ ከፊትለፊት እረጅም ሀውልት ተገትሮ ይታያል። በርቀት ሲያዩት «እንኳን ደህና መጣችሁ» የሚል ይመስላል። እየቀረቡት ሲመጡ ግን ተወርውሮ የሚከመር ነው የሚመስለው። ጣሊያን የዚሁ ትምህርት ቤት አባል የነበረውን ካዋር ላይ ባይሮፕላን ወርውሮ ስለገደለው ለዚያ መታሰቢያ የቆመ ሀውልት ነው። ካናቱ ላይ የብረት ቆብ የደፋ እግረኛ ወታደር እረጅም ጠመንጃ ይዞ አንድ እግሩን ነቅሎ ለመሮጥ ሲወረወር የሚያሳይ ምስል ነው።

ሀውልቱ ያለበት አካባቢ መሬቱ በመጠኑ ኮራ ያለ ስለሆነ ከዚያ ሆነው ወደ ፊትለፊት ባዘቅዛቂ ሲመለከቱት እመሀል ለጥ ያለ አስፋልት

አለ። ግራና ቀኝ ከላይ እስከታች የመማሪያ ክፍሎቹና የቢሮ ህንፃዎች በረድፍ በረድፍ ተከፋፍለው አሉ። ከበስተጀርባው ደግሞ ትንሽ ፈቀቅ ብለው የእጩ መኮንኖች የመኝታ ክፍሎች ይገኛሉ።

ከአስፋልቱ መጨረሻ ላይ አንድ ትልቅ አዳራሽ አለ። ግማሹ የእጩ መኮንኖች የመመገቢያ አዳራሽ ሲሆን ግማሹ ደግሞ ቤተ መፃሕፍት ነው። ከዚሁ አዳራሽ ከወዳናቱ በኩል ያንድ ህፃን ስእል ይታያል። የብረት ቆብ ደፍቶ በሁለት እጆቹ የብረት ቆቡን አንቆ ይዟል። ሲሮጥ እንዳይወድቅበት የያዘው ነው የሚመስለው። ሁለት እግሮቹን ከቋንጃው ሽብረክ አድርጎ ፊቱ የፈካ ቢመስልም ልብ ብሎ ላስተዋለው ግን የበረገገ ፊት ነው። ያጠለቀው ቦት ጫማ ደግሞ ከቋንጃው ደርሶ ከልጁ በልጧል። ከስእሉ አጠገብ የተፃፈው መፈክር «እኔም እንዳባባ!» ይላል። እንደ ገባኝ ከሆነ «እኔም እንዳባባ ወታደር ሆኜ አገሬን እጠብቃለሁ ወይንም ጀግና እሆናለሁ» ማለት ነው። ነገር ግን የራሱን ቆብ በሁለት እጆቹ ጨምድዶ ይዞ ቋንጃውን ሽብረክ አድርጎ ሳየው «እኔም እንዳባባ ልፈትለክ» ያለ ነው የሚመስለኝ።

«ያብዮታዊ መሪያችን» አባባልም ካዳራሹ እናት ላይ በጉልህ ተፅፎ ይታያል። እጩ መኮንኖችና አሰልጣኝ መምህራን በጧት በማታ እንጋጠው እያዩ በምሳሌነቱ እንዲጠቀሙበት ታስቦ ነው።

«ማየት ማመንን ያጠናክርልናል። በምሳሌነትም መታየትን የመሰለ ዋናና ውጤታማ የማስተማር ዘዴ የለም!» ጓድ መንግስቱ ሀይለማሪያም። እኛም አይተን፣ አስተውለን እርእያንታቸውን ተከትለናል። በምሳሌነትም ተጠቅመንበታል...

ትምህርት ቤቱ የተገነባው አዳዲስ ከተጨመሩት ህንፃዎች በስተቀር በጥርብ ድንጋይ ነው። ይህም ጥንታዊነቱን ያስመሰክርለታል።

ግቢው በጠቅላላ በአበቦችና በጥድ ተክሎች ተውቧል። በተለይ የጥድ ተክሎቹ ባጭሩ ተከርክመው ሲታዩ የጥንቱን ነፍጠኛ ያስታውሱናል። ባጠቃላይ ግቢው ከላይ እስከታች በልምላሜ የከበረ ነው። ተመልካችን ያማልላል። እውነትም ገነት ሊባል ይገባዋል።

ከጦር ትምህርት ቤቱ በስተምእራብ በኩል አንዲት ክብ ኮረብታ አለች። ከሷ እናት ላይ ያፄ ምኒልክ ቤተ መንግስት አለ። ኮረብታዋ በሆለታ ዙሪያ ያለውን በሙሉ ቁልጭ አድርጋ ታሳያለች። ለመመልከቻነት ይሆነኝ ተብላ የተሰራች ነው የምትመስለው። ለዚህም ይመስላል አፄ ምኒልክ ቤተመንግስታቸውን ካናቷ ላይ ያሰሩት።

ህንፃው ባላንድ ፎቅ ሆኖ ግዙፍ ነው። አንዱም ግዝፈት የሰጠችው ኮረብታዋ ነች። ልክ ከሞሶብ ላይ የተከደነ ወስከንቢያ ነው የሚመስለው። የህንፃው አሰራር ቤተ ንጉስ የሚባለው አይነት ሆኖ ከስፋቱ የተነሳ ብዙ ክፍሎች አሉት።

ይህ ቤተመንግስት ይዞት የነበረው ቤተ መዘክር፣ የመኮንኖች የግል ማህደር፤ የትምህርት ቤቱ የህትመት ክፍል፣ ሙዚየም፣ የትምህርት ቤቱ ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱም የታሪክ ቅርሶች... ባጠቃላይ ብዙ ነገሮችን አቅፎ ነበር። እነዚህ ሁሉ ዛሬ ወድመዋል! አንዳችም የታሪክ ቅርስ አልተረፈም።

ዛሬ ቤተመንግስቱ ከሚችለው በላይ መኮንኖች እንደ ንብ ሰፍረውበታል:: ባብዛኛው መኮንን ፎቁ ይደረመሳል የሚል ስጋት አለ::

ወደፊት ገነት ጦር ትምህርት ቤትን መልሶ ለመገንባት በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ይጠይቃል:: ይህም ሆኖ በፅሁፍ የሰፈሩ፣ በስእል የተደገፉ ታሪኮችን ማግኘት አይቻልም:: ያውምኮ የወደመው የታሪክ ቅርስ ከመቶ አመት ወዲህ የተከማቸው ነበር:: የታሪክ ነገር ታሪክ በላው!

ይልቅየ ከዚህ ሁሉ መአት ተርፋ ያብዮታዊ መሪያችን የግል ማህደር ተበጫጭቃ አገኘኋት:: ጨርሳ ሳትወድም መቅረቷ ያስደንቃል! እሳቸውስ ከዚያ ግንዲላ ባለስልጣን መሀል ሾልከው ሄደው የል:: ከፍላት የወጣ ባቄላ ይሏል እንዲህ ነው!! እንደ ጲላጦስ «ከፈሰሰው ደም ንፁሀ» ቢሆኑ አይደል!

የግል ማህደራቸው የያዘችው ቁምነገር:-

1ኛ «እጩ መኮንን መንግስቱ ሀይለማርያም» በጠቅላላው የተሰጠውን ትምህርት ተቀብሏል::

- የመሳሪያዎች
- ጠቅላላ ትምህርት
- የጦር ስልትን ተምሮ የሶስቱ ውጤት ተደምሮ ለሶስት ተካፍሎ 67.2 አምጥቶ ከ115 ተወዳዳሪዎች መካከል 80ኛ ሆኖ አልፍዋል::

2ኛ «ይህ እጩ መኮንን የሚሰጠውን ትምህርት የመቀበል ችሎታ ያለውና አስፋፍቶ ለማስተማር የሚችል ሲሆን ስነስርአት አክባሪነቱ ግን አጥጋቢ አይደለም:: የበላዩን የሚቃወምና ትቢተኛ ነው:: ነውሩን ለመሸፈን ሲል ብዙዎቹን ነገሮች በማስመሰል ይናገራል:: ተንኮል ስራ ውስጥ ለመግባት የመጀመሪያ ሰው ነው:: ነባር እውቀቱ 7ኛ ክፍልን የጨረሰ ስለሆነ ደህና ነው:: በጥብቅ አዛዥነት ስር በማንኛውም ቦታ ቢደለደል ሊሰራ ይችላል::»

ፊርማ የትምህርት መሪ መኮንን የተማሪዎች የሻምበል አዛዥ::

«አብዮታዊ መሪያችን» ገና ከማለዳው የተነገረላቸውን ትንቢት አሟልተዋል ማለት ነው:: «በማንኛውም ቦታ በጥብቅ አዛዥነት ስር ቢደለደል ሊሰራ ይችላል» ተብሎ የተነገረላቸው «አስተዋዩ መሪያችን» ያለጠባቂ ተለቀው ኢትዮጵያን ሰው አልባ አስቀርተው እሳቸው ፈረጠጡ!

11

አካባቢያችን ሙቀታማና ነፋሻማ ነው:: ሰሞኑን ደግሞ ሳይዘንብ አይቀርም:: ደመናው ይጉለመለማል:: ከውጭ የፈሰሱት መኮንኖች ተፈጥሮን እንዴት አድርገው በቁጥጥራቸው ስር እንደሚያደርጓት እንጃላቸው::

ምን አይነት የታሪክ አጋጣሚ ነው? ይህ አንጋፋ የጦር ትምህርት ቤት በየጊዜው ያሰለጠናቸውን በህይወት ያሉትን ባሁኑ

ወቅት ካንድ ላይ አሰባስቦ እያሳሳመ ነው:: በ20 አመታቸው ተመልሰው ትምህርት ቤቱን የረገጡት አሉ:: በዚህ ላይ «አብዮታዊ መሪያችን» በየጦር ሜዳው ማእረግ የለጠፉላቸው ዛሬ "ኮርሰኞች" ሆነዋል:: እንደገና ደግሞ ያየር ሀይል፣ የባህር ሀይል፣ የፖሊስ ሰራዊት መኮንኖች አብረው ተቀላቅለዋል:: ወያኔዎችን፣ "በታኞች!" ይሏቸዋል እንጂ እኛንስ ሰብስበውናል:: ምናልባት ከህብረተሰቡ ተነጥለን እንደ ሆነ እንጅ እኛስ አዲስ ታሪክ ከፍተናል::

ገሚሱ መኮንን የሰፈረው ከላይ ታንከኛ ማሰልጠኛ ከነበረው ነው:: ሙሉጌታ ቡሊ የቴክኒክ ትምህርት ቤትን ሁሉ ይጠቀልላል:: ይኸም 2ኛ ክፍለ ጦር ተብሎ ተሰይሟል:: ግማሹ ደግሞ ከዋናው ትምህርት ቤት ነው የሰፈረው:: ይኸ ደግሞ 1ኛ ክፍለ ጦር ተብሏል:: እኔ ያለሁት ከሁለት ጓደኞቼ ጋር 1ኛ ክፍለ ጦር ውስጥ ነው:: አንደኛው ከጃንሜዳ ጀምሮ አብሮኝ የመጣው ሻምበል አዱኛ ደቻሳ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሻምበል በድሉ ጫኔ ይባላል:: ጥሩ ክፍል አግኝተናል::

ከውጭ በየጥጉ፣ በየበረንዳው የፈሰሰው መኮንን ለጉድ ነው:: አዳራሾች፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ ቢሮዎች ጢቅ ብለው ሞልተው ከዚህ የተረፈው ነው እንግዲህ ውጭ የፈሰሰው:: ትንሽ እርሾ ያላቸው ከቤታቸው ድንኳን አስመጥተው ወጣጥረዋል:: በዚህ ሰባያ ታዲያ ብዙ ጥፋቶች ጠፍተዋል::

እነዚያ የሚያማምሩ የጥድ ተክሎች ወድመዋል:: አበቦች ጨርሰው የሉም:: የሰውም እግር እንደ እሳት ነው መሰል በጥቅጣቆ ከስለዋል:: ትምህርት ቤቱ ተዘርፎ የጠበቀን ቢሆንም እኛም ድርሻችንን አበርክተናል::

መፃህፍት እየተቀደዱ ለመጻታ ጉዝጓዝነት ውለዋል:: ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካና አሜሪካ ግንጥልጥል ብለው ድራሻቸው ጠፍቷል:: ወታደራዊ ካርታዎች እየተገነጠሉ ለምንጣፍ ውለዋል:: ጥቁር ሰሌዳዎች ከየተሰቀሉበት እየወረዱ በየጥጋጥጉ ለመኝታ ከለላ ውለዋል:: ወንበሮችና ጠረጴዛዎች ከየክፍሉ እየወጡ ባመቻቸው ቅርፅ በፋስ እየተፈለጡ የለት ጎጆ ተቀልሶባቸዋል:: የሶስት ቀናት የተሃድሶ ሰሚናር ንብረቶችንም እያደሰ ነው:: እኛን ብቻ አልሰባበረም::

የሚገርመው ግን ተቀዳደው ለምንጣፍ የዋሉትም ሆነ የተጣሉት የምእራባውያን መፃህፍትና የኛዎቹ ናቸው:: የምስራቃውያን ግን ከተደረደሩበት እንኳን ተንሸራተው አልወደቁም:: ክርችም ብለው እንደ ተደረደሩ ናቸው:: ከዚያው ቤተ መፃህፍት ከሚገኙት ውስጥ አንዱን መኮንን:-

"ምናለ ዓድ ጠቃሚ የሆኑትን መፃህፍት ባትቀዳድዷቸው:: ይልቅ እነዚህን ብትቀዳድዷቸው ይሻል ነበር" ስለው:-

"የነዚህን ውሾች መፅሀፍ መንካትም አያስፈልግ!" አለኝ:: ቢጨንቀኝ ሳኩኝ፡፡ ለካም መጣላትም ያስከብራል::

አንድ የፈረደበት መኮንን ታዲያ ከዚህ ሁሉ ዘረፋ የተረፈ አንድ ፖኬት ደስጣ ወረቀት አግኝቶ ከተማ ወስዶ ሊሸጥ ሲል ተይዞ ዛሬ ቧት በኛ ፊት ተሸክሞ ዞሯል:: እኛ እንኳን መታወቂያው ከኪሱ ተገኘበት እንጅ "የከተማ ዱርየ አምጥታችሁ አትስደቡን" ብለን ነበር:: ይኸም ሆኖ አልተረታንም:: "መንግስቱ ሀይለማርያም ከየበረንዳው

እያፈሰ ማእረግ የለጠፈለትን ሁሉ ሰብስባችሁ አትስደቡን!" ብለናቸው ስብሰባውን ጥለን ተበተን::

ለሶስት ቀናት ሴሚናር ተብለን መጥተን ሁለተኛ ሳምንታችንን ይዘናል:: እስካሁን ምንም አይነት ወሬ የለም:: ሻምበል አዱኛ ደቻሳ አስቀድሞ አውቆታል:: አስር ጊዜ የሚሉን:-«ተመዝገቡ» ነው፤ እስካሁን ወደ አምስት ጊዜ ተመዝግበናል:: ቁምነገር ያለው አይደለም:: ዝም ብለው አስቀመጧቸው እንዳይባሉ ነው:: ስም ከነ ማእረግ፣ ያባትና ያያት ስም፣ የትምህርት ደረጃ፣ ያገልግሎት ዘመን፣ የጦር ክፍል፣ ልዩ ሙያ የሚል ይሞኝበታል:: አንድ ጊዜ ብቻ የተመዘገብነው ይበቃ ነበር::

ግን ደርግ እንዴት አድርጎ ባምሳሉ ቀርፆን ኖሯል? ዛሬ ነው በውል ያጤንኩት:: የሚገርም ነው፤ መቶ አለቃው ሻምበል፣ ሻምበሉ ሻለቃ ነኝ እያሉ ማእረግና ደመወዝ እየጨመሩ የተመዘገቡ ብዙ ናቸው:: እኔ እንኳን ሁለት የማውቃቸውን መኮንኖች ባይኔ አይቼ ታዝቤያለሁ:: አንደኛውንማ ሻምበል አላስችል ብሎኝ::

"ከመቼ ጀምረህ ነው ሻለቃ የሆንከው ጓድ ሻለቃ?" ብዬ ጠየኩት:: እንደ ማፈር ብሎ:-

"በሚያዝያ ወር ተሰጥቶኝ ነበር:: ሳልበላበት ጉድ ሆንኩኝ እንጅ" አለኝ:: እኔ ግን ከግንቦት ሀያ በፊት የሻምበል ማእረጉን አድርጎ አይቼዋለሁኝ::

የኢሰፓ አባል የነበሩትም፣ «አይደለንም» እያሉ ተመዝግበዋል:: ይኸ ሁሉ ቀላል ነው:: እኔን የከበደኝ ኢህአዲግ ለተማሩ መኮንኖች ልዩ ቦታ ይሰጣል የሚል ወሬ ስለተናፈሰ ጥቂት ብልጦች ዲግሪ አለን እያሉ መመዝገባቸው ነው:: ማስረጃ አቅርቡ የተባሉ እንደ ሆን መቅለላቸው ነው:: አንዱን መቶ አለቃማ ጥቁር አንበሳ ትምህርት ቤት 11ኛ ክፍል በማታው የትምህርት ክፍለ ጊዜ የሚማር መሆኑን ደህና አድርጌ አውቃለሁኝ:: መቼም ኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግር ነው ያለባት ብሎ ነው መሰል፣ «በፖለቲካል ሳይንስ ምሩቅ ነኝ» ብሎ ምዝግብ:: ቀና ሲል እኔን ከጀርባው ቁሜ ወረቀቱ ስጠብቅ አየኝ፤ ቢሞት በወደደው:: "አይዞህ" አልኩት:: እውነቴን ነው:: መመኘት ወንጀል አይደለም:: ባይሆን ትንሽ በዛ እንጅ::

በስነ ምግባር ብልሹነት ከሰራዊቱ የተባረሩም ተገልለው የቆዩባቸውን አመቶች ሁሉ ደማምረው፣ ደመወዛቸውንም ጨምረው ተመዝግበዋል:: መቼም ነገረኛ ነኝ አንዱን መቶ አለቃ ጠጋ ብዬ:-

"ጓድ መቶ አለቃ! ከሰራዊቱ ተሰናብተህ አልነበረም እንዴ? መቼ ተመለስክ? ነው ጥረው አንተንም ይመለከታል?" አልኩት:: ይኸስ የዋዛ አይደለም::

"አንተንስ ከምንየው ኢህአዲግ መለመለህ?" ብሎ ቀንዶን አለኝ::

በርካታ ወታደሮችም፣ «መኮንኖች ነን» እያሉ ተመዝግበዋል:: ይህ ሁሉ ሲሆን ኢህአዲጎች ዝም ብለው መመዝገብ ነው:: ማስረጃ አይጠይቁም:: ነገረ ስራቸውም አያምር::

ተመዝግቤ ስመለስ የቀድሞ አለቃየን፣ ኮሎኔል ዘርጋውን አገኘኋቸው:: እሳቸውም ተመዝግበው መመለሳቸው ነበር::

"ደህና አርፍደሃል ጎርፉ" አሉኝ:: እኔን ሲያዩ ፊታቸው በመጠኑ ፈታ አለ እንጅ ተከፍቶ ነበር::

"ደህና ነኝ ጌታዬ፤ እስዎስ በርትተዋል?"

"ምኑን እበረታዋለሁ ብለህ፣ ተለዋውሼ" አሉ ፊታቸው መልሶ እየጨፈገገ:: ጊዜ ጣላቸው እንጅ እንዴት ያሉ ጀግና ነበሩ:: የሶማሌ ሰራዊት የሳቸው ስም ሲጠራ መድረሻ ነበር የሚያጣው::

"አይዞዎት ጌታዬ! ሁሉም ነገር ያልፋል::"

"በርግጥ ያልፋል:: ግን ደግሞ እስከሚያልፍ ያለፋል" ፊታቸው እየቀደመ ይጨማደድ ጀመር::

"ቢሆንም መበርታት ነው::"

"በልስቲ" አሉኝና "ለመሆኑ በየቀኑ ተመዝገቡ የሚሉን ለምንድን ነው? የዛሬውም ከመሰንበቻው የተለየ ነገር አላየሁበትም" አሉኝ::

"ጊዜ ለመውሰድ ካልሆነ በስተቀር ምንም አይነት ልዩነት የለበትም::" እያወራን ሄደን ከህውልቱ ስር ተቀመጥን::

ኮሎኔል ዘርጋው በረጅሙ ተነፈሱና ፊታቸውን ቅጭም አድርገው:-"አንድ አባባል አለኮ ጎርፉ" ሲሉኝ:-

"ምን?" አልኳቸው ቀልጠፍ ብዬ::

'ትንሽ ሰው ትንሽ ነው ከትንሽ አትዋሉ!
አጥፍቶ ጠፊ ነው አገርን በሙሉ' የሚል::

"እየውልህ! ደርግ እሱም ጠፋ፤ አገሪቱንም አጠፋ:: እኛም ከሱ ተጠግተን ጨኽን ጨኽን በመጨረሻ መፈክር ብቻ ታቅፈን ቀረን:: እስበውስቲ ግራ እጃችንን ወጥረን፣ 'ይውደም! እናወድማለን!' ብለን እኛ ወደምነው:: አባቶቻችን 'አረጋሚ ተረጋሚ ነው' ይላሉ:: 'ስር ነቀል አብዮት!' እያልን ተነቅለነው ቀረን::" አገሪቱንም እስከ ወዲያኛው ድረስ እንዳትነሳ አድርገን ነቀልናት::

"አየህ፤ ህዝብ ያልተቀበለው መሪ ምን አዋቂ፣ ምን ብልህ ቢሆን አገር ሊመራና ሊያስተዳድር አይችልም:: የመንግስቱ ችግርም ይኸው ነበር:: ጀኔራሎቹ ከፊት ለፊቱ፣ 'አብዮታዊ መሪያችን! ቆራጡ!' ይሉታል:: ዘወር ሲል ግን 'ይህ ቅርንዲላ! እንዴት በሱ እንመራለን?' እያሉ ይዶልቱበታል:: እሱም እንደሚዶሉቱበት ደህና አድርጎ ያውቃል:: ለዚህም ነው በየምክንያቱ አንድ ባንድ እየገደለ የጨረሳቸው:: የቀሩትም መፈንቅለ መንግስት ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀረ:: ያው እነሱም አለቁ:: በመጨረሻም ጠሩ ያለ መሪ ቀረና ተበታተነ:: የኔ ስጋት ታዲያ ዛሬ ምን እንደሆነ ታውቃለህ?" አሉኝ ወደኔ መለስ ብለው::

"ምንድን ነው?" አልኳቸው እኔም ወደሳቸው አትኩሬ እየተመለከትኩ::

"መቼም ለመሪ አልታደልንም:: መሪ የምናገኝ አይመስለኝም:: ሰውኮ የለም:: ታመትሯል!"

"ልክነዎት ጌታዬ! የኔም ስጋት ይኸው ነው:: እንዳሉት መንግስቱ ሀይለማርያም በህብረተሰቡ ዘንዳ ተቀባይነትን ባለማግኘቱና

በግል በተጠናወተው ባህሪው በጭፍጨፋ ለመግዛት ሞክሮ አልተሳካለትም። እንፀባራቂ ታሪክ እመሰርታለሁ ሲልም አሳፋሪ ታሪክ መሰረተ።"

"የመሪ ነገር ባፍሪካ ምድር እንደ እርግማን ተቆጥሮ በየጊዜው ጡንቸኛ እየተነሳ ያለውን ይዘርፋል፤ የተረፈውን ያወድማል። ልክ እንደ ባእድ ወራሪ። ይህም ለመሪ አለመታደል ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ትናንት በጦርነት፣ ትናንት በርሃብ የተንገረገብነው ይበቃን ነበር። ያለም መሳቂያና መሳለቂያ ሆነናል። ሌላው ቢቀር ካለፈው ውድቀታችን እንኳን ልንማር በተገባን ነበር።

"መንግስቱ ሀይለማርያም ሶሻሊዝምን ከሶቭየት ህብረት እንደ ሸቀጥ ባንቴናብ ጭና በማምጣት፣ 'ለሰላም፣ ለእኩልነት፣ ለብልፅግና፣ ለዲሞክራሲ...' እያለ ኢትዮጵያን 'የዳቦ ቅርጫት አደርጋታለሁ' በማለት አስራ ሰባት አመታት አናፍቶ አናፍቶ ሰውም ንብረትም አውድሞ ሲጨርስ ጥሎ ፈረጠጠ!

"አፄ ቴዎድሮስ ላገራቸው ክብር ሲሉ ሽጉጣቸውን በመጠጣት ህይወታቸውን አሳልፈዋል። መንግስቱ ግን ክብር የሌለው ሀሊና ቢስ በመሆኑ ያገሪቱን ክብር ባለም ፊት አስገፍፍዋታል። ኢትዮጵያ እንዲህ አይነት መሪ በታሪኳ ውስጥ አጋጥሟት አያውቅም! ይኸ ሁሉ ውርደት የደረሰባት እንግዲህ ከመጀመሪያው አእምሮው የበሰለ መሪ በማጣታችን ነው። ያለፈውስ አለፈ፣ ዛሬ ምን ይበጀን?"

"እምን አስገፍፍዋታል። ክብር አሳጥቷታል።"

"የዛሬው የበለጠ ያሳስባል። ሶቭየት ውስጥ አሜሪካ ገብታለች። ያጣቻትን ኢትዮጵያን እንደገና ጨብጣለች። መመሪያችን ማርክሲዝም፣ ሌኒኒዝም መሆኑ ቀርቶ 'ካፒኒዝም' ወይንም 'ዲሞክራሲ' ሆኗል። እጣ ፈንታችን ሆኖ የመጣውን መቀበል እንጅ የመቃወም ወይንም የማስተካከል እድሉ ተሰጥቶን አያውቅም። የማርክሲዝም የሌኒኒዝም ፍልስፍና ያጎናፀፈን ፀጋ ረሃብ፣ ጦርነት፣ ስደት እንደሆነ ሁሉ ዲሞክራሲም ዘረኛነትን፣ ጎሰኝነተን ይዞልን መጥቷል። ተበታትነው እናርፈዋለን። ይኸ ሁሉ የመሪዎች ገፀ በረከት ነው።

"በመሰረቱ ዲሞክራሲ በራሱ ሰላም አያመጣም። ሶቭየት ህብረት ኢትዮጵያን በአፍሪካ የሶሻሊዝም ሞዴል እንዳደረገቻት ሁሉ ዛሬ ደግሞ አሜሪካ የዲሞክራሲ ሞዴል ልታደርጋት ሽርጉድ እያለች ነው። ይህን ሴራ ማክሸፍ ያለበት ህዝቡ ነው።"

"እምን፤ ህዝቡ ነው ከንግዲህ የድሉ ወሳኝ መሆን ያለበት፤ አለበለዚያማ ምኑን ዲሞክራሲ ሆነው? ያሜሪካን ህዝብ ራሱም አይደል መሪውን የሚመርጠው? የኛም ህዝብ መሪውን መምረጥ መቻል አለበት" አሉኝ።

"አንድ ቁም ነገር ግን አለ ጌታዬ፤ ደርግ ሶሻሊዝምን አራምዳለሁ ብሎ በፈጠረው ጭፍን አመራር ራሱ ባጠመደው ወጥመድ ገብቶ እንደ ተሽመቀቀ ሁሉ እነዚህም ዲሞክሲን እናራምዳለን ብለው ጀምረው ከመርሁ ካፈነገጡ ያው የደርግ እጣ ይጠብቃቸዋል። በዲሞክራሲ የተሸፈነ የጎሳ መርህ ጎስ ሆነው እንዳይቀሩ እሰጋለሁ።"

"እህ፤ እኛንም ጎስ አድርገው እንዳያስቀሩን እንጅ ጎርፉ" አሉ፡- እንደ መሳቅ ብለው።

ለትንሽ ጊዜ ወጭ ወራጁን እያየን ዝም ብለን ቆየንና "እንዲያው ግን ይኸ ሁሉ መኮንን ነው ብለህ ታስባለህ? እኔማ የመርካቶ ዱርዬ ሁሉ አብሮን መጥቷል እያልኩ አስባለሁ።"

"ግምትዎ ልክ ነው። ቦርድ የወጡና በስነምግባር ብልሹነት ከሰራዊቱ የተባረሩ ሁሉ መጥተዋል። የማውቃቸውን አግኝቻለሁ። የመኮንንነት ክብር ከቀረ ቆይቷል ጌታዬ።"

"ልክ ነህ። የሞትነው ለክብራችን መሞት ሲያቅተን ነው። ለዚህ ደግሞ ስምና ክብር የሌላቸው ግፈኞች መሩን! ስማልባ ሆነን ቀረነው" አሉና በፀፀት ራሳቸውን ነቀነቁ። እውነታቸውን ነው። ጥሩ ስም ነበራቸው። ዛሬ ግን ስም የላቸውም። እናታቸው ያወጡላቸው ስም ዘርጋው ብቻ። ማእረግ ይጨመር ከተባለም፡- «የደርግ ኮለኔል» ተብለዋል። የምስራቁ ጀግና ለዚህ በቅተዋል።

ከኮለኔል ዘርጋው ጋር ጨዋታ ይዘን ሳይታወቀን ከምሳ ሰአት ደረስን። መኮንኖች ሲሰለፉ ይታየኛል።

"ጌታዬ፤ የምሳ ሰአት ደርሷል፤ እንሂድ" ስላቸው፡-

"ትንሽ ያገልግል እንጀራ አለችኝ፤ እንሂድና እሷን እንካፈላት" አሉኝ፣ ከተቀመጡበት እየተነሱ።

"እንግዲያው እሷን እርስዎ ይጉረሷት። እኔ ልሂድና ከብዙሃኑ ጋር ልጋፋ" አልኳቸውና ቀደም አልኩኝ።

"ተው ግዴለህም" አሉኝ ከተል እያሉኝ።

"ግዴለም ጌታዬ፤ በሌላ ቀን ይጋብዙኛል" ብያቸው ነጠቅ ነጠቅ እያልኩ ተራመድኩ።

የምግብ ቤት ሰልፍ በመጠኑ ተሻሽሏል። ችግሩ ሊቃለል የቻለውም ሁለቱም ክፍለ ጦሮች ለየራሳቸው ምግብ ቤቶች በመክፈታቸው ነው። ምግብ ቤት ተከፍቶ ስል ግን ላላወቀ እንጀራ ተጋግሮ፣ ወጥ ተሰርቶ የሚሰጠን ሊመስል ይችላል። ደረቅ ኮቸሮና ሻሂ ነው። አልፎ አልፎ በአራት ሰአት መኮረኒ ይቀቀልልናል።

ይልቅየ ይህን ሰሞን አንድ በላስቲክ የታሸገ ምግብ ታድሎናል። አንዱ እሽግ ለሁለት ለሁለት ነው የተሰጠን። በፈረንጅኛው ፅሁፍ ግን «አንድ ላንድ» ይላል። ምናልባት አንዱ የፈረንጅ ሆድ ሁለት ያበሻ ሆድ ይወጣው ይሆን እንጃ? በርግጥም ውቅያኖስ አቋርጦ፣ አየር ሰንጥቆ መጥቶ እንኳን የበሰለውን ጥሬውንም ቁርጥምጥም ነው የሚያደርገው። ይህም ሆኖ የፈረንጅን ሆድ የሚያጠግብ ነገር የለም።

መቼም የምእራቡ አለም ደግ ነው። ቀለምና ነገር የበላው ነው። ጦርነት ቢያስነሳም መድሃኒት ይልካል፣ ጥሬ እቃ ቢመዘብርም መልሶ እርዳታ ይሰጣል። ለኛም ይህን ሰሞን ከምግቡ ሌላ አንድ የምእራብ በጎ አድራጊ ድርጅት ብርድ እንዳይበርደን በማሰብ ብርድ ልብስ ልኮልን ነበር። የት እንደገባ እጣነው እንጃ። ብርድ ልብሱ ግን ቢሰወርም ተገቢ ነው። ቡስቅ ያለ ነው። ይኸ ሁሉ እያቆሰለን ነው። የሚያቆስለንስ ሞልቷል። ገና ምን ተይዞ...

12

ገነት ጦር ትምህርት ቤት ከገባን ጀምሮ በትምህርት ቤቱ አጥር ዙሪያና በግቢው ውስጥ ለውስጥ ሻሂና ቡና አፍሊዎች እንደ አሸን ፈልተዋል። እኛ ደግሞ እየገዛን መጠጣት ነው። በተለይ ኮሪዳ ቤጤ ከሆነች አስር ሀያው መኮንን ከቦ ዝንብ ሲከላከልላት ይውላል። ጭሱ ተጥመልምሎ ወደ ሰማይ ሲወጣ ህዳር ሚካኤል የታጠነ ይመስላል። ካጥሩ ወጣ ሲሉ ደግሞ አረቂው ለጉድ ነው። ያን እየለጉ የሚደነፋ መኮንኖች ብቅ ብቅ ማለት ይዘዋል።

ዛሬ ተረፋዱ ላይ ካንዱ መኝታ ክፍል ስገባ ስድስት መኮንኖች ውስኪ አቅርበው ይጠጣሉ። ሁለቱ ገንዘብ ቤቶች ሲሆኑ አራቱ ደግሞ ደመወዝ ከፋዮች ናቸው። እንዴት ተጠቃቅሰው እንደ ተገናኙ ደግሞ ገረመኝ። ድፍረታቸውስ። ሰው ለካ ተስፋ ሲቆርጥ እንደዚህ ነው። ሞቅ ስላላቸው አስተውለው እንኳን አላዩኝም። እኔ ግን ባይኖቼ ፎቶ አንስቻቸው ወጣሁና ወደ ሀውልቱ ሳቀና ኮለኔል ዘርጋውንና በድሉን ቁመው ሲያወሩ አየኋቸው። ሄጀ በመጨመር፦

"እግር ጥሎኝ ካንድ ክፍል ገብቼ አይኔ ጉድ አየ" አልኳቸው።

"ምን አየህ?"አሉኝ ኮለኔል።

"ደመወዝ ከፋዮችና ገንዘብ ቤቶች ከመኝታ ክፍላቸው ውስኪ አስመጥተው ይጠጣሉ።"

"ዛሬ ነው እንዴ ያየሃቸው? ከመጡ ጀምረው ውስኪ መቼ ተለይቷቸው ያውቃል። ታዝበን ታዝበን ትተናቸዋል" አለኝ ሻምበል በድሉ።

"ይሉኝታ ማጣት ነው ወይንስ ንቀት? ለምን ከተማ ሄደው አይጠጡም!" አልኩኝ ቆጣ ብዬ።

"እስቲ ለሁሉም እንቀመጥ?" አሉ ኮለኔል ትክት ባለ አነጋገር። ወደ ላይ ወጣ ብለን ከዛፉ ስር ተቀመጥን።

"ታሪካችን ተበላሸኮ ጌታዬ" አላቸው በድሉ።

"እየ በድሉ፤ ምን ታሪክ አለን ብለህ? ያለፈው ውርደት አልበቃን ብሎ ተግዘን እንኳን ከውስኪ መለኪያ መላቀቅ ሲያቅተን ምን ይባላል። ወይኔ ዘርጋው!" አይኖቻቸው ደም ለበሱ። እሳቸው ስላመረሩ የኛም ፊት ተኮሳተረ።

"ክብራችንን አጥተን የተዋረድነው ከላይም፣ ከታችም በክብረ ቢሶች ስለተከበብን ነው። ሆዳም ሰው ድሮም ቢሆን ክብርና እምነት የለውም። አስቡትስቲ ጎበዝ! ዛሬ ጮማ የምንቆርጥበት፣ ውስኪ የምንጠጣበት ወቅት ነው? እንደ መንጋ ከብት ተነድተን መምጣታችን ሊያንገበግበን ሲገባ ከመኝታ ክፍላቸው ውስኪ አምጥተው መጠጣት ምን ማለት ነው? ወያኔዎችኮ በነዚህ እንገዛም ብለው ቢወይኑ አግባብ አላቸው። የሰው ልጅ ክብር ከሌለው ይሉኝታም የለውም። ይሉኝታ ከሌለውም አዙሮ የሚያይበት አንገትም የለውም፤ አንገት ከሌለውም እንስሳ ነው፤ ቢጭኑት አህያ ቢያርዱት የሚታረድ ከብት!" በተናገሩ ቁጥር ደማቸው ይፈላ ጀመር። ዘወርወር ብለው አዩና፦

"ሌላው ቢቀር 'ተመልካች ምን ይላል?' ማለት ነበረባቸው። እንዴ! አብረንኮ ነው የምንሰደበው ምነው ጎበዝ" ሲሉ እኛ ያጠፋን ይመስል ገላመጡን። እውነታቸውን ነው፤ ትናንት ኢህአዲጎች ሰብስበው ጥንብርኩሳችንን ነው ያወጡን።

የኢህአዲጎቹ ተወካይ ነበሩ የሰበሰቡን። ፊታቸው ምጥጥ ያለና የቀይ ዳማ ናቸው። ማእረጋቸው ኮለኔል ነው። «ማእረግ አነሰኝ» ብለው ነው ወደ ኢህአዲግ የገቡት። የጎሳ ልጓም ጎትቷቸው እንጅ ዛሬም ቢሆን ያው ኮለኔል ናቸው።

"ዛሬ የምንነጋገረው ስለ ስርአት አልበኞች ጉዳይ ነው" አሉ፣ ንግግራቸውን ሲጀምሩ። ሁሉቱንም ክፍለ ጦሮች ነበር ለጥ ካለው አስፋልት ላይ የሰበሰቡን። "በርግጥ ባጠቃላይ መኮንኖችን ለመውቀስ ያስቸግራል። ጥሩ ስነምግባር ያላቸው መኮንኖች አሉና። ግን ደግሞ አንዳንድ ከስነስርአት ውጭ እንሁን የሚሉ መኮንኖችን ዝም ብለን አናያቸውም። የስነስርአት እርምጃ ለመውሰድ እንገደዳለን። እኛ መጠጥ አትጠጡ አንልም፤ ጠጥታችሁ ግን አትሰደቡን! ትናንት ማታ ሁለት መኮንኖች ከመጠን በላይ ጠጥተው ይሰክሩ ይመጡና የበር ዘቦችን 'ቅማላም ሁሉ! እናንተ ናችሁ እኛን የምታሸንፉን? አውቀን ተሸነፍንላችሁ እንጅ' እያሉ ደነፉ። በፈጠራችሁ! አረቂ ስትጠጡ ነው እንዴ ወንድነታችሁ የሚነሳው? ጀቱን፣ ታንኩን፣ መድፉን ይዛችሁ ያልተሳካላችሁ ዛሬ ባረቂ ጥይት ድል ለመቀዳጀት ትመኛላችሁ!" ሲሉን ቢጨንቀን አቋርጠናቸው ሳቅን።

"እባካችሁ አትስደቡን። ተከበሩ! እናክብራችሁ። አለበለዚያ በዚህ መልኩ የምትቀፅሉ ከሆናችሁ የስነስርአት እርምጃ የምንወስድ መሆናችንን እንድታውቁት" በማለት ነበር ንግግራቸውን የጨረሱት።

ስለመጠጥና ጠጭዎች አንስተን ስናወራ ከወደላይ በኩል ሶስት መኮንኖች የቆጥ የባጡን እየቀባጠሩ መጡ። በተራመዱ ቁጥር እግሮቻቸው ወዲያና ወዲህ ወልከምከም ይላሉ። ጨዋታችንን አቁመን ወደነሱ አተኮርን።

"ቅ... ቅ... ቅማላም ሁሉ! በ... በ... በነሱ እንሸነፋለን!!" አለ አንደኛው መኮንን

"ባ... ባ ... ባሪያው ነው ጉድ የሰራን" ሲል ሁለተኛው መለሰ።

"ባሪያው! ባሪያው! ትላላችሁ! እሱ ምን ያድርግ? ጉድ የሰሩንስ ጀኔራሎቹ! ዝምበሉ አሁን! ሰካራም ሁሉ!" አላቸው ሶስተኛው። ይኸ በመጠኑ ሚዛኑን እንደጠበቀ ነው።

"ተ... ተው እባክህ! እናግረን ይውጣልን! እ... እስከዛሬ የታፈነው አይበቃም!" በማለት የመጀመሪያው ተናጋሪ እንደ መወራጨት ሲል ሊወድቅ ነበር፤ ጓደኛው ደግፎ አስቀረው።

ኮለኔል ዝም ብለው ሲያዩ ቆዩና "እኔ እምለው ተስፋ መቁረጥ ይሆን እንዲህ የሚያደርጋቸው?" አሉ።

"በርግጥ አንዳንዶቹ የሶስት ቀናቱ ሴሚናር ስለቀረ ተስፋ ቆርጠው ሊሆን ይችላል። አንዳንዶቹ ግን የቆየ ልማድ ስላላቸው ነው" ስላቸው፦

"እረ ወዲያ!" ብለው እጃቸውን አወራጭተው ከተቀመጡበት ተነስተው ሲሄዱ በድሉ ተከተላቸው:: እኔ ግን እንደ ተቀመጥኩ ቀረሁ:: ፍዝዝ ብዬ ነበር ወጭ ወራጁን የማየው:: እረ የስካር ነገር ቅጥ እያጣ መጣ:: ከዛፍ ስር ሳይቀር ወድቀው የሚያነጉ አሉ:: ሲደጋገም የራበው ጅብ እንዳይዘረክታቸው እንጂ፤ ሰሞኑን ደግሞ ሲጮህ ነው የሚያድረው:: አንዳንድ መኮንኖች «የረሃብ ምልክት ነው» ሲሉ ሌሎች ደግሞ «የለም! የጦርነት ምልክት ነው» ይላሉ:: ከንቱ ትንበያ ነው:: ሁለቱንም ይዘናቸዋል:: ርሃብንም፣ ጦርነትንም:: አንዱ መኮንን ያለው ይልቅ እውነትነት አለው::

"ጅብስ ደርግ ነው! ኢህአዲግ ደግሞ አሳማ ነው!" አለ በሽቆ::

እኔ ከምተኛበት ጎን ነው የሚተኛው:: እንዳጫወተኝ ከሆነ ያምስት ልጆች አባት ነው:: ደመወዝ ቶሎ ባለማግኘቱ ይበሳጫል:: ከአስራ ሁለት ሰአት በኋላ ተጠቅልሎ ነው የሚተኛው:: ጧትም ቶሎ አይነሳም:: ፊቱም ግጥጥ ያለና ርሃብ የጎዳው ነው:: ሚስቱንም ባለፈው እሁድ ልትጠይቀው መጥታ አይቻታለሁ:: ክስት ያለች ነች::

ወደ ሰው ብሶት ገባሁ እንጅከ እኔም ብሶት አለብኝ:: በርግጥ እንደሱ ሚስትና ልጆች የሉኝም:: ለምን እንደ ሆነ እንጃ የኢትዮጵያ ሁኔታ እያሳሰበኝ መጥቷል:: ለነገሩማ አገር ሚስት ነች፤ አገር ልጆች ነች፤ አገር ሀብት ነች፤ ሲያገኙ መደሰቻ! ሲያጡም መለመኛ ወይንም መተከዣ:: ያለ አገር ምንም ነገር የለም:: አገር ከጠፋች ሁሉም ነገር ይጠፋል:: ዛሬና ትናንት ኢትዮጵያ የሚደሰቱባት ሳትሆን የሚያለቅሱባት፤ የሚኖሩባት ሳትሆን የሚሰደዱባት ሆናለች::

ምእራፍ አምስት

ጥንት በልማዱ የኢትዮጵያ ገበሬ ነጭ ጤፍ ነበረ
ያመርት የነበረው!
ጊዜው ተለውጦ አንበጣው ደርግ ወጥቶ ቡቃያውን በላው!

13

ትናንት ማታ ግማሾቹ ካርታ ይጫወቱ ነበር:: ግማሾቹ ደግሞ በየመኝታቸው ላይ ጋደም ጋደም ብለው በሀሳብ ተደምመዋል:: ሬዲዮ ድንገት ጢርር... ጢርር... ማድረግ ጀመረ:: አዲሱ የኢህአዲግ ማርሽ መሆኑ ነው:: ሁላችንም ጆሮዎቻችንን አቀናን::

«የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኢሰፓ መዋቅርና ድርጅቶች ከዛሬ ጀምረው ፈርሰዋል:: ሰራተኞቹም ተበትነዋል::» ከጊዜያዊ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ተገለፀ:: ሁላችንም ተመስጠን ነበር ያዳመጥነው:: እኛ የተሰባሰብን መስሎን ነበር፤ ለካ ተበትነናል...

"መከላከያ ሚኒስቴር ፈረሰ ማለት ነው?!" አለ ሻምበል አዱኛ ደቻሳ ወደ በድሉ ዞሮ:: ቀስ ብሎ መናገር አይሆንለትም:: ጮክ ብሎ ነበር የተናገረው::

"አትጮህ! ይፍረስ!" አለው በድሉ ቆጣ ብሎ:: ከሱ ቀና መልስ ሲያጣ ጊዜ ወደኔ መለስ አለና አይኖቹን አፈጠጠ::

"ምን እንደ ጉማሬ ትገላበጣለህ? አርፈህ አትተኛም" አልኩት:: ከዚህ በኋላ ትንፍሽ አላለም::

ስለወቅቱ ሁኔታ አንስቶ መወያየት አይቻልም:: ችግር ነው:: ወጥመድ ውስጥ እንገባለን እያልን እንሰጋለን:: ትግሬ መኮንኖችን የኢህአዲግ መረጃ ሊሆኑ ይችላሉ እያልን መፍራት ጀምረናል:: አብረው እንደኛው እየተሰቃዩ የጎሳ ጉዳይ በመሆኑ ልናምናቸው አልቻልንም:: በዚህ ላይ በደርግ ጊዜ ሲቋሰል የከበረው ሁሉ የጎሪጥ ይተያያል:: አብዛኛው ደግሞ ማን ምን እንደሆነ በውል አይተዋወቅም:: ውስጥ ለውስጥ የሆነ ያልሆነውን አሳብቀው ለመሾም፣ ለመሸለም የሚቅነዘነዙ መኮንኖች መታየት ይዘዋል:: ለገፀ በረከት እንዳያቀርቡን መጠራጠር ይዘናል::

ጧት ቁርሳችንን በልተን ከመነቃቀል ከተረፉት ቁጥቋጦዎች ስር ሄደን ተቀመጥን::

"ማታ እረ እንደዚያ ቀንዴን ያላችሁኝ ለምንድን ነው?" ሲል አዱኛ ጭውውታችንን በጥያቄ ጀመረው::

"ቀስ ብለህ መናገር አይሆንልህም፤ ኢህአዲግ በየመኝታ ክፍሎች የመለመላቸው መኮንኖች አሉ ይባላል:: እረ እባካችሁ ተጠንቀቁ" አለ በድሉ::

"ደርግ ትናንት የተፈጠረ ነው:: ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ግን ከጥንት ጀምሮ የነበረ ነው:: በርግጥ ኢሰፓና ሌሎች ድርጅቶች መፍረስ ይገባቸዋል:: የደርግ መጠቀሚያዎች ነበሩ:: የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴርም ይፍረስ፤ አፋኝ መስሪያ ቤት ነበር:: የመከላከያ ሚኒስቴር ግን ከኢትዮጵያ መፍረስ ጋር ተነጥሎ የሚታይ አይደለም:: በመሰረቱ ጥፋተኞችን ለፍርድ ማቅረብና ለውትድርና አገልግሎት ብቁ ያልሆኑትን ማገለል ሲገባ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መዘጋት አልነበረበትም" አለ አዱኛ በመቆርቆር አይነት አነጋገር:: እኔም ሆንኩ በድሉ ፈጥነን መልስ አልሰጠነውም:: እራሱ መናገሩን ቀጠለ:-

"አላማቸው ግልፅ ነው:: ኢትዮጵያን በጎሳ ከፋፍሎ ለማፈራረስ ነው:: ፖሊስንም ያፈረሱት በከተሞች አካባቢ ሁከት እንዲፈጠር ነው:: በዚህ ግርግርም ንብረት ወደ ትግራይ ያጓዛሉ፤ ፋብሪካዎችን እየነቀሉ ይወስዳሉ፤ ኦሮሞንና አማራን ደም እንዲቃቡላቸው ቅስቀሳ ያደርጋሉ፤ ይህ ደግሞ ለነሱ ምቹ ነው:: ከቻሉ አረግጠው ይገዛሉ:: ካልቻሉ የሚፈልጉትን አጉዘው ሲጨርሱ እስበሳችን እናክሰው ወደ ትግራያቸው ሙልቅ ይላሉ:: ከዚያ ከኤርትራ ጋር ተዋህደው አምባገነን ገዥዎች ይሆናሉ" አለና አሻግሮ ወደ መናገሻ ጋራ አተከረ:: አስተያየቱ "አንተ ጋራ ፍረድ" የሚል ይመስላል::

ካጎነበስኩበት ቀና አልኩና "ሌላውን ተወውና በጎሳ የመከፋፈላችን ጉዳይ ግን አሳሳቢ ነው። አንድ ሆነንም አልተሳካልን፤ እንኳን ተበታትነን። ህዝቡ እስካልነቃ ድረስም የገዥ መደቦች የሚያመቻቸውን መንገድ ከመምረጥ ወደኋላ አይሉም። እኔ እንደሚገባኝ ዛሬ ለዚህ የከፋ ችግር ተፈታኞቹ እነሱ ሳይሆኑ ህዝቡ ነው። ይህን ደባና ሴራ ማክሸፍ መቻል አለበት። አለበለዚያ ግን የጎሳ ሆያ ሆየ ልንወጣው ከማንችለው ችግር ውስጥ ይከተናል። በተረፈ ግን መከላከያ ሚኒስቴርንስ እንኳንም አፈረሱት! ግንብ ነበር። ባዶ ህንፃ! ሰው የሌለበት!" በስተመጨረሻው በስጨት ብዬ ነበር የተናገርኩት።

"ሰራዊቱ ግን አያሳዝንህም? ላገሩ እንዳልደማ፣ እንዳልቆሰለና ለሀገሩ አንድነት ሲል በረሃ ለበረሃ እንዳልተንከራተተ ተቆጥሮ የትም ተበትኖ በገዛ አገሩ ለማኝ ሆኖ ሲቀር" አለኝ።

"ያሳዝነኛል፤ አንጀቴን ይበላኛል፤ ግን ለዚህ ሁሉ ውርደት ማን አበቃውና? ሰራዊቱን በትኖት የሄደው መንግስቱ ሀይለማርያም፣ ያብዮታዊ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ነው። እሱ የበተነውን ሰራዊት ደግሞ ጠላት ሰብስቦ ይንከባከባል ማለት የዋህነት ነው።

"ሰራዊቱ እንደ ሆነ ድሮም አልደላው። ሲንከራተት ነው የኖረው። ለመንግስቱ ሀይለማርያምና ለጥቂት ደልቃቆች ሲሞት፣ ሲደማ፣ አካሉን ሲያጣ ኖሯል። ከእንግዲህ ግን ለራሱ መሞት አያቅተውም። መቼም እድሜውን ሙሉ ለማኝ ሆኖ አይኖር!

"በመሰረቱ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በዘመነ ደርግ ስሙ የጎደፈ፣ ሙያው የቆሸሸ ነበር። በስመ አንድነት የህዝብ ሃብት እየተዘረፈ ለደርግ ቅምጥሎች ቤት መስሪያ፣ መኪና መግዣና መንደላቀቂያ ውሏል። የነሱ ልጆች በካናዳ፣ በአሜሪካ፣ በአውሮፓ ከመዋእለ ህፃናት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ ተልከው ሲማሩ የድሀው ልጅ እጣ ፈንታ ግን እየታፈነ ብሄራዊ ውትድርና መላክ ነበር። የሚገርመው ግን ከናቅፋ ተነስቶ አዲስ አበባ እስከሚደርስ ድረስ 'አብዮታዊ ሰራዊታችን ግንባሩን አያጥፍም!' እየተባለ ኪግል ወደ ቡድን ከዚያም ለወጥ አድርገው በብርጌድ፣ በክፍለ ጦር፣ በእዝ ደረጃ ቆርቆሮ እየቀጠቀጡ 'የጀግና ሜዳይ' በማለት ለማታለል መሞከራቸው ነው። የነሱን እስትንፋስ ለማቆየት ይህ ሰራዊት የሱን እስትንፋስ ማጣት ነበረበት።

"የጦሩ ስምና አይነት ቢጠሩት ቢጠሩት አያልቅም። አበው ሲተርቱ 'ዘጠኝ ሱሪ ከፈስ አያድንም' ይላሉ። የእዙ፣ የግብረ ሀይሉ፣ የክፍለ ቦ . ብዛት በትክክል አይታወቅም። በየቀኑ አዳዲስ ስም ይሰየማል። 'ናደው፣ ገረምደው፣ ውቃው፣ ስንጥቀው፣ በርግደው፣ ተራራው፣ ስፓርታው፣ አየር ወለዱ፣ ፓራኮማንዶው፣ ሜካናይዝዱ፣ ሚሊሻው፣ ወዛደሩ፣ አብዮት ጠባቂው፣ ብሔራዊ ወታደሩ' ይኸ ሁሉ ሰራዊት ነው። ሳር ቅጠሉ፣ ጎጣጎጡ ሁሉ ሰራዊት ብቻ ነው። መሪ ግን የለውም...

"እንደ ሰራዊቱ መንጋጋት የልብሱ አይነትም ተቆጥሮ አያልቅም። ዝብርቅርቅ ያለና ቅጥያጣ አለባበስ ነበር ይታይ የነበረው። ያለ ምክንያት አይደለም ልብስን ያነሳሁት። ያንድ ሰራዊት ግርማ ሞገሱ ልብሱ ነው። አለባበሱ ያላማረ ሰራዊት ተመልካችን አይማርክም። ተመልካችን ካልማረከ ደግሞ የውትድርና ሙያ አይከበርም። ይናቃል።

መለዮው እራሱ የረኛ ጥሬ መቋጠሪያ ይመስላል። ከዚህ ብሶ ደግሞ 'ባጅ' የለውም። ታዲያ የኢትዮጵያ ሰራዊት ከፊልም ቤት ዘበኛ በምን ይለያል? ይህ ሁሉ ተፅእኖ አድርጎበታል።

"ይህ ሰራዊት አስራ ሰባት አመታት ሙሉ ካገር አገር እየተንከራተተና ከምሽግ ምሽግ እየተፈራረቀበት፤ የራሱን ፀጉር እንኳን የሚላጭበት ጊዜ አጥቶ ቅማል በላዩ ላይ እየፈላበት የሰውነቱ እድፍ መገረና ሰርቶ የኤሊ ገላ መስሎ ቅርፊት አበጅቶ ከሰው እንዳልተፈጠረ ሲሆን ከጀርባው ግን ጓድ ደርጎች ጮማ እየቆረጡ በውስኪ ይራጩ ነበር። ይህ ብቻ አልበቃቸው ብሎ ሀውልት ሳይቀር ይገነቡ ነበር። በሱ ደምና አጥንት። እየሞተ 'ገሏል መሰለኝ ዝናሩ ጎሏል' እያሉም አዘፍነውበታል። ሲሮጥም ጥሎት ሊሆን ይችላል።

"እሱ እየተንከራተተ 'ልጁ እንኳን ተምሮ ይደርስልኛል' ሲል በቀበሌ ታፍኖ ካለበት ድረስ ተላከለት። ታዲያ እንዴት ብሎ ለኢትዮጵያ ይሙትላት? ለዚያውምኮ አለገመም። ሲያጠቃ 'ይዞታህን ለቀህ ተመለስ' ይሉታል። ሲማርክ 'ልቀቅ' ይባላል። 'ጥይት' ሲላቸው ኮቾሮ ይልኩለታል። 'ኮቾሮ' ሲላቸው ጥይት ይልኩለታል። በዚህ ላይ ሹመትና ማእረግ ለፈርጣጮች ይሰጣል። ይህም አንጀቱን ያሳርረዋል።

"አንድ ጊዜ ከደብረታቦር የፈረጠጡ ባህርዳር ይገባሉ። ቀሪዎቹ የጀግና አሸሻሸት እየሸሹ ከሶስት ቀናት ጉዞ በኋላ ባህርዳር ሲደርሱ ፈርጣጮቹ ሹመት በሹመት ሆነው ቆዩዋቸው። እንዳይከሱ 'አብዮታዊ ሹመት ነው' ቢጨንቃቸው 'እንደዚህ ከሆነማ ቆይ ለወደፊቱ እኛን ማርቆስ ድረስ የሚቀድመን የለም' አሉ። ይኸ ሁሉ የሰራዊቱን ሞራል ገሎታል። ፈሪ መሪዎች ፈሪ አድርገውታል" በማለት ትንሽ ተነፈስኩ።

"ስለዚህ መከላከያ ሚኒስቴር መፍረስ አለበት ነው የምትለኝ?" አለኝ።

"አዎን፤ ሰራዊቱ ባጥፊነት ባይወቀስም በደርግ አምሳል የተቀረፀ ስለሆነ መፍረስ አለበት። ከላይ እስከታች የተግማማ ነው" አልኩት። በድሉ የሁለታችንን ክርክር በተመስጦ ያዳምጥ ነበር። ሲበዛ ከመናገር ቁጥብ ነው።

በዚህ ላይ እንዳለን ኮለኔል ዘርጋው ከወደፊት ለፊታችን መጡ። መጠነኛ ፈገግታ ይታይባቸዋል። ካጠገባችን ሲደርሱ ቁመታችንን ሙሉ ተነሳንላቸው።

"ኧረ በግዜር፤ እንደምን አረፈዳችሁ" ብለው እጃችንን ተራ በተራ ከጨበጡን በኋላ ከጎናችን ተቀመጡና፡-

"ታዲያስ እንዴት ይዟችኋል?" አሉን።

"አለነው። ሲመሽ ሲነጋ እናያለን" አልኳቸው።

"መኖር መልካም። ይህን ማን አየበት" አሉ ላላ ባለ አነጋገር።

"ጌታዬ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በመፍረሱ ምን ተሰማዎት?" ሲል አዱኛ ጠየቃቸው።

"እናንተ ምን እንደተሰማችሁ እንጃ እንጅ እኔስ መፍረሱን እምኘበታለሁ።!"

"እንዴ! ጌታዬ አገሪቱኮ ተቆርቋሪ ሀይል ከሌላት ንብረት እየተዘረፈ ወደ ትግራይ መጓዙኮ ነው" ሲላቸው ፈገግ አሉና፡-

"ሀገር መከላከያ ሚኒስቴርስ ኖሮ መች ከጥፋት አዳናት አዱኛ" አሉትና "ግዴለም ያጉዙ:: የትግራይ ህዝብ እንደሆነ ወገናችን ነው:: ወደ ሱዳን አያግዙ እንጅ:: ዋናው ነገር መከላከያ ሚኒስቴር እንኳንም ፈረሰ:: ለዚህ ሁሉ ውርደት የበቃነው አመራር ሰጭ በማጣታችን እንጅ ሰራዊት አንሶን ወይንም መሳሪያ አጥተን አልነበረም:: እርግጥ ለሽንፈታችን ብዙ ዘርፍ ሊኖረው ይችላል" አሉና አንገታቸውን ደፋ አድርገው ትንሽ አሰቡና:-

"ለውድቀታችን ተጠያቂው መንግስቱ ሀይለማርያም ብቻ አይደለም:: ጀኔራሎቹም ናቸው:: ወይ ታማኝ ሆነው ከልብ ማገልገል ነበረባቸው:: ወይ እሱን በወቅቱ አገር ሳያጠፋ ማጥፋት ነበረባቸው:: ወይ 'አልቻልንም' ብለው ስልጣን መልቀቅ ነበረባቸው:: አስራ ሰባት አመት ሙሉ በሱና በጀኔራሎቹ መካከል የድብብቆሽ ጨዋታ ይካሄድ ነበር:: በመካከሉ ግን ይኸ ሰራዊት እንደ ቅጠል ይረግፋል::

"ጀኔራሎቹ መንግስቱን ከሰራዊቱ ነጥለው እርቃኑን ለማስቀረት ሲሉ ሰራዊቱን በተለያዩ መንገዶች ይረሽኑት፣ ያስሩት፣ ያሰቃዩት ነበር:: ሰራዊቱ ግን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለመንግስቱ ከፍተኛ አክብሮት ነበረው:: ጀኔራሎቹን ግን በጠላት አይን ነበር የሚያያቸው::

"በዚህ የተነሳም መንግስቱ በጀኔራሎቹ ላይ እምነት ስለሌለው እስከ ብርጌድ ጦር ድረስ እሱ ሳያውቀው ከመከላከል በስተቀር የማጥቃት ዘመቻ ማካሄድ አይቻልም:: የክፍለ ጦር፣ የብርጌድ፣ የሻለቃ አዛገች የውጊያ እቅድ አውጥተው ጦራቸውን በመረጡት ጊዜና ቦታ ማዝመት አይችሉም:: ሁሉም ነገር ከላይ መጠበቅ አለበት:: ከላይ የሚወጡት የውጊያ እቅዶች ደግሞ ምስጢሮቹ ለባላጋራ ከወገን ቀድመው ስለሚደርሱ ሽንፈትን ያፋጥናሉ::

"የመረጃ ሰራተኞቻችንም 'ስኳር፣ ጨው፣ ካኪ ተሸጠ' እያሉ ከመዥረጥ በስተቀር ከጠላት ጓዳ ገብተው የጣመ መረጃ አያመጡም:: እንዲያውም በገንዘብ እየተገዙ የኛን የሚያቀብሉ ሞልተዋል::

'የፖለቲካ ሰራተኞቻችንም 'ሌኒን እንዳለው፣ ማርክስ እንዳለው፣ ኤንግልስ እንዳለው፣ አሁን አሁን ደግሞ አብዮታዊ መሪያችን ባንድ ወቅት እንዳስገነዘቡት' ከማለት በስተቀር ሌላ ነገር አያውቁም:: ቢያውቁም ከዚህ ውጭ እንዲሉ አይፈቀድላቸውም:: በዚህ የተነሳ ጦሩ እያደር ደነቆረ፤ ደነዘዘ...

"የጀኔራሎቹ ደባ በዚህም አያበቃ:: ጦሩ በጠላት ጦር እየተመታ ባፈገፈገ ቁጥር እንደገና በማጠናከርና ሞራል በመስጠት ፋንታ ቀድመው ይፈረጥጣሉ:: አዛዥ ከሌለ ደግሞ ጦር አውራ እንደሌለው ንብ ማለት ነው:: የጀኔራሎቹ ሽሽት ወይንም ፍርጠጣ ሁለት አይነት ገፅታ አለው:-

"አንደኛው ሽንፈቱ የመንግስቱ ሀይለማርያም ሽንፈት ብቻ እየመሰላቸው ይረኩበታል:: ለዚህም ነው እያንዳንዱ የጦር ግንባር 'ጀኔራሎቹ በብዙ ሺ ብር ሸጡት' እየተባለ የሚወራው:: ያገር ፍቅር ስሜት ያላቸው አዛገች ከጦሩ ጋር ሳይላቀቁ ሲደመሰሱ 'ጅሎች፣ መሸሽ ሲችሉ፤ እጃቸውን መስጠት ሲገባቸው' እያሉ ይስቁባቸዋል:: እራሳቸውን የሚገድሉትንማ 'አብዶች ናቸው' ነው የሚሏቸው:: መፈርጠጥ እንደ ጀግንነት የሚቆጠርበት ዘመን ነው:: ባጠቃላይ ጦርነቱ

የመንግስቱ ሀይለማርያም የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ፣ የጀኔራሎቹ መሾሚያ መሸለሚያ ነበር::

"ሁለተኛው የመሸሽ ገፅታቸው ተፈጥሯዊ ባህሪያቸው ፈሪዎችና ሆዳሞች በመሆናቸው ነው:: የሚገርመው ግን ከሀላፊነት ቦታ የሚቀመጡት ደግሞ እንደነዚህ ያሉት ናቸው:: ለዚህ ተጠያቂው መነግስቱ ሀይለማርያም ነው:: ልብ እንደሌላቸው ስለሚያውቅ አገርን ሳይሆን እሱን የሚጠብቁትን፤ እሱ ከሌለ እነሱ መኖር እንደማይችሉ የሚያውቁትን ቁልፍ ቦታ ላይ ያስቀምጣቸዋል:: ከዚህ በኋላ እንደ እቃ ይጠቀምባቸዋል:: ጀግና ጀኔራሎችን ከሀላፊነት ቦታ ላይ ቢያስቀምጥ ለሱ እንደ ማይተኙለት ያውቀዋል::

"እነዚህ ጉልቻ ጀኔራሎች ግን ሴትና ገንዘብ ከማሳደድ በስተቀር ሌላ ነገር አያውቁም:: እያንዳንዱ ብርጌድና ክፍለ ጦር በተደመሰሰ ቁጥር ለመንግስቱ ጀኔራሎች ሰርግና ምላሽ ነው:: ገንዘብ ባካፋ ይዝቃሉ:: 'ጦሩ እንዴት ተጠቃ? የትስ ደረሰ?' ሳይሆን ጥያቄአቸው 'ገንዘቡ የት ደረሰ? ይኸ ብቻ ነወይ?' ነው:: ከዚህ በኋላ ገንዘብ ቤት፣ ደመወዝ ከፋዮች፣ ደህንነትና ፖለቲካ ሀላፊዎች ካዛዥ ጋር ተከፋፍለው ጦሩን እየመሩ ከተረጋጋ ይዞታ ሲደርሱ መንግስቱ ሀይለማርያም ተቀብሎ ይሾማል፤ ይሸልማል፤ የተሻለ ቦታም ይሰጣል:: ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ልስጣችሁ:-

"ሻምበል ለገሰ አስፋው የትግራይ ራስ ገዝ አስተዳዳሪና የጦሩ የበላይ አዛዥ ሆኖ ሲሾም ጀኔራል ሙላቱ ደግሞ የሱ የበታች ሆነው የጦሩ አዛዥ ነበሩ:: ውድቀቱን አይተናል:: ከዚህ በኋላ ነው ቅስማችንም ተሰብሮ የቀረው:: ለገሰ ግን የተሻለ ስራና ሀላፊነት ተሰጠው እንጅ የሆነው ነገር የለም:: ለዚህም ነው ጦሩ:-

«ለገሰ ሲሸሽ ቤተ መንግስት፣
ሚሊሻ ሲሸሽ በጥይት!» ብሎ የገጠመው::

ጀኔራል አበበ ሀይለስላሴ ደብረታቦር ላይ ጦሩን አስጨርሶ ወደ አዲስ አበባ ቢፈረጥጥ የሁርሶ ጦር ትምህርት ቤት አዛዥ ሆኖ ተሾመ እንጅ የሆነው ነገር የለም:: ይህ ድርጊትም ጦሩን እንጀቱን አቁስሎታል:: ጀኔራል አስራት ብሩም ከባህርዳር የፈረጠጠ በወለጋ ዞሮ አዲስ አበባ ሲገባ የሆነው ነገር የለም:: እንዲያውም ጊዜው አጥሮበት እንጅ ከፍተኛ ሹመትና ማእረግ ያገኝ ነበር::

"ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ከመፈንቅለ መንግስቱ ወዲህ ሶስት ኤታማጆር ሹሞች ተሹመው ነበር:: አንዱን አንዱ ሲጠብቀው አንድ ነገር ሳይሰሩ እጃችንን አስጨበጡን! ንበዝ የሰራዊቱ ግፍ በዚህ አያበቃም:: አብዮታዊ ዲስፕሊን አስተባባሪ ኮሚቴ /አዲአኮ/ ተብሎ የሚታወቀው በ80 ዓ.ም. ፀድቆ ለጦር ክፍሎች ተበትኖ በተግባር ላይ ከዋለበት እለት ጀምሮ ወደር የሌለው ጭፍጨፋ ተካሂዷል:: ጦሩንክ የጨረሰው ጠላት ሳይሆን ወገን ነው:: የዚህ ጭፍጨፋ አላማ የሚሸሹ ወታደሮችን ለመግታት ይሁን እንጅ ያለቁት ግን ከፖለቲካው ጋር መጣጣም ያልቻሉት ነበሩ:: በዚህ የተነሳም የጦር ክፍሎች ስማቸው

እንጅ ባደ ነበሩ። ጦሩኮ ከሞተ ቆይቷል። 'ሟች አውሬ ገዳዩን ያስመሰግናል' እንዲሉ ለወያኔዎች መፎከሪያ ሆንናቸው።

"ይህ ሰራዊት ሲመለመል ባፈሳ፣ ሲረሸን ባፈሳ፣ ቦርድ ሲወጣ በመንጋ፣ ሲሸሽም በጅምላ፣ በመጨረሻም እጅ ሲሰጥ እየተሻማ በጠቅላላ ሆነ!!" አሉና ከተቀመጡበት እንደ መወራጨት አሉ። አይኖቻቸው መቅላት ይዘዋል።

"ጦሩ ሲሰለጥንም እንዲያሸንፍ ሆኖ ሳይሆን እንዲሸነፍና መሳሪያውን ጥሎ እንዲፈረጥጥ ሆኖ ነው። ለዚህ ደግሞ የስነልቦና ጦርነት የሚካሄድበት ገና ከቀበሌ ሲታፈስ ጀምሮ ነው። ከዚህ በኋላ በአእምሮው የሚታየው መግደል ሳይሆን መሞት ነው፤ መማረክ ሳይሆን መማረክ ነው።

"በየ ክፍለ ሀገሩ እንደ አስራት ወይንም ግብር ኮታ ተጥሎ የታፈሰ ወጣት ሀያ ሺና ሰላሳ ሺ ባንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለብ ለብ ተደርጎ ይወጣና 'አብዮታዊ ሰራዊታችን!' ይባልና በማስ ሚዲያ ነጋሪት ይደለቅለታል። ነገር ግን አንድ ነገር ሳይሰራ ታፍሶ ይማረካል። ኋላማ ወያኔ እያሰለጠነ ካድሬ አድርጎ ይልክልን ጀመር። ወያኔ በዚህም አልተወሰነ፤ 'ጀግና ምርኮኛ መኮንኖችን ኢዲመአን' ብሎ በመሰየም ይኸውና ዛሬ ያተራምሱናል። 'እሾህን በሾህ' እንዲሉ ...

"ለማያውቅ የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያ ጦር ሰራዊትን በጠቅላላ የሚያዝ ይመስላል። ግን አይደለም። እንደ ደንቡ ማዘዝ ነበረበት። ባዲስ አበባ ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ ክፍሎች፣ ሙዚቀኛን፣ የመቻል የስፖርት ክለብን፣ ማስተናገጃን... የመሳሰሉትን ከማዘዝ በስተቀር በሌላው ሰራዊት ግን ሀይል ከመቁጠርና ስንቅ ከማቀበል ሌላ የእዝ ሰንሰለትም ሆነ ስልጣን የለውም። ታዲያ የምድር ጦር አዛዥ መስንቆና ሳክስፎን ይዘው አይዋጉ። ወይንም ኳስ ተጫዋቾችን ይዘው አይሰለፉ። ቢጨንቃቸው የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያን ዙሪያ አጥር ማስገንባት ያዙ። ያውምኮ አምቦ ተይዛ ነው። ምን ያድርጉ! ባይሆን ለጅ መንሻ ግንብ አስገንብተው ይቆዩ እንጅ" አሉና በሀይል ተነፈሱ ሲከነክናቸው የኖረውን ሁሉ ነው የሚዘከዝኩት።

"ሌላው የመከላከያ ሀይላችን አየር ሀይላችን ነበር። አየር ሀይላችን ዛሬን አያድርገውና በኢትዮጵያ ህዝብ ተፈቃሪ ነበር። በተለይ በምስራቁ ጦርነት ጊዜ ያሳየው ትርኢት ታሪክ እየቀረ ነው መሰል እንጅ ለዘለአለም ተከብሮ የሚኖር ነበር። የታንክ ሞተርና ሰንሰለቱን እነጣጥረው ሲሙቱት እግረኛውን በወኔ ከነበልባሉ ውስጥ ያስገቡት ነበር። አየር ላየር ውጊያም ስጋ እንደሚናጠቁ ጭልፊቶች ነበር የሶማሌን ቀርፋፋ ሚግ እስ በሱ ያጋጩት የነበረው። ከካራ ማራ ጋራ ጋር ሳይቀር አላትመውታል። ብቻ እንደ አንድ እግረኛ ወታደር ያላንዳች እረፍት ጨበጣ ገብተው ተዋግተዋል።

"አየር ሀይላችን ለዝነኛነቱም ልጅ ተበርክቶለታል። ከልጅ የበለጠ የሚዳይ ሽልማትም በዚች አለም ላይ ያለ አይመስለኝም። ታዲያ ያ-ጊዜ አለፈና ሌላ ጊዜ ተተካና እነዚያ ስመጥር አብራሪዎች አለቁና፤ እንዳንዶቹም ተሰደዱና ምን ይቀራሉ በራሽያ የሰለጠኑ ወጣት አብራሪዎች። ከችሎታ ማነስ ይሆን ወይንም ባመራሩ አለመደሰት የገበሬ መንደርን፣ ገበያ ለመገብየት የተሰበሰበ ህዝብን፣ ቤተክርስቲያን

ለመሳለም የወጣን ምእመና ያጋዩት ጀመር። እንዳንድ ጊዜም የወገንን ጦር ያበራዩታል። እነዚህስ ቆርቆሮው የደርግ፣ አብራሪዎቹ የኢህአዲግ ሳይሆኑ አይቀሩም" አሉና ትንሽ ተንፈስ ብለው:-

"ሌላው ጦራችን የባህር ሀይላችን ነበር። እሱም ባህር ውጦት ቀረ" በማለት ዝግ ብለው በመቆጨት አይነት ራሳቸውን ነቀነቁ።

"ፖሊስም ደጀን ጦራችን ሲሆን ቅድመ አብዮት ጥሩ ዝና ነበረው። በተለይም ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ በህዝቡ ዘንዳ ተወዳጅ ነበር። የጠረፍ ፖሊሶችም ከጠላት ጋር አንገት ላንገት እየተናነቁ ጥለው አልፈዋል። በቢሮ ስራም በኩል ቀልጣፋ ነበሩ። ወንጀለኛን አሳዶ በመያዝ በኩልም አንቱ የተባሉበት ወቅት ነበር።

"ፖሊስ ድህረ አብዮት ግን ልክ እንደ ሌላው ሰራዊት ሁሉ እሱም ተሰቃይቷል። ፈጥኖ ደራሽም እንደ ቀድሞው አየር ወለድ ፈርሶ በጦሩ ውስጥ እንዲጨፈለቅ ተደርጓል። የቀረውም ቢሆን በተለያዩ ጊዜያት ወደ ጦሩ እየተወሰደ ሰጥሞ ቀርቷል።

"ፖሊስ በተለይም ከቅርብ አመታት ወዲህ ስሙ በጅጉ የጎደፈ ነበር። ከስታዲየም በር ላይ ቁመው የመግቢያ ትኬት በትርፍ የሚሸጡ፣ በሲጋራ ተገዝተው የሰልፍ ቦታ የሚያሲዙ፣ ጨለማን ተገን በማድረግ በቆመጥ የሚነርቱ፤ በሶሻሊዝም ማህፀን ውስጥ ተፈለፈሉ። በመጨረሻም ፖሊስ እንደ ውሻ ቡችላ ተቆጥሮ የራሱን ምስል በቆርቆሮ ተሰክቶለት ከደረቱ ላይ ለጥፎ እንዲሄድ ተደረገ" ሲሉ እኛ እንደ መሳቅ አልን። እሳቸው ፈገግም አላሉ። አንጀታቸው አሯል።

እፊትለፊታቸው እየተመለከቱ ትንሽ ከተከዙ በኋላ:-"የሲቪል ሚኒስትሮችና ኮሚሽነሮች፣ የመምሪያ ሀላፊዎች ሁሉ ለውድቀታችን ተጠያቂዎች ናቸው። የሲቪል ባለስልጣኖችም መንግስቱ ሀይለማርያምን አይወዱትም ነበር። የፓርቲ አባል የሆኑት ባላማው እምነውበት ሳይሆን ለማደግ፣ ቤት ለመስራት፣ እንዳንዶቹም ቀን ለመግፋት ነበር። በዚህ የተነሳ ታማኝነታቸውን ለሱ እየገለፁ የግል ህይወታቸውን ያመቻቹ ጀመር። ከመጠን በላይ የስልጣን መባለግ ባገሪቱ ውስጥ ተከሰተ። ስግብግብነት ነገሰ። ጦሩ በየቀኑ እየተመታ አዲስ አበባ እስከሚጠጋ ድረስ 'እረ እንዴት ነው? ጦሩ በምን ምክንያት ተሸነፈ?' ብሎ የሚጠይቅ አልነበረም። የሚንጫጫው ያው ተራው ህዝብ ነው። እሱ ደግሞ ሰሚ የለውም። ካዲስ አበባ ውጭ ህይወት የለም። ጦርነት፣ ርሃብ፣ ስደት፣ ሰቆቃ ነው። አዲስ አበባ ውስጥ ደግሞ ሰርክ ግብዣ፣ ሰርክ ሰርግ ማሸር ይቀልጣል። ቀኑ አልጠቅም እያለ ሲጨፈር ይነጋል። የጥፋት ደመና ግን በላያችን ላይ ያንዣብብ ነበር። ቀና ብሎ ላፍታ የሚያየው ጠፋ እንጅ።

"ባለስልጣን የተባለ ሁሉ ገንዘብ ለማካበት መሯሯጥ ብቻ ሆነ። እና ደርግ ሲወድቅ ካዲሱ መንግስት ጋር ተስማምተው የሚኖሩበትን መንገድ መቀየስ። በሚስት ስም፣ በልጆች ስም፣ በወዳጅ ስም ድርጅት መክፈት። ለክፉ ቀን ንብረት ወደ ውጭ ማሸሽ። ጀኔራሎቹም ከዚህ ውድድር ውስጥ የገቡት ወደው አይደለም። ሁኔታው አስገድዷቸው ነው። ፍትህ ጨርሶ ጠፋ። በእኩልነት ለመኖር ቀርቶ የበታች ሆኖ መኖር ከማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደረሰ። እና ኀበዝ አገራችንን ተረባርበን መሰለኝ ያጠፋናት። መንግስቱ ሀይለማርያምን ብቻ መኮነኑ አግባብ

አይመስለኝም። ተሳስቶ ይሆን?" ሲሉ ተናግረው ሲጨርሱ በጥያቄ አስተያየት አዩን።

"አልተሳሳቱም ጌታዬ፤ ልክ ነዎት። ለውድቀታችን መንግስቱ ሀይለማርያም ብቻ አይደለም ተጠያቂው። ከሱ የበለጠ ተጠያቂዎቹ ባንዳ ምሁራንም ናቸው። አገሪቱ ደክማ አስተምራቸው በሙያቸው አገሪቱን ማገልገል ሲገባቸው ሀሲና ቢሶች በሆዳቸው ክብራቸውን ሸጠው፤ ከነመንግስቱ ስር እያቶሰቶሱ ይችን አገር ቀበሯት! ሰው አልባ አደረጓት!" ስላቸው ቀልጠፍ ብለው:-

"ልክነህ፤ ሆዳም ሰው ከሆዱ ሌላ አገርም፣ ዘመድም የለውም። ጎበዝ! ከደርግ የተጠጉ ሆዳም ምሁራን የሚያስቁም፣ የሚያሳዝኑም ናቸው። 'ብልሁ፣ ቆራጡ...!' እያሉ ሲያንቆላጵሱት ኖረው ጉች አድርጓቸው ሲሄድ ቅሌታቸውን ታቅፈው ቀሩ። ሆዳሞች" አሉ እጃቸውን በቁጣ አወራጭተው።

"እኔ ግን ጌታዬ የመከላከያ ሚኒስቴር መፍረስ ምስጢር ያለው ሆኖ ነው የሚታየኝ። ካለፈውኮ መማር አለብን። ደርግ እያታለለ አይደለም እንዴ ያወደመን። እነዚህስ ያንድ ጎሳ ጦር ገንብተው አንባገነን ቢሆኑስ?" አለ አዱኛ።

"ይሆናሉና! ምን ጥርጥር አለው። ታዲያኮ አዱኛ ይህን ሁሉ መገንዘብ የነበረብን በፊት ነበር። ዛሬ መሳሪያችንን አስረክበን፣ እጃችንን ሰጥተን 'እንዲህ ሊያደርጉ ነው' ብንል አይሆንም። ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን የሚሰሩትን ማየት ነው። 'ለኩልነት፣ ለዲሞክራሲ' ነው የቆምነው አይደል የሚሉት? በተግባር ከተረጎሙት ከጎናቸው እንሰለፋለን። ሸፍጥ የሚሰሩ ከሆነ ግን እነሱ እንደሆኑት መሆን ነው። ህዝቡም ቢሆን የሚሆነውንና የማይሆነውን ደህና አድርጎ ያውቃል። ሌላው ቢቀር ጥይት ሳይተኩስ፣ ሸፍቶ ጫካ ሳይገባ በዝምታ ብቻ አድቅቆ ይጥላቸዋል። ደርግን ያነኳኮተው ህዝቡ እንጅ እነሱ እንደሚሉት ብቻቸውን አይደለም" አሉ።

ለትንሽ ጊዜ ዝምታ ዋጠን። ውስጥ ውስጡን ግን ነገር እንፈጭ ነበር። በተለይ በድሉ ጫኔ በሀሳብ ሰጥሟል። ይኸው ነው። ነገር ከሆዱ ሲገባ መነጋገር አይወድም። እስካሁንም ትንፍሽ አላለም።

ኮለኔልና አዱኛ ቀድመው ሄዱ። ቀጥሎ በድሉ ሄደ። እኔ ብቻየን እንደ ተቀመጥኩ ቀረሁ። ብዙ ካሰብኩ በኋላ ነው ይህን ግጥም የቋጠርኩት።

> አገር ተቃጠለች አንድ ነገር ሳይቀር እርጥቡም፣
> ደረቁም ባንድ ላይ አረረ፣
> ብርጭቆው ብርሌው የንጀራ ምጣድም ሁሉም ተሰበረ፣
> እቃ እቃው ብቻ ነው ቁጭ ብሎ የቀረ።
> ሲቃዩ እየበዛ ግፉ ገነፈለ፣
> እዛዛው ሲተከል ቡቃያው ነቀለ።
> አምላክሽን ሳትበድይ አንገትሽን በደፋሽ፣
> ኧረ ምን አረገሽነው አዞ ያስጨረሰሽ?
> ኢትዮጵያ አገሬ የጥንት ጠረንሽ የዝባድ ነበረ፣
> በዘመነ ደርግስ ጠረንሽ ለውጦ እጣኑ እያረረ፣

> በደርግ ጊዜማ ኧረምኑ ተርፎ፣
> ሁሉም በያለበት እንደ ወይራ ቅጠል ቀረ እንጅ አረግፎ!

ወደፊትም ገና እንረግፋለን። የሚታየኝ ተስፋ ጨርሶ የለም። ጨለማ ሀይወት ብቻ...

14

> ትናንት ሶሻሊዝም ዛሬ ጴንጠ ቆስጤ እያልኩኝ አላዝንም፣
> ምንም ይሁን ምንም ሀቅ ይዞ ከመጓዝ የተሻለ የለም።

የሶስት ቀናቱ ሴሚናር ደብዛው ጠፍቷል። አሁን አፍላ እየተወራ ያለው ከሰኔ 24 ኮንፈረንስ በኋላ የሽግግር መንግስቱ ሲመሰረት የሶስት ቀናቱን ሴሚናር ተካፍለን የግንቦትና የሰኔ ወር ደመወዛችንን ተቀብለን በደስታ እየጨፈርን አዲስ አበባ መግባት ነው።

ሌላው የሰሞኑ አዲስ ነገር በራሪ ወረቀት በግቢያችን መረጨቱ ነው። ሁሉም ተሻምቶ ያነበዋል። እርግጥ የመስቀል ምልክት ነው። «ፊታችሁን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መልሱ፤ ይቅር ባይ ነውና ይቅር ይላችኋል» ይላል። ጠይቄ እንደተረዳሁት ከሆነ ጴንጠ ቆስጤ የተባለ የሀይማኖት ድርጅት ነው። መመሪያው መፅሀፍ ቅዱስ ነው።በርግጥም አብዛኛው መኮንን ጥራዙ ያበጠ መፅሀፍ ቅዱስ ይዟል። ምን አይነት ሀይለኛ ድርጅት ነው፣ ይኸውና ባንድ ሳምንት ውስጥ ይበልጡን መኮንን መለመለው። ወደፊት ሌሎች ድርጅቶች ብቅ ቢሉ ዋጋ የላቸውም። ካባላቱ ውስጥ ዋናውን ሚና የሚጫወቱት የደርግ ካድሬዎች የነበሩ። ትልጥፍናቸውን አደነኩኝ።

አንድ የንቦች ማናቢያ የነበረ አዳራሽ አለ። ንቦቹን ዘራፊዎች ስለዘረፉዋቸው አዳራሹ ዛሬ በንቦቹ ምትክ መዘመሪያ ሆኗል።

ዛሬ ጧት መዝሙሩ ካደራሹ ጣራ በላይ ነግሶ ሲሰማኝ ጊዜ ሁኔታቸውን ለማየት ወደዚያው አመራሁ። ወደ ውስጥ ስገባ መኮንኑ ሁሉ አይኖቹን እንደ ውሻ ቡችላ ገጥሞ «ኢየሱስ ሆይ! ይቅር በለን!» እያለ እንባ ቀረሽ በጭንቀት ያምጣል። አውራጁ ደግሞ ድምፀ መረዋ ነው። አእምሮን ይሰልባል። አንገቴን አስግጌ ሳይ ከላይ ዳር በኩል አየሁት። በጣም ገረመኝ። አውቀዋለሁኝ። የሶማሌ ጦርነት ጊዜ አስር አለቃ ነበር። እኔ የዚያን ጊዜ ምክትል መቶ አለቃ ነበርኩ። ዛሬ እሱ ቀድሞኝ ሻምበል ሆኗል። ኧረ ኢህአዲግ ደርሶበት እንጅ በሚቀጥለው ሀምሌ ሻለቃ ይሆን ነበር። ትግራይ ዘምቶ አንድ አይኑን አጥቷል። ታዲያ ተጀምሮ እስኪጨረስ የፖለቲካ ሰራተኛ ነበር። ዛሬ ከምነየው ቀሰሰ?

ጓድ፣ የብርጌድ የፖለቲካ ሀላፊ ሲዘምር ቆይቶ ያችኑ የቀረች አይኑን ገለጥ ሲያደርጋት አየኝ። እፍር አለ። እኔ ደግሞ ፈገግ ብዬ ኮራ አልኩኝ። ሆን ብዬ ነው። እሱና እኔ የምንተዋወቅበት ጉዳይ ነበር።

ታሪክ መቼም ጉደኛ ነው። ለታደለ በቁሙ ያሳየዋል። እኔም እንዳቅሜ አየሁኝ። የዛሬው የሃይማኖት መምህር፣ የትናንቱ ካድሬ

ድሬዳዋ በነበርንበት ወቅት መፅሀፍ ቅዱስ «አድሃሪ ነው» ይባልና ከያለበት ተሰብስቦ እንዲቃጠል ይወስንበታል። እኔ ሲፈርድብኝ:-

"ጓድ ምናለ ባይቃጠል፤ ተቃጥሎ የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?" ብዬ መጠየቅ። እሱ ተቆጥቶ "ጓድ ይኸ ለዘብተኛነት ነው" ብሎ ወረደብኝ።

"እኔ እስከሚገባኝ ድረስ መፅሀፍ ቅዱስ የሃይማኖት ታሪክ ነው። መፅሀፍ ማቃጠል ደግሞ ሀቀኛ አያሰኝም" ብዬ መመለስ። "አይቃጠል ማለትም አድሃሪነትና ጎታችነት ነው!" አለኝ። ያን ጊዜ መኮንን የተባለ ሁሉ አድሃሪ ነበር የሚባለው። በተለይ ኮለኔሎች መከረኞች ነበሩ።

"ድንቁርና ነው" አልኩና በማኩረፍ ፈንጠር ብዬ በመቆም ድርጊቱን አመለከት ጀመር። ያ ሁሉ መፅሀፍ ቅዱስ ቤንዚን ተርከፍክፎበት ተቃጠለ። እኔም በማግስቱ ክፍለ ጦር ፖለቲካ መምሪያ ትፈለጋለህ ተባልኩና በስልክ ተጠራሁ። ስሄድ የቃል ክስ ተመስርቶብኝ አገኘሁ። 'ካድሬዎችን ደንቆሮዎች ናችሁ' ብለሃል የሚል ነበር። መልስ እስከምሰጥ እንኳን ጊዜ አልተሰጠኝም። ለጥብስ አደረሱኝ። በወታደር ፖሊስ ተነድቼ እስር ቤት ታጎርኩኝ። ከዚህ በኋላ ያለምንም ጥያቄ አራት አመት ጠጥቼ ወጣሁ። ያን ያደረገው ጓድ ነው እንግዲህ የዛሬው የሃይማኖት መሪ የሆነው። እኔም በማእረጌ ከማንም በታች ሁኜ የቀረሁት በዚሁ ሰበብ ነበር። ዛሬ ግን ከኮለኔሎቹም ጋር እኩል ነኝ።

ስርአተ ፀሎቱ አብቅቶ ከበሩ ላይ ጠበኩትና ሰላምታ ሰጠሁት፤ ሆን ብዬ ነበር።

"ታዲያስ ጌታዬ" ሲል ተሽቆጥቁጦ እጀን ጨበጠኝ።

"ታዲያስ ጓድ! እንዴት ይዞሃል?" ስለው:-

"ጓድ አትበለኝ" አለኝ ትንሽ ቅር ተሰኝቶ።

"እንዴት?" አልኩት።

"አልፈልገውም። የውሸት መጠሪያ ነው። እነመንግስቱ ሀይለማርያም እኛን ለማታለል የተጠቀሙበት ዘዴ ነው" አለኝ።

"ታዲያ በምትኩ ምን ብዬ ልጥራህ?"

"ማእረግ አለኝ! በማእረጌ ጥራኝ።"

"ማእረግህም የነመንግስቱ ነው" አልኩት ትንሽ ፈገግ ብዬ።

"ከፈለክ በስሜም ጥራኝ። አልቀየምህም። ሁሉም ነገር አክትሟል። የእግዚአብሄር ሀይል ብቻ ነው ማክተሚያ የሌለው" አለኝ ኮስተር ብሎ።

"አንድ ነገር ልጠይቅህ" ስለው ቀልጠፍ ብሎ:-

"ምን ልትጠይቀኝ እንደ ፈለክ አውቄዋለሁ። 'የዚያን ጊዜ ድሬደዋ መፅሀፍ ቅዱስ አቃጥለህ አልነበረም?' ልትለኝ ነው። ማቃጠሌን አልክድህም። አቃጥያለሁ። ያኔየ ጨቅላ ነበርኩ። ዛሬ ግን አውቃለሁ። ብዙ ነገሮችን ተምሬአለሁ። አምላኬንም ይቅርበለኝ ብየዋለሁ። ከእንግዲህ ወዲያ በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን በስተቀር የሚያዋጣ ነገር የለም። አንተንም ቢሆን ባለፈው የተገናኘን እለት ይቅርታ ጠይቄሃለሁ። 'ምንም አይደል፤ አልፏዋል' ብለኸኛል። አንተን መበደሌንም ላምላኬ

ነግሬዋለሁ። አሁንም ቢሆን በድጋሚ ይቅር በለኝ" ብሎ ወደ ጉልበቴ ቀንበስ አለ።

"በፍፁም! እኔ ቂም አልያዝኩብህም። ብይዝብህማ ኖሮ አላናግርህም ነበር" ብዬ በጄ ቀና ሳደርገው:-

"አመሰግናለሁ። እግዚአብሄር ይስጥህ" አለኝ አነጋገሩን ረገጥ አድርጎ።

"አሜን" ብዬው ፈጥኜ ተለየሁት።ትህትናውንስ ምንየ ተላብሶታል።

ትዝ ይለኛል፤ ከየኔነሽ አሰፋ ጋርም ፍቅራችንን ሳንጨርስ የተለያየነው በመታሰሬ ምክንያት ነበር። ምን አይነት እድል ነው። ባለፈውም እንደ ጀመርነው ተቋረጥን። ዛሬስ ናፍቃኛለች። ሰኔ 24 ቀን ከመድረሱ በፊት አዲስ አበባ ደርሽ መመለስ አለብኝ። ትመጣለች እያልኩ በጉጉት ብጠብቃት አልመጣችም፤ ማን ያውቃል፣ አንድ ችግርስ ገጥሟት እንደሆን?

ምእራፍ ስድስት

«ስማችን ወያኔ ስድባችን ቅማላም፣
የደርግን ወታደር ነዳነው እንደላም!»

«እረ እናንተ ሆዬ ምንም ቀን አልወጣ፣
አንድ አህያ ቢሄድ መንጋ ፍዬል መጣ!»
የኔነሽን ፍለጋ አዲስ አበባ ሄጄ የሰማሁት ግጥም ነበር።

15

ከጥዶቹ ቁጥቋጦዎች ስር ነው የተቀመጥኩት። ከፊት ለፊቴ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ትውለበለባለች። እንጋጥጨ አየኋት። ነፋስ ወዲያና ወዲህ ያላጋታል። ከግንዶት ሀያ ወዲህ የሚሰቅላት፣ የሚያወርዳት የለም። ሌትም ቀንም ትውለበለባለች። ባለቤት የላትም። እረ ለመሆኑ የማን ባንዲራ ነች? እሷም ያማራ ባንዲራ ትሆን እንዴ?

ካዲስ አበባ የተመለስኩት ትናንት ነው። አዲስ አበባ ቀዝቀዝ ብላ ጭርታ ውጧት ነው ያገኘኋት። ለምን እንደ ሆነ እንጃ ሰዉ ጨርሶ ተስፋው ተሟጧል። በዘፈቀደ ነው የሚንጠራወዘው። ሲመሽ ሲነጋ ማየት ብቻ... ተስፋ ማጣት መጥፎ ነው። ያዲስ አበባ ህዝብ ደግሞ ሁሉ ነገሩ ተስፋ ማጣት አይወድም። እረ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተስፋ ነው የኖረው። ደርግ «አስተባባሪ ኮሚቴ፣ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፣ ኢማለዲህ፣ ኢሰፓአኮ፣ ኢሰፓ» እያለ በተስፋ አቆይቶቅሎበት ትንሽ ተስፋው የተሟጠጠበት «ኢህድሪን»

ከመሰረተ በኋላ ነበር:: ከዚህ በኋላ የሚለው የለውማ:: እነዚህስ ባንድ ጊዜ ተስፋ አሳጡት:: ህዝቡ ኢህአዲጎቹን ፈፅሞ አልተጠጋቸውም:: የጎሪጥ ያያቸዋል፤ ይሸሻቸዋል፤ መጥፎ አዝማሚያ ነው:: ፈጣሪየ «የመንግስቱ ሀይለማርያም አስተዳደር ይሻላል» ከሚባልበት ዘመን እንዳያደርሰን ፈራሁኝ::

ካውቶቡስ እንደ ወረድኩ ነበር በህዝብ ስልክ ለየኔነሽ የደወልኩላት:: ስልኩ መጥራት ሲጀምር ልቤ እመር እመር ይልብኝ ጀመር::

"ሀሎ!" የሚል ድምፅ ሲመጣልኝ፣

"ሀሎ! የኔነሽን ነበር፤ ላገኛት እችላለሁ?... የት ሄደች? ሆለታ? መቼ? ትናንት?... እሺ" ብዬ ስልኩን ዘጋሁት:: ስሜቴ ሁሉ ኩምሽሽ አለ:: ልክ ከፍም ላይ ውሃ ሲፈስ ትሽ.ሽ.... እንደሚለው::

ለመሆኑ ማንን ለመጠየቅ ነው ሆለታ የሄደችው? እኔን ቢሆን ኖሮ ታገኘኝ ነበር:: ደግሞስ ትናንት ከሆነ የሄደችው ዛሬ የት ደረሰች? ኡዲያ ፀባይዋን እያወኩኝ፤ ኧረ እሱስ ያባከናት መሆኑን አለ:: ወይኔ ጎርፉ! በቅናት እርር ኩምትር አልኩኝ:: በየኔነሽ ለምን እንደ ምቀናባት አይገባኝም:: ከበርካታ ሴቶች ጋር ተገናኝቻለሁ:: ካንዳንዶቹም ጋር ዋል አደር ብያለሁ:: ግን አላስታውሳቸውም:: ስለያቸው መለየት ነው:: የኔነሽ ግን አትረሳኝም:: ጠብ እርግፍ አድርጌ ብተዋትም ሳገኛት አዲስ ትሆንብኛለች:: የምተዋትምኮ ስለምቀናባት ነው::

የኔነሽኮ መኝታ ላይ እንደ ሌሎቹ ሴቶች አይደለችም:: የተለየች ናት:: እብዳ ነው የምታሳብደው:: በዚህ ላይ ልስላሴዋ፣ ጠረኗ፣ የከንፈሮቿ መጣፈጥ ማር ከረሜላ ናቸው:: ለፍቅር ንፍገት አታውቅም:: ታዲያ ምን ይሆናል! እንደ አደይ አበባ ሁሉ ይቀስማታል:: እግዚአብሄር ይይላት! ያንን ገላ ለሁሉ ታስዳስሰዋለች::

ካውቶቢስ መናኸሪያ ወጥቼ ቁልቁል ተዳፋሁ:: ለጊዜው ወደየት አቅጣጫ ለመሄድ እንዳሰብኩ አላውቅም:: በጣም በሽቆኛል:: አይፈረድብኝም፤ ከሆለታ በጉምጃታ መጥቼ ሳጣት ምን ላድርግ!

መሀል መርካቶ ካንድ ሆቴል ዘው ብዬ ገባሁና ጥግ ይዤ ተቀመጥኩ:: ሰዉ ድራፍት ይጠጣል:: ሰአቱ ወደ አስራ አንድ ሰአት ይጠጋል:: አንዲት ጠየም ያለች ቆንጆ መጥታ:-

"ምን ልታዘዝዎት?" አለችኝ:: ፈገግታዋ ለዛ ነበረው:: ጨምድዶ ያዘኝ::

"ድራፍት" አልኳትና መለስ ብላ ስትሄድ ባይኖቼ ተከተልኳት:: ትዘለ መልካም ናት፤ ሸንቀጥ ያለች:: ከሁሉም ጥርሶቿ ይምጡብኝ:: የተቀሰጤ ልብን ይከፍታሉ:: ድራፍቱን ይዛልኝ መጣችና ከፊቴ ላይ አስቀምጣልኝ ፈቀቅ ብላ ጥግ ይዛ ቆመች:: ስርቅ አድርጌ አየኋት:: ፀጉሯም ዘንፋላ ነው::

መሸተኛው ጠጥቶ ለመሄድ ተቻኩሏል:: እፍግፍግ ብሎ እየተጣደፈ ይጠጣል:: ብዙ ሁካታ አይሰማም:: ፈገግታ የሚባል ነገርም የለም::

ትስተብ ቅሬፋው ሙሽሽ ሲልልኝ ብርጭቆውን ብድግ አድርጌ ... እንደ መጎምዘዝ አለኝ:: ይልቅየ ቅዝቃዜው ያተኮሰ ሰውነቴን አበርዶልኛል:: ... አሁንም ጠጥቶ ለመሄድ ይሻማል:: እኔም እጋባሁና

እንድትደግመኝ ጠቀስኳት:: ለምን እንደ ሆነ እንጃ ወደኔ ስትመጣ ፈገግታዋን ታደምቀዋለች:: ብርጭቆውን ስታነሳ:-

"ይቅርታ፤ ጠምቶኝ ነው:: አጣደፍኩሽ መሰል" አልኳት:: ገና አሁን ነበር ያናገርኳት::

"አይ! ምንም አይደል፤ ስራየ አይደል" አለችኝ፤ አንገቷን መታ ስታደርገው ሀብሏን አየሁት፤ ከጠይም አንገቷ ላይ አርፎ ውበት ሰጥቷታል:: ድራፍቱን ይዛልኝ ተመለሰች:: አሁንም አስተውየ አየኋት:: አንጀት የላትም:: ሽልግ ያለ ነው፤ ከፊቴ አስቀምጣልኝ መለስ ስትል:-

"የት ትሄጂ" አልኳት ፈገግታየን አድምቄ::

"የትም አልሄድ" አለችና መለስ ብላ በትከሻየ በኩል ጠጋ ብላ ቆመች:: መቀመጫ ወንበር አልነበረም:: ደግሞ በጇ ትከሻየን ተመረኮዘችው:: ደስ አለኝ:: የየኔነሽን ራስ ምታት የምትፈውስ ክኒን አገኘሁ::

"ሰዉ የት ለመድረስ ነው እየተጣደፈ የሚጠጣው?" ስል ጨዋታ ለመጀመር ያህል ጠየኳት::

"ሰአት እላፊ ሳይደርስበት በጊዜ ጠጥቶ ወደ ቤቱ ለመሄድ ነው::"

"ሰአት እላፊ እስከ ስንት ነው?" አልኳት ልክ እንደማላውቅ ሰው ሁኜ::

"እስከ ምሽቱ አንድ ሰአት ድረስ:: እንግዳ ነህ እንዴ?"

"እዎን፤ እንግዳ ነኝ:: ከክፍለ ሀገር እንደ መጣሁ ሆለታ ገባሁ:: እጮኛ ነበረችኝ እሷን ልጠይቅ ብመጣ የለችም አሉኝ" ስላት ከንፈሯን መጣ:-

"የት ሄደች አሉህ?"

"ትናንት ሆለታ እንሄደች አልተመለሰችም አሉኝ::"

"እንተኑ ለመጠየቅ ሄዳ ይሆናላ::"

"ሊሆን ይችላል" አልኳትና ትንሽ ዝም ብዬ ቆይቼ "ስምሽ ማን ይባላል?" አልኳት::

"ዕጌ" አለችኝና "ያንተስ?" ስትል ጠየቀችኝ::

"ሙቶ እለቃ ጎርፉ እንደሻው እባላለሁ:: ምንድን ነው የምትጠጭው? ልጋብዝሽ::"

"ድራፍት" ብላኝ ልታመጣ ስትል:-

"እንዳትመላለሽ ለኔም አምጭልኝ" አልኳትና ብርጭቆየን አጋብቼ ሰጠኋት::

ዕጌ ድራፍቱን ይዛ መጣችና የኔን ከፊቴ ላይ አስቀምጣልኝ የሷን አጋመሰችለት:: ደንገጥ አልኩ:: ጠጭ ከሆነች ኪሴ አይችላትም:: ጥርሶቼን ነክሸ ከያዝኳት አምሳ ብር አርባ ቀርታኛለች::

ብርጭቆውን ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችና ከንፈሯን አባብሳ ትከሻየን ደገፍ ብላ በመቆም:-

"ተጫወት" አለችኝ:: የኪሴ መቅለል ቅፅበታዊ ስጋት ወሮኝ ነበር::

"እሺ" አልኳትና ድራፍት ተጎነጨሁ::

"ለመሆኑ መኝታ አገኝ ይሆን?" አልኳት:: አጠያየቁ የቢሆን ይሁን ነበር::

"ልጠይቅልህ እንዴ?"

"አዎን" ስላት ፈጠን ብላ በውስጥ በር ገባች:: ሰአቴን ሳይ ላስራ ሁለት አምስት ደቂቃ ጉዳይ ይላል:: መሸተኛው ቀስ እያለ መሹለክ ይዟል::

ፅጌ ወዲያው ተመለሰችና "እድለኛ ነህ፤ ለትንሽ የመጨረሻውን አልጋ አገኘህ:: ስምንት ብር ስጠኝ" አለችኝ እየተጣደፈች:: አውጥቼ ሰጠኋት:: ሰላሳ ሁለት ብር ቀረኝ:: ጉዶ ፈላ:: አራት አለ፤ ድራፍቱንም ገና አልደጋገምንም:: እሷስ ስንት ትጠይቀኝ ይሆን? ወገቤ ክፍል አለ::

ያልጋውን ሂሳብ ከፍላ መጣች:: ከኔ እልፍ ብለው ይጠጡ የነበሩ ሁለት ሰዎች ሂሳብ ከፍለዋት ሄዱ:: ብርጭቆዎቹን አነሳስታ፣ ጠረጴዛውን ወላውላ አንዱን ወንበር ይዛ በመምጣት ከፊት ለፊቴ ተቀመጠች:: መስተዋት ሆነችልኝ:: በማደሬ ደስ ብሏታል:: ያይኖቿ ቅንድቦች ሳይቀሩ ስቀዋል::

"ተጫወት" አለችኝ ተመቻችታ ከተቀመጠች በኋላ::

"እሽ" አልኳት ፈገግ ብዬ:: ከንግዲህ መሞሽራችን አይደል:: የሂሳቡ ነገር ወዝቤን እርቆኛል::

መከራከሩን ደግሞ አላውቅበት:: ያለኝ ምርጫ ሀቁን መናገር ነው:: ትጠጣ፤ እራት እጋብዛታለሁ:: ያለኝ ገንዘብ ለዚህ ይበቃኛል:: ከዚህ በኋላ እሽ ካለች አብረን እናድራለን:: እንቢ ካለችም ተጠቅልየ መተኛት ነው::

እሷ ከድራፍቱ ከደገመች በኋላ እራታችንን ለመብላት ወደ ምግብ አዳራሽ ገባን:: ሰአት እላፊ በመቃረቡ ነው መሰል ጭር ብሏል:: ከመቀመጣችን ነጭ ካኪ የለበሰ ቦይ መጥቶ:-

"ምን ይምጣላችሁ?" አለን::

"ምን ምን አላችሁ?" ስለው ማት ነገር አነበነበልኝ:: እኔ ይህን ሁሉ የምግብ አይነት አላውቅም:: ቶሎ ብዬ:-

"ጥብስ" አልኩት እሱን ሲጠራልኝ:: ፅጌም እሱን አዘዘች::

"ሂሳብ በቅድሚያ" ሲለኝ:-

"ስንት ነው?" አልኩት እጄን ወደ ኪሴ እያስገባሁ::

"አስራ ሁለት ብር" አለኝ:: አውጥቼ ሰጠሁት:: ሀያ ብር ቀረኝ:: ድራፍቱ ገና አልተከፈለም እንጅ ለፅጌ ይበቃት ነበር::

ጥብሱ መጣልን:: ትኩስ ነው:: ደግሞ ስጋ ነው:: እሱስ ፅጌም ስጋ ነበረች:: ኪሴ ነው ደርቆ ያደረቀኝ::

"ብይ እንጅ" አልኳት እንደ መቅለስለስ ስትል ጊዜ:: የየኔነሽን አለህ በፅጌ አበረድኩት::

በልተን ካበቃን በኋላ ተጣጥበን ወደ መጠጥ ቤቱ ተመልሰን ድራፍታችንን እንጠጣ ጀመር:: ሳይታወቀን ነበር አንድ ሰአት የደረሰው:: ሴቶች እቃ መሸካከፍ፣ ሂሳብ ማስረከብ ይዘዋል:: እኔም ለፅጌ እንዳለ ሀያውን ብር አስረከብኳት:: ዘጠኝ ብር ከሀያ ሳንቲም መለሰችልኝ:: ጓደኞቿ ወደ ቤታቸው ውልቅ ውልቅ አሉ:: አሳዘኑኝ:: ወረቱን የተቀማ ነጋዴ ይመስሉ ነበር:: ወንዱ ወኔው ተሰልቧል...

ፅጌ ሂሳቧን አስረክባ መጣችና ካጠገቤ ተቀመጠች:: አንድ ነገር ልትጠይቀኝ ፈልጋ ትቅለሰለስ ጀመር:: ፈገግታዋ ደግሞ የትህትና አይነት ነበር:: የሴትነት ክብሯ ደግሞ አፍኖ ያዛት:: ቢጨንቃት:-

"ቤቴኮ እሩቅ ነው" አለችኝ::

"የት ነው?" አልኳት::

"ወደ መሳለሚያ ነው::"

"ታዲያ ምን አስጨነቀሽ::"

"ማለቴ ... " ብላ አንገቷን ደፋ አደረገች::

"ማለትሽ?" አልኳት ፈገግ ብዬ::

"አብረን ነወይ የምናድረው ብዬ ነው" አለችኝ::

"ታዲያስ:: አንቺን ብዬ እንጂኮ የማድርበት አላጣሁም:: ለምን እንደሆነ እንጃ ሳይሽ ደስ አልሽኝ" ስላት ፈገግታዋ ጨመረ:: ትንሽ አሰብ አደረኩና "ፅጌ" አልኩና ጠራኋት፤ አጠራሬ ራሱ ለዛ ነበረው::

"ወይየ" አለችኝ እሷም በፍቅር አይን እያየችኝ::

"እንዴት መሰለሽ፤ በምን ሁኔታ እንደ መጣሁ ነግሬሻለሁ:: ዛሬ የገንዘብ ችግር አለብኝ:: በሌላ ጊዜ ግን እጥፍ አድርጌ እክስሻለሁ" ስላት ቁራታ በፊቷ ላይ ሽው ብሎ ሲያልፍ አየሁት::

"ምንም አይደል" አለችኝ:: አመላለሷም በይልኙታ የታፈነ ነበር:: እርግጠኛ ነኝ:: የጋበዝኳት ግብዣና አቀራረቤ ተለሳልሼ እንጅ ፅኔ በዋዛ የምትቀመስ አይደለችም::

ከዚህ በኋላ ወደ መኝታ ክፍላችን አመራን:: ፎቅ ነው:: ደረጃውን ስንወጣ ትንፋሻችን ይፈጥን ነበር:: ክፍላችን ውስጥ እንደ ገባን እኔ ወዳልጋው ሳመራ፣ እሷ በሩን ከረቸመችው:: ካልጋው ጫፍ እግሮቼን አንጠልጥየ ጠበኳት:: ወደኔ ስትመጣ አይኖቿ ማረፊያ አጥተው ተቅበዘበዙ:: ጥርሶቿ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ተገልጠዋል:: ከቅፌ ላይ ወደቀች:: ምንኛ የዋህ ኖሬአለሁ:: የቡና ቤት ሴቶች ገንዘብ እንጅ ፍቅር የሚያውቁ አይመስሉኝም ነበር:: ከንፈሮቿን ሳም አደረኳቸው:: ወለላ ማር ናቸው:: ልብሳችንን ለማውለቅ ሽሚያ ገጠምን::

መብራቱን እረስተነው አላጠፋነውም ነበር:: ብዙም ሳንቆይ ሁለተኛውን ዙር ተያያዝነው:: ለካም ነገር ያለው ሁለተኛው ላይ ነው:: የሰማይ የምድሩን፣ የኢሰፓውን፣ የኢህአዲጉን እንቀባጥር ጀመር::

ጧት ሰአቴን ሳይ አንድ ሰአት ይላል:: ፅጌ ውድቅ ብላ ነበር:: ቀሰቀስኳት:: አይኖቿን አሻሸችና "ነጋ እንዴ?" አለችኝ::

"እረ እረፍዷል" አልኳት:: አይኖቿ እንደ መርገብገብ አሉ:: የሆነየ ከንፈሮቿን ሳምኳቸው:: ወደ ሰውነቴ ጥብቅ አለችና መልሳ ሳመችኝ:: አድረንበት እንደገና ተናነቅነው:: መብራቱም ሲበራ እንዳደረ ነው:: ማህበራዊ ኑሮው ብቻ ነው የጨለመው...

ተነስቼ ልብሴን ስለባብስ እሷም መልበስ ያዘች:: ፀጉሯ ድራሽ አባቱ ጠፍቷል:: ነፋስ እንደ አመሰቃቀለው የጤፍ ነዶ:: በመልክ በመልኩ ካስተካከለችው በኋላ ቦርሳዋን እንግታ ተከተለችኝ:: መብራቱን ያጠፋነው ክፍሉን ስንለቅ ነው::

ከታች ወርደን ፊታችንን ከታጠብን በኋላ ቁርሳችንን ለመብላት ከሆቴል ወጥተን ወደ አንድ ቁርስ ቤት አመራን:: ግሩም የሆነ እንቁላል ጥብስ ነበር የበላነው::

"እንግዲህ ፅጌ የዛሬን መዋሌ አይቀርም" ስላት:-

"እጮኛህን ፍለጋ ነው?" አለችኝ ፈገግ ብላ:: በፈገግታዋ ውስጥ ግን የቅናት ምልክት እየሁባት::

"እሷን ተያት፤ ያልነገርኩሽ ነገር አለ" ስላት ደስ አላት:: በመካከላችን ጠብ እንዳለን በመገመት::

"ከዋልክ ብቅበላ ታዲያ::"

"እመጣለሁ::"

"እንዳትቀር እጠብቅሃለሁ::"

"አልቀርም::"

ከፅጌ እንደተለየሁ በቀጥታ የሄድኩት ወደ ቤቴ ነበር:: እማማ ልኬን ከበሩ ላይ ቁመው አገኘኋቸው::

"ጎርፉ!" አሉና በደስታ ጮሁ:: "ልጄ እንደ ዋዛ ወጥተህ በዚያው ቀረህ! እስቲ ግባ" ብለው ድብርክ ድብርክ እያሉ ቀድመውኝ ገቡ::

"ተለቀቃችሁ?" አሉኝ ከተቀመጥኩ በኋላ::

"አልተለቀቅንም:: መቆየታችን የማይቀር ነው:: እማማ ልኬ እስከዚያው መበርታት ነው::"

"እኔማ ምን እሆን ብለኸኝ ልጄ! አንተ ተጎዳህ እንጂ:: ይስፓ ያልሆነውን አይተናከሉም አሉ:: 'አንተ ዛዲያ ይስፓ አይደለህ:: ለምን አትነግራቸውም? ወዲህ ደሞ ተማሪ ነህ! ከጣጣው የለህበት:: ይህን ሁሉ አብራርተህ ንገራቸው::... የደርግ ጊዜም ታስሬ ነበር በላቸው::"

"እስቲ እሞክራለሁ" አልኳቸው:: የረሳሁትን ይልቅ ቀሰቀሱብኝ:: ይሆናል መስለኝ ዩኒቨርስቲ ትምህርት ጀምሬ ነበር:: ፈተና ሲቀረን'ኮ ነው የተቋረጥነው:: ምን አይነት እድል ነው? ከማድ ላይ መነሳት...

እማማ ልኬ እምበላው ለማዘጋጀት ተፍተፍ ሲሉ እኔ ወደ መኝታ ክፍሌ ገብቼ ሳጥኔን ከፍቼ ስፈትሽ ለችግር ቀን ብዬ ያስቀመጥኩት ሁለት መቶ አምሳ ብር አገኘሁኝ:: ልክ ወድቆ ያገኘሁት ያህል ነበር የተደሰትኩት:: አምሳ ብሩን ለማማ ልኬ ሰጠኋቸው::

ምሳየን በልቼ ወደ ውጭ ሳልወጣ ከቤት ዋልኩኝ:: እማማ ልኬን ተሰናብቻቸው የወጣሁት ልክ አስራ አንድ ሰአት ሲሆን ነበር:: ወደ ፅጌ ከመሄዴ በፊት ለየኔነሽ ስልክ ደወልኩላት::

"ሀሎ!" የሚል የሴት ልጅ ድምፅ ሰማሁ::

"ሀሎ! የኔነሽን ነበር... አልተመለሰችም?... መቶ አለቃ ጎርፉ ደውሎ ነበር በይልኝ፤ ሆለታ ነው ያለሁት:: ጎሽ እንዳትረሺ" ብዬ ስልኩን ዘጋሁት:: ፅጌን ተለዋጭ በማግኘቴ አልተበሳጨሁም:: አደዋዉሌም የቢሆን ይሁን ነበር:: ወደ ፅጌ ገሰገስኩ::

ከምትሰራበት ሆቴል ስገባ ሰዉ ይህን ድራፍት አፍላ ተያይዞታል:: መቀመጫ ፍለጋ ባይኖቼ ዘወርወር ብዬ ሳይ ፅጌን ከወዲያ በኩል ቁጭ ብላ አየኋት:: ፈገግ ብላ ጠቀሰችኝ:: ካጠገቧ ስደርስ ተነሳችና እጄን ጨበጠችኝ::

"ታዲየስ" ብያት ተቀመጥኩ:: ሁለት ሰዎች ካጠገቧ ተቀምጠው ድራፍት ይጠጡ ነበር:: እኔ ሶስተኛ ሁኘ ጠረጴዛ ተጋራሁኝ::

"ምን ይምጣልህ?" አለችኝ ትከሻየን በጇ ደገፍ ብላ:: የሚወዱትን ወይንም የፈቀዱትን ወንድ ሳይሆን አይቀርም እጃቸውን ጣል የሚያደርጉበት::

"ድራፍት" አልኳት:: የጠረጴዛ ባልደረቦቼ አረጋ ያለ ጨዋታ ይዘው ነበር:: ስለጊዜው ሁኔታ ነው:-

"... ምን እንዳያመጡ ብለሃቸው ነው? 'ጨው ለራስህ ብትል ጣፍጥ፤ አለበለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል' የሚባል አባባል አለ:: ለራሳቸው ቢሉ የህዝቡን ትንፋሽ ያዳምጡ:: አለዚያ ግን የደርግ እጣ ይጠብቃቸዋል:: የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሆነ ከንግዲህ ወዲያ አይታለልም" አለ ጥርሰ በላዛው ሰውየ::

"እንደ ደርግ መላ የሚፈጥሩ ከሆንማ እዳልከው የደርግ እጣ ይጠብቃቸዋል" አለ ራሰ በራው::

ፅጌ ድራፍቱን አምጥታ ከፊቴ አስቀመጠችልኝና ወደ ጆሮየ ጠጋ ብላ "እጮኛህን አገኘህት?" አለችኝ

"አልፈለኳትም" አልኳት::

"ቀጣፊ!" አለችኝ::

"ሙች" ስላት:-

"ልክ አይደለህም" አለችኝ::

"ልክ ነኝ እባክሽ:: ከተወችኝ መተው ነው:: ይልቅ የምትጠጭው ያዥ:: በነገራችን ላይ አልጋ እንዴት ነው?"

"ይገርለሁኝ" ብላኝ ድራፍት ልታመጣ ሄደች:: ወደ ሰዎቹ ወሬ ጆሮዬን ጣል አደረኩ::

"ለመሆኑ መመሪያቸው ምንድን ነው?" አለ ራሰ በራው::

"ዲሞክራሲ ነው" ሲል ጥርሰ በላዛው ሁሉቱም ሳቁ:: እኔም ፈገግ አልኩኝ::

"ጦሩ ነው አንተው ጉድ የሰራን፤ ሸንጡን ገትሮ ቢዋጋ ይኸ ሁሉ ነገር አይመጣም ነበር" አለ ራሰ በራው::

"ጦሩ ምን ያድርግ ብለህ፤ እንደምንሰማው ከሆነ እያንዳንዱ የጦር ግንባር በገንዘብ ተቸብችቧል አሉ:: በዚህ ላይ ጀኔራሎቹ እየጣሉት ይፈረጥጣሉ" ሲል መለሰለት::

ፅጌ መጥታ ስለቆመች የነሱን ጨዋታ ማዳመጡን ተወት አድርጌ ወደሷ መለስ ብዬ:- "መቀመጫ አጣሽ?" አልኳት::

"የለም፤ በሙሉ ተይዟል" አለችኝ:: እኛ ሶስተኛ ስንይዝ የጠረጴዛ ባልደረቦቼ ሂሳብ ከፍለው ሄዱ:: ብርጭቆዎቹን አነሳስታ ስትመለስ:-

"እራታችንን እንብላ፤ እርቦኛል" አለችኝ:: ገንዘብ እንደያዝኩ አውቃለች::

"እሽ" ብያት ይዢው የነበረውን ድራፍት ጨልጬ ቀድሜያት ወደ ምግብ አዳራሽ ገባሁኝና ጥብስ አዘዝኩኝ:: ቁርጥስ እሷኑ ብቆርጥ ይሻለኛል::

ጥብሱ ቀርቦልን እየበላን እያለን "በቃ በእጮኛህ ጨከንክባት ማለት ነው?" በማለት ከፊቴ ላይ አንዳች ነገር የምታነብ ይመስል ትክ ብላ ታየኝ ጀመር::

"እውነቱን እንድነግርሽ ትፈልጊያለሽ?"

"እስቲ ንገረኝ::"

"እንዳንቺ ድንገት ያገኘኋት ፍቅረኛዬ እንጅ እጮኛዬ አይደለችም:: ግን ለብዙ ጊዜ በፍቅር አብረን ቆይተናል" ስላት:-

"እስቲ እጅን ምታኝ" ብላ እጇን ወደኔ ዘረጋች:: መታኋት:: ልክ የግሏ ያደረገችኝ ያህል ደስ አላት:: እንዳጤንኳት ቶሎ ፍቅር የሚያጠቃት፣ እና ደግሞ ቅናት የሚጠብሳት አይነት ናት:: ምስኪን፤ አሳዘነችኝ:: ቡና ቤት ገብታ ተንገረገበችው:: ዛሬ አንዱን ነገ ሌላውን:: በቃ ጥቂት ብሮች መለቃቀም፤ ሽቶ መግዛት፤ ያችን መቀባባት፤ ብልጭልጭ ልብሶች ለብሳ መብለጭለጭ... ጊዜውም ፍሬ የሌለው ብልጭልጭ ጊዜ ነው...

"ቡና ቤት ኖሯል የምትሰራው?" ስትል ጠየቀችኝ::

"ነገሩስ የቢሮ ፀሀፊ ነበረች" ስላት በንቀት ከንፈሯን ለጠጥ አድርጋ:-

"ይችስ ሸጣሃለች:: ደግሞ የቢሮ ፀሀፊዎች ሁሉ አይደል እንዴ የሚጎትታቸው:: ቡና ቤት ያለነው በቁርጡ እንሻላለን::"

"እስቲ መሻላችሁን ወደፊት ባንቺ ላያችሁ አይደል" አልኳት::

እራታችንን በልተን ወደ መጠጥ ቤቱ ስንመለስ ሰዉ ሄዶ መጠጥ ቤቱ ጭር ብሎ ነበር:: ጊዜውም ጭርር ብሏል... እኛንም ጊዜው አላዝናናንም:: ወዲያው ሰአት ደረሰ::

ሂሳቧን እስረክባ እየተጣደፍን ወደ ፎቁ ስንወጣ አደናቅፍዋት ባፍጢሟ ልትደፋ ስትል:- "እኔ ልደፋልሽ!" ብዬ ቀለብኳት:: ጥርሶቿ ሊረግፉ ነበር:: በሳቅ ተንካካች:: ለብ ብሏታል::

ለካ የፍቅርም ጣእሙ የሚታወቀው ሲደገም ነው:: ከትናንቱ የተለየች ሆነችብኝ:: አቤት ትንፋሻችን! ላባችን ደግሞ ምንድን ነው? ሰውነታችን ጨርሶ ቀለጠ...

"መጥቼ እጠይቅሃለሁ::"

"እሺ::"

"አይከለክሉም አይደል?"

"አይከለክሉም::"

የፍቅርና የሰላም ሌሊት ነበር:: ኢትዮጵያ ብቻ ነች የልጆቿን ፍቅር አጥታ ሰላሟ ተናግቶ የምትታመሰው፤ እኔና ፅጌስ በሰላም አነጋነው::

ጧት ቀድሜያት በመነሳት ልብሴን ስለባብስ በጀርባዋ ጋደም እንዳለች ታየኝ ነበር::

"ተነሽ እንጅ" አልኳት::

"እሁ!" አለች ለመነሳት እየተንጠራራች:: ትክት ብሏታል:: አይፈረድባትም:: ሁለት ሌሊት... ያለእረፍት፤ እኔም በፅናት ይዘው እንጅ ራሴ ኸው ሲልብኝ ይታወቀኛል::

ልብሷን ለባብሳ እንዳበቃች ሃምሳ ብር ከኪሴ አውጥቼ ሰጠኋት::

"እቁብ ደርሶብኝ እንጅ አልቀበልህም ነበር:: ዝርዝር የለህም?" አለችኝ::

"የምን ዝርዝር?"

"ያምሳ ብሩ:: መልስ የምሰጥህ ስለሌለኝ ነው::"

"መልስ አያስፈልገኝም::"

"እንዴ! እስረኛኮ ነህ" አለችኝ::

"እስረኛ አይደለሁም:: ታዳሽ ነኝ:: አዲስ ሰው እንድሆን" ሳቅ አልኩኝ፤ በገዛ አነጋገሬ:: ቃል ሳትናገር ተከተለችኝ::

ቁርሳችንን በልተን አውቶብስ ተራ ስንገባ የሰዉ ትርምስ ለጉድ ነው:: ስንጋፋ፣ ላይ ታች ስንል ባንድ ሰአት የሄድን ካምስት ሰአት ደረስን:: ትግስቴን ጨረስኩ:: ፅጌን ወደ ቤትሽ ሂጂ ብላት እንቢ አለችኝ:: በዚህ ላይ ፀሀዩ እናት ይነድላል:: የሰኔ ፀሀይ አይጣል ነው:: ፅጌ እኔ በሄድኩበት ትከተለኛለች:: ከንፈሮቿ ደርቀዋል:: ድክም እንዳላት እርምጃዋ ያስታውቃል::

ግፊያውን ባለመቻሌ አንድ ሀሳብ ስለመጣልኝ እየገሰገስኩ ወደ ስምሪት ክፍሉ ገባሁ:: ፅጌም ተከትላኝ በመግባት ከኋላየ ቆመች:: ቱታ የለበሰች ሴት ለሹፌሮች የመውጫ ወረቀት ትሰጣለች:: ልቅና እንዳላት ተረዳሁ:: ሹፌሮቹ ሁሉ ይሽቆጠቆጡላታል::

"የኔ መቤት ችግር ገጥሞኝ ነው:: ተባበሪኝ:: ሆለታ ሀጅ ነበርኩ:: መኮንን ነኝ:: ይኸውና ከጧት ጀምሬ እስካሁን ድረስ ብጋፋ ወረፋ አልደረሰኝ አለ" አልኳት::

"አንችስ?" አለቻት ፅጌን ለኔ መልስ ከመስጠቷ በፊት::

"የኔ ባለቤት ነች" ስላት:-

"እስከነ ባለቤትዎት ነው እንዴ እጅዎን የሰጡት?" አለችኝ:: ተሳሳቅን:: ምን ይደረግ:: ደግነቱ እንዲህ ብላኝ አልቀረችም:: ይዛኝ ወጥታ ላንድ የመለስተኛ አውቶቢስ ሹፌር ሰጠችኝ:: ያቆያት::

"ሳምንት እሁድ እመጣለሁ:: እንድትጠብቀኝ::" አለችኝ ፅጌ አውቶቢስ ውስጥ ከመግባቴ በፊት ስንሰነባበት::

"የመኪና ችግር አለ:: እንደምታይው ነው:: ከስራሽ እንዳትሰናከይ::"

"ግዴለህም፣ እንደ ሰው እሆናለሁ::" ብላኝ ወደ ቤቷ ሄደች:: አይኖቼ ተከትለዋት ነበር:: ተሃድሶ ይሏል እንዲህ ነው:: በዚህ ሁኔታ ነበር ፅጌ አድሳ የለቀቀችኝ:: የኢህአዲግ ተሃድሶ ነው ደብዛው የጠፋ!

ምእራፍ ሰባት

አሰበን እንስራ ለነገም እንዲሆን፤
ይሁን ይሁን ብለን የማይሆን እንዳይሆን።

16

ቀኑ ሰኔ 24 ቀን 83 ዓ.ም. ነው። የሽግግር መንግስቱ የሚመሰረትበት እለት።

ሌሊቱን ዝናብ ሲወርድ ነው ያደረው። ከውጭ በየጥጉ የተኙት መኮንኖች ሲንጫጩ ነው ያነጉት። ቀኑ አሁንም ቢሆን እንደ ጨፈገገው ነው። የመኮንኖቹም ፊት እንደ ቀኑ ምርግ ያለ ነው። በየመኝታቸው ላይ ተደምመው በህሊናቸው አንዳች ነገር የሚዳስሱ ይመስላሉ። ከኔ ጎን የሚተኛው መኮንን ተጠቅልሎ እንደተኛ ነው። ፊፅሞ ተስፋ ቆርጧል። ደግሞ ሲጋራ አጭያሽ ነው። ሱስም ሳይገለው አይቀርም። እርሃብም ጎድቶታል። ለምን እንደሆነ እንጃ መኮንኖቹ አያቀርቡትም። ድሃ በመሆኑ ይሆን? ሊገባኝ አልቻለም። እሱም ቢሆን ከማንም አይጠጋም። ደስ ሲለው ትንሽ ከኔ ጋር ይነጋገራል። በተረፈ ዝም ነው። አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው ተጠቅልሎ በመተኛት ነው። መኝታ ሲበዛ ደግሞ መጥፎ ነው። እርሃብም ካንጀት ይገባል። ስሙን ገና በቅርቡ ነው ያወኩት። መቶ አለቃ ሀይለሚካኤል ይባላል።

የወታደር ጃኬቴን እስከ አንገቴ ድረስ ቆልፌ በመልበስ፣ ፎጣ ደግሞ በመከናነብ ከመኝታየ ተቀምጬ መፅሀፍ አነባለሁ። ሻምበል በድሉና ሻምበል አዱኛ እንደተኙ አፍላፍ ገጥመው ያንሾካሹካሉ። የሚሉት አይሰማኝም።

መቶ አለቃ ሀይለሚካኤል ድንገት ከተኛበት ወርጫ ሲል ጎኔን በክርኑ ስለጎሸመኝ ትንሽ ፈቀቅ አልኩኝ።

"ይቅርታ" አለኝ ከራሱ ቀና አለና።

"ምንም አይደል" አልኩት። ደጋግሞ አዛጋና ተመልሶ ተኛ። ከነጋ ምንም ነገር አልቀመሰም። አንጀቱ ታጥፍዋል። ብዙም ሳይቆይ ብርድ ልብሱን እንደለበሰ ተቀመጠ። አሁንም ደጋግሞ አዛጋና ትክ ብሎ አየኝ። እስተያየቱ አንድ ነገር የመሻት ነው።

"ምን ልርዳህ?" አልኩት እነበው የነበረውን መፅሀፍ አጠፍ አድርጌ በመያዝ።

"ያንዲት ሲጋራ መግዣ ሀያ አምስት ሳንቲም" አለኝ።

"እሺ" አልኩትና በነጠላ ጫማ ወደ ውጭ ወጣሁና ቆም ብዬ ላፍታ አካባቢውን ቃኘሁት። ዝናብ ያደረባቸው መኮንኖች ልብሳቸውን ያሰጣጣሉ። ጥቂት መኮንኖች ደግሞ ወደ ላይ ወደ ታች ይንከላወሳሉ። ፊታቸው እንደ ቀኑ የከፋ ነው። በሀሳብም፣ በብርድም ተጨባብጠዋል።

ከሲጋራ አዟሪዎች ላይ አንድ ፓኬት ኒያላ ገዝቼ በመግባት ስሰጠው "ምነው መቶ አለቃ ጎርፉ? መግዛቱንማ እኔ እገዛው ነበር። ደግሞ የጠየቁህ ያንዲት ሲጋራ መግገ ነበር። አይይ...! እግዚአብሄር ይስጥህ" አለኝ።

"አሜን" ብዬው ተቀመጥኩ። ተስገብግቦ ነበር ከብሪት ጭሮ አንዱን ሲጋራ ያያያዘው። ጠምቶት ኖሯል። እያከታተለ ያቦነው ጀመር። ሰረቅ እያደረኩ አየዋለሁ። ያለማቋረጥ አንዷን ሲጋራ አጭሶ ጨረሰና ከዚያው ላይ ሌላ ለኮሰ።

"በባዶ ሆድህ ሲጋራው አይጎዳህም? ባታበዛ ጥሩ ነው" ስለው፡-

"ይጉዳኝ፤ መኖር አልፈልግም" አለኝ።

"አይዞህ ተስፋ አትቁረጥ" አልኩት። ቶሎ መልስ አልሰጠኝም፤ በጭሱ ውስጥ አንድ ነገር የሚያይ ይመስል ነበር። በሀሳብ እርቆ ሲያይ ቆየና ድንገት ፈገግ ብሎ፡-

"ልጆች አሉህ መቶ አለቃ ጎርፉ?" ሲል ጠየቀኝ።

"የሉኝም።"

"ሚስትስ?"

"የለኝም። ጠብደል ወንደላጤ ነኝ።"

"ታድለህ" አለኝ።

"መታደል አደረከው። እኔ ደግሞ ባልታደል ነው የምለው" አልኩት።

"የለም፤ መታደል ነው። ለምሳሌ እኔ ዛሬ ልጆቼና ሚስቴ ባይኖሩብኝ ኖሮ ላንድ ህይወቴ አልጨነቅም ነበር። የልጅን አስፈላጊነት አጥቼው እንዳይመስልህ። ሁሉም ነገር ሲደላ ነው ደስ የሚለው። በእውነት ነው የምልህ ለጆቼ የሚቀምሱት የላቸውም። በኑሮየ መሰረት የለኝም። በረሃ ለበረሃ ስንከራተት ነው የኖርኩት። ልጆቼ የንጀራ እርሃብ ብቻ ሳይሆን የኔም ርሃብ አለባቸው። እኔም ብሆን ልጆቼ ይርቡኛል፤ ሚስቴ ትናፍቀኛለች። አንድም ቀን ቁጭ ብዬ አጫውቻቸው አላውቅም። ሁልጊዜም በደብዳቤ። መደምደሚያውም ስቃይ ሆነልህ..."

"አይዞህ፤ ዛሬ 24 ቀን አይደለም? የኛም ችግር እልባት ያገኝ ይሆናል?" ስለው እንደ መሳቅ አለና፡-

"ከንቱ ተስፋ ነው መቶ አለቃ ጎርፉ። ወያኔዎችን ደህና አድርጌ አውቃቸዋለሁ። ዘመዶቼ ናቸው። ቅንጣት ካላማቸው ንቅንቅ አይሉም። መነሻቸውን ካወክ መድረሻቸውም አይጠፋህ። በቀለኞች ናቸው።"

"ትግሬ ነህ እንዴ ጓድ መቶ አለቃ?" አልኩት ትንሽ ፈገግ ብዬ።

"ንፁህ ትግሬ አይደለሁም። አማራም ነኝ። አንዱም የሚያሳዝነኝ ይኸ ዘር ቆጠራ ነው። እኔ ከማንኛው ወገን እንደ ምሆን ወደፊት እንጃልኝ? አባቴ ጎንደሬ ነው። እናቴ ደግሞ ትግሬ ነች። አባቴ ፖሊስ ነበር። በስራ ምክንያት ትግራይ ሄዶ ነው እናቴን አግብቶ እኔን የወለዱት። ቢደንቅህ ባለቤቴ ግማሽ አደሬ፣ ግማሽ ኦሮሞ ናት። ሀረር 3ኛ ክፍለ ጦር እያለሁ ነው የተጋባነው። እንግዲህ የኛ ልጆች የየትኛው ብሄረሰብ አባል ሊሆኑ ነው?" አለና ሶስተኛ ሲጋራ አቀጣጠለ።

"ኧረ ሲጋራው ይጎዳሃል!"

"ይጉዳኝ አንተው። ኢትዮጵያ ከንግዲህ የኔ አትሆንም። ንፁህ ዘሮች ይፈንጩባት!" አለ ምርር ብሎ።

"ተው መቶ አለቃ ሀይለሚካኤል፤ እንደዚህ አይባልም። በኔ ይሁንብህ፤ ከዛሬው ኮንፈረንስ አንድ ውጤት እናገኛለን። እርግጠኛ ነኝ የግንቦትን ወር ደመወዛችንን ይሰጡናል።"

"በዚህ ተስፋ አታድርግ። አጉል ተስፋ በሽታ ነው። መብታችንን የሚጠብቁ፣ ደመወዛችን የሚሰጡን ቢሆን ኖሮ እኛን ከዚህ ድረስ ማምጣት ባላስፈለጋቸው ነበር። ሲያታልሉን ነው። እኛ መቼም ሁልጊዜ እንደተታለልን ነው። ሀይለስላሴ አስር እጅ ዋሽቶ ነበር። ደርግ ደግሞ ሺ ጊዜ ዋሽቷል። እነዚህ ደግሞ ገና ሚሊዮን ጊዜ ይዋሻሉ። እድገት ነው" አለኝ። ማፅናናት አልሆነልኝም። እንገቴን ደፋሁ። እሱም ዝም ብሎ ሲጋራውን ይለበልብ ጀመር። ሳየው ፓኬቱ ካላለቀ በስተቀር የሚያቆም አይመስልም።

ሻምበል በድሉ ጫኔና ሻምበል አዱኛ ደቻሳ ከመኝታቸው ተነስተው ጠቅሰውኝ ወደ ውጭ ወጡ። መፅሀፌን ከራስጌየ አስቀምጬ ተከተልኳቸው። ፀሀይዋ አሁን ፍዋ...! ብላለች። ወደ ዳገቱ ሄደው ጠፍታ ቦታ መርጠው ተቀመጡ።

"ለምን ነበር የፈለጋችሁኝ?" አልኳቸው ከተቀመጥኩ በኋላ።

"ከዚያ መቶ አለቃ ጋር ምንድን ነበር ስታወራ የነበረው?" ሲል በድሉ ጠየቀኝ።

"የግል ችግሩን ነበር ሲያወራኝ የነበረው" ስለው አዱኛ ቱግ አለና:-

"ምን የግል ችግሩን ያወራሃል! 'ወያኔዎችን አውቃቸዋለሁ፤ ዘመዶቼ ናቸው...' ይልህ አልነበረም?" አለኝ ልክ እንደ ህፃን ልጅ በማፋጠጥ።

"ይህን ያለኝ ታዲያ ከግል ችግሩ ተነስተን ስናወራ ነው..." ስለው በድሉ ደግሞ አቋረጠኝና:- "ዋናው ነገር ሰውየው የኢህአዲግ መረጃ ስለሆነ ብትጠነቀቅ ይሻልሃል! ትግሬ መኮንኖችን ብዙ ባንቀርባቸው ጥሩ ነው" አለኝ።

"ኧረ በፈጠራችሁ እሱ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ነው። ችግር ነው የሚያቆላምመው።"

"አንድም ችግር የለበት። አውቆ ነው ችግረኛ በመምሰል ተቆልምሞ እየተኛ የሚያደባው። ደግሞ ካንተ ላይ ነው ጥላውን ያጠላው" አለኝ አዱኛ።

"ምንድን ነው የምታወራው? ለመሆኑ እሱ ከኔ ምንድን ነው የሚያገኘው? ከንቱ ሃጢአት አትግቡ" አልኩኝ ቆጣ ብዬ።

"ብቻ ብትጠነቀቅ አይከፋም። መኮንኖቹ ሁሉ አውቀውት ነቅተውበታል። አንተ ብቻ ነህ ያልነቃህበት" አለኝ በድሉ።

ሁለቱን ተከራክሬ ማሸነፍ ስላቃተኝ አኩርፌ ጥያቸው ወደ መኝታ ክፍል ገባሁ። ሀይለ ሚካኤል ተኝቶ ነበር። ለካ የመኝታ ክፍላችን መኮንኖች የማያስጠጉት ለዚህ ነው። እውነት የኢህአዲግ መረጃ ይሆን? ኧረ ይኸ ኮንፈረንስ ተካሄደ በተገላገልነው።

ኮንፈረንሱ ልክ ዘጠኝ ሰአት ከሀያ አምስት ደቂቃ ሲሆን ተከፈተና መጠነኛ መተዋወቅ አድርጎ የመነጋገሪያ አጀንዳዎችን አፅድቆ ለቀጣዩ ቀን ተቀጥሮ አበቃ።

«ምኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ፣
ግብሩ እንቁላል ነበር እህን ጊዜ አበሻ!»

በማግስቱ፣ ሰኔ 25 ቀን ኮንፈረንሱ በመጀመሪያ ፕሬዚዳንት ከመረጠ በኋላ የመነጋገሪያ ቋንቋ አማረኛና እንግሊዘኛ እንዲሆን ተወሰነ። እንደ አማራጭ አረብኛም ቀርቦ ነበር። የፈለገ ደግሞ በራሱ ቋንቋ ባስተርጓሚ መናገር እንደሚችል የዲሞክራሲ መብት ተሰጥቶታል። ሁላችንም ጆሮዎቻችንን ከራዲዮኑ ለግተናል። አብዛኛው ተሰብሳቢ እየጎላ ይናገር የነበረው «ስለ መቶ አመት ታሪክ» ነበር። ያንድ ብሄረሰብ ተወካይ ምርር ባለ አነጋገር:- «... ከምኒልክ ጀምረን ተጨቁነንና ተረግጠን የኖርን ነን። እንኳንስ ለመንግስት ስራ ልንመክር ቀርቶ ከሸንኮራ አገዳ ቆረጣም ወጥተን አናውቅም። ሌላው ቀርቶ ስማችን ጌደቦ የተባለው ገዳሙ እየተባለ ያማራ ስም እየተሰጠን ወግና ባህላችን ተረግጦ ነበር። ዛሬ ለዚህ በመብቃታችን ከልብ ተደስተናል።»

ሌላው አከራካሪ ነጥብ የኤርትራ ጉዳይ ነበር። «መዋጋት ለሚፈልግ መንገዱን ጨርቅ ያድርግለት!» አሉ አዲሱ ፕሬዚዳንት። እስካሁን የተከፈለው መስዋእትነት መለስ ዜናዊን ፕሬዚዳንት ለማድረግና ኤርትራን እስከ ማስገንጠል ድረስ ነበር ማለት ነው።

ቀጥሎ የቀረበው ጥያቄ ደግሞ የባንዲራ ጉዳይ ነበር። ለዚህ ጥያቄ ፕሬዚዳንቱ ሲመልሱ ልክ ቁስላቸው የተነካ ያህል ተቆጥተው ነበር። «... እኛ ከጨርቁ ነገር የለንም! ከጨርቁ በስተጀርባ ካለው እንጅ! ለማንኛውም ስለባንዲራ ጉዳይ ወደፊት የኢትዮጵያ ህዝብ የሚወስነው ይሆናል!» ብለው ባጭሩ ዘጉት። የኛም የማዳመጥ ስሜት አብሮ ተዘጋ።

ኮንፈረንሱ ስለኛ ጉዳይ አንድም ነገር ሳያነሳ ተጠናቀቀ። አብዛኛው መኮንን ክሽልሽል ነበር ያለው።

ወደ ማታ ገደማ እኛ ሶስታችን፣ አራተኛ ኮሎኔል ዘርጋው ሆነን ስለኮንፈረንሱ ማንሳት መጣል ያዝን። ዳገቱ ላይ ነበር የተቀመጥነው።

"እንዲያው ጎበዝ ይኸ አማራ የሚወነጀልበት መብዛቱ። ሰው ሙቼስ አካባቢ የሚፈጥረውን ሰርቶ ይኖራል። አሁን አገዳ ቆረጣን ምን አመጣው? ይህም ይሁን ቢሻው። 'ጌዴቦን ገዳሙ....' ተብሎ የተነገረው እውነት የኢትዮጵያ አጣዳፊው ችግር የስም ለውጥ ነው? ደግሞስ ሙቼ ነው አማራ ስማችሁን ለውጡ ያለው? ኧረ ወዲያ! ከደርግ የባሰ ሆያ ሆየ!" አሉ ኮሎኔል አዝነው።

"እየ ጌታየ! ወደፊት ከነ አገዳ ቆረጣው ሲያጣው ያነየ ደግሞ 'ድሮስ አገዳ ቆርጠን በሰላም እንኖር ነበር፤ ዛሬስ ከነ አገዳ ቆረጣውም አጣን' ብሎ የሚናገርበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም" አላቸው በድሉ።

"ልክ ነህ። ይኸ የማይቀር ነው። በዚህ አይነትማ ምኑን ሰላም ተፈጠረው" አሉት። አዱኛ ደግሞ ቀበል ብሎ:- "ጌታዬ ባንዲራችንን ፕሬዚዳንቱ 'ጨርቅ' አሏት ሲላቸው:-

"ኤዲያ! ማቅም ይበላት! ከሱ የምንጠብቀው ነው!" አሉት። በዚህ ጊዜ እኔ ካጎዘበስኩበት ቀና አልኩና:-

"ዋናው ነገር ወሳኙ ህዝቡ ነው። ሁልጊዜ ባፈ ጮሌዎች መነዳት የለበትም። የጎበጠውን ማቃናት፣ የተጣመመውን ማስተካከል አለበት። የደርግ ድለቃ ይበቃናል። ጦርነት የኋላ ቀርነት ምልክት ነው።

የሙቶ አመት ታሪክ እየጠቀሱ ጦር ጠማኝ ማለት ወደባሰ ችግር ነው የሚከተን:: በዚያን ጊዜ ስህተቶች ተፈፅመው ሊሆን ይችላል:: ታዲያ እንደነዚያ ያሉ ስህተቶች እንዳይደገሙ መጣር እንጅ ማባባስ ለማንኛችንም የሚበጅ አይምስለኝም:: ታሪክን መጋራት እንጅ ላንድ ብሄረሰብ ብቻ መቆለልም የኋሏ ኋላ ፀፀት ላይ የሚጥል ይመስለኛል:: 'ዘማች አማራ፣ ጦረኛ አማራ፣ ያንድነት ጠበቃ አማራ፣ ነፍጠኛ አማራ፣ ባንዲራ ያማራ፣ ኢትዮጵያ ማለት አማራ' እየተባለ የሚነገረው ትክክል አይመስለኝም:: ስም የሌለው የሰው ስም ያጠፋል:: ታሪክ የሌለውም የሌላውን ታሪክ ያጎድፋል:: ቅርስ የሌለው ቅርስ አልባ ያደርጋል:: ዛሬ የተያዘው ይህን ይመስላል:: አሳዛኝ ኢትዮጵያ!' ስል አምርሬ ተናገርኩ::

"ልክ ነህ" አሉ ኮሎኔል ራሳቸውን እየወዘወዙ:: ከዚህ በኋላ የረባ አልተነጋገርንም:: ድንገዝገዝ እንዳልን ነበር የተለያየነው:: ሰማዩም ክብድብድ ብሏል:: የኛም ፊት ከብዷል...

17

የጠበቅነው ቀርቶ ያልጠበቅነው መጣ፣
እባቡን ብንቀብረው ከስር ጊንጡ ወጣ::

በየክፍለ ጦራችን እንድንሰባሰብ በድምፅ ማጉሊያ የተነገረን ቁርሳችንን በልተን እንዳበቃን ነበር:: ከኮንፈረንሱ በኋላ ስንሰበሰብ የመጀመሪያ ጊዜያችን ስለሆን የታመሙ እንኳን አልቀሩም:: ከሀውልቱ ፊትለፊት ከዳገቱ ላይ ነበር የተሰበሰብነው::

ሶስት የኢህአዴግ አባላት እየተጣደፉ መጡና ከፊት ለፊታችን ቆሙ:: ቶሎ ንግግር አልጀመሩም:: እኛ ደግሞ ቸኩለናል:: አንድ አይነት ውሳኔ እንደያዙልን ቅንጣት አልተጠራጠርንም:: እስበሳቸው አንሾካሽኩና አንዱ ታጋይ ወደኛ ወጣ ብሎ በድምፅ ማጉሊያ በመጀመሪያ ኮንፈረንሱ እንዴት ተጀምሮ በምን መልክ እንደተጠናቀቀ አጠር አድርጎ ካብራራልን በኋላ የድጋፍ ሰልፍ እንድናደርግ ስልት በተሞላበት ሁኔታ በመግባቢያ ቃላት ያጎርፍልን ጀመር:: እኛ ገነፈልን:: አንድ መኮንን ብድግ ብሎ:-

"በመጀመሪያ መብታችንን ጠብቁልን:: ከዚያ ደግሞ ስለ ኢህአዲግ አላማና ፕሮግራም በሰሚናር መልክ ይሰጠን:: ከዚህ በኋላ የድጋፍ ሰልፍ ማድረግ እንችላለን" ብሎ ሲቀመጥ ሌላው መኮንን ተነስቶ:-

"ሰልፉንም ሆነ ሴሚናሩን ቀስ ብለን እንደርስበታለን:: ጊዜ የማይሰጠው እርሃብ ነው:: ደመወዛችንን ስጡን:: ቤተሰቦቻችን በርሃብ አይለቁ!" ሲል ጠቅላላ መኮንኑ ሀሳቡን ደግፎ አጨበጨበ:: ሶስተኛ መኮንን ተነሳና ደግሞ:-

"እኛ የኢትዮጵያ መኮንኖች እንጅ የደርግ መኮንኖች

አይደለንም:: ለምንድን ነው በማስ ሚዲያ 'የደርግ መኮንኖች' እያላችሁ የምትጠሩን?" አለ::

"ይኸ አያጣላንም:: ወደፊት እንዲስተካከል እናደርጋለን' ሲል ታጋዩ መልስ ሰጠ::

"እኛም ሰልፉን የምንሰለፈው ደመወዛችንን ስትሰጡንና ስታስተካክሉ ይሆናል" ሲል አንድ መኮንን ተሸምቆ መለሰ:: ከዚህ በኋላ ፈዕሞ መጣጣም አልተቻለም:: ከፍተኛ መቃቃር ተፈጠረ:: የኛ ቁጣ እየበረታ መጣ::

"እሺ እረጋ በሉ" አለንና ፀጥ ስንልለት "ያለፍላጎታችሁ በግድ ተሰለፉ አንላችሁም:: ነገር ግን አንድ እውቃችሁት መሄድ የሚገባችሁ ጉዳይ አለ:: ይኸውም በነዚህ ሶስት ቀናት ውስጥ ወደ ጦላይ ትሄዳላችሁ:: የተሃድሶ ትምህርቱን ለመጀመር በዚህ በተጨናነቀ ሁኔታ አይቻልም" ሲለን ጠቅላላችን ኩምሽሽ አልን:: ድንገተኛ መብረቅ ነበር የመታን:: ወዲያው ጥለናቸው ተበተን::

"ያልኩት እውነት አልሆነም ታዲያ ሙቶ አለቃ ጎርፉ" አለኝ ሙቶ አለቃ ሀይለ ሚካኤል:: ወደ ክፍል ጥልቅ ብዬ ከመኝታዬ ላይ ከመቀመጤ :: እሱ ቀድሞኝ በመግባት ከመኝታው ላይ ተቀምጦ ሲጋራ ያጨስ ነበር:: እሱም ጭሷል...

"አንተስ ብለሃል" አልኩት እራሴን እየነቀነኩ::

"እኔ ሀይለሚካኤል ካሁን በኋላ የነሱ መጫወቻ አልሆንም!" አለና ሌላ ሲጋራ አቀጣጠለ:: ሰውነቱም በንዴት ተቀጣጥሏል:: ከዚህ በኋላ አልተነጋገርንም::

መኮንኑ ሁሉ ሌላ ወሬ የለውም፤ ስለጉዟችን ሁኔታ ነው:: ግማሾቹ "ሰልፉን ብንሰለፍ ኖሮ ከዚህ አያነሱንም ነበር" ይላሉ:: ግማሾቹ ደግሞ "የለም፤ ብንሰለፍም ከዚህ መልቀቃችን የማይቀር ነው:: እንኳንም አልተሰለፍን!" እያሉ እልህ ይተናነቃቸዋል:: አንዳንዶቹ ደግሞ "የጦላይ ወባ ቀንኘስ ነው፤ እባቡና ዘንዶውም መከራ ነው:: ብዙ ብሄራዊ ወታደር ተውጦ ቀርቷል" ይላሉ:: እኔ ጦላይን አላውቀውም:: ጭንቅ ጥብብ አለኝ:: ኧረ ከመሄዳችን በፊት ደግሞ ዕጌ በመጣችልኝና በተሰናበትኳት::

18

ዛሬ እለተ ሰንበት ነው፤ ዕጌ እንደማትቀር እርግጠኛ ነበርኩ:: የማለዳ ቤተሰቦች በድምፅ ማጉሊያ ሲያስጠሩ ይሰማኛል:: ወደ ውጭ ስወጣ ሙቶ አለቃ ሀይለ ሚካኤል ልብሱን በሚገባ ለብሶ፣ ፀጉሩን አበጣጥሮ ጫማውን ያስወለውላል:: እንደዚህ ሆኖ ሳየው ደስ አለኝ:: ዘወር ብሎ እየኝና:_

"ሙቶ አለቃ ጎርፉ፣ እፈልግሃለሁ" አለኝ::

"እሺ" አልኩት:: ገብቶኛል:: የሲጋራ መግዣ ሊጠይቀኝ ነው:: ጫማውን አስወልውሎ እንደ ጨረሰ ካጠገቤ መጥቶ ቆመ::

"ለምንድን ነበር የፈለከኝ?" አልኩት::

"ልሰናበትህ ነው" ሲለኝ ደንገጥ አልኩና:-

"የት ትሄድ?" አልኩት ትክ ብዬ እያየሁት:: የተሟላ አለባበስ ይልበስ እንጅ ፊቱ የበረገገ ነው::

"መሄዴ ነው:: ዳግመኛ አንገናኝም:: እስካሁን ድረስ ላደረክልኝ የሞራል ድጋፍ ከልብ አመሰግንሃለሁ:: ከኛ ክፍል የሚተኙት መኮንኖች አይወዱኝም:: በጠላት አይን ነው የሚያዩኝ:: በግማሽ ትግሬ በመሆኔ የኢህአዲግ መረጃ ነው ብለው ይጠረጥሩኛል:: ማን እውነተኛ እንደሆነ ግን ወደፊት ያዩታል:: አንተ ግን ከዚህ ጭንቅ ይገላግልህ" አለኝ::

"ለተራ አሉቧልታው ቦታ አትስጠው:: ይልቅ ልትጠፋ አስበህ ከሆነ ሊይዙህ ይችላሉ" ስለው:-

"አይዙኝም:: ካሁን በኋላ ስጋዬን እንጅ ነፍሴን አያገኟትም::" እነጋገሩ ሁሉ ጠጠረብኝ::

"ከኢትዮጵያ ውጭ ለመውጣት አስበህ ከሆነ ባሁኑ ሰአት የሚቻል አይመስለኝም:: ያልጠበከው እንቅፋት ይገጥምሃል:: እባክህን ይህን አይነቱን አሳብ ሰርዘው::"

"አልሰርዘውም መቶ አለቃ ጎርፉ:: ልጆቼ በርሃብ እየተሰቃዩ ማየት አልቻልኩም" አለና እንደ እንባ ተናነቀው:: እኔም ጭንቅ አለኝ:: የምሰጠው መልስ አጣሁ:: በቅፅበት በመካከላችን ፀጥታ ሰፈነ:: ሁለታችንም መሬት መሬት እናይ ነበር::

"በል ቻው" አለኝ ካቀረቀረበት ቀና ብሎ:: እጅ ለጅ አልተጨባበጥንም:: ጠቋሚ የማሲዘው ይመስል ቁልቁል ተጣድፎ ወረደ:: ፍዝዝ ብዬ እንደ ቆምኩ ቀረሁ:: ብዙ ተክዤ ቆየሁ:: ከሀሳቤ የነቃሁት በርካታ መኮንኖች በድምፅ ማጉሊያ "ቤተሰብ ይፈልጋችኋል" ተብለው ሲጠሩ ነበር:: ወደ ዳገቱ ሄጄ ተቀመጥኩ:: መቶ አለቃ ሀይለሚካኤልን "ይቅናው፤ያሰበው ይሳካለት" አልኩና ትኩረቴን ወደ ፅጌ አደረኩ::

ዛሬ እንዴት ተውባ ትመጣ ይሆን? ባይኑ ህሊናየ ሽቅርቅር ብላ ልክ እንደ ዕጌረዳ አበባ ፈንድታ ታየችኝ:: ትምጣ እንጅ ከንፈሮቿን ግምጥ ነው የማደርጋቸው:: ጥርሶቿን ግን ምን አደርጋቸዋለሁ? አይሳሙ ነገር:: በመጀመሪያ ያየኋት ጊዜኮ ጥርሶቿ ናቸው አቅሌን ያሳጡኝ:: ውሸት ምን ያደርጋል፤ የደም ገንቦ ነች እንጂ በመልክ ከየኔነሽ አትደርስም:: በፍቅር ግን ማንኛቸው ይበልጣሉ? ለመለየት ተቸገርኩ:: አየ የሚቻል ቢሆን ከሁለቱ መሀል ተኝቼ አንድ ጊዜ ወደ ፅጌ ሌላ ጊዜ ወደ የኔነሽ እየዞርኩ ማጣጣም ነበር:: ለምንድን ነው ግን የኔነሽን ካንጀቴ ላወጣት ያልቻልኩት? አንድጊዜ እራቁታችንን አሳብዳኝ ነበር:: ምናልባት በዚህ ምክንያት ይሆን? ከዚያ በፊት ግን እንኳን እራቁቴንና ከብርድ ልብስም ውስጥ ሆኘ መብራት ካልጠፋ በስተቀር አልሞከርም ነበር:: በጣም አፋራም ነኝ:: አጅሬት ግን መብራቱን ሳታጠፋ እራቁቴን አድርጋ ስታንከባልለኝ አደረች:: ከዚያን በኋላ «ሞኝ ያሲያዙትን አይለቅም» እንዲሉ እራቁታችንን ካልሆነ በስተቀር አይጥመኝም:: ሁልጊዜም የሚታየኝ ታዲያ ከኔ ጋር እንደምትቀብጠው ሁሉ ከሌሎቹም ወንዶች እንዲሁ እንደምትቀብጥ ነው:: በሷ የምቀናውም ለዚህ ነው:: ከሌሎች ሴቶች ጋር ብተኛም ላመል መክለያ

ያህል ካልሆነ በስተቀር የሚጥመኝ ነገር የለም:: ገና ባለፈው ፅጌን አገኘሁ:: እሷም እልጋ ላይ እብድ ነች::

"መቶ አለቃ ጎርፉ እንደሻው፤ ከድምፅ ማጉሊያው ድረስ ዘመድ ይፈልግሃታል" ተባልኩ:: ከተቀመጥኩበት ፈጥኜ በመነሳት ተንደርድሬ ወረድኩ:: ወዲያው አይኖቼ ፅጌን ፈቀዳ ገቡ:: አየኋት:: ካጠገቧ አራት ያህል ሴቶች ቁመዋል:: የሁሉም አስተያየት በመገረም ነው:: የኛ ሁኔታ ሳያስገርማቸው አልቀረም:: ካጠገቧ እስከምደርስ ድረስ አላየችኝም ነበር:: አይኖቿ እርቀው ነው የሚያዩት ፤ እኔኑ ፍለጋ:: ኮት መሰል ቡላ ሹራብ ለብሳለች:: ሻርፕ ነገር ደግሞ ከትከሻዋ ላይ ደርባለች:: ለጭቃው ብላ ቡና አይነት የቆዳ ቦት ጫማ አጥልቃለች:: ከግራ ስር ነጣ ባለ ቆዳ የተለጎመ አገልግል ጉብ ብሏል::

"ፅጌ" አልኳት፤ ዘወር ስትል አየችኝ::

"ውይ! ወዲያኮ ነበር የማየው!" አለችና በደስታ ድንጋጤ አንገቴን አቀፈችኝ:: ከንፈሮቿን አገኘኋቸው:: ልክ ማር የተቀቡ ያህል ጣፈጡኝ::

"እንቿስ ቶሎ ቀናሽ" አሏት አብረዋት የነበሩት ሴቶች::

"አይዟችሁ፤ የናንተም ይመጡላችኋል" አልኳቸውና አገልግሉን ተሸክሜ መንገድ መራኋት...

"እንደዚህ ብዙ ናችሁ እንዴ?" አለችኝ ተገርማ::

"እየውልሽ እንደዚህ ብዙ ነን" አልኳትና መኝታ ክፍል ይዣት ገባሁ:: ጓደኞቼ ብድግ ብለው በክብር ተቀበሏት:: ከመኝታየ ላይ አስቀመጥኳት:: የእንግድነት ፍርሃት ይታይባታል:: እየተገላመጠች ክፍሉን ቃኘች::

"እይውልሽ እንደዚህ ተቆላልፈን ነው የምንተኛው::"

"ምንም አይደል" አለች ከንፈሯን መጣ:: ምንጊዜም ቢሆን ቤተሰብ ሲመጣ ያረፍንበትን ካሳየን በኋላ ወደ መናፈሻ ይዘን ነው የምንወጣው:: ምግብም ሆነ ጨዋታ ከዚያው በየዛፉ ስር ነው::

"ተነሽ" አልኳት እኔ ቀድሜ በመነሳት::

"የት ልንሄድ ነው?" አለችኝ እየተነሳች::

"ውጭ መናፈሻ አለ፤ ከዚያ ነው" አልኳትና እሷን አስቀድሜ ወጣን:: እኔ አዱኛ አገልግሉን ይዘው ቀድመውን ሄደዋል::

"አትምጭ ስልሽ በጭቃ ደከምሽ::"

"እንኳንም መጣሁ፤ ደስ ነው ያለኝ::"

"የመኪና ችግር አልገጠመሽም?"

"የመኪናውን ችግር አታንሳው:: አውቶቢስማ ስቃይ ነው::"

"ታዲያ በምን መጣሽ?"

'አስራ ሁለት ብር ከፍየ በታክሲ መጣሁ" ስትለኝ እራሴን ነቅንቄ ዝም አልኩኝ::

"ምነው? በመምጣቴ ቅር አለህ እንዴ?"

"ለምን ቅር ይለኛል፤ በዚህ ጭቃ በመድከምሽ አሳዘንሽኝ እንጅ::"

"ለኔ መድከምስ አታስብ::"

እነ በድሉ ከትልቁ ዛፍ ስር ሄደው ተቀመጡ። ጥሩ አድርገዋል። ለድጋፍም፣ ለጥላውም ትልቅ ዛፍ ጥሩ ነው። ቁጥቋጦ ምንጊዜም ቁጥቋጦ ነው…

ዙሪያውን ከበን ከተቀመጥን በኋላ አገልግሉን ከፈትነው። የዶሮ ወጥ ከንቁላል ጋር፣ በመልክም ነጭ ጤፍ እንጀራ እፍን አድርጋ ነው ያመጣችው። አልተረፈችም። ያችኑ የሰጠኋትን አምሳ ብር ለዚሁ ተግባር ነው ያዋለቻት። ገለጥለጥ አደረገችልን። እሷ ለመቁረስ ፈራ ተባ ስትል እኛ ሽሚያ ገጠምን። አበላላችን ይኸው ነን። ለማያውቀን ሰው እናስፈራለን። ይሉኝታ የሚባል ነገር አናውቅም። አየ ሙያ! ቁንጅና ብቻ አይደለችም። የኔነሽ በዚህ በኩል እጇን ትሰጣለች። አንድም ቀን የሰራችውን ቀምሼላት አላውቅም። ሳያትም ድስት ጥዳ ወጥ ሰርታ የምታውቅ አትመስለኝም። አዲስ የሚከፈቱ ክትፎ ቤቶች ግን አያመልጧትም። ደግሞ ወንድ አስከትላ ነው የምትሄደው። እኔንም አንድ ሰሞን ይዛኝ ትዞር ነበር። ዛሬስ ደስ አይበላት፣ ዕጌ አለችልኝ።

"ብይ እንጂ፣ ምን ዳርዳር ትያለሽ" ብዬ አንድ እንቁላል በፍትፍት ጠቅልዩ አጎረስኳት።

"ለራስህ ብላ፣ እኔ በጄ እበላለሁኝ" አለችኝ። እነ አጅሬ እብድ የወረወረው ድንጋይ እያስመሰሉ ከጎረሱ በኋላ አጥንቱና እንቁላሉ ሲያልቅ ፍትፍቱን እንዳለ ትተውት ተነሱ።

"ብሉ እንጂ ተዋችሁትሳ" አለች።

"ዘምበይ፣ እነሱ ሳይጠግቡ አይተውም" አልኳት። ከኛ የተረፈውን ያካባቢው ልጆች አሰፍስፈው ይጠባበቁ ስለነበረ ለነሱ ሰጠናቸው። ተረባረቡበት።

"እረ አገልግሌን!" አለች ስቃ፣ ሽሚያ ሲገጥሙ አገልግሉን ወዲያና ወዲህ ሲመነጫጭቁት ጊዜ።

"ልጆች፣ እንዴ! እረ ቀስ በሉ!" ብዬ ተቆጣኋቸው።

እነ በድሉ እጃቸውን አባብሰው፣ መሬርቀው ጥለውን ሄዱ። ምንጊዜም ቢሆን ሚስትም ትምጣ ወዳጅ ምግብ የጋራ ነው፣ ጨዋታ ግን የግል ነው። ልጆቹም አገልግሉን አጋብተውልን ሄዱ።

"መቼ ነው የምትለቀቁት?" ስትል ጠየቀችኝ።

"ቢደንቅሽ ገና ወደ ጦላይ ሊወስዱን ነው" ስላት ደንገጥ ብላ፦

"ጦላይ ደግሞ የት ነው።"

"በጅማ መስመር ነው።"

"ከዚያ ወስደው ደግሞ ምን ሊያደርጓችሁ ነው?"

"ትምህርት ትማራላችሁ ይሉናል" አልኳት ፈገግ ብዬ።

"ትምህርት ጨርሳችሁ መስሎኝ ስራ የተቀጠራችሁት?"

"ነበር፣ ነገር ግን ደርግ ስላደነቆራችሁ እኛ እንደገና እናድሳችሁ ነው የሚሉን።" አልኳት አሁንም ፈገግ ብዬ። እንገቷን ደፋ አድርጋ ዝም አለች።

ዕጌ ትንሽ ዝም ብላ ቆይታ "ለመሆኑ እጮኛህ መጥታ ጠየቀችህ?" ስትል ጠየቀችኝ። ጥርሶቿ ብልጭ ሲሉ ህይወት ይዘራሉ።

"አልመጣችም።"

"እስቲ ሙች በለኝ።"

"ቅሌታም ነች" አለቻት።

እስከ ስምንት ሰአት ድረስ ከተጫወትን በኋላ መኪና ላሳፍራት ወደ ከተማ አብረን ወጣን። አውቶቢስ ተራው ወደ አዲስ አበባ አቅጣጫ ትንሽ ወጣ ይላል። ስንደርስ መኪና የለም። ተሳፋሪው ግን በሁለት መስመር ተሰልፍዋል። ከኋላ ሄደን ቆምን።

"ወይ ዛሬ! መኪና ቢገኝም ወረፋ አይደርሰኝም" አለች እንደ መጨነቅ ብላ። እስከ ዘጠኝ ሰአት ድረስ ተገትረን አንዲት መለስተኛ አውቶቢስ ብቻ መጣች። ወዲያው የቻለችውን ያህል ጭና ተፈተለከች። አስር መኪናም ቢመጣ ሰልፈኛውን ጨርሶ የሚያነሳው አይመስልም። ከኋላ እየመጣ ይጨመራል።

"ዕጌ፣ ይኸ ነገር ነገም የሚደርስሽ አይመስለኝም። ስለዚህ ወደ ከተማ እንመለስና ሌላ መኪና ብንፈልግ ይሻላል" አልኳት።

"ይሻላል፣ እንደ ባቱ ታክሲም ቢሆን ካገኘሁ ጨምሬ እሳፈራለሁ" አለችና ተመለስን። መሀል ከተማም ቢሆን መኪና የሚባል ነገር የለም። እቃ የጫነ መኪና ጋቢናው ባዶ የሆነ ባየን ቁጥር ሁለታችንም እንገታችንን እናስጋለን። ሹፌሮቹ ግን ጭቃ እረጭተውብን ይሄዳሉ። ሰአቱም አስር ሰአት ሆነ። ዝናቡ ደግሞ ማንጠባጠብ ያዘ። ሰዉ እየተሯሯጠ ከመንገድ በላይ ካለው ሆቴል ገባ። እኛም አብረን ገባን። ዝናቡ የምሩን ለቀቀው።

"አንተን ጨምሬ አስቸገርኩህ" አለችኝ ከተቀመጥን በኋላ፣ ልቧ ተንጠልጥላለች።

"አንቺ እኔን ብለሽ ተቸገርሽ እንጂ እኔን ምን ብለሽ ታስቸግሪኛለሽ! መቼም ካሁን በኋላ ሄደሽ ለስራ አትደርሽ። ለነገው እንደሆነ አድረሽም ቢሆን ትደርሻለሽ" አልኳት።

"ማደር ይቻላል እንዴ?"

"ለምን አይቻልም? ሆቴል ሞልቷል።"

"ማለቴ አንተ ውጭ ማደር ትችላለህ?"

"ለምን አልችልም? እችላለሁ።"

"እኔማ እንግዲያው ለዛሬ ፈቃድ ወስጃለሁ።"

"ለነገስ እንግዲያው ተለምነሽ ነው።"

"በል እሺ" ስትለኝ ልቤ በደስታ ዳንኪራ መታች። እሷን አስቀምጨ በጀርባ በር ፈጥኘ በመግባት አልጋ ተከራይቼ ተመለስኩ።

"አገኘህ?" አለችኝ።

"አዎን" አልኳት። ለምንድን ነው ግን አይኖቻችን የተሰራረቁት? እስካሁን ድረስ ለማደር ስላላሰብን ነው መሰል የፍቅር ስሜት አልተቀሰቀሰብንም ነበር። ማን እስከ መሻታ ሰአት ይጠብቃል።

"ተነሽ ከመሻታ ክፍላችን እንሂድ፣ ከዚህ ጫጫታ ነው" አልኳትና ተያይዘን ገባን። ወዲያው በሩን ዘጋነው። ከዚያ ካልጋው ጫፍ ተቀመጥንና በዝምታ ተያየን። እንደ መቅለስለስ ስትል እቅፍ አድርጌ ሳም አደረኳት።

"ቆይ ጫማየን ላውልቀው" አለችኝ የልቧ ምት ናር ናር እያለ። ለቀኳትና እኔም ጫማየን አወለኩት። ከዚያማ ምን ተይዞ! እንደ

ተጠማጠምን ገነት ገባነው... ስስማትኮ ነው የበለጠ የምረካው:: ከከንፈሮቿ ላይ የማር ጠብታ አለ::

አምሮታችንን ከልተን ስንወጣ ዝናቡም አባርቷል:: ከሆቴሉ ስንገባ እምብዛም ሰው የለ:: ቢራ ብንጠይቅ የለም ተባልን:: ለብርድም ቢሆነን ብለን መሎቲ ኮኛክ አዘዝን::

"እራትስ ምን እንዘዝ" አልኳት::

"እኔ ምንም ነገር አልቀምስም:: ቀን የበላሁትም ጎደል አላለ::"

"ባይሆን ለሁለት አንድ ጥብስ ይምጣልን" አልኩና አዘዝኩ:: ጥብሱ መጣልን:: ደግሞ የበግ ነው:: ያውም ለጋ ጥብስ:: እሱስ ፅጌም ቀንበጥ ነች:: ምን ይሆናል ታዲያ! ቡና ቤት ገብታ እንደ ሸንኮራ አገዳ ልትመጠጥ ነው:: ከንፈሮቿን ማንም አልፎ ሀጅ ሊስማቸው ነው:: በራሴ አስቤ በቅናት ተቃጠልኩ::

"ጉረሽ እስቲ፤ ኧረ ግሩም ጥብስ ነው::"

"አንተ ጉረስ፣ እኔ ጠግቤያለሁ" አለች አንዳንድ ፍሬ ስጋ በማንሳት፤ እኔም ብሆን አጎራረሴ የጥጋብ ነበር:: ነካክተን ተውነው:: ከመጠጡ ይልቅ ደጋግመናል:: ሞቅ ብሎን ነበር ወደ መኝታ ክፍላችን የገባነው::

በጥሩ ሁኔታ ጠላይ ተሸኘኋት:: ጥሩ የፍቅር ስንቅ... ጧት አሳፍሬአት እየተጣደፍኩ ካምፕ ስደርስ አዱኛና በድሉ ከኮሎኔል ዘርጋው ጋር ቆመው ያወራሉ:: ውጭ በማደሬ እንደ ማፈር ብዬ አይቼ እንዳላየኋቸው ሁኘ ወደ መኝታ ክፍል ልገባ ስል:-

"ና ወዲዚህ ጎርፉ" አሉኝ ኮሎኔል:: መለስ አልኩና:-

"እንደምን አደራችሁ ጌታዬ" ብዬ እጆቻቸውን ተራ በተራ ጨበጥኳቸው:: እንዳች ድንጋጤ ወሯቸዋል:: ፈገግታ የሚባል ነገር ከፊታቸው ላይ የለም:: እርግጠኛ ነኝ:: የጠላዩ ጉዞ ይህን ያህል ቅስማቸውን አይሰብረውም:: ሌላ የሆኑት ነገር አለ::

"ደህና አድረሃል፤ የት ጠፍተህ አድረህ ነው?" አሉኝ፣ ኮለኔል ሀዘን በተሞላበት አስተያየት እያዩኝ::

"አንዲት ልጅ ትናንት መጥታብኝ እሷን ለማሳፈር ሄጄ መኪና ሲጠፋ ጊዜ ከተማ አድረን፤ አሁን አሳፍሬያት መምጣቴ ነው::"

"ወይ አገጣጣሚ! አይገርማችሁም?" አሉ ወደነ በድሉ ዞረው::

"እየለፈለፍን ነው ጌታዬ፤ አልሰማን ብሎ ነው" አለ በድሉ ዝግ ባለ አነጋገር::

"ትናንት ጧት ያ መቶ አለቃ ሀይለሚካኤል ምንድን ነበር ይልህ የነበረው?" ሲል አዱኛ ጠየቀኝ::

"የት ለመሄድ እንዳሰበ አልነገረኝም እንጅ 'መሄዴ ነው ከንግዲህ አንገናኝም' ብሎኛል:: እንደ ተረዳሁት ከሆነ መጥፋቱ መሰለኝ::"

"መቼም ከኛ የምትደብቀው ምስጢር አይኖርም ጎርፉ:: የነገረህ ነገር ካለ ንገረንና እንመካከርበት:: መኮንኑ ትናንት ካንተ እንደተለየ ከዚህ ታች ራሱን በገመድ ሰቅሎ ተገኝቷል" ሲሉኝ:-

"ኧረ!!" አልኩ በድንጋጤ ደርቄ:: በሁለት እጆቼ እራሴን ያዝኩኝ::

"እና የሆነ ወረቀት ፅፎ ከኪሱ ውስጥ ተገኝቷል አሉ:: ያንተንም ስም ጠቅሷል አሉ:: ለምን እንደፃፈህ የታወቀ ነገር የለም:: ኢህአዲጎቹ ከትናንት ጀምረው ይፈልጉሃል" ሲሉኝ ድንጋጤ ወረረኝ::

"ለምንድን ነው የሚፈልጉኝ? እኔን ሰቀለው ብለው ነው?" አልኩ:: ከሰውየው ሞት ድንጋጤ ወደ ራሴ ጭንቀት ከመቅፅበት ተሸጋገርኩ::

"ለምን እንደፈለጉህ የታወቀ ነገር የለም:: ደግሞ ያጋጣሚው ነገር እንጅ:: እሱ እራሱን ሲገድል ያንተ ውጭ ማደር" አሉ በመጨነቅ::

"መክረነዋል ጌታዬ! በገዛጁ ነው መዘዝ ያመጣው፤ አሁንም ጊዜ ሳያጠፋ ቢጠፋ ይሻላል! መቼም ያላንዳች ምክንያት የሱን ስም አልጠቀሰው:: አንድ ነገር መኖር አለበት:: እነሱ ደግሞ ከያዙ አይለቁም:: እውነቱ እስከሚረጋገጥ ድረስ ለምን ይሰቃያል" ሲል አዱኛ የራሱን ሀሳብ ሰነዘረ::

"መጥፋቱ እንኳን ጥሩ አይሆንም:: አድራጊ መምሰል ነው::" ሲሉ ኮለኔል ሀሳቡን ተቃወሙ:: በዚህ ውይይት ላይ እንዳለን:-

"መቶ አለቃ ጎርፉ እንደሻው፤ የምድር ጦር ማስተናገጃ ባልደረባ የነበሩ፣ ከኢህአዲግ ፅፈት ቤት ቢሮ ቁጥር 3 ድረስ በመምጣት ሪፖርት እንዲያደርጉ" በድምፅ ማጉሊያ ነበር የተጠራሁት:: እራታችንም በሀይል ተነፈስን:: ፊቴ ኮስተር ይበል እንጅ ድንጋጤ ወሮኛል:: ከምጠላው ነገር ቢኖር በገዳይነት መወንጀል ነው::

"አይዞህ አትደንግጥ፤ ሀቁን ንገራቸው" አሉኝ ኮለኔል:: ፈንጠር ፈንጠር እያልኩ ስራመድ እነሱ ቀስ ብለው ከኋላዬ ተከተሉኝ::

የኢህአዲግ ፅ/ቤት እሩቅ አይደለም:: ከዚያው ከግቢያችን ውስጥ ነው:: ደቂቃ አልፈጀብኝም:: ቢሮ ቁጥር ሶስትን በሩን አንኳኩቼ ስገባ ፀጉሩን ያንጨፈረረ፣ ፊቱ ገጠጥ ያለ ወጣት ኢህአዲግ ቁጭ ብሏል:: የሚፅፈውም፣ የሚያነበውም ፋይል ነገር ከፊቱ የለም:: የፈጥኝ አስረው ያስቀመጡት ይመስላል::

"ምን ነበር" አለኝ ኮስተር ብሎ::

"መቶ አለቃ ጎርፉ እንደሻው እባላለሁ:: አሁን ተጠርቼ ነው" አልኩት እኔም ኮስተር ብዬ::

"ምን አሁን ብቻ፤ ኧረ ከትናንት ጀምረን ነው የምንፈልግዎት:: እስቲ ይቀመጡ" በማለት ከፊት ለፊቱ እንድቀመጥ ወንበር አሳየኝ:: ፈጠን ብዬ ተቀመጥኩ:: ከዚያም ከጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ አንዲት የተጣጠፈች ወረቀት አወጣና:-

"እስቲ ይችን ወረቀት ያንብቧት" አለና ሰጠኝ:: ተቀብዬ ገለጥ በማድረግ ማንበብ ጀመርኩኝ:: ሲጋራ አቀጣጠለና እያጨሰ አሙልቆ ያየኝ ነበር::

"የወታደር ልጅ ነኝ:: አባቴ እድሜውን ሙሉ ሲንከራተት ኖሮ ጡረታ ወጥቶ እንኳን ማረፊያ አጥቶ በዳግም ዘማችነት ዘምቶ የኤርትራ መሬት በልቶት ቀርቷል:: እኔም በግሩ ተተክቼ ያቅሜን ያህል እናት አገሬን አገልግያለሁ:: በውትድርና አለም 23 አመት አገልግያለሁ::

"ያምስት ልጆች አባትና ባለ ትዳር ነኝ:: በምስራቅ፣ በሰሜን ከመንከራተት በስተቀር ያካበትኩት ሀብት የለም:: ዛሬ ታዲያ ልጆቼን

ምን ላብላቸው? ፈፅሞ የሚቀምሱት ነገር የለም። እርሃብ ጊዜ አይሰጥም። በርሃብ ማለቃቸው ነው። ቁሜ እየሄድኩ ደግሞ ልጆቼ በርሃብ ሲያልቁ ማየት ልሸከመው የማልችለው ስቃይ ነው። ይህን በማስብበት ወቅት ሁሉም ነገር ከቁጥጥሬ ውጭ ሆነ። የነበረኝ ተስፋ ሁሉ ተሟጠጠ። ስለዚህ እራሴን ከመግደል ሌላ አማራጭ አላገኘሁም። መገላገል ነው ከማንኛውም ነገር...

"ውድ ልጆቼ! እራሴን የሰዋሁት ለናንተ ፍቅር ስል እንጅ ጠልቻችሁ እናንተን ለመገላገል ስል አይደለም። ቁሜ ካልጠቀምኳችሁ እኔ ሙቼ 'የሙት ልጆች' ተብላችሁ ብትረዱ ይሻላችኋል። የናንተ ባላደራም የኢትዮጵያ ህዝብ ነው..." በጉያው ሸጉጠ፣ የጎረሰውን እጉርሶ ያሳደጋችሁ።

"ውድ ባለቤቴ! መሪር ሀዘን እንዳይገባሽ። በተቻለሽ አቅም ልጆችሽን ለማሳደግ ሞክሪ። እኔ ተዋርዶ መኖርን ሀሊናየ ሊቀበልልኝ አልቻለም። ጥርጣሬ እንዳይገባሽ። እራሴን በራሴ ነው የገደልኩት። ለማንኛውም ነፍሴ ይቅርታ ትጠይቅሻለች፣ ይቅርታ አድርጊላት...

"ውድ ወዳጄ፣ የጥቂት ቀን ጓደኛዬና አፅናኜ ሙቶ አለቃ ጎርፉ፣ አንተንም ከፍተኛ ይቅርታ እጠይቅሀለሁ። የምጠፋ መስሎህ ሀሳቤን ለማስለወጥ ጥረት አድርገህ ነበር። ለመሆኑ የምጠፋው አልሰረቅኩ፣ አልገደልኩ፣ አልቀጠፍኩ፣ ለምንድን ነው? ያለ ስራየ የኢህአዲግ መረጃ ነው ስለተባልኩ? እስቲ ያለ ስሜ ስም የሰጡኝን ይስፋቸው። እኔስ ለጭራሹ ተገላግያለሁ። ብዙ ለመፃፍ ያሰብኩት ነገር ነበር፣ ግን ጠፋብኝ። አእምሮየን ጭንቅ ጭንቅ አለኝ። ለማንኛውም በኔ መሞት አትፀፀት። ለኔ እፎይታ ነው። አንተም ቢሆን ተዋርዶ መኖርን በፀጋ አትቀበል። ሆዳም ሰው ብቻ ነው በሆዱ እየተገዛ ውርደትን ክብሩ አድርጎ የሚኖረው። በል ለጭራሹ ቻው፣ ሀይለሚካኤል ግዛው።"

እንብቤ ስጨርስ ቀና ብዬ በረጅሙ ተነፈስኩና "የሚያሳዝን አሟሟት ነው" አልኩኝ።

"ለመሆኑ ከስዎ ጋር ግንኙነታችሁ እስከምን ድረስ ነበር?" አለኝ ሲጋራውን እያቦነነ።

"ያው አብረን ባንድ ክፍል ውስጥ በመተኛት ነው። የተዋወቅነውም ከዚሁ ነው።"

"ለህይወታቸው መጥፋት ምክንያት የሆነው የኢህአዲግ መረጃ ናቸው ተብለው መጠርጠራቸው ይመስልዎታል?"

"በዚህ እንኳን እራሱን የሚያጠፋ አይመስለኝም። በርግጥ በነገሩ በጣም አዝናበታል። እንደ ገባኝ ከሆነ ግን ለመሞቱ ምክንያት የሆኑት ልጆቹ ናቸው። ጧት ማታ 'ልጆቼ የሚቀምሱት የለም' እያለ ያዝን ነበር።"

"ከዚህ ውጭ የሚያውቁት ነገር የለም?"

"በጭራሽ አላውቅም"

"እሽ፣ ስፈልግዎት ይመጣሉ" ብሎ አሰናበተኝ። ከቢሮ ስወጣ እነኮለኔል በትካዜ ሲጠብቁኝ አገኘኋቸው።

"ምን አሉህ?" ሲሉ ኮለኔል ቀድመው ጠየቁኝ።

"የኔን ስም ከፃፈው ወረቀት ላይ ጠቅሶ ስለነበረ የማውቀው ነገር እንዳለ ብለው ነው።"

"ለመሆኑ ምን ብሎ ነው ያንተን ስም የጠቀሰው?"

"የምጠፋ መስሎህ ሀሳቤን ለማስለወጥ ሞክረህ ነበር። እራሴን በመግደሌ እንዳይፀፀትህ። 'ይቅርታ አድርግልኝ' ነው የሚለው።"

"በመጨረሻ ታዲያ በምን ተለያያችሁ?"

"ስንፈልግህ ትመጣለህ" አሉኝ።

"ጣጣው ገናነው አትለኝም ታዲያ!"

"ሟቹ ያሳዝናል እንጅ እነሱስ ዳግመኛም አይጠይቁኝ። ይህን ያህልም ትኩረት አልሰጡት። የሚጠይቀኝን እንኳን በማስታወሻ ለመያዝ አልሞከረም።"

"ትኩረትማ ምኑን ትኩረት ይሰጡታል። ጥይት ከማባከን እራሳችንን በገመድ እየሸመቀቅን ከተገላገልናቸው ጥሩ ነው እንጅ" አሉ ተቆጭተው።

"ሰምተዋል ጌታዬ! ሁለተኛ ክፍለ ጦርም አንድ ሻለቃ ማላታይን ጠጥቶ ሙቷል" አለ አዱኛ።

"ሰምቻለሁ። አንድ ሻምበልም ሸጉጥ ጠጥቶ ሞቷል። ምን አደከማችሁ! በዚህ ሳምንት ብቻ አምስት መኮንኖች መሞታቸው ነው። ጠላይ ስንሄድ ደግሞ ወባ ይጨርሰናል" አሉ ኮለኔል በብርቱ አዝነው።

የጠላይ ጉዞ ደግሞ ተሰነቀረብን።

19

ገነት ገብተን ነበር ለሶስት ቀን እድሳት፣
ጠላይ ተመረጠ ታርቆ ለመውጣት።

ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ጀምረው ወደ ጦር ትምህርት ቤቱ ሲገቡ የዋሉት አውቶቢሶች ግቢውን ሞልተውታል። ከሌሊቱ አስር ሰአት ጀምረው ነበር አንደኛ ክፍለ ጦርን ማጓጓዝ የጀመሩት። ለጊዜው «ጉዞው የማይመለከታችሁ ወዲህ ወዲያ እንዳትንቀሳቀሱ» ስለተባልን በየበራችን ላይ ቁመን እንመለከት ነበር። ብርዱም አጥንት ይቆረጥማል። የመኪናው ጩኸት፣ የመኮንኖቹ ጫጫታ ምስቅልቅል ያለ ትርኢት ነበር። ልክ ከንጋቱ አንድ ሰአት ሲሆን የመጨረሻው አውቶቢስ ከግቢው ለቀቀ።

ከጉዞ የተረፍነው መኮንኖች በሀሳብ ክልውስውስ አልን። ኮለኔል ዘርጋው ቀድመውን ሄደዋል። እኛ ሶስታችን ግን ገና ተራችንን እንጠብቃለን። ስለጠላይ የሚወራው ወሬ መቼም አስጨንቆኛል። እንዲያው የበሽታ አይነት ሁሉ መጠራቀሚያ ነው አሉ። እኔ ጠላይን አላውቀውም፤ ቢጨንቀኝ፡-

ኦጋዴን ወርጄ በጥይት ሳልሞት፤
እንዴት ጦላይ ሄጄ በትንኝ ልሙት አልኩኝ::

በዚሁ እለት አራት ሰአት ተኩል ሲሆን ከጉዞ የቀረነው እንድንሰበሰብ ተደረገና የሆለታ ከተማ የጤና ባለሙያዎች ናቸው ተብለው ባንድ ዶክተር መሪነት መጥተው ንግግር አደረጉልን::

"... ምክርም፣ ማስጠንቀቂያም፣ ማሳሰቢያም ነው:: የጤና ጉዳይ በመሆኑ ችላ ልንለው አንችልም:: በርግጥ ከሞራል አንፃር ሲታይ ሊሰማችሁ ይችላል:: እኛ ደግሞ ከሀላፊነት አንፃር ስናየው ሌላ ምርጫ የለንም:: እንደ እውነቱ ከሆነ በናንተ አፍረናል:: ጨብጥ፣ ቂጥኝ ... የመሳሰሉትን በሽታዎች በመድሃኒት እንኳን ማዳን አልቻልንም:: የናንተ ከዚህ መምጣት እናንተ የፈጠራችሁት ችግር ባይሆንም፤ ለሆለታ ህዝብ ግን ጠንቅ ነው የሆናችሁበት:: በርግጥ ቀላሉ መንገድ ለህዝቡ ነግሮ እናንተን እንዳያስጠጋ ማድረግ ነበር..." በማለት እየተናገረ እያለ:-

"ብስብስ! አንተን ብሎ ዶክተር!" ብለነው አውክተን ጥለነው ሄድን::

"እውነት ይኸ ዶክተር ነው? በጭራሽ አይደለም! አንዱን ወያኔ ጋዋን አልብሰው አቅርበውት ነው!" አለ አዱኛ በሽቆት::

"ነገሩስ ዶክተር ነው:: መኮንኖቹ ውሽማውን ስለቀሙት በበቀል ነው የሰደበን::" አለ በድሉ::

"እናንተው ጊዜው አዘንብሎብናል" አሉ አንድ ጠና ያሉ ሻምበል:: ያም ሆነ ይህ ለቀቅንለት:: በሶስት ቀናት ውስጥ ሁለቱም ክፍለ ጦሮች ተጠናቀን ጦላይ ገባን:: ጓድ ዶክተርም ሆለታን አንድ ላንድ ይያዛት፤ ይስፋው:: ሰው ያለሰው ግን ባዶ መሆኑን የኋላ ኋላ ይገባው ይሆናል::

ምእራፍ ስምንት

በዘመነ ደርጉ ናውጌ ናውጌ፣
በኢህአዲግ ጊዜ ከጦላይ ከረምኩኝ በማእረግ ተይጌ::

20

ጦላይ የገባነው ማታ ነበር:: እንደ እድል የቀናው አልጋ አገኘ:: ያልቀናን ደግሞ ቅጠል ዘነጣጥፈን፣ ሳር በጃችን በጫጭቀን እንደ ነገሩ ጎዝጉዘን ከዚያ ላይ ተጋድመን አደርን:: ታዲያማ በማግስቱ ጧት ያልጋው ርብራብ ስለተዘረፈ ጣውላ ቢጤ ለመፈላለግ እንደ ዋዛ ወጣ ብዬ ቀረሁ:: ኧረ ጉድ ነው የሆንኩት! ያደርኩበት ክፍል ጠፍቶኝ ብወጣ ብወርድ ላገኘው አልቻልኩም:: ካንዱ ክፍል ወጥቼ ከሌላው ክፍል ስገባ ከዚያኛው ክፍል ያየሁትን እያለሁ:: ጣራው፣ ግድግዳው፣ በረንዳው አንድ አይነት ነው:: ልክ እንደ መንታ ልጆች ለመለየት ያስቸግራል::

ካንዱ ብሎክ ተነስቼ ከሌላው ስሄድም ያው ነው:: ካንዱ የሻለቃ ካምፕ ተነስቼ ወደ ሌላው ሻለቃ ካምፕ ብሄድም ካምፑ አንድ ነው:: ብርጌድ ከብርጌድም መለየት አይቻልም:: ሳር ቅጠሉ፣ ዛፉ፣ ሁሉም አንድ አይነት ነው:: እንዲሁ ስንከራተት፣ በባዶ አፌ ከዘጠኝ ሰአት ደላኩኝ:: የሚያውቁኝ መኮንኖች:-

"ምን ጠፋህ?" ሲሉኝ:-

"ምንም" እላቸዋለሁ:: ምንላድርግ? ያደርኩበት ክፍል ጠፍቶኝ ለማለት አፈርኩኝ:: እንዴት እንደ ህፃን ልጅ ያደርኩበት ክፍል ጠፋኝ እንደ ወጣሁ እቀራለሁ? ቅሌት ነው፤በኋላማ ደከመኝ:: እረማመዴ እጥፍ እጥፍ ሆነ:: አፌ ደርቋል:: ውሃ ጥምም ይዞኛል፤ እርሃብ እየበገበገኝ ነው:: ማታ የረባ አልበላንም ነበር:: ዳቦቆሎ መሳይ ነገር ቆረጣጥመን ያደርነው:: የማደርገው ባጣ ከመንገዱ ዳር ካለው ትልቅ ዛፍ ስር ሄጄ ግንዱን ደገፍ ብዬ ቆምኩ:: ምንላድርግ፤ ደከመኝ:: መኮንኖቹ ወዲያና ወዲህ በጥንድ በጥንድ ሆነው ይንጠራወጣሉ:: መንገዱ ዙሪያ ጥምጥም ነው:: ፍሬ አላገኘሁበትም እንጅ አስርጊዜ ይሆናል የዞርኩት::

ከዛፉ ስር እናቱ ገበያ እንደ ሄደችበት ህፃን ፍዝዝ ብዬ እንደ ቆምኩ ከወደ ፊት ለፊቴ ኮለኔል ዘርጋው ቸኮል ቸኮል እያሉ በመሪድ ሲመጡ አየኋቸው:: አቤት ደስታዬ! የተጫጫነኝ ነገር ሁሉ ቀለለኝ:: ፈገግ ብዬ ከዛፉ ስር ስወጣ እሳቸውም አዩኝ::

"ጎርፉ!" አሉኝ ከፊቴ ላይ ምን እንዳዩ እንጃ ለቅ እየቃጣቸው:: ተቃቅፈን ትከሻ ለትከሻ ተሳሳምን::

"እንኳን ደህና መጣችሁ ልላችሁ ብመጣ አንተ የለ፣ ... ኝ እነበድሉኮ ተጨንቀዋል:: ያደርክበት ክፍል ጠፋህ እንዴ?" በጥርጣሬ አስተያየት እያዩኝ:: ደግሞ ለመሳቅ አቆብቁበዋል::

"ለስምስ አልደብቅዎትም ጌታዬ:: ብወጣ ብገባ ያደርኩበት ክፍል አልጠፋብኝም መሰለዎት" ስላቸው በሳቅ ፈንድተው ሊሞቱ

"ገና ሳይህኮ ነው ግራ እንደ ተጋባህ የተረዳሁት" አሉ ስቆ ያወጡትን እንባ በመሀረባቸው እየጠረጉ::

"እንዲህ አይነት ቅሌት ገጥሞኝ አያውቅም:: ከኦጋዴን በለጠ አደናጋሪ መሬት የለም:: ለዚህ ግን ተወዳዳሪ የለውም:: አሁንም አዲስ አበባ በየት አቅጣጫ እንደ ሆነ አላወኩትም" ስላቸው እንደ ገና ... ርፍር እስከሚሉ ሳቁና:-

"ኧረ ባክህ በሳቅ አትግደለኝ" አሉኝ አሁንም አይናቸውን በመሃረብ እየጠረጉ:: "በል እንሂድ ላድርስህ" በማለት መንገድ ጀመርን::

"መቼስ አይጣል ነው ጌታዬ፤ እኔ ለተጎዳሁ የማዝነው ... ናዱኛ መሳቂያ መሆኔ ነው::"

"አንተኮ ብቻ አይደለህም ጎርፉ:: እኛ የመጣን እለት እንዲህ ስንቶቹ ተዋርደዋል መሰለህ:: አንድ ሻምበል ለሽንት ወጥቶ ... መመለሻው ጠፍቶት ከዚያው ሽንት ቤት ተገትሮ አድሮ ጧት ተገኝቷል:: አንድ መቶ አለቃ ደግሞ እንደ ዋዛ ወጥቶ መመለሻው ጠፍቶት ሲዳክር አምሽቶ! አሳድሩኝ እንዳይል ደግሞ ማፈር፤ እንደ ጦጣ ከዛፍ ላይ ተንጠልጥሎ አድሮ ጧት ሳይወርድ ተገኝቷል:: እስጠጉን እያሉ

በየክፍሉ የሚያድሩትማ ብዙ ናቸው:: ሰሞኑን ስንስቅ የነበረው በዚሁ ነው:: ጦላይ ለንግዳ ደራሽ አስቸጋሪ ነው:: በጥንቃቄ ልዩ ምልክት ካልያዝክ በስተቀር እንደ ሰባራ አህያ ስትዟዟር መዋልህ ነው:: ቀደም ሲል ብራዊ ወታደሮች ከዳን ይሉና ሲዳክሩ ውለው ካምፑን ሳይለቁ ይያዙ ነር" በማለት ተረኩልኝ::

እነ አዱኛ ገና ሲያዩኝ ሳቃቸውን ለቀቁት:: ኮለኔልም እነሱን ተከትው ይስቁ ጀመር::

"ምን ያስቃችኋል?" አልኩ ቆጣ ብዬ:: ማንም አላናገረኝም:: እየተባበሉ እንባ እስከሚወጣቸው ድረስ ሳቁ:: እኔ የኮዳ ውሃ እነሳሁና በባሁዴ አንደቀደኩት::

"ጌታዬ የት አገኙት?" አላቸው በድሉ ጠጋብሎ::

"እኔን ሊጠይቅ ሄዶ ኖሮ እኔን ሲያጣ ጊዜ ከዚያው ቁጭ ብሎ ነበት::"

"እስቲ ሙት ይበሉኝ" ሲላቸው:-

"ለምን ትሞታለህ?" ሲሉት እንደ ገና በሳቅ ይንፈቀፈቅ ጀመር::

ንድዷልኩኝ፤ አዱኛ ደግሞ ወደኔ ጠጋ ብሎ:-

"የኔ ጎርፍ፤ ጎርፉ በለህ" አለኝ::

"አንተን ይጠረግህ! አሁን እርቦኛል" አልኩት::

"እረ ባካችሁ በሶ መሳይ በጥብጡና ስጡት" ሲሉ ኮለኔል በድሉ ቀበሉ:-

"ምነው ጌታዬ! በባህላችን እንግዳ ክቡር ነው፤ እስዎን ሊጠይቅ ሄደዶት አላስተናገዱትም?"

"ባለቤቱ ወደ ገበያ ሄዳ ከባዶ ቤት መጥቶ ነው" ሲሉ ቀለዱ::

ወዲያ አዱኛ በሶ በጣሳ ሲበጠብጥልኝ በድሉ ደግሞ ዳቦቆሎ ዘግኖ ሰጠኝ ባቄላ ክምር እንደ ገባ መንጋ ፈየል ይህን የደረቀ ዳቦቆሎ ቁርጥም አደርግ ጀመር:: በሶውንም ሰጠኝ:: ተቀብዬ ባንድ ትንፋሽ ለጋሁ ለመም እያለ ነበር የገባው::

ልድገምህ?" አለኝ::

አዎን" አልኩት:: ሀይለኛ እርሃብ ተለቆብኛል::

ለኢህአዲግኮ ልናመለክት ነበር ጌታዬ" አለ በድሉ::

ምን ብላችሁ" አሉት::

ሬዲዮ እንዲያስፈልግልን ነዋ::"

ባካችሁ ተውት አሁን:: ከድካሙ ወዲህ የፈራው የናንተን ሽሙጥና ልድ ነው::"

ለኔል ሲጫወቱ ቆይተው ሄዱ:: እኔም ደክሞኝ ስለነበረ ተጠቅልዩ ተኛሁ:: ይልቅየ ቆንጆ አልጋ ሰርተው ጠበቁኝ:: እግዜር ይስጣቸው:

21

«ጦሩ ላይዋጋ ይሰለጥናል!»

ጦላይ በገባን ማግስት ያገኘነው አባባል ነው:: በድርግ ጊዜ ምን ያልተባለ ነገር አለ? ጦላይ ከገባን አንድ ሳምንታችንን ይዘናል:: በመጠኑም ቢሆን ተላምደነዋል:: እባቡ፣ ዘንዶው፣ ጊንጩ፣ የወባው ትንኝ እየተባለ የተወራው ሁሉ ከመጠን በላይ የተጋነነ ነው:: እስካሁን ድረስ በእባብ የተነደፈም ሆነ በዘንዶ የተዋጠ የለም:: በርግጥ ወባ እንዳለ ይነገራል:: ቢሆንም ጊዜው ክረምት ስለሆነ ይህን ያህል የሚያሰጋ አይደለም:: ጥናም ቢል ከመስከረም በኋላ ነው:: ለጊዜውም ዲዲቲ ተረጭቶልናል::

ባለፈው ጦላይ በገባን ማግስት ያደርኩበት ክፍል ስለጠፋብኝ በሽቁ ስለጦላይ ያልኩት ነገር አልነበረም:: ዛሬ ግን በሚገባ አጢኛታለሁ::

ከሆለታ ተነስተን ምእራብ አዲስ አበባን እያቆራረጥን ከጅማው መንገድ በመግባት ጉዟችንን በረጋ ሁኔታ ቀጠልን:: በመንገድ የሚያየን ህዝብ ሁሉ በሀዘን ከንፈሩን ይመጥልን ነበር::

ምሳችንን ወሊሶ በልተን ጉዞአችንን በመቀጠል ከወልቂጤ አስር ኪሎ ሜትር ያህል እንደ ተጓዝን ዋናውን ጎዳና ለቀን ወደ ቀኝ በመታጠፍ የምእራብን አቅጣጫ ያዝን:: የጠጠር መንገድ ነው:: አንድ ትልቅ ወንዝ አለ፣ ከዚያ እስከምንደርስ ድረስ የመንገዱን ዳር ተከትለው አልፈው፣ አልፈው አዳዲስ የሰፈራ መንደሮች ተቆርቁረዋል:: ከወንዙ ወዲያ ግን ግቤ እስከምንደርስ ድረስ ምንም አይነት የሰው ዘር አላየንም:: ጭልጥ ያለ በረሃ ነው:: ሆኖም ግን የክረምት ወቅት በመሆኑ በልምላሜ ተውጦ አይንን ይማርካል:: ዛፎች ቅጠል ለብሰዋል፤ መሬቱ በሳር ተሸፍኗል:: እርቃኑን የሆነ ነገር የለም:: እኛ ነን ከንግዲህ ከሰው ዘር እርቀን እርቃናችንን የቀረን ...

መንገዱ በመጠኑ ስላች እየሰራ፣ ቀናታ እየጨመረ ይሄድና ግቤ መዳረሻ ላይ ያዘቀዝቃል:: የምእራቧ ፀሀይ ፊትለፊታችን ትመታን ነበር:: ሹፌሮች የፀሀይ መከላከያ ባለቀለም መስተዋታቸውን ጋርደዋል:: ከፊትለፊታችን ከግቤ ወንዝ በርቀት አንድ ትልቅ ጋራ ተገትሮ ይታያል:: ፀሀይዋ ከዚያ ላይ ቁማ እንደ ጦር የምትወጋን ትመስላለች::

ግቤ ወንዝ ስንደርስ አፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ ጎሽቷል:: መሬቱ ረባዳ ስለሆነ እረጋ ብሎ ነው የሚጥመለመለው:: ሳር ቅጠሉን ያግበሰብሰዋል:: እኛም ተግበስብሰን ነው የመጣነው...

ወንዙን ተሻግረን እንደ ገና ወደ ምስራቅ ደቡብ ታጥፈን አንድ ሀያ ኪሎ ሜትር ያህል እንደሄድን ከታ የተባለች ትንሽ ከተማ አለች:: ከተማ ስለሚሏት ከተማ አልኳት እንጅ መንደር ናት:: ከወሎና ከደቡብ ሸዋ መጥተው የሰፈሩ ናቸው:: ወደፊት እንጃ እንጅ ዛሬስ ቋንቋ፣ ባህል፣ ሃይማኖት ሳያራርቃቸው በፍቅር ተሳስበው ነው የሚኖሩት::

ከከታ በኋላ መንገዱ ለጥ ያለ አግድመት ነው:: አስራ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል እንደ ሄድን ደግሞ ዋዩ የምትባል ከተማ እናገኛለን:: ዋዩ በመጠኑም ቢሆን የከተማነት ባህሪ አላት:: አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣

አንድ ሆቴል፣ በርካታ ትንንሽ ሱቆች፣ የሰፈር መጠጥ ቤቶች አሏት። ሳምንታዊ ትልቅ ገበያም አላት፤ ቅዳሜ ቀን ነው የሚውለው።

ከዋዩ በኋላ አንድ አግድመት ተፈትልከን ካንድ ወንዝ ውስጥ እንደርሳለን። መጠነኛ ድልድይ አለው። እሱን ከተሻገርን በኋላ የጦላይ ማሰልጠኛ ማእከል ክልል ነው። ከዋናው በር መዳረሻ በስሚንቶ የተገነባ ጠፍጣፋ ግንብ አለ። ከላዩ ላይ የብረት ቆብ የደፋ ባንድጁ ክላሽ ጠመንጃ፣ በሌላ እጁ ደግሞ ጡሩንባ ይዞ የሚነፋ ስእል ተስሎበታል። የክተት ጥሪ መሆኑ ነው። ስናስከትት ኖረን በመጨረሻ እኛው ከተትን። ፅዋ አይደል!

ጡሩንባ ነፊውን እንዳለፍን መንገዱ ለሁለት ይከፈላል። መሀል ለመሀል አትክልቶችና አበባዎች አሸብርቀውበታል። የቸርችል ጎዳናም እንደዚህ አያምር። እንግዲህ ከዚህ በኋላ ያለውን ውስጣውስጡንና የመንገዶቹን ቅያስ ከናዝሬትና ከድሬዳዋ ወይንም ከባህርዳር ጋር ማነፃፀር ነው። አበባው ተንተርክኮ ሲያዩት መንፈስን ያድሳል።

የመግቢያውን በር አስከፍተን ገባን። በስተግራ በኩል የማሰልጠኛ ማእከሉ ዋና መስሪያ ቤት ይገኛል። ባላንድ ፎቅ ሲሆን ዘመናዊ ህንፃ ነው። ካናቱ ላይ እንደ ተለመደው «ካብዮታዊ መሪያችን ከጓድ መንግስቱ ሀይለማርያም ብልህ አመራር ጋር ወደ ፊት!» የሚል በቀይ ቀለም ተፅፎ በሩቁ ይነበባል። መርተው መርተው ዝምባብዌ ደርሰዋል። እኛም እሳቸውን በመከተል ከጃን ሜዳ ተነስተን በሆለታ አድርገን ይኸው ጦላይ ደርሰናል። ካሁን በኋላስ ንቅንቅም አንላት! «ወደ ፊት!» እያልን ወደ ኋላ ተፈንግለናል። አጅሬ ግን እውነትም ብልህ! «ወደፊት!» እንዳሏት ተፈተለኩ፣ ኧረ ከሳቸው ያላነሱ ብልሆችም አሉ! ጦሩን ትጥቅ አስፈትተው ጣሊያን ኤምባሲ የተሸጎጡ። ይብላኝላቸው፣ ፓስታ ያልቅና ውጡ የተባሉ እንደሆን እንጂ ዛሬስ ታድለዋል። ቅንቡርስ ቅንቡርሱ ባለስልጣን ነው እንደኛ ተጋፎ ስንዳፋ የገባው። ይኸ እንግዲህ «በብልሁ መሪያችን» ጀርባ ታዝሎ የኖረ ነው። የራሱ ጭንቅላት የሌለው...

ከዋናው መስሪያ ቤት ትንሽ ከፍ ብለን ወደ ቀኝ ታጥፈን ትንሽ አለፍ እንዳልን የባህል ማእከል አዳራሽን እናገኛለን። ይህ አዳራሽ በጣም ዘመናዊ ነው። አዲስ አበባ ካሉት ቲያትር ቤቶች ቢበልጥ እንጂ አያንስም። ካዳራሹ አለፍ እንዳልን ያንደኛ ክፍለ ጦርን ካምፕ እናገኛለን። እንግዲህ የሰሜኑን አቅጣጫ አንደኛ ክፍለ ጦር ሲይዝ የደቡብን ደግሞ ሁለተኛ ክፍለ ጦር ይይዛል። አወቃቀራችንም በክፍለ ጦር፣ በብርጌድ፣ በሻለቃ፣ በሻምበል ነው። በዚህ መሰረትም ሁለት ክፍለ ጦሮች፣ ስድስት ብርጌዶች፣ አስራ ስምንት ሻለቆች፣ ሰባ ሁለት ሻምበሎች አሉ። እያንዳንዱ ሻለቃ የራሱ የሆነ ምግብ ቤት፣ የመሰብሰቢያ አዳራሽ አለው። መኖር የምንችለው ግን አንድ ሻምበል ጦር ባንድ ብሎክ ነው። በዚህ ድልድል መሰረት እኔና በድሉ፣ አዱኛ ሆነን የምንኖረው 1222 ነው። ይህ ማለትም አንደኛ ክፍለጦር፣ ሁለተኛ ብርጌድ፣ ሁለተኛ ሻለቃ፣ ሁለተኛ ሻምበል ማለት ነው።

በሁለተኛ ክፍለ ጦር ማዶ ያይሮፕላን ማረፊያ አለ። ከዚህ ነው እንግዲህ ባንቴኖቭ የከተተው ወጣት ሁሉ ተከቶ ወደ ተለያዩ የጦር ግንባሮች የሚወሰደው።

ባጠቃላይ ጦላይ የመንገዶቿ ቅያስ፣ የዛፎቹ አተካከል፣ ያበባዎቹ ፍካት የበረሃ ገነት አስኝቷታል። በዚህ ላይ የወፎቹ ዜማ፣ የጦጣዎቹ ሁካታ ልዩ ደስታን ይሰጣሉ። ዛፎቹ ቀንዘልና ቀንዘላቸውን አገጣጥመው የቆርቆሮውን ቤት ውጠውታል። ባይሮፕላን እንኳን ሆኖ ቁልቁል ማእከሉን ማየት አይቻልም። ሌላው ቀርቶ ካንደኛ ክፍለ ጦር ሆኖ ሁለተኛ ክፍለ ጦርን ማየት አይቻልም። ወዲያና ወዲህ ባልን ቁጥር ፀሀይ አይመታንም፤ ጥላ ለጥላ ነው መንገዳችን።

ጦላይን በርቀት ለሚመለከታት ደግሞ የበለጠ ትማርካለች። ለጥ ካለና በደን ከተሸፈነ ልምጥ ዋልካ ላይ ነው የተመሰረተችው። በስተምእራብ በኩል እንደ ሰንሰለት የተያያዙ ጋራዎች የተፈጥሮ መከታ ሆነዋታል። ከጋራዎቹ በስተጀርባ ያለውን አገር ማየት አይቻልም። ከነዚሁ ጋራዎች የሚነሱ ሁለት ወንዞች ማእከሉን አማክለው ግቤ ወንዝ ሄደው ይጨመራሉ። በወንዞቹ ውስጥ ለውስጥ ዘንዶ አለ እያሉ በፊት ከዚያ አሰልጣኝ የነበሩ መኮንኖች ያስፈራሩናል። እኔ ግን ያለ አይመስለኝም። ጦጣዎች ናቸው ሲያሽኩበት የሚውሉት። ከካምፑ ድረስ በመምጣት አሹፈውብን ይሮጣሉ።

የጦላይ አየርም ተስማምቶናል። እንደ ጊዜው አልጠመመብንም። እስካሁን የሞተም፣ የታመመም የለም። ይልቅ እዳ የገባነው ሁለት ድርጅቶች ተቋቁመው ጠቅላላ መኮንኑን ማመስ በመጀመራቸው ነው።

1ኛው. ሸብር ፈጣሪ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ሸፈዲድ)

2ኛው ሞራል ገንቢ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ሞገዲድ) ይባላሉ። ሁለቱም የተለያዩ አላማዎች አሏቸው። ሸፈዲድ መኮንኖቹና ኢህአዲጎቹ እንዳይጣጣሙ ወይንም እንዲጋጩ ይጥራል፤ አባላቶቹ ገንዘብ ቤቶች፣ ደመወዝ ከፋዮች፣ ካድሬዎች፣ የደህንነት አባላት፣ አዛዦች ናቸው ይባላል። ሞገዲድ ደግሞ የሌለ ተስፋ እየሰጠ እኛን በቁም የሚያጠወልግ ድርጅት ነው። የዚህ ድርጅት አባላት ከኛው መካከል የወጡ ጥቂት እንጀራ ፈላጊዎች ሲሆኑ ከኢህአዲጎቹም ውስጥ ቃል አቀባይ አላቸው። ሌሎች በህቡእ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችም እንዳሉ ይነገራል። ዲሞክራሲ በደንብ ስላልሰፈነ ገና ይፋ አልወጡም። መቼ ይሆን ግን ከዚህ ሁሉ ውዥንብር የምንገላገለው? እስካሁን ያሉን ነገር የለም።

22

ምንም ቢቸግረኝ አጥቼ ብነጣ፣
ሲጋራስ አልሸጥም ካገሬ ሳልወጣ፣
የትናንት መኮንን ተብየ አልጠራም፣ 'ጀብሎ ሲጋራ አምጣ!'

ጀብሎ መኮንኖች በካምፑ ውስጥ በስፋት ተንሰራፍተዋል። በየመንገዱ ዳር ለዳር የጉሊት ገበያ ጀምረዋል። ሲጋራ፣ ቃሪያ፣ ነጭ ሽንኩርት መሸጥ ይዘዋል። ኧረ ነጭ ሽንኩርትስ መድረሻ አሳጥቶናል። ከውጭ ወደ መኝታ ክፍላችን ስንገባ የሽንኩርቱ ሽታ ወደ ውጭ መልሶ

ይገፈትራል። ምግብ አዳራሽም እንዲሁ ስቃይ ነው። ባጠቃላይ ቤት ደጁ ጠንብቷል። ደግነቱ ሁሉም ስለሚበላ እንደ ነውር አልተቆጠረም። «ሸተትከኝ» የሚልም የለም። የማይወድ ቢኖርም በግዱ ፊቱን አጨፍግጎ ሁለት ፍሬዎችን መብላት አለበት። የህይወት ጉዳይ ነው። እሱ ካልተበላ ወባዋ አንድ ቀን አታሳድርም አሉ። በዚህ የተነሳ ሁሉም ነጭ ሽንኩርት ይከሰክሳል። አንዳንዱ መኮንንማ አንድ ራስ ሽንኩርት ከስክሶ የሚጨርስ አለ። እኔ ፈርዶብኝ እንኳን ልበላ ይቅርና ሲበሉ ሳይም ያንቀጠቅጠኛል። እነ በድሉ ተቆጥተውኝ ለሁለት ቀናት ያህል ሁለት ሁለት ፍሬዎችን ከሽ ከሽ አድርጌ ነበር። የገዛ አፌ ጠነባኝ። ከዚህ በኋላ «ወባዋ እንዳሻት ታድርገኝ» ብዬ ተውኩት። ካፍንጫቸው የሚወትፉትም አሉ። የሬጋ ንፍጥ መስሎ ተለጉዶ ሲያስጠላ። ያ ሁሉ ትቢተኛ ኮለኔልና ሻለቃ ህይወቱን ለማቆየት የማይቆፍረው ጉድጓድ የለም። ጉድጓድ ብል ጉድጓድ ትዝ አለኝ።

ጠላይ ከገባን ጀምሮ ዋነኛ ስራችን ጉድጓድ መቆፈር ነው። ለምን ግዙፍ ግዙፍ ጉድጓዶች እየቆፈርን እንደምናጠራቅም አልገባኝም። ጥልቀት 2 ሜትር፣ የጎን ስፋት 2ሜትር፣ ርዝመት 8ሜትር የሆኑ በርካታ ጉድጓዶች በየሻለቃው እየተቆፈሩ ነው። ዛሬስ ሰግተናል። የኋላ ኋላ ለኛው ማዳፈኛ እንዳይሆኑ እንጃ።

ሌላው ስራችን በሳምንት አንድ ቀን የምግብ ማብሰያ እንጨት መልቀም ነው። ጫካ እንሄድና የቻለ ግንድ ተሸክሞ ይመጣል። ያልቻለ ጭራሮ አንከርፍፎ ይገባል። ሻለቃ የለ ኮለኔል፤ እንደ መብሉ ስራውም እኩል ነው። ስራችን በጉድጓድ ቁፋሮና በእንጨት ለቀማ ብቻ አያበቃም። ምግባችንንም ተራ እየገባን በጥይት ሳጥን ተሸክመን ወደ መመገቢያ አዳራሾች የምናመጣው እኛው ነን። የቦታው እርቀት ደግሞ ከማድ ቤት እስከ መመገቢያ አዳራሽ ያለ እርቀት አይደለም። ከካምፑ ሶስት ኪሎ ሜትር ያህል ይርቃል። የምግብ ሸክሙም ማእረግ አይለይም።

ባለፈው እሁድ ታዲያ ባህል አዳራሽ አጠገብ አንድ ትርኢት አየን። ማእረጋቸው ሌ/ኮለኔል ነው። አብሯቸው የተሸከመው መቶ አለቃ ነው። እሱ ፊት ፊት፤ እሳቸው ከኋላ ናቸው። እንጀራውን ተሸክመው ቱስ ቱስ እያሉ በዚያ ሲያልፉ ሚስት ካዲስ አበባ ባለቸውን ሊጠይቁ መጥተው ኖሮ ድንገት ግጥምጥም። ሚትስ ሆየ ኡኡታቸውን መልቀቅ። በዚህ ጊዜ ባል ሀፍረት ይይዛቸውና የተሸከሙትን ሳጥን አምዘግዝገው መጣል። እስቲ ጓደኛቸውን እንኳን «ጣል መጣሌ ነው» ቢሉት ምነበር? ክፉኛ ነው ትከሻው የተጎዳው። ከዚያማ ባልና ሚስት እንገት ላንገት ተቃቅፈው መላቀስ። እኛ ደግሞ ድራማውን በነፃ መመልከት። ከዚያማ አንድ መኮንን ሴትየዋን አስለቀቃቸውና:-

"ይተው እንጅ! ነውር ነው! የሞቱ መሰለዎት እንዴ!" ማለት።

" ምነው ሸዋ! ሞት ከዚህ ወዲያ አለ እንዴ! ሞትስ በቁርጡ ይሻላል!" ብለው በምሬት ተናገሩ። በዚህ በዚህ ምክንያት እሮሮ ስላበዛን ነው መሰል ዛሬ እንጀራ ሸክሙ ቀርቶልናል። ባንድ ትራክተር እየተጫነ በየሻለቃው የምግብ አዳራሽ እየዞረ ይታደላል።

ሆለታ ሳለን ደመወዝ ካልተሰጠን ሰንል የነበረው ጠላይ ከሄድን በኋላ ደግሞ መውጫ ቀዳዳ ፍለጋ ሆነ። በቃ፤ የደመወዝ ነገር አከተመ።

23

በደርግም ስብሰባ፣
በኢህአዲግም ስብሰባ፣
ኧረ መቸ ይሆን ሰርተን የምንገባ?

ስብሰባ ቆይተን ገና አሁን መውጣታችን ነው። የተሰበሰብነው በየሻለቃችን ነበር። ስብሰባ አይበለው። የነጭ ሽንኩርት ሽታ የምገባበት ነበር ያሳጣኝ። አንድ ሻለቃ ጦር አንዳንድ ራስ ሽንኩርት በልቶ በዚህ ላይ ባፍንጫው ወትፎ የመጣው በርካታ ነው። የትንፋሹ ግለት፣ ከበርሃው ሙቀት ጋር ተዳምሮ የት ልድረስ ያሰኛል። መቼ ይኸ ብቻ!! መኮንኑ ከመቶ ዘጠና ዘጠኙ እጅ አጫሽ ነው። እንደ ጃርት ታፍነን ሙተነው ነበር። ጭሱ ሲግፈጠፈጥ ምጣድ የተጣደበት የገጠር ቤት ምስጋና ይንሳው። በመስኮት በኩል እንኳ ንፁህ አየር እንዳይገባ ወንበር ስለማይበቃን መስኮቱን ከበው የሚቆሙት መኮንኖች ከዛፍ ላይ የሰፈረ ንብ ይመስላሉ። አቅለሸለሸኝ። ሲያስመልሰኝ ምንም ያህል አልቀረኝም ነበር።

ኢህአዲጎቹም ስብሰባውን የሚመሩት እንደ መፋቂያ ሲጋራ ከከንፈራቸው ሰክተው ነው። ይኸው ናቸው። ሲያልቅባቸው ከዚያው ላይ መለኮስ ነው። ትንሽ ፋታ የሚያገኙት በጃቸው እንደያዙት ሲናገሩ ብቻ ነው። ደግሞኮ የኢህአዲግ አባል የሆነ ሁሉ የማያጨስ አላየሁም፣ ታዲያ የኛዎቹን መኮንኖች:-

"ለምንድን ነው አዳራሽ ውስጥ በስብሰባ ጊዜ የምታጨሱት?" ያልናቸው እንደ ሆነ:-

"ተመልከቱ ኢህአዲጎቹን፤ ደግሞ የዲሞክራሲ መብታችን ነው" ይሉናል። ኧረ ዲሞክራሲ ግራ አጋብቶናል! ከትናንት ወዲያ አንድ መቶ አለቃ እንዲሁ በምሳ ሰአት ሲጋራ አቀጣጥሎ እያጨሰ ምሳውን በላስቲክ ሳህን ተቀብሎ ከኔ ጋር አንድ ጠረጴዛ ተጋራን። ታዲያማ ሲጋራውን በግራ እጁ ያዝ አድርጎ በቀኝ እጁ እንጀራውን እየቆረሰ ሁለት ጊዜ ያህል ጎረሰና እንደ ገና ደግሞ ከሲጋራው ይምግ ጀመር።

"ጓድ መቶ አለቃ፣ ምግቡ ነው መቅደም ያለበት ሲጋራው?" አልኩት ጥርሶቼን ብልጭ አድርጌ።

"ሁለቱም የዲሞክራሲ መብቴ ነው" አለኝ። ይድነቅህ አለና ወደኔ ጢሱን አቦነነብኝ። ምን ላድርግ፣ ተናድጄ ምሳየን ሳልበላ ወጣሁኝ። ይኸ ይሆን ዲሞክራሲ ማለት?

ትናንት ማታ ደግሞ አንዱ ያስም በሽተኛ "እባካችሁ ጓዶች ሲጋራ በተወሰነ ሰአት አጭሱ። ቢቻልማ መኝታ ቤት ባታጨሱ ጥሩ ነበር" ብሎ ቢማፀን ከያቅጣጫው ተነሱበት። ቡትቶ ጨርቅ ነው ያደረጉት። ስሎ ዝም አለ። ለካ እንደዚህ ምግባረ ብልሹዎች ኖረናል? በዚህ አይነትስ «የደርግ መኮንኖች» መባል ሲያንሰን ነው። ባምሳሉ አድቦልቡሎን ኖሯል!

ዛሬ የተሰበሰብንበት ጉዳይ ግን ከሰሞኑ ለየት ያለ ነበር። ስብሰባውን የመራው ታጋይ ሀጎስ ይባላል። ለኛ ሻለቃ ላስተማሪነት የተመደበ ነው። ባንድ ስብሰባ ላይ አይቸዋለሁ። ሲናገር ትንታግ ነው።

ነገር ስጋውን አላምጦ ጨርሶታል:: በየሻለቃው የተመደቡት ታጋዮች በሙሉ አስተማሪዎች ተብለው ነው የሚጠሩት:: ምን እንደ ሚያስተምሩን ለብዙዎቻችን እንቆቅልሽ ነው የሆነብን:: ቢጨንቀኝ:-

"እነዚህ ታጋዮች አስተማሪ የሚባሉት ምንድን ነው የሚያስተምሩን?" ብዬ በድሉን ጠየኩት::

"ስለ መቶ አመት ታሪክና ስለዲሞክራሲ፣ ስለብሄር፣ ብሄረሰቦች መነጣጠል" ብሎ አሳቀኝ::

ታጋይ ሀጎስ ሲጋራውን ቡልቅ ቡልቅ አደረገና "ያው 'የድጋፍ ሰልፍ እንሰለፍ' ብላችሁ በጠየቃችሁት መሰረት እንድትሰለፉ ተፈቅዶላችኋል:: ስለዚህ በዛሬው እለት መፈክር የሚያዘጋጁ፣ የካርቱን ስእል የሚስሉና ልዩ ልዩ ስራዎችን የሚያከናውኑ ሰዎችን ትመርጣላችሁ" ሲለን ጭጭ አልን:: ከሰሞኑ "እንሰለፍና እንገላገል! ደመወዛችንን የያዙት ሰልፍ ባለመሰለፋችን ነው" እየተባለ ውስጥ ውስጡን ቅስቀሳ ተደርጎ ሁላችንም ለመሰለፍ ተስማምተን ነበር::

"የተናገርኩት ለቤቱ ግልፅ አይደለም እንዴ?" ሲል ጠየቀ::

"ኧረ ግልፅ ነው" አሉት ከፊትለፊት የተቀመጡት::

"እንግዲያማ ተጨማሪ ሀሳብ ስጡበትማ" አለ:: ከዚያ ጠና ጠና ያሉ መኮንኖች እየተነሱ የድጋፍ ሰልፍ ማድረግ እንደሚገባን በስፋት አስረዱ:: እኛም በመስማማት አጨበጨብን:: በዚሁ የሰልፉን አዘጋጅ ኮሚቴ መርጠን ካዳራሽ ወጣን:: የሽንኩርቱ ሽታ ግን አሁንም አለቀቀኝ:: እንጃልኝ በዚህ ከቀጠለ አንድ ቀን ከስብሰባ ላይ ማስመለሴ የማይቀር ነው:: ኧረሱስ የኢህአዲግ ስራም ያስታውካል::

ምእራፍ ዘጠኝ

በቀን ደክመን ደክመን እውነቱን ያጣነው፣
አሁን በጨለማው ለምን እንደክማለን ደስታን ላናገኘው?

24

«የቀድሞው መንግስት የጦር መኮንኖች እጃችንን ከተጨማለቀው ስርአት ለማንፃት ዝግጁ ነን!!"» ነገ ከምንይዛቸው መፈክሮች አንዱ ነበር:: ገና ከማታው ጀምሮ የዝግጅት ኮሚቴው መፈክሮችን ለየሻምበሉ ጦር አከፋፍሏል::

ካልጋዩ ላይ ጋደም ብዬ መፈክሩን አትኩሬ እያየሁ በቁጭት ተጠበስኩኝ:: ፊቴ ተጨማዷል:: እንደኔው በየመኝታቸው ላይ ሆነው መፈክሩን አትኩረው እያዩ ፀጉራቸውን የሚነጩ ነበሩ:: ከናካቴው ምንም ያልገባቸውም ነበሩ:: ልክ በማግስቱ እንደሚሞሸሩ ሁሉ

ይጨፍሩ ነበር:: ምንፈቀዱኝ:: እነሱ የሚያኮርፉት ሆዳቸው ሲጎድልና ሲጋራ ሲያጡ ብቻ ነው::

"አፈር ይብሉና! የዝግጅት ኮሚቴ ተብዬዎች የመረጥናቸው እኛን የሚያዋርድ መፈክር እንዲያወጡ ነው እንዴ?!" አለ አዱኛ ደቻሳ:: ጮክ ብሎ ነበር የተናገረው::

"ቀስ በል!" አለው በድሉ ጫኔ ቆጣ ብሎ::

"ምኑን ቀስ እለዋለሁ! እነመንግስቱ ባጨማለቁት ስርአት እኛ ተጠያቂ እንሆናለን እንዴ!" አሁንም ቀስ ብሎ መናገር አልሆነለትም::

"ጤናም የለህ! ምናለ ዝም ብትል!" ደግሞ ተቆጣው::

"ለምን ዝም እላለሁ? ከዚህ የበለጠ ምን ይመጣል? እንዳህያ መፈክር አሸክመው ሊነዱን ነው!" አለ እንደ እልህ እየተናነቀው:: ለትንሽ ጊዜ ዝም ብሎ ቆየና እየተንካኩ የሚስቁትን አፍጥጦ እያየ "እነዚህን መፈክር ማሸከም ብቻ ሳይሆን መድፍም ማስጎተት ነበር! አሁን ምኑ ደስ ብሏቸው ነው እንደ እንቁራሪቶቹ የሚያሽካኩት!" አለ:: ሳቃቸውን ቆም አድርገው ዘወር ዘወር እያሉ አዩት::

"አንተ ጤናም የለህ እንዴ!" ስል እኔም ተቆጣሁት:: ዳግመኛ ትንፍሽ አላለም፤ ተሸፋፍኖ ተኛ:: እኔም ተጠቅልዩ ተኛሁ:: እንቅልፍ ግን አልሞከረኝም::

ከውጭ የእንቁራሪቶቹ እልልታ ይሰማኛል:: ደስታቸው ይችው ክረምት ነች:: ከዚያ ወዲያ ጭጭ ይሏታል:: ዛሬ ግን እልልታቸው መቁረጫ የለውም:: ቀንም፣ ሌትም ከኩሬ ኩሬ እየተዛለሉ ፍቅራቸውን ይጨርሳሉ:: የፍቅር መጨረሻ ትንሽ ኩሬ...

የሰልፉ አዘጋጅ ኮሚቴዎች ጫት እየቃሙ ሲወጡ፣ ሲገቡ ነው ያነጉት:: ልክ ወጧ እንዳማረላት ሴት:: እኛንም የቀሰቀሱን ልክ አስራ ሁለት ሰአት ሲሆን ነው::

ሀምሌ 18 ቀን 1983 ዓ.ም. እለተ ሀሙስ ነው:: ጠላይ ከትናንት ጀምራ ብራ ናት:: የዛሬዋ እለትም ቁልጭ ያለች ቀን ነች:: ቁርሳችንን ከበላን በኋላ በየሻለቃችን ተሰለፍን:: መፈክሮች ይኾጎደጎዳሉ፤ የባህል ዘፋኖች ይቀልጣሉ:: የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ በብዛት ይዘን እናውለበልባለን::በዚህ አጋጣሚ «ጨርቅነቷን» ሰርዘን ደምና አጥንት የተዋሀዳት መሆኗን ለማሳወቅ እየተቀባበልን በመያዝ ጉሯሯችን እስከሚነቃ እንጮሃለን:: ደግሞ የማንንም የድርጅት አርማ አልያዝንም:: የኛን ሻለቃ የሚመራው ሰልፈኛ የያዛት በራ ልታመልጥ ስትል የተያዘች የእንዲት ነጭ እርግብ ስእል የሚያሳይ ነው:: ትርጓሜውም «ሰላም ልታመልጠን ስትል ያዝናት» ማለት ነው:: ከኛ ኋላ የሚከተለን ሰልፈኛ ደግሞ 3ኛ ሻለቃ ነው:: እሱ የያዘው የካርቱን ስእል ደግሞ ሁላችንንም አስቆናል:: በውድድሩም አሸናፊ የሆነው ይኸው ሻለቃ ነው::

«አብዮታዊ መሪያችንን» የወታደር ልብስ አልብሰው ከሳሏቸው በኋላ ከወደ ግንጭላቸው በኩል ልክ የችምፓንዚ ግንጭል አስመስለውባቸው እግሮቻቸውን እንደ ሽረሪት እግሮች አቅጥነዋቸዋል:: ያጠለቁት ጫማ ደግሞ አካፋ ያክላል:: በቴሌቪዥን እንደሚታዩት የህፃናት ፊልም ነው ያስመሰሏቸው:: ካጠገባቸው ደግሞ ለመብረር

ያኮበኮበ ዳሽ ፋይፍ አይሮፕላን አለ:: ብር ያጨቁበትን ቦርሳ እንጠልጥለው ወደሱ የሚሮጡ ይመስላሉ:: ከካርቱን ስእሉ ግርጌ የተፃፉት መፈክሮች:-

«ትንሽ ትንሽ እንድማ! አንድ ሰውና አንድ መሳሪያ እስከሚቀረኝ ድረስ እዋጋለሁኝ» የሚል ነው:: ሰልፈኛው ያሰማው የነበረው መፈክር ደግሞ:-

«የዝምባብዌ መንግስትና ህዝብ ፈርጣጩንና ፋሽስቱን መንግስቱ ሀይለማርያምን ለኢትዮጵያ ህዝብ አሳልፎ መስጠት አለበት! የሀገርን ሀብት የዘረፉ ባስቸኳይ ለፍርድ ይቅረቡ!» የሚል ነው::

ተጥመልምለን የባህል አዳራሽን እንዳለፍን ጋዜጠኞች ፎቶ ለማንሳት፣ በቴሌቪዥን ለመቅረፅ ይሯሯጡ ጀመር:: ልክ ጦላይ አደባባይ ስንደርስ ቦታ ቦታችንን ይዘን ቆምን:: ይዘናቸው ከነበሩት መፈክሮች ውስጥ:-

- የብሄሮችና የብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የዲሞክራሲ መብት ነው!
- ኢህአዲግ የሰላምና የዲሞክራሲ ዋስትና ነው!
- ህዝባችን የተጠማውን ሰላም ያግኝ!
- የሰላምና የዲሞክራሲ ኮንፈረንስ የኢትዮጵያ ህዝብ ምጥ የወለደው ነው!
- የተጎሳቆለችውን አገራችንን መልሰን እንገነባለን!
- የህዝቡ የበላይነት ይከበራል! የሚሉ ናቸው::

የክብር እንግዶች መጥተው ቦታቸውን እንደ ያዙ የሰልፉ አዘጋጅ ኮሚቴ ሰብሳቢ የመግቢያ ንግግር አድርገው ፕሮግራሙን ለሚመራው መኮንን ለቀቁለት:: ከዚህ በኋላ በተከታታይ ሶስት ግጥሞች ተነበቡ:: ሁሉም ግጥሞች ከብሶት የመነጩ ነበሩ:: አቅራቢዎቹም ወጣት መኮንኖች ናቸው:: ከጨለማ ህይወት ላይ መውደቃቸውን ግጥሞቻቸው ይጠቁማሉ:: ተስፋን እያጭሩም! ያስቆዝማሉ እንጅ::

ሁሉም ነገር ተብሎ ካበቃ በኋላ የማእከሉ ሀላፊ ንግግር ለማድረግ ሲነሱ ለክብራቸው ርችት ተተኮሰላቸው:: ወዲያው እርጭ ሲል መናገር ጀመሩ:: ባማረኛ ነበር የተናገሩት:: መነፀር አድርገዋል:: የቀይ ዳማ ናቸው::

"... ወደፊት በዚህ ማእከል ውስጥ ላጭር ጊዜ በምትቆዩበት ወቅት ጥሩ ጥሩ ተግባራትን ታከናውናላችሁ ብለን እንገምታለን..." በቃ ይኸው ነው:: ሌላው ስለሽግግር መንግስቱ፣ ስለቻርተሩ አላማ ነው:: ይኸ ደግሞ ምናችንም አይደል:: በዚሁ የሰልፉ ፍፃሜ ሆነ::

ይች "አጭር ጊዜ ቆይታ" የምትለዋ አባባል የሁላችንንም ጭንቅላት በጥብጠዋለች:: ለሶስት ቀናት ሴሚናር ተብለን ሆለታ ገብተን ይኸውና ሶስተኛ ወራችንን ይዘናል:: ይች አጭር ጊዜ ደግሞ ትረዝም ይሆን?

25

ጉድ አይመጣ የለም እያደር ጉድ መጣ፣
«እመኑ» ተባልነ እምነን ብንመጣ::

ሌሊቱን ሲዘንብ ነው ያደረው:: ከነጋም በኋላ ካፊያ ቢጤ ነበር:: እየቆየ ግን ፈተት እያለ መጣ:: የጦላይ ያየር ፀባይ ይኸው ነው:: ይዘንብና ወዲያው ፀሀይ ትወጣለች:: ከዚያ ደግሞ ጭቃው ምጥጥ ይላል:: ታዲያ ይኸ የዋልካ ጭቃ ስንረግጠው እንደ ካትራሚ ንክስ ንክስ ያደርግና ወዲያው ተተምትሞ ሀስፋልት ሆኖ ቁጭ ያላል:: ሲዘንብ ደግሞ ሙልጭልጭ ይልና አፍርጦ ይጥላል:: ዛሬስ አፍርጦ የጣለን የኢህአዲግ ነገር ነው:: እያደር ከበደን፤ ሰልፍ ተሰልፈን አንጀቱን እናራራለን ብለን ነበር፤ እሱ ግን ሽቦ አንጀት ሆነ:: እንደ ኮራን ብንቀመጥ ይሻለን ነበር:: በመሰለፋችን ያላሱብነውን መዘዝ መዘዙብን:: አውቀነዋል፤ አጭሯን ጊዜ ለማስረዘም ነው::

ዛሬ ስብሰባ እንደ ምናደርግ የተነገረን ማታ ነበር:: ያው እንደ ሁልጊዜው በየሻለቃችን ነው የተሰበሰብነው:: አዳራሹ ጢም ብሎ ሞልቶ የመስኮቱ ዙሪያ እንደ አጥር ክርችም ብሏል::

የነጭ ሽንኩርት ሽታ አንጀት ያማስላል፤ አፍንጫን ይቆርጣል:: ሲዘንብ ስላደረ ነው መሰል የሙቀቱ መጠን ቀነስ ያለ ነው:: የሲጋራው ጭስ ግን የማርፈጃውን ጉም ተክቶ ወደ ኮርኒሱ ይበናል:: ተጠራቅሞ ካፊያ እንዳይሆን እንጅ...

ታጋይ ሀጎስ ጉሮሮውን ጠራረገና "ዛሬ የተሰበተብንበት ምክንያት ባለፈው ያካሄድነውን ሰልፍ ለመገምገም ሲሆን ዋናው ትኩረታችን ግን 'የበደልነውን ህዝብ መልሰን እንክሳለን!' የሚለውን መፈክር ሳትይዙ በመቅረታችሁ ሰልፉ የተሟላና ከልብ ነበር ለማለት አንችልም:: ስለዚህ ዛሬ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተወያይተን የዚህን መፈክር ፅንሰ ሀሳብ ተረድታችሁና አምናችሁ ካወጣችሁት ያቋም መግለጫ ጋር ተጨምሮ ይተላለፋል" ሲል አብራራልን:: ለካም ያቋም መግለጫው በሬዲዮ ያልተላለፈው ለዚህ ነው:: ቤቱ በግለት እጁን አወጣ:: ላንድ ሻምበል እድል ሰጠው::

"በመጀመሪያ ለምጠይቅህ ጥያቄ ተገቢ መልስ ስጠኝ፣ ለመሆኑ ሰልፉ የኢህአዲግ ነው የኛ?" ሲል ጠየቀው::

"ሰልፉ የኢህአዲግ አይደለም፤ የናንተ ነው:: ሆኖም ግን የመቆጣጠር ሀላፊነት አለብን" ሲል መለሰለት::

"በመቆጣጠሩ በኩል ያላችሁን ድርሻ እኛም እንቀበለዋለን:: ሰልፉን ግን የጠየቅነው እኛ እስከሆንን ድረስ የምንይዘውንም መፈክር መወሰን ያለብን እኛ ነን:: በርግጥ እናንተን የሚፃረር መፈክር እንዳንይዝ መከልከል ትችላላችሁ:: ይህም ቢሆን የዲሞክራሲን መርህ ይፃረራል:: ነገር ግን እናንተ የምትፈልጉትን መፈክር እንዴት እንሸከማለን?" በማለት ተናግሮ ተቀመጠ:: በርካታ መኮንኖች ደግሞ እጃቸውን አወጡ:: ሀጎስ ለማንኛውም እድል ሳይሰጥ እራሱ:-

ያኮበኮበ ዳሽ ፋይፍ አይሮፕላን አለ:: ብር ያጨቁበትን ቦርሳ እንጠልጥለው ወደሱ የሚሮጡ ይመስላሉ:: ከካርቱን ስእሉ ግርጌ የተፃፉት መፈክሮች:-

«ትንሽ ትንሽ እንድማ! አንድ ሰውና አንድ መሳሪያ እስከሚቀረኝ ድረስ እዋጋለሁኝ» የሚል ነው:: ሰልፈኛው ያሰማው የነበረው መፈክር ደግሞ:-

«የዝምባብዌ መንግስትና ህዝብ ፈርጣጩንና ፋሽስቱን መንግስቱ ሀይለማርያምን ለኢትዮጵያ ህዝብ አሳልፎ መስጠት አለበት! የሀገርን ሀብት የዘረፉ ባስቸኳይ ለፍርድ ይቅረቡ!» የሚል ነው::

ተጥመልምለን የባህል አዳራሽን እንዳለፍን ጋዜጠኞች ፎቶ ለማንሳት፤ በቴሌቪዥን ለመቅረፅ ይሯሯጡ ጀመር:: ልክ ጣላይ አደባባይ ስንደርስ ቦታ በታችንን ይዘን ቆምን:: ይዘናቸው ከነበሩት መፈክሮች ውስጥ:-

- የብሄሮችና የብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የዲሞክራሲ መብት ነው!
- ኢህአዲግ የሰላምና የዲሞክራሲ ዋስትና ነው!
- ህዝባችን የተጠማውን ሰላም ያግኝ!
- የሰላምና የዲሞክራሲ ኮንፈረንስ የኢትዮጵያ ህዝብ ምጥ የወለደው ነው!
- የተጎሳቆለችውን አገራችንን መልሰን እንገነባለን!
- የህዝቡ የበላይነት ይከበራል! የሚሉ ናቸው::

የክብር እንግዶች መጥተው በታቸውን እንደ ያዙ የሰልፉ አዘጋጅ ኮሚቴ ሰብሳቢ የመግቢያ ንግግር አድርገው ፕሮግራሙን ለሚመራው መኮንን ለቀቁለት:: ከዚህ በኋላ በተከታታይ ሶስት ግጥሞች ተነበቡ:: ሁሉም ግጥሞች ክብሶት የመነጩ ነበሩ:: አቅራቢዎቹም ወጣት መኮንኖች ናቸው:: ከጨለማ ህይወት ላይ መውደቃቸውን ግጥሞቻቸው ይጠቁማሉ:: ተስፋን እያጭሩም! ያስቆዝማሉ እንጅ::

ሁሉም ነገር ተብሎ ካበቃ በኋላ የማእከሉ ሀላፊ ንግግር ለማድረግ ሲነሱ ለክብራቸው ርችት ተተኮሰላቸው:: ወዲያው እርጭ ሲል መናገር ጀመሩ:: ባማረኛ ነበር የተናገሩት:: መነፀር አድርገዋል:: የቀይ ዳማ ናቸው::

"... ወደፊት በዚህ ማእከል ውስጥ ላጭር ጊዜ በምትቆዩበት ወቅት ጥሩ ጥሩ ተግባራትን ታከናውናላችሁ ብለን እንገምታለን..." በቃ ይኸው ነው:: ሌላው ስለሽግግር መንግስቱ፤ ስለቻርተሩ አላማ ነው:: ይኸ ደግሞ ምናችንም አይደል:: በዚሁ የሰልፉ ፍፃሜ ሆነ::

ይች "አጭር ጊዜ ቆይታ" የምትለዋ አባባል የሁላችንንም ጭንቅላት በጥብጠዋለች:: ለሶስት ቀናት ሴሚናር ተብለን ሆለታ ገብተን ይኸውና ሶስተኛ ወራችንን ይዘናል:: ይች አጭር ጊዜ ደግሞ ትረዝም ይሆን?

25

ጉድ አይመጣ የለም እያደር ጉድ መጣ፤
«አመኑ» ተባልን አምነን ብንመጣ::

ሴሊቱን ሲዘንብ ነው ያደረው:: ከነጋም በኋላ ካፊያ ቢጤ ነበር:: እየቆየ ግን ፈተት እያለ መጣ:: የጣላይ ያየር ፀባይ ይኸው ነው:: ይዘንብና ወዲያው ፀሀይ ትወጣለች:: ከዚያ ደግሞ ጭቃው ምጥጥ ይላል:: ታዲያ ይኸ የዋልካ ጭቃ ስንረግጠው እንደ ካትራሚ ንክስ ንክስ ያደርግና ወዲያው ተተምትሞ ሀስፋልት ሆኖ ቁጭ ያላል:: ሲዘንብ ደግሞ ሙልጭልጭ ይልና አፍርጦ ይጥላል:: ዛሬስ አፍርጦ የጣለን የኢህአዲግ ነገር ነው:: እያደር ከበደን፤ ሰልፍ ተሰልፈን እንጀቱን እናራራለን ብለን ነበር፤ እሱ ግን ሽቦ እንጀት ሆነ:: እንደ ኩራን ብንቀመጥ ይሻለን ነበር:: በመሰለፋችን ያላሰብነውን መዘዝ መዘዙብን:: አውቀነዋል፤ አጭሯን ጊዜ ለማስረዘም ነው::

ዛሬ ስብሰባ እንደ ምናደርግ የተነገረን ማታ ነበር:: ያው እንደ ሁልጊዜው በየሻለቃችን ነው የተሰበሰብነው:: አዳራሹ ጢም ብሎ ሞልቶ የመስኮቱ ዙሪያ እንደ አጥር ክርችም ብሏል::

የነጭ ሽንኩርት ሽታ እንጀት ያማስላል፤ አፍንጫን ይቆርጣል:: ሲዘንብ ስላደረ ነው መሰል የሙቀቱ መጠን ቀነስ ያለ ነው:: የሲጋራው ጭስ ግን የማርፈጃውን ጉም ተክቶ ወደ ኮርኒሱ ይበናል:: ተጠራቅሞ ካፊያ እንዳይሆን እንጅ...

ታጋይ ሀጎስ ጉሮሮውን ጠራረገና "ዛሬ የተሰበተብንበት ምክንያት ባለፈው ያካሄድነውን ሰልፍ ለመገምገም ሲሆን ዋናው ትኩረታችን ግን 'የበደልነውን ህዝብ መልሰን እንክሳለን!' የሚለውን መፈክር ሳትይዙ በመቅረታችሁ ስልፉ የተሟላና ከልብ ነበር ለማለት አንችልም:: ስለዚህ ዛሬ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተወያይተን የዚህን መፈክር ፅንስ ሀሳብ ተረድታችሁና አምናችሁ ካወጣችሁት ያቋም መግለጫ ጋር ተጨምሮ ይተላለፋል" ሲል አብራራልን:: ለካም ያቋም መግለጫው በሬዲዮ ያልተላለፈው ለዚህ ነው:: ቤቱ በግለት እጁን አወጣ:: ላንድ ሻምበል እድል ሰጠው::

"በመጀመሪያ ለምጠይቅህ ጥያቄ ተገቢ መልስ ስጠኝ፤ ለመሆኑ ሰልፉ የኢህአዲግ ነው የኛ?" ሲል ጠየቀው::

"ሰልፉ የኢህአዲግ አይደለም፤ የናንተ ነው:: ሆኖም ግን የመቆጣጠር ሀላፊነት አለብን" ሲል መለሰለት::

"በመቆጣጠሩ በኩል ያላችሁን ድርሻ እኛም እንቀበለዋለን:: ሰልፉን ግን የጠየቅነው እኛ እስከሆንን ድረስ የምንይዘውንም መፈክር መወሰን ያለብን እኛ ነን:: በርግጥ እናንተን የሚፃረር መፈክር እንዳንይዝ መከልከል ትችላላችሁ:: ይህም ቢሆን የዲሞክራሲን መርህ ይፃረራል:: ነገር ግን እናንተ የምትፈልጉትን መፈክር እንዴት እንሸከማለን?" በማለት ተናግሮ ተቀመጠ:: በርካታ መኮንኖች ደግሞ እጃቸውን አወጡ:: ሀጎስ ለማንኛውም እድል ሳይሰጥ እራሱ:-

"ደርግ ያራምደው የነበረው ስርአት ጨቋኝ ስርአት ነው አይደለም?" ሲል ጥያቄ አቀረበልን:: ማንም አላመናታም፤ ባንድ ድምፅ:-

"ጨቋኝ ስርአት ነው!" አልነው:: በዚህ ጊዜ ፈገግ አለና:-

"እንግዲህ የስርአቱን ጨቋኝነት ካመናችሁ ስርአቱን ያራምዱ የነበሩት ደርጎችም ፋሽስቶች ናቸው! በዚህስ ታምናላችሁ አታምኑም?"

"የደርግን ፋሽስትነትም እናምናለን!" አልነው::

"ታዲያ ደርግን ደግፎ ያቆየው ማነው? እናንተ አይደላችሁም? በዚህስ አታምኑም?" ሲለን ፀጥ አልን::

"ምነው ዝም አላችሁሳ?" አለን ፈገግ ብሎ፤ አገኘኋችሁ በሚል አይነት:: በዚህ ጊዜ አንድ መቶ አለቃ ብድግ አለና:-

"በርግጥ የደርግን ፋሽስትነት ማንም ሳይነግረን እኛ እራሳችን እናውቀዋለን:: 'ታዲያ ካወቃችሁት ለምን ተሸከማችሁት?' ልትለን ትችላለህ:: መልሳችን 'ባንድነት ስም ተወጥረን ስለተያዝን አገርን ከመገንጠል ለማዳን ባደረግነው ተጋድሎ የደርግ እድሜ ሊራዘም ችሏል::' ታዲያ ላገር መሞት፤ ለዳር ድንበር መፋለም ህዝብን በዳይ ያደረጋል እንዴ?" ብሎ ተቀመጠ:: በርካታ እጆች ደግሞ ወጡ:: ሀጎስ ፊቱን ቅጭም አድርጎ በሲጋራው ጭስ በኩል አጮልቆ እያየ ላንድ ሻምበል እንዲናገር ፈቀደለት::

"ሀቅ እንናገር ካልን እኛ የኢትዮጵያን ህዝብ አልበደልነውም:: እንዲያውም አንወቅሰውም እንጂ የበደለን እሱ ነው:: ከበስተጀርባችን ከደርግ ጋር ሆኖ እየጨፈረ... ' ገሏል መሰለኝ ዝናሩ ጎሏል... ፈጣን ነው ባቡሩ...' እያለ ቤቱ አቋረጠውና አጨበጨበ:: ሀጎስ አሁን ፈገግ ብሎ ነበር:: ፈገግታው ግን 'ሞኞች ናችሁ' የሚል አይነት ነው:: ሻምበሉ ንግግሩን በመቀጠል:-

"በምስራቅ፤ በሰሜን፤ በደቡብ፤ በምእራብ፤ በተንከራተትን፤ ቤተሰቦቻችን መጠለያ አጥተው በተበተኑ እንዴት የኢትዮጵያን ህዝብ በድላችኋል ትሉናላችሁ? እንዲያውም የኢትዮጵያ ህዝብ ሊክሰን ይገባል" አለና ተቀመጠ:: ወዲያው ደግሞ በተጣደፈ ሁኔታ "ተጨማሪ! ተጨማሪ!" እያሉ ብዙ መኮንኖች ተንጫጩ:: አዱኛ ደቻሳ እድል አገኘ::

"ለመሆኑ 'የበደልነውን ህዝብ መልሰን እንክሳለን' በሉ የምትሉን የኢትዮጵያ ህዝብ 'ልጆቻችን ይለቀቁልን' ብሎ ጥያቄ አቀረበ እንጅ፤ 'በድለውኛልና ለፍርድ ይቅረቡልኝ' አለ? ይህ ሁሉ ጥረታችሁ መብታችንን ለማሳጣት ነው:: ለምን ምክንያት ታበዛላችሁ? እንዲሁኮ መግፈፍ ትችሉ ነበር!" አለና ተወራጭቶ ተቀመጠ::

በዚህ ጊዜ ሀጎስ ፊጠን ብሎ "ዋእ! በምትናገሩበት ጊዜ ከግል ስሜታችሁ በመነሳትማ መሆን የለበትም! እኛ መብታችሁን ለመግፈፍ ሀሳብ የለንም:: በርግጥ በግል ደረጃ ሲታይ አብዛኞቻችሁ ተበዳይ እንጅ በዳይ ላትሆኑ ትችላላችሁ:: እኛም ይህን በሚገባ እናውቃለን:: ለዚህም ነው የሽግግር መንግስቱ ኮሚሽን አቋቁሞ ጭቁኑን መኮንንና ወታደር አሰባስቦ ተሃድሶ አስገብቶ ለማነፅ ጥረት የሚያደርገው:: ለመሆኑ አልበደልንም የምትሉት የሀውዜን ጭፍጨፋ እንዲህ በቀላሉ የሚረሳ ይመስላችኋል?" ሲል ለመልሱ እጅ እንደ ችቦ ሽቅብ ቆመ:: ከሁሉም ፊት ላይ ደግሞ ቁጣ ይንቦገቦጋል::

አንድ ወጣት መኮንን ተጣድፎ በመነሳት "የሀውዜንን ጭፍጨፋ ብቻ መጥቀስህ የሚያስተዛዝብ ነው፤ የጎንደር፤ የወሎ ህዝብ በደርግ ጆት አልተደበደበ ይሆን? ደግሞስ የሀውዜን ህዝብ ነው እንዴ የኢትዮጵያን ህዝብ የሚወክለው? የሚቆረቆርለት አጥቶ እንጅኮ ያሰሳ ህዝብም አልቋል!" ሲል ጠረጴዛ ሳይቀር እየተደበደበ ቅልጥ ያለ ጭብጨባ ተጨበጨበ:: የሀጎስ ፊት ኩምትርትር አለ::

"ዋእ! ስነስርአት! መኮንኖች አይደላችሁም! ጫጫታውና ጠረጴዛ ድብደባን ምን አመጣው!" ሲል ተቆጥቶ ተናገረ:: ያስቆጣው ግን ጭብጨባው ብቻ ሳይሆን ያሰሳ እልቂት መነሳቱ ነው:: ያሰሳ እልቂት ሲነሳ ታጋዮችን ኩምትርትር ነው የሚያደርጋቸው:: አንዳንዶቹ "እኛ በዚያ ግንባር አልተሰለፍንም:: አንግን ጠይቁ" ይላሉ:: አንዳንዶቹ የግም ሾላ በደፈናው ይቆጡና ጥያቄው እንዳይነሳ ይከላከላሉ:: ከሆለታ ጀምረን ያወዛገበ ጉዳይ ነው:: እነሱ ሀውዜንን ሲያነሱ እኛ አሰሳን እናነሳለን:: በዚሁ በጠብ እንለያያለን::

"ማሳሰቢያ" አሉ አንድ መኮንን ከተቀመጡበት ተነስተው::

"እሽ! ማሳሰቢያውን ይቀፅሉ» አላቸው::

"ስነስርአት የምታሳጣን አንተ ነህ! ባንድ በኩል 'የመናገር መብታችሁ የተጠበቀ ነው' ትለናለህ:: እውነቱን ስንነግርህ ደግሞ ትቆጣለህ:: አንተ የምትፈልገውን ከተናገርንማ ምኑን ዲሞክራሲ ሆነው?" ብለው ተቀመጡ::

"እኔ አሁንም ቢሆን የዲሞክራሲ መብታችሁን አልተጋፋሁም:: የሆነ ሆኖ ማሳሰቢያውን ተቀብየዋለሁ" አለና በርካታ እጆች ወጥተው ስለነበረ ላንድ ኮለኔል ፈቀደላቸው::

"ቅራኔዎችን ለማስፋት ከሆነ ብዙ ድርጊቶችን መጥቀስ ይቻላል:: ሀውዜንን ስትጠቅሱም አሰሳን ማንሳታችን የማይቀር ነው:: የሚያሳዝነው ግን ለሁለቱም ህዝቦች መቆርቆር ስንችል ዘር መረጣ መግባታችን ነው::

"አስራ ሰባት አመት ሙሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተቋረጠ ጦርነት ተካሂዷል:: በዚህ ጦርነትም ከወዲህም ሆነ ከወዲያ ያለቀው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው:: በዳይም ተበዳይም ያለ አይመስለኝም:: እለ ከተባለም ደርግና ስርአቱ ናቸው:: እኛ እንዴት እንደ በዳይ እንቆጠራለን? ለመሆኑ እኛ ህዝቡን ስንገድል እናንተ ህይወት እየዘራችሁ ነበር የመጣችሁት? እናንተ አልገደላችሁም? ስለዚህ ይቅርታ ጠይቁ ካላችሁን አብረን እንጠይቅ፤ ምሩን እንከተላችኋለን!» ሲሉ የጭብጨባው ነገር አይነሳ! ክፍሉ ተናጋ::

"ዋእ! አሁንም ቢሆን አነጋገራችሁ ወደ መፍትሄ የሚያመራ ሳይሆን የሽሙጥ አነጋገር ነው:: ትክክል አይደላችሁም! እኛ የተጋደልነው ከናንተ ጋር እንጅ ከህዝቡ ጋር አይደለም:: ታዲያ ምን ብለን ነው ይቅርታ የምንጠይቀው? ከደርግ የጭቆና አገዛዝ ስላላቀቅነው? እኛኮ እንደናንተ ስንቅ ሰንቅ፤ ልጅህን እምጣ፤ ነጋ ጠባ መዋጮ፤ አብዮት ጠባቂ፤ ታጣቂ እያልን ህዝቡን አላሰቃየነውም:: ከዚህ የበለጠስ ምን ልታደርጉት ኖሯል?" በማለት ተናገረ:: ለመልሱ አንድ ጠና ያሉ ሻለቃ ተነሱና:-

ውይይቱ የሚካሄደው ባሸናፊዎችና በተሸናፊዎች መካከል ሆኖ እንጅ እኛም በናንተ ቦታ ብንሆን ኖሮ ስንት ስም በሰጠናችሁ ነበር" ሲሉ አቋረጣቸውና:-

"ገንጣይ፣ አስገንጣይ፣ ወያኔ፣ ወንበዴ... ስትሉን አልነበረም" ሲላቸው:-

"እሱማ ሕናንተም ያልሰደባችሁን ስድብ የለም:: ዛሬም ቢሆን 'የደርግ መኮንኖች' እያላችሁ ትሰድቡናላችሁ:: የሆነ ሆኖ እኛ ለኢትዮጵያ ህዝብ ሞትንለት እንጅ አልገደልነውም:: እሱም ገደሉኝ አላለም::

"የደርግንም እድሜ ያራዘማችሁት እናንተ ናችሁ እንጅ እኛ አይደለንም:: እኛማ እሱን ለመጣል መፈንቅለ መንግስት ሳይቀር ሞክረን ነበር:: ደግሞ ከገባችሁ እናንተን ለድል ያበቃናችሁ እኛ ነን" ብለው ሲቀመጡ ጭብጨባ ቀለጠ:: ጭስጨባው ማናደጃም ጭምር ነው::

"እኛ ለድል የበቃነው በራሳችን ጥረት እንጅ በናንተ ድጋፍና እርዳታ አይደለም:: ምናልባት መሳሪያችሁን አስረክባችሁ እጃችሁን በሰላም መስጠታችሁን እንደ ውለታ ቆጥራችሁት ከሆነ ተሳስታችኋል:: ሰላም ፈላጊ ብትሆኑማ ኖሮ ቀደም ሲል አፈሙዛችሁን ወደ ደርግ አዙራችሁ መፋለም ነበረባችሁ:: በሬዲዮም ጥሪ አድርገንላችሁ ነበር:: ሰላም ፈላጊና የህዝብ ልጅ የመሰላችሁት ደርግ ፍርክስክሱ ሲወጣና መንግስቱ ሀይለማርያም ጥሏችሁ ሲፈረጥጥ ነው:: መፈንቅለ መንግስት ሞክረን ነበር ያሉትም እኛ እንደግፈውም:: በጀኔራሎች የተካሄደ መፈንቅለ መንግስት ስለሆነ በሌላ ደርግ ለመተካት ካልሆነ በስተቀር ፋይዳ አይኖረውም ነበር:: አሁን ወደ ዋናው ነጥብ ልመለስና የኢትዮጵያን ህዝብ አልበደልንም ነው የምትሉት?" በማለት ጥያቄ አቀረበ::

"አዎን" የሚል ድምፅ አስተጋባ::

"መልካም፤ የዛሬው ስብሰባችን ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተወያይተን በማመንና በማሳመን ሳይሆን በእንቢተኛነት፣ ነገሮችን አጣሞ በመተርጎም፣ በተለይም የደርግ ኢሰፓ አስተሳሰብ ያልተላቀቃቸው መኮንኖች የቤቱን መልካም አዝማሚያ በርዘውታል:: ሀቁን ነገር ክዳችሁ የምታደርጉት መፍጨርጨር የትም አያደርሳችሁም" ሲል አስጠንቀቀንና ሲጋራ አያያዘ:: እሱ ሲለኩስ ደግሞ የባረከላቸው ይመስል ሁሉም ለኮሱ:: ባዳራሹ ውስጥ ጭስ ይግፈጠፈጥ ጀመር:: ነገርም አብሮ እየጨሰ ነው...

ለትንሽ ጊዜ ተፋጠን ሳለ አንድ መኮንን ብድግ አለ:: ፊቱን ብጉር በንጉሮታል:: "እኔ የፖሊስ መኮንን ነኝ:: በፖሊስነቴም ብዙ ምስጢሮችን አውቃለሁ:: እንዳጋጣሚ ደግሞ አለቆቼ ስለማይወዱኝና ከቦታ ቦታ ስላንከራተቱኝ ብዙ ነገሮችን አይቻለሁ:: በደርግ ጊዜ ያልተፈፀመ ጉድ የለም:: ይህን ሁላችንም እናውቃለን:: ታዲያ ለማን ብለን ነው ይህን ያህል ክርክር የምናነሳው? ለደርግ ጥብቅና ለመቆም ወይንስ ታማኝነታችንን ለመግለፅ? እንዲህ አስበን ከሆነ የዋሆች ነን:: ጉማ ክፍሉ አንባል:: ለምን እሽ ብለን አንገላገልም" ሲል የሳቅ ሁካታ አስተጋባ:: ወዲያው ደግሞ ተስማምተናል በሚል አይነት ጭብጨባ አስተጋባ:: ሀጎስ ደስ አለው:: በሲጋራ የበለዙ ጥርሶቹን ገለጣቸው:: በዚሀ መካከል እንዳለን ኮለኔል ዘርጋው እጃቸውን አወጡ:: ጠቅላላ

ባደራሹ ውስጥ ያለው አይን ከሳቸው ላይ አረፈባቸው:: ከኔ ፊትለፊት ነበር የተቀመጡት:: ፊታቸው የተቆጣ ነበር መስሏል:: አይኖቻቸው ቀልተዋል:: ሲቆጡ ይኸው ናቸው:: ቶሎ ብለው ነው አይኖቻቸው የሚቀሉት::

"ተጨማሪ ነው" አላቸው ሀጎስ ቀልጠፍ ብሎ::

"አዎን" አሉት ዝግ ባለ አነጋገር::

"ይናገሩ! ይናገሩ! " አላቸው ተጣድፎ::

አዳራሹን አንድ ጊዜ ዳር እስከ ዳር ቃኙና "ጎበዝ! እንዴት የኢትዮጵያን ህዝብ አልበደልንም ብለን እንከራከራለን? የበደል በደል ፊፅመንበታል እንጅ:: ያውም ትውልድ የማይረሳው:: 'ልጆቼ ከጥቃት አድኑኝ' እያለ ስንቁን፣ ልብሱን ከልጆቹ ጉሮሮ እየነጠቀ ሳያንድልብን ፈርጥጠን በመምጣት ታሪኩን አትድፈንበታል:: ስለዚህ በበደልነው ልክ ልንክሰው ከቻልን፣ እሱም ይቅርታ የሚያደርግልን ከሆነ በበኩሌ ይቅርታ መጠየቅ ተገቢ ነው ባይ ነኝ:: እንዲያውም በነሀጎስ በኩል ከመጠየቃችን በፊት እኛ አውቀን መጠየቅ ነበረብን:: አልበደልንም ብለን መከራከር የነበረብን ትጥቃችንን ሳንፈታ ነበር:: አሁንማ ከንቱ መንፈራገጥ ነው:: ሀጎስምኮ ልካችንን ነግሮናል:: ትጥቃችንን የፈታነው ፈርተን እንጅ ሰላም ፈላጊ ሆነን አይደለም:: ይህን እኔም አምንበታለሁ፣ ጨርሻለሁ!" ብለው ተቀመጡ:: ጭብጨባ የለም:: ሁሉም በቁጭት ከንፈሩን ይነክስ ጀመር:: ጠረጴዛ ሳይቀር በቡጢ የሚደልቁ ነበሩ:: የተረጋጋው ቤት እንደ ገና ቤንዚን ተርከፈከፈበት::

"ዋእ! ይህማ ግልፅ ነው! ኮለኔሉ እንሽፍት ነው የሚሉት!" አለ ሀጎስ ተቆጥቶ:: በዚህ ጊዜ እኔ እጄን አወጣሁኝ::

"በርሳቸው ላይ ተጨማሪ ከሆነ አያስፈልገኝም!"

"ራሴ የተሰማኝ ነገር ስላለ እሱን ለመናገር ነው::"

"እስቲ" አለኝ በመጠራጠር አይነት:: ከተቀመጥኩበት ቀስ ብዬ ተነሳሁና:-

"የኢትዮጵያን ህዝብ 'በድለነዋል' ወይንም 'አልበደልነውም' ለማለት ብዙ አጨቃጫቂ ነጥቦች ሊነሱ ይችላሉ:: እስቲ በመጀመሪያ ከህዝቡ ሰቆቃ እንነሳ:: ከዚህ በኋላ ነው መበደል ወይንም አለመበደላችንን የምናውቀው::

"የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘመነ ደርግ ንብረቱ፣ ቤቱ ተወርሶ በመጨረሻ የቀሩት ልጆቹና ሚስቱ ብቻ ነበሩ:: እነዚህንም ሚስቱን አኢሴማ የሚባል በደርግ አምሳል የተቀረፀ ድርጅት እንዳሻት ትሁን ስላለ የስንቱ አባወራ ቤት ፈረሰ:: ልጆቹን ደግሞ በገጠር የገበሬ ማህበራት፣ በከተማ ከነማት የተባሉ እንደ አዳኝ ውሻ በየጓዳው እያነፈነፉ፣ እየመነጠቁ ለኮሚሳርያት ሲያቀብሉ ኖረዋል:: ኮሚሳርያት ደግሞ ለብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት ያስረክባል:: ብሄራዊ ውትድርና ለብ ለብ አድርጎ ለጥብስ ያደርሳል:: ወጣቱን እንደ እጅ ኳስ እየተቀባበሉ ተጫውተውበታል:: በዚህ መካከል ደግሞ የሚካሄደው ሽያጭ ራሱን የቻለ ታሪክ ነው:: የጥንቱ ባሪያ ፍንገላ ምስጋና ይንሳው:: እስቲ ህዝቡ ሲብሰው የሚያንጎራጉረውን ልጥቀስላችሁ:-

'ኑሮ ጎመዘዘኝ አጅትን ገለማኝ፣
የትስ አቤት ልበል ጨኸቴን ማን ይሰማኝ፣
ጧት ማታ መዋጮ አንጀቴን አወጣኝ፣
ይኸ አልበቃኝ ብሎ ልጄንም አምጣሉኝ::
እኔ መኢገማ፣ ሚስቴ አኢሴማ፣ ልጁ አኢወማ፣
ፈጣሪ ግደለኝ ይህንን ሳልሰማ::' ይል ነበር::

"ይህ ሁሉ ድርጊት ሲፈፀምበት እኛ እናውቅ ይሆን? ለምልመላ የተስማራን መኮንኖችስ የለንም?

"የኢትዮጵያ ህዝብ የደም እንባ እያነባ፣ በርሃብ እንደ ቅጠል እየረገፈ ደርግ ኢሰፓን በመሰረተበት ወቅት ከተማዎችን በቀይ ጨርቅና ባንፔል በኮሪያ ኤክስፐርቶች ያሸበርቅ ነበር:: ያዲስ አበባ አረንጓጅም ፎቆች በቀይ ጨርቅ ተሸልመው ከተማዋ በተለያዩ ቀለማት ባጌጡ አፑሎች ስትብረቀረቅ በዚያን ወቅት መሬት ላይ ያለን ይመስለን ነበር? በርግጥም አልነበረንም:: ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ስር አድርገን እንጨፍር ነበር:: ይህንም ህዝቡ በዝምታ አላለፈውም:-

'በደርግ ጊዜስ ሁሉም ተደበረ፣
ግንቡ ሳይቀር ቀይ ጨርቅ ለብሶ አያደረ::'

"ደርግ ህዝቡን የተስፋ ዳቦ እያስገመጠ እሱ በውስኪና በጮማ በመቀማጠሉ ከዛሬ ነገ ያልፍልኛ ይሆናል በማለት በችግር የተጠበሰው ህዝብ በኢህድሪ ምስረታ ወቅት ተስፋው በመሟጠጡ:-

'እነሱው ደግሰው እነሱው በሉት፣
መቼም አያምርበት የባለጌ ቤት' ብሏቸዋል::

"ደርግ ግን ቢነግሩት የሚገባው አይደለም:: ልክ ከቋጢኝ ድንጋይ ላይ ውሀ እንደ ማፍሰስ ይቆጠራል:: ወይንም 'ደንቆሮ ቢጠቅሱት መልሶ ይጠቅሳል፣ ለምን ቢባል እሱ ስለማይሰማ ሌላው የሚሰማ ስለማይመስለው ነው::' እውነትም የድንቁርናው ድንቁርና (እብሪትም ሊሆን ይችላል) የኢትዮጵያን ህዝብ በካኪ አንገቱን አነቀው:: ህዝቡ አሁንም ደርግን ከመጎንተል ወደ ኋላ አላለም:-

'ደርግ ተራመደ ሄደ ገሰገሰ፣
ባስራ አንድ አመቱ 'ጥልቆ ለበሰ::' ብሎታል::

"የደርግ እብሪት እንዲህ በዋዛ የሚታለፍ አይደለም:: 'መንደር ምስረታ' ብሎ ባወጣው ፖሊሲ መሰረት የኢትዮጵያን ህዝብ ቤቱን እንዲያፈርስ አደረገው:: ያለ ጥናት፣ ያለ እቅድ አጋርፋ በሰለጠኑ የገበሬ መሀንዲሶች እየተቀየሰ ገበሬው በእድሜው ያነፃቸው ቤቶች 'አሞራው ቡድን' የሚባል አቋቋሞ ጣራው እየተገነበረ እንዲወድቅ ተደረገ:: ይህንም ገበሬው በምሬት ሲገልፀው:-

'እርሻ አነሰኝ ብዬ ስቆጣ ስቆጣ፣
እዩት ተመልከቱት የባሰ ቀን መጣ፣
ቤት እያፈረሰ የሚያባርር መጣ::
መሬታችን እንኩ፣ እህላችንን እንኩ፣ ልጆቻችን እንኩ፣
የሬሳችን መውጫ ቤታችንን አትንኩ::'
ብሎ አልቅሷል::

"እንዲህ ያለውን ሰው በላ ስርአትና መንግስት ነበር ለአስራ ሰባት አመታት ተሸክመን ያቆየነው:: ታዲያ ህዝቡ የደም እንባ ሲያነባ እኛ መለዮ ለባሽ ልጆቹ ደርሰንለታል? ከደርግ መንጋጋ አላቀነዋል? የኢትዮጵያ ህዝብ ግፍ መች በዚህ ብቻ ያከትምና:-

"እህል ሰብል ገበያ ድርጅት ወይም 'እሰገድ' የተባለ አቋቋሞ ገበሬ ያመረተውን ምርት እንዳሻው እንዳይሸጥ ሸማች ግብረ ሀይል በየገጠሩ በማስማራት እርሶ አደሩን ገፎታል:: በዚህም ገበሬው ዝም አላለም:-

'ኧረ እነዚህ ደርጎች ጤፍ አምጡ፣ ቅቤ አምጡ ይላሉ፣
ቅቤ የት ተገኝቶ በሀይለስላሴ ተቀልጦ ተበልቶ' ብሏቸዋል::

"አዎን፤ የደርግ መፈጠር ህዝቡ እንገሽግሾት አንቅሮ የተፋውን የሀይለስላሴን አስተዳደር እንደገና እንዲናፍቀው አስገድዶታል:: ቢልም አይፈረድበት:: ባይሆን ያኔ የሚስቱ፣ የልጆቹ፣ የቤቱ ባለቤት ነበር:: የኔ የሚለው ነበረው:: የደርግ እብሪት በዚህም አልተገታ:: ከተሜውን መኪናውን እሁድ እሁድ እንዳያንቀሳቅስ በህግ አገደው:: ህዝቡ ቢጨንቀው የጋብቻ ቀትን ወደ ቅዳሜ አዛወረ:: ይህም አዲስ ታሪክ ነበር::

"የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ አዬ መሸከም አቅቶት ሲንቀጠቀጥ መቶ ሀያ አዬዎች ተሸከም ተብሎ ተፈረደበት:: ያውም መንጋ ደናቁርት:: ኧረ መቼ ይሆን እንባው የሚደርቀው? ኧረ መቼ ይሆን ባገሩ ኮርቶ የሚኖረው? እስከመቼስ ያንባገነኖችን ጡጫ ችሎ ይኖራል? ፍርዱን ለዚያው ሲቃይተኛ ህዝብ እተወዋለሁ::

"ቀደም ሲል አንድ መኮንን 'ለደርግ መቆየት ኢህአዲግ አስተዋፅኦ አድርጎለታል' ያሉትን እኔም አምንበታለሁ:: ለምን ቢባል የኢህአዲግ አቋም ባለመታወቁ ህዝቡ ጎሰኝነትን አጥብቆ ስለሚቃወም ደርግ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም 'ገንጣይ፣ አስገንጣይ፣ ጎጠኛ፣ ወያኔ...' እያለ በፕሮፖጋንዳ ወጥሮ በመያዝ ለድሜው መራዘም ፋታ እንዲያገኝ አግዞታል:: እንዲያውም ባንድ ወቅት አዲስ አበባ ይወራ የነበረው 'ደርግ ያለ ኢህአዲግ፣ ኢህአዲግም ያለ ደርግ አይኖሩም' እየተባለ ነበር::

"መታወቅ ያለበት ግን ደርግ ይህን ሁሉ ግፍ ሲፈፅም የመጀመሪያው ግፍ የተፈፀመበት ይህ ሰራዊት መሆኑን ነው:: በመጨረሻም ውድቀታችን የከፋና አሳፋሪ ሆኖ 'እመኑ' እየተባልን እንወገጣለን:: በክብ ጠረጴዛ መሆኑ መልካም::

"የኢትዮጵያን ህዝብስ 'አልበደልንም' ብለን እንከራከር ጥሩ፣ ታዲያ የኢትዮጵያን ህዝብ ልጆች ነን ካልን መንግስቱና መሰሎቹ

ሲፈረጥጡ ለምን ፍርክስክሳችን ወጣ? ለምን የሳምንት እድሜ እንኳን አልመከትንም? እውነት ከዚህ ሁሉ መኮንን መካከል አንድ ወይንም ከዚያ በላይ አሞት ያለው ጠፍቶ ነው? ልብ ያለው ከሌለ ደግሞ ያሁኑ ክርክር መነሳት የለበትም:: ያሉንን ከመፈፀም ሌላ ምርጫ የለንም:: እኔ እንደ ሚገባኝ የኢትዮጵያን ህዝብ በድለነዋል ባይ ነኝ:: ታዲያ እኔ ኢህአዲግን ብሆን ከዚህ አስቀምጬ የርዳታ እህል እየለመንኩ አልቃልብም ነበር:: ሱሪውን አስወልቄ ቀሚስ እያስጠለኩ፣እንዝርት አስጨብጬ 'ሂዱ ከሚስቶቻችሁ ጋር ጥጥ ፍተሉ' ነበር የምለው::

'ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንዳባቱ፣
አመልማሎ ይፍተል ቁጭ ብሎ እንደናቱ!'

ይላሉ አበው:: አመሰግናለሁ::" ብዬ ስቀመጥ ቅልጥ ያለ ጭብጨባ ተጨበጨበ:: ለምን እንዳጨበጨቡ ግን አልገባኝም:: ማጨብጨብ ልማድም ስለሆነ ይሆናል::

ሀንስ ሲጋራውን እያያዘና ሁለት ጊዜ ምጎ "መቶ አለቃ ጥሩ ተናግረው በስተመጨረሻ ብቻ ያልሆነች ሀሳብ ሰንዝረው ነው የተቀመጡት:: የሆነ ሆኖ ጥቅል ሀሳባቸው 'በድለናል' የሚል ስለሆነ በሳቸው ሀሳብ የምትስማሙ እጃችሁን አውጡ" ሲል ጠቅላላ እጅ ወጥቶ ጨራሮ መሰለ::

"ተቃውሞ?" ሲል ጠየቀ:: ከተቀመጠበት ተነስቶ ቆሞ ነበር:: አንድም መኮንን የተቃወመ አልነበረም:: በዚሁ "የበደልነውን ህዝብ መልሰን እንክሳለን!" ብለን ተገላገልን::

ጤፍ አምጡ፣ ቅቤ አምጡ፣ ልጅ አምጡ በማለት ያስቃየናችሁ፣
ዛሬ ማሩን ስንል ማሩን አባካችሁ::

ምሳ ላይ የሞገዲድና የሸፈዲድ አባላት በየሻለቃው የተካሄዱትን የውይይት ውጤቶች በሙሉ አዘነቡልን:: ካንደኛ ክፍለ ጦር አንደኛ ብርጌድ ሶስቱም ሻለቆች አምነዋል:: ከሁለተኛ ብርጌድ አንደኛ ሻለቃ ያለምንም ችግር "የበደልነውን ህዝብ መልሰን ለመካስ ዝግጁ ነን:: ይኸ ደግሞ ምን ችግር አለው?" ብለው ነው ባንድ ድምፅ የተስማሙት:: ሺፈዲድ ግን ውሳኔአቸውን አንኳሷል:: ሞገዲድ ደግሞ ግንዛቤያቸውን አድንቋል::

እኔ ባለሁበት ሁለተኛ ሻለቃ ያው ስንዳረቅ ብንውልም በመጨረሻ አምነናል:: ከኛ ብርጌድ ውስጥ እምቃ ያለው ሶስተኛ ሻለቃ ነው:: ከምሳ በኋላም ስብሰባው ይቀጥላል:: ሸፈዲድ ያነሷቸውን ነጥቦች አድንቆላቸዋል:: "ኢህአዲግ እንደ የፖለቲካ ድርጅት እንጅ የኢትዮጵያ ህዝብ የወከለው መንግስት ባለመሆኑ በሱ እንጠየቅም:: የኢትዮጵያን ህዝብ እንዴ ጨራሽ ኢህአዲግ ስለሆነ ተጠያቂው አይጠይቀንም" የሚሉ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል:: ሶስተኛ ብርጌድ ሶስቱም ሻለቆች ተጨፋጭፈው ተጨፋጭፈው በመጨረሻ አምነዋል::

ሁለተኛ ክፍለ ጦር ደግሞ ካንዱ ብርጌድ ውስጥ አንዱ ሻለቃ ብቻ ሲያምን የቀሩት ግን እንሞክርም ብለዋል:: እንዲያውም ሁለት

ሻለቆች ታጋዮችን ካዳራሽ አባረዋል:: እነዚህን ሻለቆች ሸፈዲድ እጅግ ሲያደንቃቸው ሞገዲድ ግን «ስርአት አልበኞች» ብሏቸዋል::

ምሳየን በልቼ እንዳበቃሁ በቀጥታ እየገሰገስኩ የሄድኩት ሶስተኛ ሻለቃ አዳራሽ ነበር:: መቀመጫ ቀርቶ መቋሚያም አልነበረም:: ከሰአት በፊት ያመኑት መኮንኖች ለማዳመጥ አዳራሹን አጨናንቀውታል:: በስተመግቢያው በር በኩል ሰርስሬ በመግባት ደረቴን ገልብጬ ቆምኩኝ::

ከሰአት በፊት ሻለቆቻቸውን ያሳመኑት ታጋዮች ተሰብስበዋል:: እየተቀባበሉ በመደስኮር መኮንኑን አደነዘዙት:: መኮንኑ በነገርም፣ በሙቀትም እየዛለ መጣ:: ከሰአት በፊት ያመኑት ሻለቆች ይህን ሻለቃ ተስፋ አስቆረጠውታል:: ታጋዮቹ ተናግረው ተናግረው ሲያልፍላቸው አንድ መኮንን ብድግ አለና:-

"አብዛኛው ጦር አምኗል:: ስለዚህ የኛ መንገታገት ዋጋ የለውም:: እንመንና እንገላገል" ሲል ቤቱ በመስማማት አጨበጨበ:: ታጋዮቹም ያሸናፊነት ኩራት ተሰማቸው:: ፈገግ አሉ::

"አሁንስ መቶ አለቃ ተስማማህ?" አለው ሰብሳቢው ታጋይ ወንዳንድ ወጣት መኮንን አትኩሮ እያየ::

"በርግጥ እኔ እንደ ጥፋት ሆኖ ያገኘሁት በወታደርነቴ መንግስት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ተቀብዬ ተግባራዊ ማድረጌ ነው:: ዛሬ እንዲህ መጠየቄን ባውቀው ኖሮ ያንዬ ስታዘዝ እንቢ ብዬ መረሸን ነበረብኝ" ብሎ ሲናገር አንድ መኮንን ገንፍሎ በመነሳት:-

"እንዲህ ያሉትን ሀሳብ ግትሮች እየወሰዳችሁ በግል አሳምኑልን:: ይኸ መቶ አለቃ ቢነግሩት የማይገባው ነው:: ከሰአት በፊትም እሱው ነው ጎትሮን የዋለው!" በማለት በቁጣ ተናግሮ ተቀመጠ::

"አሁንስ?" አለው ታጋዩ::

"አሁን አምኛለሁ:: ያመንኩት ግን ተገድጀ እንጅ በሀሳብ ተረትቼ አይደለም:: ከኛው መካከል ተወስጀ ለብቻየ እንዳምን ሀሳብ ስለተሰጠብኝ ነው" አለ ከፍተኛ ቅሬታ ተሰምቶት::

"እስቲ አምነናል የምትሉ እጃችሁን እውጡ?" ሲል ጠቅላላ እጅ ወጣ:: ሁሉም አመኑ ማለት ነው:: ከዚህ በኋላ የስብሰባው ፍፃሜ ሆነ::

አንደኛ ክፍለ ጦር እንግዲህ በሙሉ አመነ ማለት ነው:: ሁለተኛ ክፍለ ጦር ደግሞ ያላመኑትን ለማሳመን ስብሰባው ከሰአት በኋላም እንደ ቀጠለ ስለሆነ ወደዚያው እየገሰገስኩ ሄድኩ:: እየተጣደፍኩ የገባሁት አራተኛ ብርጌድ አንደኛ ሻለቃ አዳራሽ ውስጥ ነበር:: እነዚህ ደግሞ በዕሁፍ አጠቃለው ነው ያቀረቡት:: አንድ መኮንን ጥቅል ሀሳቡን ቁሞ በንባብ ሲያሰማ ነበር የደረስኩት::

«1ኛ. በማሸነፍ በትር ስልጣኑን የጨበጠው ኢህአዲግ በመሆኑ በኛና በሱ መካከል የተፈጠረው የጦርነት እልቂት እራሱን ከተጠያቂነት ለማዳን ሲል፣ የኢትዮጵያን ህዝብ 'በድለናል' በሉ ማለቱ አግባብ ስላልሆነ በዳይም ተበዳይም ህዝብ ሳይሆን ሁለቱ ጦርነቱን ያካሄዱት ወገኖች ናቸው:: ስለዚህ እንበድልም እንበድልም 3ኛ ጠያቂ ሀይል እስቲ ፈጠር ድረስ ባንቸኩል ጥሩ ነው::

«2ኛ. የምስራቁ ጦርነት ዳርድንበርን ለማስከበር ስለሆነ በዚህ ጦርነት ወቅት ተበድያለሁ የሚል ካለ በማእዘን ተለይቶ ይቅረብ::

«3ኛ. 'ተበድለናል' የሚለው ጥያቄ የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄ ከሆነ በህዝቡ በኩል ይቅረብ።

«4ኛ. ዲሞክራሲ ሲባል የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመደራጀት፣ የመከራከር ሙሉ መብት ሲሆን እኛ ግን ያለንበት ሁኔታ ስለማይፈቅድልን ለማመንም ሆነ ለማሳመን ወይንም ተመጣጣኝ መልስ ለመስጠት አንችልም። ብንችልም እንኳን የምንሰጠው ሀሳብ ያቋም መለኪያ ተደርጎ ስለሚወሰድ የዲሞክራሲ ነፃነት የሚለው ቃል በዚህ ስብሰባ ላይ ወይንም ጨርሶ በዚህ ማእከል ውስጥ መነሳት የለበትም» የሚሉ ነበሩ። በነዚህ ነጥቦች ላይ ከፍተኛ ፍጭት ከተካሄደ በኋላ ያው «ሌሎቹ ካመኑ የኛ ብቻ መነታረክ ምን ዋጋ አለው» ብለው አመኑ።

መኮንኑ ለልጆቹ፣ ለሚስቱ ሲል የማይከፍለው መስዋእትነት የለም። ልጆቹና ሚስቱ ይጎትቱታል። በሌላ በኩልም በጅምላ መታጎራችን በብዙ መንገድ ጎድቶናል። ከእስር ያመለጠው ታማኝነቱን በመግለጽ፣ ኢህአዲግን አሞጋግሶ ከንፁህን ጋር ንፁህ ተብሎ መለቀቅ ይፈልጋል። ነፍስ የገደሉ፣ ገንዘብ የመዘበሩ ደግሞ አድፍጠው ከጅምላው ጋር ተቀላቅለው መሸሎክ ይፈልጋሉ። ምንም የሌላቸው ድሆች ደግሞ ከኢህአዲግ ጥግ ለማግኘት ሲሉ ጅራታቸውን ይቆላሉ። በዚህ ምክንያት አንድነት የለንም። ያለ ጠባቂ ቂጥ ለቂጥ ስንጋፋ እንውላለን። በዚህ ላይ በጎሳ መከፋፈል ተጀምሯል። ይህ የጎሳ ጉትቻ የት እንደሚያደርሰን ግን አላወቅነውም።

ምእራፍ አስር

በረባው ባረባው ጀግና ደግናው ሙቶ፣
መንጋ ለከስካሳ እንቶ ፈንቶው ቀርቶ፣
ስም አልባ ልንሆን ነው ስማችነን ጠፍቶ።

26

እንቁራሪቶች ይሽከመከማሉ። ደግሞ ይተዛዘላሉ። መተቃቀፋቸው ይሆን? በተለይ ከመሽ በኋላ በነሱ እልልታ ድንቁር ነው የምንለው። ፋታ የላቸውም። በጊዜአቸው፣ በወቅታቸው እልል ይበሉ እንጂ...

ባለፈው ስብሰባችን የበደልነውን ህዝብ መልሰን እንክሳለን ካልን ወዲህ አዲስ ነገር ብቅ ያለው ካዲስ አበባ፣ ከወሊሶ፣ ከወልቂጤ ሴቴ ሳጤዎች፣ ሊስትሮዎች፣ በራሪ ነጋዴዎች ተነቅለው መምጣታቸው ነው። ተስፈኞች ደግሞ ከበቾና ከሊሙ ሰቃ ገንፍለው መጥተዋል። ደግሞ ህፃናት ናቸው። በያንዳንዱ ሻለቃ የምግብ አዳራሽ በምሳ ሰአትና በራት ወቅት መጥተው ከበሩ ላይ ይሰፍራሉ። በዚህ የተነሳ ዛሬ ጣላይ በሰው ተጨንቃለች። በማእከሉ ውስጥ አዳዲስ ንግድ ቤቶች እንደ እንጉዳይ እየፈሉ ናቸው። ሻሂና ቡና አፍሊዎች በየጥጋጥጉ፣ በየዛፉ

ስር ቁጭ ቁጭ በማለት የቅምጥ ገበያ ጀምረዋል። አንደኛ ክፍለ ጦር፣ አንደኛ ብርጌድ አጠገብ፣ «ታይዋን» ተብሎ ተሰይሟል። የማይሸጥ ነገር የለም። በተለይ ሽንኩርት፣ ቃሪያ፣ ሰንደል፣ ወረቀት... ይዘው እንደ ዝንጀሮ ጠባቂ ይጎለታሉ መኮንኖቹ።

በየሻለቃው መኖሪያ ክልል ውስጥ ለውስጥ ደግሞ በረንዳው ሁሉ ሻሂና ቡና እየተፈላ መሸጥ ተይዟል። ይህ እንግዲህ የሰፈር ገበያ መሆኑ ነው። የሚንስ ቤት ሰራተኞችም በፈረቃቸው ተኳኩለው ቡናና ሻሂ ቸርቻራ ገብተዋል። ሁሉም የኛን ኪስ ለማራገፍ ሽሚያ ይዟል። የሰከረ አሳ ሆነናል። ስካር ብል ስካር ትዝ አለኝ።

ስካር ከሆለታ ወዲህ ትንሽ ፋታ ሰጥቶን ነበር። ይህን ሰሞን እንደገና ተቀስቅሶ ከዋዩ በድጋፍ ካምፕ መግባት ተይዟል። አረቂ ከወልቂጤ በጀሪካን በቀን የሚያመላልሱ አራት ሳንድሮቨሮች አሉ። እኛ ዋዩ እየሄድን መገልበጥ ነው። ባለፈው ሰሞን አንድ መኮንን ከመጠን በላይ ጠጥቶ በመስከሩ ውሃ ውስጥ ገብቶ ሙቷል። ሞት ባነሳ የሞቱት ሁሉ ታወሱኝ። ነፍሱን ይማረውና መቶ አለቃ ሀይለሚካኤልንም እየረሳሁት ነው። ለነገሩማ እንኳን የሞቱት ያለነው እየተረሳን ነው።

ሌላው ከሰሞኑ የተከሰተው አዲስ ነገር የድርጅት ጋጋታ ነው። በሽፈዲድና በሞገዲድ ስንማረር ሌሎች በህቡእ ይንቀሳቀሱ የነበሩት አሁን ዲሞክራሲ በሚገባ በመስፈት ፕሮግራማቸውን ይፋ አድርገው ካምፑን ያተራምሱታል።

1ኛ. አገልግል መንትፍ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (አመዲድ)
2ኛ. አገልግል ጠላፊ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (አጠዲድ)
3ኛ. ሚስት ነጣቂ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ሚነዲድ)
4ኛ. ፖስታ ቀዳጅ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ፖቀዲድ)
5ኛ. ኪስ ዳሳሽ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ኪዳዲድ) ናቸው።

አመዲድና አጠዲድ ካንድ ላይ ተዋህደው ለመስራት ቃል ገብተዋል። ምክንያቱም በፕሮግራማቸው ላይ ምንም አይነት ልዩነት የለም። ኪስ ዳሳሽና ፖስታ ቀዳጅ ትንሽ ልዩነቶች ስላሏቸው በህብረት ለመስራት ወስነዋል። ሁሉም ድርጅቶች ግን ፕሮግራማቸውን ይፋ ከማድረጋቸው በፊት በተግባር ብዙ ድርጊቶችን አከናውነዋል። አሁን በቅርቡ ፕሮግራሙን ይፋ ያደረገው ኪዳዲድ የተባለው ድርጅት አስደናቂ ተግባር በመፈፀሙ የተነሳ በርካታ አባላትን ለማፍራት ችሏል።

ነገሩ እንዲህ ነው። ያንድ መኮንን ሚስት ባሏን ለመጠየቅ ካዲስ አበባ መጣች። ያንዱ ቤተሰብ ሲመጣ ተሰባስበን ማጫወት፣ ስላዲስ አበባ መጠየቅ ባህላችን ነው። በመሆኑም አንድ የኪዳዲድ ስራ አስፈፃሚ አባል ጠጋ ይልና ፍትፍቱንም፣ ወሬውንም ሲፈተፍት ያመሻል።

ሚስት ለባሏ "ጓደኛህ መቶ ብር ልኮልሃል" ትልና ከቦርሳዋ ውስጥ አንዲት ሌላ ትንሽ ቦርሳ ታወጣና "እንካ" ትለዋለች። ባልም ለሚስቱ አሳቢ ኖሮ ጓደኛውን አመስግና "እኔ ለጊዜው ችግር የለብኝም። አንቺ ልጆች ይዘሽ ስለሚቸግርሽ ላንቺ ይሁንሽ" ይላታል። ሚስትም ችግር ኖሮባት ኖሮ ሳታንገራግር መልሳ ከሚጢጢ ቦርሳዋ ከታ እሷን ደግሞ ከትልቁ ቦርሳዋ ክትት ታደርጋለች። እጅሬ ኪዳዲድ እይት።

ከመብል፣ ከመጠጥ፣ ከጨዋታ በኋላ በየካምፓችን ለንግዳ ማረፊያ ብለን የፀዖር ቤቶችን፣ የልብስ መተኮሻ የነበሩትን ጎጃጆችን

እንግዶች እንዲያድሩበት አድርገናል:: ይህ መኮንንም ሚስቱን ይዞ ወደ ማረፊያው ይሄዳል፤ በኪዳዲድ አጃቢነት:: ታዲያማ ከመኝታው ሲደርሱ ሚስት ቦርሳዋን ታስቀምጥና ወደ መፀዳጃ ቤት ለመሄድ ስትነሳ ባል ሊያሳያት አብሮ ብድግ ይላል:: ተያይዘው ውልቅ፤ ኪዳዲድ ብቻውን ቅርት:: ቦርሳ ጠባቂ ሆኖ...

ባልና ሚስት ከመፀዳጃ ቤት ሲመለሱ "መልካም ሌሊት" ብሎ ውልቅ:: እነሱም ተነፋፍቀው ኖሮ ወዲያው የፍቅር ጨዋታቸውን ጅምር:: ዕጌ ትዝ አለችኝ:: ምነው በመጣችልኝ:: በየኔነሽ መቼም ተስፋ ቆርጫለሁ::

በማግስቱ ጧት፣ እሁድ ማለት ነው፣ ሚስት ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ቀድማ ትነሳና ባሏ ለሷ ሲያስብ እሷም ማሰብ ነበረባትና ትንሽ ብሮች ልትሰጠው ፈልጋ ቦርሳዋን ከፍታ ሚጢጢን ታወጣና ክፍት ስታደርግ መቶ ብሩ የለም:: ክው ትላለች

"ምን ሆንሽ?" ባል ካጠገቧ ቆሞ ይጠይቃል::

"መቶ ብሩን ወሰድከው እንዴ?"

"አረ አልወሰድኩም" እሱም ይደነግጣል::

"ታዲያ የት ደረሰ?" ትልና ትልቁን ቦርሳዋንና ያችኑ ትንሽ ቦርሳ ኑ ውለዱ ትል ጀመር:: ባልየው ደግሞ የተኙበትን ዙሪያ ይመነቅር ጀመር::

ሚስት ቦርሳዎቿን አገላብጣ ምንም ነገር ስታጣ ቆም ብላ ትንሽ ታስብና "አንተ! ብሬን የወሰደው ማታ አብሮን የነበረው መቶ አለቃ ነው:: ወደ መፀዳጃ ቤት ስንሄድለት ነው የወሰደው" ትለዋለች::

"አረ ተይ አያደርገውም:: መኮንንኮ ነው" ይላታል::

"በኔ ይሁንብህ፣ ብሬን ያለሱ የወሰደው የለም" ትለዋለች በርግጠኛነት::

"እስቲ ለሁሉም 'ወድቆ አግኝተህ እንደ ሆነ' ብዬ ልጠይቀው" ይላትና እሷን ከውጭ ንፋስ ላይ አስቀምጦ እሱ ወደ መኮንኖች መኝታ ክፍል ይገባል:: ጓድ ኪዳዲድን ግን ከመኝታው ላይ ያጣዋል:: ካጠገቡ የሚተኙትን ሲጠይቃቸው በሌሊት ከታ ከተማ ብለው ካንድ ጓደኛው ጋር መሄዳቸውን ይነግሩታል:: ወደ ውጭ ይወጣና ለሚስቱ ይህንኑ ይነግራታል:: አጅሪትም ትንታግ ኖራ:-

"ዛሬ አልሄድም! ይህን ክብረቢስ ከስሸ ነው ክብሩን የማላጣው" ትልና ከጉዞዋ ተሰናክላ ትቀራለች::

ማታ ጓድ ኪዳዲድ ጥንብዝ ብሎ ሰክሮ በጓደኛው ተደግፎ ይመጣል:: ባለ ብሯ እመቤት ትጨሳለች:: ያኔስ ባልየውም ጭሶ ኖሮ ተንደርድሮ ከመኝታው በመሄድ:-

"ቀስ አድርገህ ጉድ ሳይፈላ የሰረከውን መቶ ብር አምጣ!" ይለዋል:: ቅንቡራ ቅንቡራ ይላል:: በዚህ ላይ ደግሞ 'የሌባ አይነደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ' ነውና ከጓደኛው ጋር በመሆን በተደፈርኩ ባይነት ካልገደልኩ ይላል:: እኛ ትርኢቱን እያየን እንስቅ ጀመር::

"አንተ ሌባ! እዳ ልታስገባኝ እንጅ አቅም ኖሮህ አይደለም" ይልና ውልቅ ብሎ የሻለቃውን ጠርናፊ ወይንም ካቦ ይዞ በመምጣት አንጠልጥሎ ወደ ኢህአዲጎቹ ያስወስደዋል:: ኢህአዲጎቹ ሲጠይቁት መልስ ሰጭው አረቂ ይሆናል:: ኪሱ ሲፈተሽ አምሳ ሰባት ብር ይገኛል::

እርባ ሶስት ብር ውሃ በልቶታል:: የሚያደርጉት ቢያጡ እኩሉ የተገኘው ብር በኤግዚቪትነት ይያዝና እሱ ለይደር ይለቀቃል:: እንደ ደነፋ ነበር ያነጋው::

ጧት ቀርቦ ሲጠየቅ ወደላይ ወደታች በመርገጥ ለማምታታት ሞከረ:: "እውነቷን" ሲሉት ኢህአዲጎቹ እንደ ነገር ሳይቀር ዝክዝክ:: በመጨረሻ የሆነው ነገር የለም:: አምሳ ሰባቱ ብር ለወይዘሮዋ ተመልሶ እሱ ተለቀቀ::

ሚስት ነጣቂ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ደግሞ ጠላይ ከተቋቋሙት ድርጅቶች መካከል አንዱ ነው:: ተግባሩም ሴቶችን እየጠለፉ ለሁለት ለሶስት የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ነው:: ምናልባት ሌሎቻችን አረመኔነት ልንለው እንችል ይሆናል፤ ሚኒዲዶች ግን «እርካታን ይሰጠናል» ይላሉ::

ሚኒዲድ ባለፈው ሳምንት ከባህል አዳራሽ ያንድ መኮንን ሚስት ካውቶቢስ እንደ ወረደች «የባልሽ ጓደኞች ነን፤ ነይ እንውሰድሽ» ይሉና ያመጣችውን ያገልግል ፍትፍት በመሸከም ወስደው ከባዶ ክፍል በመዝጋት ፍትፍቱን ፈትፍተው እሷንም ላምስት ሲፈተፍቷት አደሩ:: ጧት ደም ሸንታለች:: ጊዜው ይሆን እንዴ እንዲህ ያስጨከነን?

27

በእምነት ከሆነም ኢትዮጵያ አገራችን ክርስቲያን ነበረች፤
እስልምናም ቢሆን እሷ በየቦታው በርካታ መስጊዶች፤
እእምሮ አጥተን ነው ተቀብራ የቀረች::

እንቁራሪቶች ከየኩሬያቸው እየተንበጫረቁ ደስታቸውን ይገልፃሉ:: የተፈለፈሉትም ደርሰዋል:: ቁርቁር... የሚል ድምፅ ይሰማል:: ድሪያው ደርቷል... አሁንኮ ነገ፣ ከነገ ወዲያ ይች የኩሬ ውሃ ድርቅ ስትል እልም ለማለት ነው:: ያንድ ሰሞን ቡረቃ:: እያ እንቁራሪቶች! በሉስቲ እስከ ጊዜው ድረስ ጨፍሩ...

ከእንቁራሪቶቹ እልልታና ፍልቅልቅታ ጋር በትልልቅ ዛፎች ስር የጴንጤ መዝሙር ያስተጋባል:: አቤት የዜማው ቃና! አእምሮን ይሰልባል:: አሁንማ መኮንኑ በሞላ ተለቅቀበታል:: መፅሃፍ ቅዱስ ያልጨበጡት መኮንኖች በጣም ጥቂቶች ናቸው:: ልክ እንደ ማሌ ጥናት በክብ ይዘውታል:: እየ ማሌ! በመፅሃፍ ቅዱስ ተተካ! ያሁሉ እብዮተኛ ነኝ ባይ መኮንን ዛሬ ቂጡን ገልቦ ያዘጠዝጣል:: ጊሙን ያላሳደገ የለም:: ያንዳንዶቹማ ልክ ያባ ማስያስን ጢም አክሏል::

አዱኛ ደቻሳና በድሉ ጫኔ በጧት ነው ወደ ከታ የሄዱት:: እንቢ ብያቸው እንጅ አብሬያቸው እንድሄድ ለምነውኝ ነበር:: ለምን እንደ ሆነ እንጃ ሁሉም ነገር እያስጠላኝ መጥቷል:: ብቸኝነትም መምረጥ ይቀለሁ:: ቂጣ ቂጣም ይለኛል:: ምናልባት ተስፋ መቁረጥ ይሆናል::

ካምፑ ጭር ሲልብኝ ጊዜ ወደ ዋዩ ከተማ ምሳየን በልቼ ወጣሁ። ከሆለታ እንደ መጣን ሰሞን ብቅ ብዬ ነበር። በተረፈ ዛሬ ገና መዝለቄ ነው። የመንገዱ ግራና ቀኝ እስከ ወንዙ ማዶ ድረስ ቡናና ሻሂ መቱን ገጥሞ፣ በየዛፉ ስር ይፈላል። የሚያፈሉት ደግሞ ኮረዳዎች ናቸው። ቡናውን፣ ሻሂውን ሲቀዱ ባይኖቻቸውም መኮንኖቹን ይቀዳሉ። ጠጣዎቹም ከዚያው ወንዝ ለወንዝ ቂኝ ቂኝ... እያሉ ይንጋጋሉ። ጎደኞች አገኘን ብለው ተደስተዋል። መኮንኖቹም ከበው ይስቃሉ። እየ ጥርስ ሞኙ...

ከከተማው መሀል ስደርስ ደግሞ ሁለቱን የዋርካ ዛፎች ከበ የሰፈረው መኮንን ብዛት ገበያተኛ መስሏል። ነገሩስ ገበያ ነው። የመዝናኛ ገበያ። አረቂው፣ ቡናው፣ ሻሂው፣ ቆሎው... የማይሸጥ ነገር የለም። ከፍተኛውን ገበያ አድርቶ የያዘው አረቂ ነው። በቡድን በቡድን ሆነው ጠርሙስ አረቂ አቅርበው ያን እየለጉ ይጫፍራሉ። ሴቶቹ ደግሞ የማያስቀው ሁሉ ያስቃቸዋል። በሰማይ ላይ የስጋ ቁራጭ እንደ ሚናጠቁ ጭልፊቶች የኛን ገንዘብ ይናጠቃሉ። አንዳንዶቹማ ዳሊያቸውን ሲነቀንቁት በሩቁ ይጣራል። እኛ ደግሞ ፈርደብን የዳሌ ነገር አይሆንልንም። «ጥሬ ስጋና ሴትን ለወታደር ነው» ሲሉ እሰማለሁ። በዚህ አባባል ቅር እሰኛለሁ። ጥብስ መብላት ጠልተን ሳይሆን የመጥበሻ ጊዜ ስለሌለን ጥሬውን ጎራርደን፣ ተጣድፈን በበላን ተተረተብን። ሽረ ስንቱ ነጋዴ በቢና እያወራረደ ሲገሽልጠው አያለሁ።

ሴትም ቢሆን ሚስታችንም ትሁን ወዳጃችን በወቅቱ የማግኘት እድል የለንም። ፍቅርን መጀመር እንጂ መጨረስ አንችልም። ይኸው እኔ ዛሬ እንኳን ዲሞክራሲ አለ እየተባለ በሚለፈፍበት ወቅት ፅጌን ጀመርኳት እንጅ መቼ ጨረስኳት።

እኔም ከዋርካው ስር ቁጭ ብዬ እንደ ሰዉ ሆንኩኝ። ሁለት ስኒ አረቂየን ሳፍኩኝ። ያንዱ ስኒ አረቂ ዋጋ አንድ ብር ነው። «ጨሌ» ይሉታል። ንፁህ አረቂ ለማለት ነው። ከዚያ እያፎጫጩሁ ወደ ካምፕ ተመለስኩ። በቃ ደስታው ይኸው ነው። ባረቂ ሞቅታ የተሸበረ መንፈስን ማደስ።

ወንዝ ለወንዝ ያሉት ሻሂና ቡና አፍሊዎች ከጧቱ አሁን ነው የደመቁት። አረቂውን፣ ጠላውን ሲገፍ የዋለው ከዚህ አረፍ ብሎ ቡናውን፣ ሻሂውን ጠጥቶ፣ ተጫውቶ ወዲያውም የስካር መንፈሱን አብርዶ ወደ ካምፕ ይመለሳል። ባህል አዳራሽ ስደርስ ኮለኔል ዘርጋውን ከዛፍ ስር ቁመው አገኘኋቸው። ትክዝ ብለው ነበር።

"ምነው ጌታየ ብቻዎትን ቁመዋል?" አልኳቸው እጃቸውን ለመጨበጥ ወደሳቸው ስሄድ።

"ባለቤቴ ዛሬ እመጣለሁ ብላ ልካብኝ ስለነበረ እሷን እየጠበኩ ነው። ምላድርግ ብለህ ነው፣ ሚኒዲዶች ያፈኑብኝ እንደሆነ ብዬ ነው" ሲሉኝ ተሳሳቅን።

"ዋዩ ውስህ ነው?" አሉኝ ከሰላምታ በኋላ።

"አዎን፣ እራሴን ላዝናና ብዬ።"

"ደግ አድርገሃል። አንዳንድ ጊዜ ያስፈልጋል። እነ በድሉስ?"

"እነሱ ጧት ነው ወደ ከታ የሄዱት።"

"አንተስ አብረህ አትከትም ኖሯል?"

"መከተቻው እንጅ ችግሩ ጌታዬ።"

"እሱስ ልክ ነህ። በዘመነ ደርግ ባዶህን የቀረህ አንተ ነህ። ሌላውስ ትንሽም ቢሆን ከራሴ ጀምሮ በየምክንያቱ ያልቦጨቀ የለም። ይህም ባይሆን በማእረግ እድገ ጠቀም ያለ ደመወዝ አግኝቶ እነሱም በዛ እራሱን ያላሻሻለ የለም። አንተ ብቻ ነህ ተቀብረህ የቀረህ።"

"አዎን፣ ቀብረው አስቀርተውኛል። የደርግ ካድሬዎች እንደ ጠላት ነበር የሚያዩኝ። ዛሬ ግን እኩል ወድቀናል። ግን ደግሞ ማን ያውቃል! ዘመኑ ጥሩ ከሆነ አንድ ቀን ከነሱ ልቄ እታይ ይሆናል።" አልኳቸው።

"ትልቃለህ እንጅ ምን ጥርጥር አለው። አገር እማን ከሆነ ትምህርትህን መጨረስ ነው። ከዚያ ስራና ደመወዝ ማግኘት ነው። ትልቅ ሰው መሆን ማለት ይህም አይደል? ለመሆኑ ምን አሏችሁ? የዩኒቨርትቲ ተማሪዎች ሲሄዱ ነው እየተባለ የተወራው ወሬ ውሸት መሆኑ ነው?"

"ውሸት ነው ጌታዬ። እነሱ ያሉን ነገር የለም። ሞገዲድ ያስወራው ወሬ ነው። በዋዛ የሚለቁን አይመስለኝም።"

"አንድ ተረት ልንገርህ" አሉኝ ትንሽ ፈገግ ብለው።

"እሺ" አልኳቸው።

"አንድ ሰው አይኑን በጠና ይታመምና ሆስፒታል ይገባልህና 'ኦፕሬሽን' ይሆናል። ከዚያም የሱ አይኖች ከጥቅም ውጭ ስለሆኑ ወጥተው ይወድቁልህና በምትካቸው የድመት አይኖች ይገቡለታል። በሽተኛው ከመጠን በላይ ይደሰትልህና አይን ያስገባለትን ሃኪም:- 'ዶክተር እድሜዎን ያርዝምልኝ። ከጨለማ አላቀው ብርሃን አሳይተውኛልና ከፍ ያድርግዎት' እያለ ይመርቅ ጀመር። ዶክተሩም:-

'አሁን አይኖችህ በደንብ አዩልህ?' ሲል ይጠይቀዋል።

'አዎን እንጅ። ቁልጭ አድርገው ያዩልኛል።'

'እስቲ ምን ምን ይታይሃል?' ብሎ ሲጠይቀው ምን ብሎ መለሰ መሰለህ:-

'ዶክተር መንጋ አይጦች ይታዩኛል' ብሎህ እርፍ" ሲሉኝ ሁላችንም ሳቅን።

"እኛምኮ መንጋ ከብት ሆነው ጌታዬ። ሲነዱን መነዳት፣ ሲያጉሩን መታጎር፣ እንቢተኛነትከ አንዳንድ ጊዜ ያልተገራ ፀባይ ያላቸውን እብሪተኞች ይገራል። ይኸው እነሱ ደርግን ገርተውት የለ እንዴ።"

"የኛን መንጋነትማ ምኑን ታወራዋለህ? እርባ ስምንተኛ ኮርሶች ሲመረቁ የትምህርት ቤቱ አዛዥ ምን እንዳሉ ሰምተሃል?"

"አልሰማሁም።"

"እንግዲያው ልንገርህ፣ የቀድሞውን የሀረር ጦር አካዳሚ ሲንቅቁ ነው 'አስራ አምስትና ሃያ እጩ መኮንኖችን የቀድሞው ባለስልጣኖች ባምስት አመት አስልጥነው ያስመርቁ ነበር። ዛሬ ግን በውድ አብዮታዊ መሪያችን ብልህ አመራር አምስትና ስድስት ሺህ እጩ መኮንኖችን በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለማሰልጠን ተችሏል' በማለት መንግስቱ ሀይለማርያምን አሞግሰውታል።"

"ለዚህ ነዋ እርባ ስምንተኛው ኮርሶች 'ግሪሳ' የተባሉት።"

"ታዲያስ። ስድስት ሺህ አጩ መኪንኖችም አይደሉ እንዴ ባንድ ጊዜ የተመረቁት። ታዲያ እንደ መንጋ ከብት መነዳት ይነሰን እንዴ ጎርፉ? ምግባረ ብልሹስ ብንሆን ይፈረድብናል እንዴ? የቱን የመኪንንነት ስነምግባር ተምረነው ነው? ሽረ ባክህን ተወኝ ጎርፉ" አሉ በስጨት ብለው ወዲያው ደግሞ ቁንዲፍቱ እየተገፊተረ የሚያንገዳግዳቸውን ሁለት መኪንኖች አዩና:-

"እየውልህ፣ ከነዚህ ጋር ነው የታጎርነው! ወይኔ ዘርጋው!" አሉ ጭሰው። እኔም ጨስኩ! ግን ምን እናደርጋለን? ጊዜው እራሱ ሰካራም ነው። ሁሉም ነገር ግልብጥብጥ ያለበት። ወይ መቆየት! ደርግምኮ ተገለበጠ!

በደል ቢበዛብኝ ቢቆረጥ አንጀቴ፣
ሞቴን እመኝ ነበር በየዋህነቴ፣
በመቆየቴ አይደል ይህንን ማየቴ።

ምእራፍ አስራ አንድ

ወሮች እንኪን አውቀው ጎጆ ሲቀልሱ፣
እኛ ብቻ ቀረን ተባልተን እስበሱ።

28

ነሃሴ ወር ከገባ ዋል አደር ብሏል። ሰማዩም፣ መሬቱም ቅልል ብሏል። አረንጓዴው ሳር ገርጥቶ ወደ ቢጫነት መለወጥ ይዟል።

የእንቁራሪቶች ድምፅም ቀነስ እያለ መጥቷል። በነሱ ምትክ ግሪሳ ወፎች ከቧት ጀምረው እንደ ተንጫጩ ነው የሚውሉት። ለጎጆ ስራ እየተጣደፉ ነው። ዛፉ ሁሉ የነሱን ጎጆ ተሸክሟል። እኛ ከምንተኛበት ክፍል ከበሩ አጠገብ አንድ ግራር ዛፍ አለ። ከትመውበታል። ሲነጋ ያን ዛፍ እንጋጥጨ ማየት ይገርሰሁ። በጥንድ በጥንድ ሆነው ጎጆ ስራ ይጣደፋሉ። መክነፍ... መብረር... ከዚያም ሳር ነጭተው ባፋቸው ነክሰው በማምጣት ከግራሩ ቅንዘሎች ላይ እያይዘው መታታት፣ መተብተብ፣ ማጠላለፍ፣ ከዚያም ጎጆ ስርት፣ እንቁላል ጣል፣ ጫጩት ፍልፍል፣ አምሳያን ተክቶ ማለፍ። እኔ ግን አምሳያ የለኝም። ቤትም የለኝም። ከማማ ልኬ ተጠግቼ ነው የምኖረው። አንድ ቀን ያባርሩኛል፤ ያው ዋታች መሆን ነው...

ከትናንት ወዲያ ግን ከረፋዱ ላይ ከፍተኛ ጦርነት ተነስቶ ነበር። ሁላችንም ጉድ ብለናል። መልካቸው ያው አንድ አይነት ግሪሳ ወፎች ናቸው። ጎጇቸውን ምንዝርዝር እያደረጉ አፈራረሱባቸው። እንቁላሎቻቸው ከዛፉ ላይ እየጎተቱ በመውደቅ እንቦጭ እያሉ ፈረጡ። ጫጩቶች ደግሞ ገና ላባ ያልበቀለባቸው እየወደቁ ትንሽ ከተንፈራፈሩ በኋላ ይሞታሉ። ግራ ተጋብቼ:-

"እነዚህ ወፎች ምንካቸው?" አልኩኝ እንጋጥጨ ወደ ዛፉ እያየሁኝ።

"በነሱም ጎሳ ሳይኖር አይቀርም" አለኝ በድሉ እየሳቀ። ወዲያው ሌሎች ወፎች ግርር... ብለው ደረሱ። ለካም ጎጆ አፍራሾቹ ወራሪዎች ኖረዋል። በጥንድ በጥንድ ሆነው ተናነቁ። እፍላፍ እንደ ተናከሱ ከዛፉ ላይ ይወድቃሉ። ደግሞ እይላቀቁም። ሁለቱን እንደ ተናነቁ ያዝኳቸው። ተዳክመው አፋቸው ክፍት ክፍት ይላል። አሳዘኑኝ። ደግመው እንዳይተናነቁ አልኩና በተለያዩ አቅጣጫዎች ለቀኳቸው። ይህን በማድረጌ ደስ አለኝ። ሌሎቹንም "እሽ" ብዬ አባረርኳቸው።

"አንተስ ወፎቹን ገላገልካቸው፤ እኛን ከኢህአዲግ ማን ይገላግለን?" አለኝ በድሉ ከግንቡ ጥግ ተቀምጦ የምሰራውን አትኩሮ እያየ።

"ፕሬዚዳንት ቡሽ ወይንም ኽርማን ኮኽን" ስለው ከልቡ ሳቀ።

"እውነቴን ነው፤ ምን ያስቅሃል? ከንግዲህ ሌላ ተቀናቃኝ ብቅ እስከሚል ድረስ አለምን የምታሽከረክር አሜሪካ ነች። ለታሃድሶም የበቃነው በሷ ችሮታ ሳይሆን ይቀራል?"

ያን አለት ዛፉ ጭር ብሎ ዋለ። የጦርነት ውጤቱ ጭርታ ነው። ገና ዛሬ ነው መልሰው መቋቋም የጀመሩት። እኛ መቼ ይሆን የምንቋቋመው? ምኑን እንቋቋመዋለን፤ ባካልም፣ በመንፈስም ክልውስውስ ብለን። ስነምግባርም ጨርሶ እያጣን ነው።

ቁማር ጨዋታ ከመጠን በላይ ተጠናክሯል። ባንድ ለሊት ውስጥ እስከ አንድ ሺ ብር ድረስ የሚበሉ አሉ። ካዲስ አበባ እስከ አስር ካርታ ድረስ አስመጥተው መደብ በመስራት እያከራዩ በቀን ከሃያ እስከ ሰላሳ ብር የሚያገኙ አሉ። ከካርታው የሚገኘው ገቢ «ጋሞታ» ይባላል። እውነትም ጋሞታ ሆነናል።

የሜዳ ላይ ቁማር ከተጀመረ ወዲህ የተቋሙ እትክልት እንዳልነበረ ሆኖ ወድሟል። የሙዝ ተክሎች እየተዘነጠፉ ለድልዳል ውለዋል። ለውበት መስመር ይዘው የተተከሉት ጥርብ ድንጋዮች እየተፈነቀሉ መቀመጫ ሆነዋል። ከድንጋዮቹ ላይ ድንጋዮች ተቀምጠው መቆመር ነው። ኢህአዲግም እየቆመረን ነው። ይህ ሁሉ ውድመት ሲደርስ እየተደ አይሉም። እንደ እውነቱ ከሆነ የግቢን ድልድይ ለማፍረስ ብንዘጋጅ ቀድመው መደሻ በመያዝ ይሰለፋሉ። አሰራራቸው ሁሉ ከቶ ሊገባን አልቻለም፤ ማፍረስ ብቻ... መናድ ... መበተን ... በቃ ይኸው ነው ተግባራቸው።

እኔ አንዳንድ ጊዜ ድርጊታቸው ሁሉ ግራ እያጋባኝ ስለነሱ ተጠግቼ ለማጥናት ሞሬአለሁ። አብዛኞቹ በድሜ ለጋ ከመሆናቸው የተነሳ ያመራር ብቃት የላቸውም። የትምህርት ደረጃቸው አይነሳ። ከስብት እረኛ እስከ ገበሬዎች ነው የተሰለፉት። እነዚህ ህዝብን መምራት ቢችግሩም አይፈረድባቸውም። ዋናውን ችግር የሚፈጥሩት ግን እንደነዚህ ያሉት አይደሉም። ትንሽ ፊደል ቆጠርን የሚሉት ናቸው። ጨርሶ ከተከዜ ወዲህ ያለው አገርና ህዝብ ጠላት እንጂ ወገን መስሎ አይታያቸውም። ሁሉን ነገር ከደርግ ጋር ያመሳስሉታል። ለዚህም ነው ለባንዲራ ደንታ የሌላቸው። ለመንግስት ገንዘብ ቁብ የላቸውም፤ ለህዝብ ሀብት አይጨነቁም። ከቻሉ ይዘርፋሉ፤ ካልቻሉ ደግሞ ያወድማሉ።

ታዲያ አንዱ ተስፋ የሚያስቆርጠን ይኸ አይነት ተግባራቸው ነው:: የመኮንኖቹ ቁማር እየደራ መምጣት መንስኤው ተስፋ መቁረጥ ሳይሆን ይቀራል:: ጨርሶ የመለቀቅ ነገር የለም::

ሽፈዲድና ሞገዲድ ሰሞኑን እንዳናፌሱት ከሆነ አንድ ተባዝቶ የመጣ ፎርም አለ:: ምናልባት እሱን ከሞላን በኋላ እንለቀቅ እንደ ሆነ አላውቅም:: ኧረ እውነት ሆኖ በተገላገልን:: እንዳመላችን ቤታችን በቻለን:: ግን ምን ቤት አለን? ያብዛኞቻችን ቤት የቀበሮ ጉድጓድ ነበር:: እሱንም ተነጥቀናል:: ለነገሩ ዛሬም ቢሆን ጉድጓድ ውስጥ ነው ያለነው:: ኧረ መቼ ይሆን ደግሞ ከዚህ ጉድጓድ የምንወጣው?

29

ያባት የናታችን ስም ሞልተን ጨረስን፣
የኛ ስም ብቻ ነው የጎደለብን::

ወሮቹ በየዛፉ ላይ ይንጫጫሉ:: እንቁራሪቶቹ ግን ፀጥ ብለዋል:: ኩሬዎቹ መምጠጥ ስለያዙ ነው:: አንዳንድ ጊዜ በሳሩ ውስጥ እንጡጥ እንጡጥ ሲሉ እናያቸዋለን:: ዘለው ዘለው የት ይደርሱ ይሆን? አንድ ተረት አለኩ:-

"እንቁራሪት የት ትሄጃለሽ?"

"መተማ::"

"እንደዚህ ብለሽ?"

"ልብማ::"

"እየ የመተማ ጉዞ! እውነትም ልብማ! እስቲ እንጡጥ... እንጡጥ... በይ!"

አክሱም ጊዮን ምን ታርግ አሷን የምንወቅሳት፣
መልአኩ እሱ ነው ጎንደርን የፈታት::
ይህን ብሶታችን አጥተን ተመልካች፣
ወንዶቹ ቁጭ ብለን ሴቲቱ ሄደች:

ዛሬ ቅፁን የምንሞላበት እለት ነው:: ካንዳንዶች በስተቀር ያብዛኛው መኮንን ፊት ፈታ ያለ ነው:: ዘግየት ብዬ ነበር እኔ ወዳዳራሹ የገባሁት:: ውስጡ ጢም ብሎ ሞልቶ ዙሪያውን በመስኮት በኩል አገርግሮ የቆመው መኮንን በማገር ያልተያዘ ግድግዳ ይመስላል:: ሲጋራ ከያቅጣጫው ይስተጎለላል:: ነጭ ሸንኩርት አልሸተተኝም:: ባፍንጫው የወተፈም አላየሁም:: አሁን ደግሞ ለወባ መድሃኒት ነው የተባለው አረቄ ነው:: መቀመጫ ስላጣሁ ከወደ በሩ በኩል አገርግረው ከቆሙት ጋር ቆምኩ::

ታጋይ ሀጎስ መጥቶ ከፊት ለፊታችን ሲቀመጥ አዳራሹ መጠነኛ ፀጥታ ሰፈነበት:: ከሱ በስተግራ በኩል ከኛው ውስጥ

ለመዝጋቢነት የተመረጡ አምስት መኮንኖች ብእርና ቅፁን አስተካክለው ተቀምጠዋል:: ቅፁን አግድሜ አየሁት፣ እንሰላ ያክላል::

ሀጎስ ከተቀመጠበት ተነስቶ እንዴት መሙላት እንዳለብን ካብራራልን በኋላ ተቀመጠ:: ወዲያው መዝጋቢዎቹን ከበቧቸው:: "እኔን መዝግበኝ፣ እኔን አስቀድመኝ" ትንቅንቅ ሆነ:: ሲጋፉ ደግሞ ከፀሀፊዎቹ ላይ ወደቁባቸው:: የጠፈ ጫጫታ ተፈጠረ:: ሀጎስ ተፈናጥሮ በመነሳት ትን እስከሚለን ነገረን:-

"ዋእ! የት ለመድረስ ነው?! እየ የደርግ መኮንኖች!" ሲለን አበዛኞቻችን እርር አልን::

"እውነቱን ነው! የት ለመድረስ ነው? እየተሰገበገቡ የሚያሰድቡን?" አልኩት ካጠገቤ የቆመውን መኮንን::

"በመጀመሪያ የተመዘገበ ለማግባባት ሲባል ጥያቄ አይበዛበትም ስለተባለ ነው" አለኝ::

"ማነው ይህን ያለው?"

"ሽፈዲዶች" አለኝ ፈገግ ብሎ::

"ሀይ! ሽፈዳ ሁሉ!" አልኩኝ በሽቄ::

ምዝገባው ቁሞ የሰላምና የመረጋጋት ኮሚቴዎችን ከመረጥን በኋላ ስማችን እየተጠራ ቅፁን እንድንሞላ ወስነን ስራው ተጀመረ:: በወሰነው መሰረት አምስት መኮንኖች ቅፁን ከሞሉ በኋላ በረድፍ ከኛ ፊትለፊት ቆሙ:: ከዚያም ሀጎስ የሞሉትን ለኛ በንባብ አሰማን:: ከቤቱ ጥያቄ ስላልቀረበባቸው ፈርመው ተቀመጡ:: ሌሎች አምስት መኮንኖች ተተኩ:: እንግዲህ አሰራሩ በመጀመሪያ ቅፁን መሙላት ነው፤ ቀጥለው ተራ በተራ ወደ ሀጎስ ይቀርባሉ:: አንዳንድ ጥያቄዎችንም ይጠይቃቸዋል:: ከቤቱ ጥያቄ ወይንም ተቃውሞ የቀረበባቸው መኮንኖች ቁመው ሲንቀጠቀጡ መዋላቸው ነው:: በዚህ መልኩ እስከ አስራ ሁለት ሰአት ድረስ አስራ ሁለት መኮንኖች ብቻ ቅፁን ሞሉ:: ብዙ ችግሮች ተከስተው ነበር::

ካዳራሹ ከመልቀቃችን በፊት ሀጎስ ስለቅፅ አሞላሉ አስተያየት ስለጠየቀን አንዳንድ መሻሻል የሚገባቸውን ነገሮች ጠቆምነው:: ከነዚህ ውስጥ አንደኛው የፀሀፊዎቹ ቁጥር ወደ አስር ከፍ እንዲል፤ ሁለተኛ ዝርዝር የህይወት ታሪክን መጠየቁ ጊዜ ከማባከን በስተቀር ጥቅም ስለሌለው ዋና ዋናዎቹን ብቻ መጠየቅ እንደሚገባው አሳሰብነው:: እሱም በቀረበው ሀሳብ ቅር ሳይሰኝ ተስማማ::

ዋና ዋና ጥያቄዎች የተባሉት ወይንም በመኮንኖቹ አጠራር ስምንቱ ወርቃማ ጥያቄዎች የሚባሉት:-

1ኛ. በዘመነ ደርግ የስራ ሀላፊነት፣
2ኛ. ቤት አለህ የለህም?
3ኛ. ባንክ ገንዘብ አለህ የለህም?
4ኛ. ኢሰፓ ወይንም የደህንነት አባል ነህ?
5ኛ. የደመወዝ መጠን::
6ኛ. ልዩ ሙያ::
7ኛ. ልዩ የገቢ ምንጭ::
8ኛ. የቤተሰብ ብዛት ናቸው::

ከዚህ ውጭ ያሉት ጥያቄዎች ይህን ያህል ዋጋ የላቸውም:: "የት ተወለድክ፣ ያገልግሎት ዘመን፣ ብሄረሰብ፣ የትምህርት ደረጃ..." የሚሉ ናቸው:: በዚሁ የዛሬው ቅፅ መሙላት ተጠናቀቀ::

30

ወፎቹ ሲከንፉ እኔም እከንፋለሁ፣
እነሱ ዛፍ ሲያርፉ እኔ የት አርፋለሁ::

ጧትም ሆነ ቀን ከምተኛበት ክፍል ብቅ ባልኩ ቁጥር አንጋጥጬ ያን ዘርፋፋ ግራር ነው የምመለከተው:: የወፎቹን እንቅስቃሴ ለማየት:: ነግቶ እስከ ማመሽ ድረስ እረፍት የላቸውም:: መክነፍ ነው:: ጎጇቸውን ችምችም አድርገው ሰርተው ከጫሪሱ ሰንብተዋል:: የግራሩ ቀንዘሎች በሙሉ የወፍ ጎጆዎች ተሰርቶባቸዋል:: ነፋስ ሲነፍስ፣ የግራሩ ዛፍ ሲወዛወዝ የወፎቹ ጎጆዎችም አብረው ይወዛወዛሉ:: እኛም እየተወዛወዝን ነው::

ቅፁን በመሙላት ላይ ነን:: ሁለተኛ ሳምንታችንን ይዘናል:: ይህ ቅፅ መሙላት እውነትም በመጀመሪያዎቹ ቀናት ረገብ ያለና የቀዘቀዘ ነበር:: መፈራራትም፣ ምን እገባኝም ነበረበት:: አሁንማ ካንዱ ሻለቃ ወደ ሌላው ሻለቃ የመወያያ አዳራሽ የሚሬወጡ እሳት የላሱ አጋላጮች ፈልተዋል:: ኢህአዲግ የዋዛ አይደለም:: እንኳን ቅሳት ገና እናትና ልጅን ያስተናንቃል:: ቀስቅሶ እኛኑ በኛው አስተናንቆን ቁጭ አለ:: ዛሬ እነሀጎስ ባንድ በኩል ብር በጆንያ ያጭቃሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ ነፃ ትርኢት ያያሉ:: በጥይት ቢገሉን እንኳን እንደዚህ አይረኩም:: እስከ ወዲያኛው መተረቻና መሳቂያ ሆነነው ቁጭ አልን::

ከሆለታ ጀምረን እያንዳንዱ ደመወዝ ከፋይና ገንዘብ ቤት ትንሹ ሰማኒያ ሺ፣ ትልቁ ሶስት ሙቶና አራት መቶ ሺ አስገብቷል:: ግማሽ ሚሊዮን ሳይቀር ያስገቡ አሉ:: ይኸ ሁሉ እንግዲህ ከቸክ ሌላ በጥሬ ገንዘብ ነው:: የሚገርመው ግን ይኸ ሁሉ ገንዘብ ሲገባ ያለ ህጋዊ ደረሰኝ መሆኑ ነው:: አንዳንዶች «ታጋይ እከሌ» የምትል ፊርማ ያለባት ብጣሽ ወረቀት ይዘዋል:: አንዳንዶቹ ግን ባዷቸውን ቀርተዋል:: ደግነቱ ዳግመኛ የሚጠይቃቸው ያለ አይመስለኝም:: ቁምነገሩ ብሩን ማስረከባቸው ነው:: ተረካቢዎቹ ታጋዮች ደግሞ መቶ ብር እንኳን ቆጥረው የሚያውቁ አይመስሉም:: በሰምሶናይት እንደ ታጨቀ ወስዶ ሲዘረግፍላቸው "ዋእ!" በማለት ከው ብለው ይደነግጣሉ:: እየቆዩ ግን ስሙኒም እታሙልጠን አሉ:: ዛሬ ካይናቸው ላይ ገንዘብ በቅሎ ተንሰፍስፈው ሲሞቱ ነው::

'ታዲያ ይኸ ሁሉ ብር ወዴት ነው የሚገባው?' መቼም ወደ መንግስት ካዝና አልገባም:: ወደ ላይ ነው የተጋዘው::

ከስምንቱ ወርቃማ ጥያቄዎች መካከል «ቤትና ሌላ የገቢ ምንጭ» ከሚሉት ውስጥ እየተመዘዙ የሚወጡ ምስጢሮች እጅግ አስገራሚዎች ናቸው:: ባለጉዳዮቹ ሽምጥጥ ቢያደርጉም የውስጥ አዋቂዎች እየጎለጎሉ ያወጧቸዋል:: በሚስታቸው ስም ቡና ቤት

የከፈቱ፣ መኪና የገዙ፣ ኬክ ቤት የከፈቱ፣ ታክሲ የገዙ... ሁሉ ተጋልጠዋል:: አንድ አዛውንት ሻለቃ ቤትና መኪና እያላቸው «ምንም ነገር የለኝም» ብለው ቅፁን ይሞላሉ:: በኋላ ምስጢር አዋቂ ከሌላ ሻለቃ ይመጣና ጣቱን ይቀስርባቸዋል:: ሀጎስ ሆየ ከፊታችን ይገትራቸውና:-

"ለምንድን ነው ምስኪን መስለው በቅፁ ላይ 'ምንም ነገር የለኝም' ብለው የሞሉት? ይላቸዋል::

"አሁንም ቢሆን ምስኪን ነኝ" ብለው መለሱ::

"እሽ፣ ምስኪንነትዎትን ይተውትና፣ ቤትና መኪና አለዎት የለዎትም?" ሲል ከረር ብሎ ጠየቃቸው::

"በርግጥም ምርት የተላጠ አሮጌ ቤት አለኝ::"

"ታዲያ በቅፁ ላይ 'ምርት የተላጠ ቤት' ብለው አይሞሉም ነበር?" ሲላቸው እኛ እውክተን ሳቅን:: እሳቸው ግን ላብ በግንባራቸው እየተንቆረቆረ እስር ጊዜ በመሃረባቸው ይጠርጉ ነበር::

"እስቲ ደግሞ ስለመኪናዋ ጉዳይ ያብራሩልን" አላቸው::

"መኪናዋ የባለቤቴ ስለሆነች ነው በቅፁ ላይ ያልሞላኋት:: ደግሞ አሮጌ ቮልስዋገን ናት:: ለልጆች ትምህርት ቤት ማድረሻ ብላ የገዛቻት" አሉ:: ሀጎስ በዚህ ጊዜ የሞሉትን ቅፅ ገልበጥ አድርጎ አየና:-

"ባለቤትዎት የቤት እመቤት እንደ ሆኑ ነው በቅፁ ላይ የሞሉት:: ታዲያ ገንዘብ ከየት አግኝተው ነው አሮጌዋን ቮልስዋጎን የገዟት?"

"እ... ቀደም ሲል እኛ ከመንግስት ቤት እየኖርን ቤታችንን ላንድ የውጭ ዜጋ ሶስት መቶ ብር በወር አከራይተን ያን በማጠራቀም ነበር የገዛቻት" አሉ::

"ምርት የተላጠው ቤት ነው ወይንስ ሌላ?"

"ምርቱ አሁን በቅርቡ ነው የተላጠው::"

"ኢህአዲግ ሲገባ ነው የተላጠው? ይበሉ ይቀመጡ" አላቸው በንቀት እስተያየት እያያቸው:: ሹክክ ብለው ተቀመጡ:: አንድ መቶ አለቃ ደግሞ ተራ ይደርሰውና ለጥያቄ ይቀርባል::

"ቤት አለህ ወይ?" ሲል ሀጎስ ጥያቄውን ያቀርባል::

"አዎን"ይልና ይመልሳል::

"ስንት አሰራኸው?"

"በነፃ" አለና ኮራ ብሎ መለሰ::

"እንዴት በነፃ ትለኛለህ? በገንዘብ አሰርተኸው ከሆነ በገንዘቤ ነው በልና መልስልኝ" አለ ሀጎስ ቆጣ ብሎ::

"አምስት ሳንቲም አላወጣሁበትም:: የኔ ቤት ናቅፋ ምሽግ ነው:: አስራ ሰባት አመት የኖርኩበት:: ዛሬ ኢህአዲግ ምትክ ቤት ሊሰጠኝ ይገባል" ሲል እኛ በሳቅ ፈነዳን::

"ዋእ! ታሾፍብኛለህ እንዴ?!" አለ ሀጎስ ከተቀመጠበት በቁጣ እየተነሳ:: እኛ በመሳቃችንም በሽቆበታል::

"እኔ አላሾፍኩብህም! ሀቁን ነው የምነግርህ!" አለው እሱም ተቆጥቶ::

"ቁጭ በል!" አለውና እሱም በመቀመጥ ሲጋራ አቀጣጥሎ አከታትሎ ቡልቅ ቡልቅ አደረገና ትንሽ ከንዴቱ በረድ ሲል እያጨሰ መጠየቅ ያዘ:: እንደ ሙቶ አለቃ ደግሞ ተጠርቶ ከፊቱ ሲቆም:-

"ሙያህ ምንድን ነው?" አለው::

"አየር መቃወሚያ" ሲል መለሰ::

"ስንት አይሮፕላን ጣልክ?" ሲለው::

"እናንተ አይሮፕላን የላችሁማ" ሲለው እኛ ሳቅን:: አሁንስ ሀጎስም ሳቀ:: ሲግል እንደ ብረት ምጣድ ነው:: ሲበርድ ደግሞ የገለባ ፍም ነው::

አንድ ሻምበል ደግሞ ለጥያቄ ቀርቦ "ባንክ ያለዎት ገንዘብ?" ብሎ ሲጠይቀው::

"ሶስት ብር ከ60 ሳንቲም" ይልና ይመልሳል::

"ይኸ ባንክ ገንዘብ እንዳለዎት አይቆጠርም" ሲለው::

"ካልክስ ይኸም ያደራ እንጅ የኔ አይደለም" ሲለው:-

ሀጎስ ብው ብሎ:-

"ሆን ብላችሁ እኔን ለማብሸቅ ነው እንዴ!" አለና ከተቀመጠበት ተወራጨ:: ወዲያው ደግሞ ሲጋራ ለኮሰ:: ለትንሽ ጊዜም በመቆጣቱ የተነሳ ቅፅ መሙላቱ ቀሞ ነበር:: ከሲጋራው ጋር ቁጣውም አብሮ ስላለቀ የቅፅ መሙላቱ ተግባር ቀጠለ:: አንድ ሻምበል ነበር ለጥያቄ የቀረበው:: ወዲያው ከሀጎስ ቀድመው ሁለት መኮንኖች በመነሳት:-

"ሽሬ ላይ ጦሩ ሲደመሰስ ግማሽ ሚሊዮን ብር ይዞ ወሎ በመግባት በልቶት ቀርቷልና ይጠየቅልን" አሉት:: ሻምበሉ ደንግጦ ዝም ብሎ ቆመ::

"ይመልሱ እንጅ" አለው ተቆጥቶ::

"ግማሽ ሚሊዮን ብር ለግል ጥቅሜ ባውል ኖሮ ልጆቼና ባለቤቴ ዛሬ ከመቀሌ መጥተው ጃንሜዳ ከስደተኞች ጋር ባልተቀመጡ ነበር" አለ እንደ እንባ እየተናነቀው::

"እውነት ሚስትዎትና ልጆችዎት ዛሬ ጃንሜዳ አሉ? በስልክ እናረጋግጥ?" በማለት ሲያፋጥጠው:-

"ዛሬስ ወጥተዋል" አለ ቀዝቀዝ ብሎ::

"መልካም ፤ዛሬ የት ነው ያሉት?"

"ከባለቤቴ እናት ቤት::"

"የባለቤትዎት እናት ስራቸው ምንድን ነው?"

"ሆቴል አላቸው"

"ማን ገዛላቸው?"

"እራሳቸው::"

"ገንዘብ ከየት አግኝተው?" ሲለው አንገቱን ደፍቶ ዝም አለው::

"ይብሉ ይቀጥሉ" ካለው በኋላ "እኒህ ሻምበል ምስኪን መስለው ከናንተ ፊት ለመታየት ቢሞክሩም እኛ ግን አጣርተን የያዝነው ጉድ አለ:: አሁን ጥያቄው ከተነሳ ብዬ ጠየኳቸው እንጅ የሚጠየቁበት ጊዜ ገና ነው:: መኪኑ በሚስታቸው ስም አንዲት ዳትስን መኪና የገዙ ሲሆን በሚስታቸው እናት ስም ደግሞ አንድ ሆቴል ገዝተዋል:: ግማሽ ሚሊዮን ብር ብቻ ሳይሆን ካንድ ሚሊዮን ብር በላይ ለመብላታቸው

ጥርጥር የለውም" በማለት ሀጎስ ሲተነትንልን ሻምበሉ በሁለቱ እጆቹ እራሱን ይዞ ተነሳ:: ሀሰት ነው ለማለት::

"ይቀመጡ! በሚጠየቁበት ጊዜ መልስ ይሰጣሉ" ብሎ አስቀመጠው:: ቀይ ስለሆነ ፊቱ ባንድ ጊዜ ሳንባ መሰለ::

እንግዲህ ይህ ቅፅ መሙላት ይኸ ሁሉ ጉድ የተፍረጠረጠበት፤ የኛም ማንነት ቁልጭ ብሎ የወጣበት ነው:: ከሽንፈታች የበለጠ ይኸ እስበሳችን መዘራጠጣችን የበለጠ አሳፋሪ ሆኘ:: ዘራፊውን ዘራፊ ሲያጋልጠው እኛ አፋችንን ከፍተን መመልከት ነው:: ባንድ ሰው ጉዳይ ብቻ ተገትረን የምንውልበት ቀን አለ:: ያንዳንዶቹማ ስራ ጭራሽ ለማመን ያዳግታል::

ደርግና ስርአቱስ እንኳንም ሞቱ!

31

አንግተን አንግተን ከቀን ባደረስን፤
በድላችኋልና ካሸናችሁ ተባልን::

ከሶስት ቀናት በፊት ነበር ቅፁን ሞልተን የጨረስንነው:: ታዲያማ በቅፅ መሙላቱ ወቅት በምዝበራ የተጋለጡት መኮንኖች በትናንትናው እለት ከሁለቱም ክፍለ ጦሮች ተጋፊው እስር ቤት ታጎሩ:: ሁኔታዎች ሁሉ ክብድ እያሉ መጥተዋል:: አብዛኛው መኮንን ተደናግጧል:: አንዳንዶች እንደ ከብት እረኛ መኮብለል ጀምረዋል:: ደግሞኮ ቢያመልጡ ደህና ነበር:: መያዛቸው የበለጠ መሳቂያ አደረገን እንጅ:: ከትናንት ወዲያ ግቤ ላይ አራት ሻለቆች ተይዘው መጡ:: ባለፈው ሳምንት ደግሞ በሲሙ በኩል ሊያመልጡ ሲሉ ገበሬ ይዞ አስራ አንድ መኮንኖችን አምጥቶ አስረክቧል:: እኛው በኛ እየሳቅን አለነው::

ዛሬ የተሰበሰብነው ባህል አዳራሽ ነው:: ከሁለቱም ክፍለ ጦሮች ተወጣጥተን ወደ ሁለት ሺ እንጠጋለን:: ካዲስ አበባ የተሃድሶ ኮሚሽኑ ተወካይ ሊያነጋግሯችሁ ነው ተብለን ነው::

የኮሚሽኑ ተወካይና የተሃድሶ ማእከል ሀላፊ በጥቂት ታጋዮች ታጅበው በጀርባ በር በመግባት ከፊት ለፊታችን ተቀመጡ:: ጠየም ያሉ ናቸው::

የማእከሉ ሀላፊ መነፅራቸውን አስተካክሉና ሰላምታ ክሰጡን በኋላ "የኮሚሽኑ ተወካይ ስለተሃድሶው አላማና ተግባር ማብራሪያ ይሰጧችኋልና በጥሞና አዳምጧቸው" ብለው ንግግራቸውን ቋጭተው መድረኩን ለንግዳው ለቀቁላቸው::

እንግዳው በመጀመሪያ የደርግን ፀረ ዲሞክራሲነት ካወገዙ በኋላ "...ይህ መኮንን የዚህ ፀረ ሰላም አራማጅ ፋሽስት መንግስት ዋነኛ መሳሪያ ነበር:: በመሆኑም ይህ ደርጋዊ እመለካከቱ ጨርሶ እንዲፋቅ ለማድረግ መኮንኑን ተሃድሶ ማእከል ማስገባት አስፈላጊ በመሆኑ ጣላይ ማእከል ውስጥ ባሁኑ ወቅት ትገኛላችሁ:: የናንተ ጥረት ከታከለበት በኛ በኩል ማንኛውንም ነገር አጠናቀን ጨርሰናል:: በቅርብ ቀን ትምህርቱን

ትጀምራላችሁ:: ህንፀቱን እንደ ጨረሳችሁም ወደ ህብረተሰቡ ትቀላቀላላችሁ" በማለት ንግግራቸውን ጨረሱ:: ወዲያው ለጥያቄ ብዙ መኮንኖች እጃቸውን አወጡ::

"ለመሆኑ ከኛ ምንድን ነው የምትፈልጉት? ለሰስት ቀናት ብላችሁ አምጥታችሁ ይኸውና አራተኛ ወራችንን ይዘናል:: ዛሬ ደግሞ 'ጥቂት ቀናት' የምትሉን ጥቂት አመታት ልታስቀምጡን ነው? ለምን ያህል ጊዜ እንደምታቆዩን ቁርጥ አድርጋችሁ ንገሩን:: ስለመብታችን ጉዳይም ማወቅ እንፈልጋለን!" ብሎ ተቀመጠ:: ሀሳቡን ደግፈን አዳራሹ እስከ ሚነቃነቅ አጨበጨብን:: እንደ መገንፈልም ብለን ነበር:: ሌላ መኮንን ከተቀመጠበት ተነሳና:-

"እኔ ተጨማሪ አድርጌ የማቀርበው ጥያቄ ለመብታችንም አጠባበቅ ሆነ ከዚህ ያለአግባብ ተግዘን ለሚፈፀምብን በደል የውጭ ተመልካች ነጮቹ ይምጡልን!" አለና በቁጣ ተወራጭቶ ተቀመጠ::

"ሽም!" አሉ የኮሚሽኑ ተወካይ ተቆጥተው:: "ፈረንጅ መስሎኝ ሲያፋጀን የኖረው:: መስኮብኮ አመድ የመሰለ ነጭ ነው" ሲሉ ቢጨንቀን ሳቅን:: ንግግራቸውን ቀጠሉ:: "ዛሬ ደግሞ የትኛውን ፈረንጅ እንጥራላችሁ?" እያሽሟጠጡ ልክ ልካችንን ነገሩን::እስተካክሎ አይደል የሰጣቸው! የልባቸውን ተወጡ:: "ይልቅ በመጀመሪያ 'ከኛ ምንድን ነው የምትፈልጉት?' ብለህ ለጠየከኝ ብዙ የምንፈልጋቸው ነገሮች ይኖራሉ:: እንደኛ መታነፃችሁን በጅጉ የምንፈልገው ነው:: ህንፀት ደግሞ በሂደት እንጅ በሀያ አራት ሰአት የሚከናወን አይደለም:: ዋናውና መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ግን ከናንተ መካከል አሁንም ቢሆን ገና ተመንጥሮው መውጣት ያለባቸው ዘራፊዎችና ነፍሰ ገዳዮች አድፍጠው እንዳሉ ናቸው:: እነሱን በማጋለጡ በኩል እርብርብ ማድረግ አለባችሁ:: በይሉኝታ መታፈን የለባችሁም ::

"ሌላው ጥያቄህ 'ለምን ያህል ጊዜ እንደምንቆይ' የሚል ነው:: በእውነቱ ይህን እኔም ብሆን አላውቀውም:: ነገር ግን የናንተ ሙሉ ትብብር ከታከለበት እርግጠኛ ነኝ በጣም አጭር ጊዜ ብትቆዩ ነው:: በሶስተኛ ደረጃ የጠየከው ስለመብት ጉዳይ ነው:: የመብትን ጉዳይ በሶስት ደረጃ ከፍሎ ማየት ይቻላል:-

1ኛ. የጡረታ ደብተር ያላቸው ወይንም ዳግም ዘማቾች በዚህ ሳምንት ውስጥ ትመለሳላችሁ:: መብታችሁም እንደተጠበቀ ነው::

2ኛ. የድሚ ጣራችሁ አምሳ አመት የሞላችሁ የጡረታ ቅፅ የመጣ ስለሆነ ቅፁን ትሞላላችሁ:: ስለመብታችሁ ግን የተሃድሶ ኮሚሽኑ የሚያውቀው ነገር የለም:: ምናልባት የጡረታ ኮሚሽን የሚፈታው ይሆናል::

3ኛ. በዚህ ክልል ውስጥ የምትገኙ መኮንኖችን (አብዛኞቻችሁ ማለት ይቻላል::) እንደ ገና በሶስት ከፍሎ ማየት ነው:-

ሀ/ በግል ለሚስተዳደሩ መንግስት አስፈላጊውን ድጎማ ያደርግላቸዋል:: ግብርናም ሆነ ንግድ እንዲሰማሩ ይደረጋል::

ለ/ ምንም አይነት መተዳደሪያ ለሌላቸው መንግስት መጠነኛ ስልጠና እየሰጠ እንዳስፈላጊነቱ ክፍት የስራ ቦታ ሲያገኝ እያወዳደረ ስራ ለማስያዝ ይሞክራል::

ሐ/ ያካል ጉዳት የደረሰባቸው ቦርድ እንዲወጡ ይደረጋል:: በሀኪም ውሳኔም ጡረታ ማግኘት የሚገባቸው ወደፊት እንደ ሁኔታው ተጠንቶ እንዲያገኙ ይደረጋል:: ከዚህ ውጭ ግን የሚወሰድ እርምጃ የለም" በማለት ማብራሪያቸውን ጨረሱ:: እኛ ጭጭ አልን:: ለካ የሚያወራጨን ተስፋ ኖሯል:: አሁን ግን ተስፋችን በመሟጠጡ ፀጥ አልን:: ፀጥታችን ግን ጤነኛ አልነበረም:: "ሌላ ጥያቄ ካለ?" አሉ ትንሽ ከተፋጠጥን በኋላ:: እኛ ግን ትንፍሽ አላልንም:: ቁጭ እንዳሉ ጥለናቸው ወጣን::

ከነገ ጀምረን ደግሞ "ግለ ሂስ" እንደ ምናካሂድ ቅፁን ሞልተን የጨረስን እለት ነግረውናል:: እረ ጉዳችን ገና ነው::

ምእራፍ፡ አስራ ሁለት

መቆየት መልካም ነው እየሁ ብዙ ነገር፣
ጠያቂ ሲጠይቅ አሳሪው ሲታሰር::
ያ ሁሉ ድንፋታ ያ ሁሉ እብሪት ሲቀር፣
ቁርኝ ሳይደረግ ሳያርፍበት ጨንገር፣
የቆጡን የባጡን ይቀባጥር ጀመር::
ለካ እንደዚህ ኖሯል «አብዮታዊ» ጦር?

32

ሰማዩ ጭው ብሎ ጉም የሚባል ነገር የለም:: መሬቱም መደራረቅ ይዟል:: በጣላይ ማእከል ግራና ቀኝ የሚፈሱት ወንዞች ደክም እያሉ መጥተዋል:: እያደር የማይደክመውና እየተሟሟቀ ያለው ንግድና ቁማር ጨዋታ ነው::

ሌላው እስከዛሬ እያየኋቸው ነገር ግን ያላጤንኳቸው ወደ ሰላሳ የሚጠጉ ጥጆች ናቸው:: በማእከሉ ውስጥ አንዷ ጥጃ በሄደችበት ሌሎቹ እየተከተሉ ከኛው ጋር ይጋፋሉ:: ቀደም ሲል የማስልጠኛ ማእከሉ ነበሩ:: እናቶቻቸው ስለታረዱባቸው ዛሬ እናት አልባ ናቸው:: እኛም፣ እነሱም እኩል ነን:: እኛም ከዋኝ የለን፣ እነሱም ከዋኝ የላቸውም:: ቀተር ሲል ደግሞ ዝንቡና ትንኙ ያሯሩጣቸዋል:: ፍዳ ነው የሚያሳያቸው:: እኛንም ኢህአዲግ "እመኑ" እያለ ፍዳችንን እያሳየን ነው:: ብናምንም አላመነን:: ዛሬ ደግሞ ግለ ሂሱን የምንጀምርበት እለት ነው::

ቀደም ብዬ ነበር በመስኮት በኩል ወንበር የያዝኩት:: ከጎኔ በድሉ ጫኔ ተቀምጧል:: ስማችን ተጠርቶ እንዳበቃ ሀጎስ ጠረጴዛውን መታ መታ አድርጎ ፀጥ ካሰኘን በኋላ በግለ ሂሱ ላይ በቅድሚያ ሀሳብ ወይንም አስተያየት እንድንሰጥበት ጋበዘን:: በዚህ መሰረት ስላብዮታዊ መሪያችን ፋሽስትነት፣ ስለስርአቱ አረመኔነት... እየተነሳ በተለያዩ መኮንኖች ውግዘት ወረደ:: እነ መላኩ ተፈራ፣ እነ አሊ ሙሳ፣ እነ ለገሰ

አስፋው... እየተጠቀሱ ተረግመዋል:: በመጨረሻም በምዝበራም ሆነ በቀይ ሽብር ተዋንያን የነበሩ መኮንኖች ግለ ሂስ ማውረድ እንደ ሚገባቸው ከተብራራ በኋላ ሀጎስ:-

"እንግዲህ ስለ አላማው ይህን ያህል ከተነጋገርንና ለቤቱ ግልፅ ከሆነ በቀጥታ ወደ ግለ ሂሱ እንገባለን" አለና ሲጋራ አቀጣጥሎ ሳብ እያደረገ የሂስ አውራጅ እጅ ለማየት አይኖቹን በዝግታ ከወዲያ ወዲህ እያዘዋወረ ያይ ጀመር:: አዳራሹ ግን ፀጥታ ሰፍኖበታል:: እስበስ መተያየት ሆነ:: እንደ ቅፅ መሙላቱ ሽሚያ አልተገጠመም::

"እንዴት ነው ዝም አላችሁሳ? ግለ ሂስ የሚያወርድ የለም ማለት ነው?" አለ ሃጎስ ፈገግ ብሎ:: ማንም መልስ አልሰጠም:: ዝምታ ነግሷል:: ቢጨንቀኝ እኔ እጄን አወጣሁ::

"እንዴ! ምን ልትሆን ነው?" አለኝ በድሉ::

"እሽ ሙቶ አለቃ ጎርፉ" አለኝ፤ ሀጎስ የያንዳንዳችንን ስም ለመያዝ ሞክሯል::

"እንዴት ነው ጎበዝ? የማይቀርልን ከሆነና በመሰረተ ሀሳቡ ከተስማማን ጊዜ ባናባክን ጥሩ ነው:: ምነው ዕዋው በኛ ሲደርስ ከበደን? ባንድ ወቅትስ የነፍስ አባት ሆነን ኢህአፓዎችን እናዘን ነበር:: የምንለው ካለ ማለት ነው" ብዬ ስቀመጥ:-

"ኢህአዲግን ደግሞ ማን ያናዝዘው ይሆን?" አለኝ በድሉ ወደ ጆሮየ ጠጋ ብሎ::

"ባለጊዜ" አልኩት::

ወዲያው አንድ መኮንን "ጥያቄ አለኝ" ብሎ ከተቀመጠበት ተነሳና "ይኸ ግለሂስ እንደ ቅፅ መሙላቱ እያንዳንዳችንን ይመለከታል?" አለ::

"በርግጥ እንደ ቅፅ መሙላቱ እያንዳንዳችሁን ላይመለከት ይችላል:: የሆነ ሆኖ አይመለከተንም ብላችሁ ደግሞ ብታደፍጡ የኋላ ኋላ በሂሱ ወቅት ችግር ላይ ትወድቃላችሁ:: ስለዚህ ትንሽም ትሁን ግን ሂስ ብታወርዱ ነው የሚጠቀመው" ብሎ ሀጎስ መልስ ሰጠ:: አሁንም እስበሳችን እየተያየን ዝም አልን::

ቀጠል አርጎ "ጊዜ ባንገድል ጥሩ ነው:: ይኸ ግለ ሂስ ደግሞ የሚጠቅመው እናንተኑ ነው" ሲል አግባባን:: ወዲያው አንድ ሻምበል ብድግ ብሎ:-

"እኔ የሚፀፀተኝ ለደርግና ለፋሽስታዊ ሥርአት አራማጅ መሆኔ ነው:: በተለይ የኢሠፓ መሠረታዊ ድርጅት አንደኛ ፀሐፊ ሆኜ ማገልገሌ ዛሬ ይቆጨኛል:: ከዚህ ውጪ ግን የሰራሁት ስራ የለም" ብሎ ተቀመጠ:: ለካስ መድረኩ እስከሚከፈት ድረስ ኖሯል:: ሽሚያ ገጠሙ:: ሌላው ተነሳና ደግሞ:-

"እኔ የሚፀፀተኝ፤ ደሞ ያኔ በጦርነቱ ወቅት ገና ተራ ወታደር ነበርኩ:: እናም ብዙ አላውቅም ነበር:: አንድ የሶማሌ ወታደር ማረኩና ነዶኝ ስለነበር በጥይት ገድየ እሬሳውን በሳንጃ ዘነጣጠልኩት:: ይኸ ይቆጨኛል" ብሎ ተቀመጠ::

"ትክክለኛ ግለ ሂስ ነው:: ምንም እንኳን የጠላት ወታደር ቢሆንም በሰብአዊ ርህራሄ ሊይዙት ሲገባ መግደላቸውና ይልቁንም

በሬሳው መጫወታቸው አግባብ አልነበረም" በማለት ሀጎስ ለማግባቢያነት ተጠቀመበት::

አንድ ያረብ ክልስ የመሰለ ወጣት መኮንን ተነሳና ደግሞ "ሰሜን ጦር ግንባር በነበርኩበት ወቅት ጠጅ ቤት ያላቸው አንዲት ወይዘሮ ነበሩ:: በየጊዜው ጠጅ በዱቤ እየጠጣሁ በደመወዝ ወቅት እከፍላቸው ነበር:: በመጨረሻ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሰባ ጠርሙስ ጠጅ ጠጥቼ ሳልከፍላቸው ወዲህ ልመጣ ችያለሁ" ሲል እኛ ሳቅን::

"ቦቴ ነህ ማለት ነው?" አለው ሀጎስም ስቆ::

በድሉ ነካ አደረገኝና ወደሱ ዞር ስልለት "አፈር ይጠጣና! ሻቢያ የወገኖቻችንን የወርቅ ጥርስ በመዶሻ እያወለቀ እንደ ገና ጠጅ የዱቤ ጠጣሁ ብሎ እዳ ይሰደናል እንዴ!" አለኝ::

"አይዞህ አትስጋ፤ የሚነግራቸው የለም:: ሀጎስ የነሱ ወኪል አይደለም" አልኩት:: ቀጥሎ የተነሳው ግለ ሂስ አውራጅ ሙክክ ብሎ የለመጨ ነው:: ጨርሶ ፀሀይ ነክቶት አያውቅም:: ነካ ቢያደርጉት ፍርጥ የሚል ይመስላል:: ማእረጉ ሻምበል ነው::

"በ69 ዓ.ም. ተራ ወታደር ነበርኩ፤ ሁለት ኢህአፓዎችን ይዘን እንዲመረምሯቸው ለፖሊሶች ሰጠናቸው:: ፖሊሶቹ ሳይመረምሯቸው ኢህአፓዎች አይደለንም ብለውናልና ልንለቃቸው ነው ብለው ይነግሩናል:: እኔና ጓደኛዬ በራሳችን አነሳሽነት ፖሊስ ጣቢያ ሄደን አስወጥተን ወደ ጫካ በመውሰድ እንበርክከን በጆሯቸው አስጠግተን ጥይት በመተኮስ አሳመናቸው:: ከዚያ በኋላ መልሰን ለጣቢያው አስረከብናቸው:: በማያገባኝ ስራ ገብቼ ይህን በመፈፀሜ ዛሬ ይፀፀተኛል" ብሎ ሲቀመጥ በድሉ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ:-

"ውሸቱን ነው:: ወደ ጣቢያ አልመለሷቸውም:: ገለዋቸዋል:: ማእረጉንም ያገኘው ይህን በመስራቱ ነው" አለኝ::

"ታውቀዋለህ እንዴ?" አልኩት::

"ማወቅ አላውቀውም:: ነገር ግን የሰው ደም የጠጣ ወዙ ያስታውቃል:: አስተውለህ እየው፤ የደርግ የበኸር ልጅ ነው" አለኝ:: ቢጨንቀኝ ቀና ብዬ እየሁት:: እውነትም የፊቱ ወዝ ይቀዳል::

ሁለት መኮንኖች ደግሞ "የገበሬ ፍየሎችና በጎችን በልተናል" ብለው እራሳቸውን ወቅሰዋል:: በዚሁ ስአት ደረሰና ተበተን::

33

ምሳየን በልቼ እንዳበቃሁ ከግንቡ ስር በመቀመጥ የወፎቹን ጫጫታ አዳምጥ ጀመር:: ጫጩቶች ፈልፍለዋል:: ከጎጇቸው ውስጥ ሲንጫጩ ይሰማሉ:: እናቶቻቸው የሳር ፍሬ፤ ትላትል ለቃቅመው በማምጣት ጠቅጥቀውባቸው ተመልሰው ይበራሉ:: ጫጩቶቻቸውን ሳያጠግቡ አንድ ነገር ወዳፋቸው አይሉም::

እነሱን አትኩሬ ባየሁ ቁጥር በትካዜ እዋኛለሁ:: የወፎቹን ጎጆ ባየሁ ቁጥር ጎጆ መያዝ ያምረኛል:: ጫጩቶቻቸውን ሲመግቡ ሳይ ልጅ

ወልዶ መሳም ያጓጓኛል:: ግን የት ሆኘ? ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኘ? አልሞክረውም! በየጊዜው ባለጊዜ እየተነሳ የሚረግጣት አገር! እኔ ብረገጥ አንሶኝ ሌላ ተረጋጭ አልፈጥርም:: ወንጀል ነው!

በትካዜ እንደ ተዋጥኩ በድሉ መጥቶ ከጎኔ በመቀመጥ "የሚዐዕትህ ነገር ካለ ቶሎ ብለህ ግለሂስ ማውረድ ነው" ሲል ቀለደብኝ::

"እንኳን የማወርደው የምስቅለውም የለኝ::"

"ታዲያ ምን ያስተክዝሃል? ዘመን ዲሞክራሲ ነው:: የተሰማህን መናገር ነው::"

"እኔን የሚያስተክዙኝ እነዚህ ወፎች ናቸው:: እኛ ከዚህ ሳንንቀሳቀስ እነሱ ጎጆ ሰርተው እንቁላል ጥለው፣ ጫጩት ፈልፍለው እያሳደጉ ናቸው" አልኩት::

"አይዞህ፣ ከዚህ እንደ ተመለስን ሚስት አጭቼ አደርሃለሁ::"

"ለጥሩ ጓደኝነትህ አመሰግናለሁ:: እኔ ግን ሚስት ማግባት አልፈልግም::"

"ለምን?" አለኝ ወደኔ አትኩሮ እየተመለከተ::

"እኔ እየተሰቃየሁ ለምን ሌላ ስቃይተኛ እፈጥራለሁ?"

"ይኸ የዋህነት ነው:: ሌላው ቢቀር ስቃይህን የምትነግረው ልጅ ሊኖርህ ይገባል::"

"ለልጅ ንብረት፣ ቅርስ፣ ታሪክ ታወርሳለህ እንጅ እንደኔ ስቃይ ትናዘዛለህ?" ስል መልሼ ጠየኩት::

"የኢትዮጵያ አባ ፋንታ ይኸው ነዋ! ቢደንቅህ ወደ ፊት ንብረት፣ ቅርስ፣ ታሪክም ማውረስ አይቻልም:: ታሪክ በሙቶ አመት ተወስኗል፣ ቅርስም ታቦት ሳይቀር እንደ ሸቀጥ እየተሸጠ ነው:: የግል ሀብትም በጉልበተኞች እየተዘረፈ ነው:: ታዲያ ምኑን ነው የምታወርሰው? ስቃይህን ግን ማውረስ ትችላለህ:: ስለዚህ ሚስት አግባና ልጅ ውለድ፣ ችግርህን ለልጅህ አካፍል:: ማን ያውቃል? አንተ የወለድከው ልጅም ባለጊዜ ሊሆን ይችላል?" አለኝ ፈገግ ብሎ::

"ከዚህ ላይ ልክ ነህ:: አምሳ አለቃ ሀይለማርያም ልጅ ወልደው የኢትዮጵያን ህዝብ ይሙትራል ብሎ በዚያን ዘመን ማን ያስብ ነበር? እንዲህ አይነት ልጅም እንድፈጥር አልፈልግም:: ደህማ መረገም ነው:: በተለይም የውጭ ቅጥረኛ ሆኖ አገርን በትቶ ጨርቅ የሚያደርግ አባቱን ገሎ እናቱን ላባቱ ባላንጣ የሚድር ልጅ ነው" ስለው:-

"ልክ ነህ፣ ከሞሰለኒ ጎን ተሰልፈው አርበኞችን የጨፈጨፉ፣ የገዛ ወገናቸውን ቤት ያቃጠሉ፣ ንብረት የዘረፉ ስንት ባንዳዎች ነበሩ:: እንደዚህ አይነቶቹም አይደሉ አባታቸውን ገለው እናታቸውን ለአባታቸው ባላንጣ የሚድሩ?" አለኝ::

"አዎን" አልኩት::

"ታዲያ ባሬም ቢሆን ባንዳዎች በመካከላችን አሉ::"

"ትክክል:: ያውም ሁለት አይነት ባንዳዎች:: አንደኛዎቹ ጊዜ የፈለፈላቸው፣ በለት ክርሳቸው እየተገዙ ሰሞኑን የሚያተራምሱን ናቸው:: ሁለተኛዎቹ ያው ካየት፣ ከቅድመ አያቶቻቸው የወረሱናቸው ቀንደኛ ባንዳዎች ናቸው::"

የሪጋ ጨዋታ ይዘን ሳለ እነዚያ እናት አልባ ጥጆች እየተማሩ ከወደ ፊትለፊታችን መጡ:: ትንኙና ዝንቡ መከራ ያሳያቸዋል:: ጭራቸው ከመከላከል አያርፍም፣ አስር ጊዜ ያወናጭፋታል፣ ትንኙና ዝንቡስ እኛንም አላስቀመጠን:: እንደነሱ ጭራ የለን:: በምን እንከላከለዋለን? ተያይዘን ማለቅ ነው እንጅ፣ አንዳንዱ ዝንብማ ከገራችን ላይ ሲነድፈን ደም ነው ዝርር የሚለው:: እንዲህ አይነቱን ዝንብ ያካበቢው ገበሬዎች «ቡትሪ ዝንብ» ይሉታል:: በቡትሪ አለቅን!

ትልቁ ጥጃ እየመራቸ ሌሎቹ እየተከተሉ ጥቅልል ብለው ባጠገባችን አልፈው ሄዱ:: እስተውለን አየናቸው፣ ደራርቀዋል:: ማለታቸው የማይቀር ነው:: ወተት ሳይጠግቡ እናቶቻቸው ታረዱባቸው:: ያለ እናት ታዲያ ስንቱን እቀበት ወጥተው ነው ኮርማ የሚሆኑት? እረወዲያ! በቅማንኛ ርግ ያልቁታል!

ወዲያው ደግሞ በታች በኩል ያካበቢው እርሶ አደሮች አህዮች ጆሮቻቸውን እያራገፉ እስበሳቸው እንደ መጋመጥ እያሉ በኛ በኩል መጡ:: እነሱንም ዝንቡና ትንኙ እያጣደፋቸው ነው:: ያውም እህያ ሁሉን ቻይ ነበር:: እኛን አለፍ እንዳሉ ትልቁ አለሌ እናፋ:: ደግሞ ፈሱ መቆረጫ የለውም:: ቆረጥ... ቆረጥ... ያደርገው ጀመር:: በድሉና እኔ ሳቅን:: ደርግም እናፍቶ እናፍቶ ነው ፈስቶብን የሄደው::

እንደገና ወደ ጨዋታችን ተመልሰን እያለን "ሙከራ፣ ሙከራ" አለ በድምፅ ማጉሊያው፣ በዚህ ጊዜ ወጋችንን አቁመን ጆሮዎቻችንን አቆረፍን::

"የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ነገ ከጧቱ ሁለት ሰአት በማእከሉ የባህል አዳራሽ እንድትገኙ" በማለት ደጋግሞ እስተጋባ::

"እንኳን ደስ አለህ! ጨብጠኝ!" አለ በድሉ ቀልጠፍ ብሎ:: ከኔ በበለጠ ነበር የፈነደቀው::

"ገና ምኑ ታውቆ? የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ስላለ" አልኩት::

"በቃ መሄዳችሁ ነው:: ምንም ጥርጥር የለውም" አለኝና በደስታ ተጨባበጥን::

ደስታም ለካ እህል አያስበላም:: እራቱን በቅጡ አልበላሁም:: ሁለመናዬ በደስታ ጠገበ:: ሌሊትም እንደ ያንለት እንቅልፍ ወስዶኝ አያውቅም::

ጧት ቁርሳችንን በልተን ልክ በተባለው ሰአት ባህል አዳራሽ ተሰበሰብን:: ወደ ሁለት መቶ እንጠጋለን:: ወዲያው ፀጉራቸውን ያጎፈሩ ሁለት ታጋዮች መጥተው ከፊት ለፊታችን ተቀመጡ:: ሁለቱም ሲጋራ ያጨሱ ነበር:: እስበሳቸው ካሾከሹኩ በኋላ አንደኛው ወደኛ መለስ ብሎ ሰላምታ ሰጠንና "የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ያልሆናችሁ ካላችሁ ብትወጡልን ጥሩ ነው" አለ አትኩሮ እየተመለከተን:: በርግጥም ለምን እንደ መጡ እናውቅም፣ አምስት መከንኖች ብድግ ብድግ እያሉ ተከታትለው ወጡ:: የሸፈዲድና የሞገዲድ አባላት ሳይሆኑ አይቀሩም::

"ዛሬ የሰበሰብናችሁ ትምህርታችሁን እንድትማሩ ኮሚሽኑ ፈቅዶላችኋል" ሲለን ንግግሩን አቋርጠን ሞቅ ያለ የደስታና የምስጋና ጭብጨባ አጨበጨብን::

"እንግዲህ ትምህርታችሁን የምትማሩ መሆናችሁ አጠያያቂ አይደለም:: አጠያያቂው ከናንተ ጋር ወንጀለኞች ተቀላቅለው እንዳይሄዱ

ነው። ስለዚህ ሰሞኑን ታካሂዱት እንደ ነበረው ግለ ሂስ ታካሂዳላችሁ። ይህም በራሳችሁ ፈቃደኝነት ይሆናል። አሁን ወደ ግለ ሂሱ እናመራለን አለና ሲጋራ አቀጣጠለ። እኛ እስበሳችን እየተያየን ዝም አልን።

"እንዴት ነው! ጊዜ ባትገድሉ ጥሩ ነው። ሌሎች የምንሰራቸው ስራዎች ይኖራሉ። ቶሎ ብለን አጠናቀን በነዚህ ሶስት ቀናት ውስጥ መሄድ አለባችሁ" ሲል የሁላችንንም ልብ አንጠለጠለው። ወዲያው አንድ መኮንን ብድግ አለና:-

"እኔ የፖሊስ መኮንን ስሆን የኢስፓ አባልም ነኝ። የሚፀፀተኝ ነገር ቢኖር ኢህዲሪ ሊመሰረት አቅራቢያ መርካቶ! ከታላቁ መስጊድ ጀርባ በርካታ ድሆች ላስቲክ ነገር በመወጠር ሰፍረው ይኖሩ ነበር። ቦታው ስለሆኑ ፀረ ህዝብ ሀይላት በነሱ በመጠቀም ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉና ታፍሰው ወደ አሶሳ አካባቢ እንዲወሰዱ ተብሎ ተወሰነ። በወቅቱ የፖሊስ ጠቅላይ አዛዥ የነበሩት ሜ/ጀኔራል ወርቁ በቀዴ እኔንና ሁለት ሌላ መኮንን በመያዝ ቤተመንግስት ከጓድ ለገሰ አስፋው ቢሮ ወሰዱኝና ስለአፈፃፀሙ ከጓድ ለገሰ አስፋው ትእዛዝ ተቀበለን ወጣን። ትእዛዙም:-

"ከሄዱበት ቦታ ሁከት ቢፈጥሩና ለማምለጥ ቢሞክሩ በጥይት እንድትረሽኗቸው። ይህን ሳታደርጉ ቀርታችሁ አምልጠው ከዚህ ደርሰው ችግር ቢፈጥሩ በናንተ ላይ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን እንድታውቁ" የሚል ነበር።

"በዚህ መሰረት በሌሊት በሰራዊት አስከብበን በማፈስ ወደ ተባለው ቦታ ወሰድናቸው። ለወር ያህል እንደ ተቀመጡ ሀይለኛ ዝናብ ጣለ። በእውነት ዶፍ ነበር። መጠለያ አልነበራቸውም። ዱሉ ነገር ነበር። ከላያቸው ላይ ተደረመሰ። ከላይ ዝናብ! ከስር ጎርፍ አጥለቀለቃቸው። 'ድረሱልን' እያሉ ይጮሁ ነበር። ግን ምንም ልንረዳቸው አልቻልንም። እርዳታ ሲያጡ ክልላቸውን ጥለው በመውጣት በየቅጥቃጡ መሮጥ ያዙ። ሌሊት ነበር። ወደ ሰማይ እየተኮስን ለማስታገስም ሞከርን። ግን አልቻልንም። ያለን ምርጫ በተሰጠን መመሪያ መሰረት መፈፀም ነበር። በርካታዎቹን ገደልናቸው። እንደ ምንም ተጨፋጭፈን የተወሰኑትን አስቀረን። ያመለጡትም ቢሆን በፈሃ አቋርጠው ሲሄዱ ከላ ጠባቂዎች አራቱን ገደሏቸው! የቀሩትን ደግሞ ይዘው በማምጣት ለኛ አስረከቡን። ይህ ድርጊት እጅግ ይዘገንነኛል። እንደ እውነቱ እነዚህ ጭቁኖች ድሃ አዲስ አበባ ውስጥ እንደ ካልተባለ በስተቀር ምንም አይነት ወንጀል አልፈፀሙም ነበር። ወንጀላቸው ድህነታቸው ብቻ ነው።

"ዛሬ ጓድ ለገሰ አስፋውም ተይዟል። ጓድ ጀኔራል ወርቁም የሉም። እኔ ኑሬ ይህን ደባ ለመመስከር በመብቃቴ ባንድ በኩል ሀዘን ቢሰማኝም በሌላ በኩል ግን ደስታ ይሰማኛል። ይኸው ነው" ብሎ ተቀመጠ።

ታጋዩ ፊቱን ጭፍግግ አድርጎ "አዎን! የደርግ መንግስት እንደዚሁ ያለ ነበር። ለጭቁኖች ቆሜአለሁ እያለ ጭቁኖችን ይጨፈጭፍ ነበር። እናንተም የዚህ ፋሽሽት መንግስት መሳሪያ መሆናችሁ ይኸ ተግባራችሁ ይመሰክራል" አለና መደዳውን ወቀሰን።

ከዚህ በኋላ የተካሄደው ግለ ሂስ የረባ አልነበረም። "የኢስፓ አባልና የደህንነት ሰራተኛ ነበርኩ" የሚሉ ብቻ ነበሩ። በመጨረሻም በመኮንኖች ፊት በየሻለቃችን የመወያያ አደራሽ እንደ ምንቀርብ

ተነገረን። አላማውም ተቃውሞ ወይንም ጥያቄ የቀረበበት ተማሪ ለትምህርት እንዳይላክ ማድረግ ነበር። በተረፈ ተዘጋጅተን እንድንጠባበቅ ተነግሮን ካዳራሹ ወጣን።

34

«መልካም አዲስ አመት!» ይላል ከመመገቢያ አዳራሻችን በር ላይ በጉልህ የተፃፈው የመልካም ምኞት መግለጫ። አደራሹም ኘሮ ተብሎ ተጎዝጉዟል። አበባዎች በብርጭቆ ተደርገው በየጠረጴዛው ላይ ተቀምጠዋል። ወጋወጉ ተሟልቷል። በቃ መስከረም ባተ።

ሳንጠብቀውና ሳናስበው ኢህአዲግ በየሻለቃው በሬዎችን አርዶ አንበሸበሸን። ሲጋው ሳይሆን ስግንቱ ነበር ደስ ያሰኘን። ምነው ስራና ተግባሩም ስጋ ስጋ ቢሸት። ደስ ብሎን ነበር የተመገብነው። ምን ይሆናል ታዲያ እኛ ብንጠግብ በርሃብ የሚቆሉ ደግሞ አሉ።

ተሰፈኞች አፈር መስለው በሩን ከበው ቆመዋል። እንደ ጥጆቹ ከዋኘ ያጡ ልጆች ናቸው። መቼ ነው ከቁራሽ ልመና የምንገላገለው? የሰውን እጅ እንደ ማየትኮ ስቃይ የለም። በሌላ በኩል ትርፍራፊ መልመድ ዋልጌነትን ያስፋፋል። ለም መሬት እያለን የኛ መራብ አንቀቅልሽ ነው። ወደ ፊትማ ጭራሽ እንጃ! በጎሳ ተከፋፍሎ መናቆር እንጂ ስራን ማን ጉዳይ ብሎት። ሲርብ አንዱ ጎሳ ሄዶ ሌላውን መዝረፍ! ማቃጠል ነው። የግቤ ወንዝ እንኳን የስንቱን ጉሮሮ ዘግቶ ባደረ። አንድ ሰሞን ደርግ «አባይ! አባይ! አንተ የባድ ሲሳይ!» እያለ በሬድዮ ያላዝን ነበር። አባይ ምን ያድርግ? አልገደብም አላለ። ዛሬስ ከናካቴውም እንኳን አባይን ልንገድብ ይቅርና በደም ካሳ የተገደበችውንም የቆቃን ግድብ እንዳንደረምሳት ያሰጋል።

መኮንኑ ሁሉ ምሳውን ከበላ በኋላ ወደ ዋዩ ሄደ። ቅንጡራ ለመቀንበር ነው። እነ አዱኛም ጥለውኝ ቀደም ብለው ሄደዋል። እኔም ቀንቡሬ ለመምጣት ወደዚያው አመራሁ።

ባህል አዳራሽ ስደርስ ቆም ብዬ አስተዋልኩት። ግዙፍ ነው። ከዚያ በረሃ ላይ ተገጭሮ ግርማ ሞገስ አለው። ትናንት ከዚሁ አዳራሽ ለሁለተኛ ጊዜ ተማሪዎች ተሰብስበን ነበር። ማጣሪያ ተብሎ ነው! በርግጥም አበጠሩን...

መሰንበቻችንን በየምንወያይበት አዳራሽ ከመኮንኖች ፊት እየቀረብን ንፁህ መሆናችን ተረጋግጦልን ነበር። አንድም ተማሪ ጉድፍ አለበት! ይቆይ አልተባለም ነበር። እኛም ቅዱስ ዮሐንስን አዲስ አበባ ለመዋል ቸኩለን ነበር። ኢህአዲግ ግን ጎተተን። ከናካቴውም ትናንት በሁለት ሰዓት ሰበሰቡንና:-

"ይቅርታ አድርጉልን! የኢስፓና የደህንነት አባል የሆናችሁ የተሃድሶ ትምህርቱ እስከ ሚያልቅ እንደ ማንኛውም መኮንን ትቆያላችሁ። አሁን ውጡልን" ሲላቸው ታጋዩ እንዳቸውም ጥያቄ አላነሱም። ውልቅ ውልቅ አሉ። አሳዘኑኝ። የቀረነው ስማችንን እንደ ገና ባዲስ ተመዝግበ ለጉዞ ተዘጋጅተን እንድንቀመጥ ተነገረን ካዳራሹ ወጣን። የኛ መሄድም ቢሆን አጠራጣሪ ነው።

"ጎበዝ ተስፋ እንዳታደርጉ፡፡ የወፍ ወንዱ የኢህአዲግ ሆዱ አይታወቅም" ብሎ ውጭ ከወጣን በኋላ አንዱ ተማሪ አስቆናል፡፡

ግለ ሂሱን የጨረስነው ከትናንት ወዲያ ነበር፡፡ ችግሩ አንዱን ስንወጣው ሌላው እየተተካ ነው፡፡ በነፍሳችን ነው የተጫወቱብን፡፡ ከነገ ጀምረን ደግሞ ሂስ እናካሂዳለን አሉ፡፡ ይሄ ደግሞ አደገኛ ነው አሉ፡፡ ብዙ መኮንኖች ፈርተውታል፡፡ በተለይ ከደርግ ጋር ቀረቤታ የነበራቸው እንደ ጨው ሚሙተው ሊያልቁ ነው፡፡

ምእራፍ አስራ ሶስት

ሌላውን ከመውቀስ፣ ወንድሙን ከማርከስ፣
ምናለ በስራ ሰው እራሱን ቢያድስ፡፡

35

የመስከረሚ በሀይ ገረር ብላ እናት ትበጠብጣለች፡፡ ሂሱም እናት ይበጠብጣል፡፡ ሂሱን ከጀመርን ሰባተኛ ቀናችንን ይዘናል፡፡ ተፋፍሟል፡፡ የትርኢቶች ሁሉ ትርኢት ተብሏል፡፡ ከቅፅ መሙላቱ ጀምረው ተሽፋፍነው የተቀመጡትን ሁሉ እንደ ተርብ የሚናደፉ አጋላጮች እየመዠለጡ አወጧቸው፡፡ የሚያውቋቸውን ለመሸሸ ሲሉ ክፍላቸውን እየቀየሩ ያደፈጡትን ሁሉ ከያሉበት አጋለጧቸው፡፡ የሚገርመው ግን ቁሞ ሲሂስ የነበረው ሳይቀመጥ ከዚያው ላይ "አንተም ተጠየቅ" ሲባል ነው፡፡

አዳራሹ ግጥም ብሎ ሞልቷል፡፡ እኔ የዘወትር መቀመጫዬን፣ በመስኮቷ በኩል ተሸቀዳድሜ ይገየስሁ፡፡ ሀጎስ ከፊት ለፊታችን ጉብ ብሎ ሲጋራውን ካቦነነ በኋላ በመጠኑ ፈገግ ብሎ "አንድ ነገር ልንገራችሁ?" አለን፡፡ ንገረን በሚል የጠቀላላችን ጆሮ ቆመ፡፡ "እኛ የማንኛውንም እምነት ተከታይ አንቃወምም፡፡ ሁሉም ሰው ይጠቅመኛል ያለውን እምነት መከተል ይችላል፡፡ ነገር ግን በሃይማኖት ሽፋን ጴንጠ ቆስጤዎች በየዛፉ ስር በፀሎት ፈንታ እርግማን እያወረዱ ናቸው፡፡ 'አጋላጩን ያዝልኝ፡፡ አይኑን ጨለማ፣ ጉልበቱን ቁጠማ፣ ወገቡን ሽባ አድርገው፣ ጆሮውን ደፍነህ መስሚያ ንሳልኝ እያሉ ይፀልያሉ" ሲለን እንደ ተለመደው አውኩተን ሳቅን፡፡ በዚህ ላይ እንዳለን ሁለት የምድር ጦር ማስተናገጃ ደመወዝ ከፋዮች ባንድ ታጋይ እየተነዱ ገብተው ከፊትለፊታችን ተገተሩ፡፡ የጠቅላላችን አይን አፈጠጠባቸው፡፡ የዛሬው ሂስ የተጧጧፈ ነው የሚሆነው፡፡

ሀጎስ ከተቀመጠበት ብድግ አለና "እነዚህ ከፊትለፊታችሁ ቆመው የምታዩዋቸው መኮንኖች የምድር ጦር ማስተናገጃ ደመወዝ ከፋዮች የነበሩ ናቸው፡፡ መቶ አለቃ ለሜሳን የምታውቋቸው መሰለኝ፡፡ ባለፈው በቅፅ መሙላቱ ወቅት በሰማኒያ ሺ ብር ተጠያቂ በመሆናቸው

ያው በስር ላይ ይገኛሉ፡፡ አሁን በመካከላችን የተገኙት አብረዋቸው በቀሙት መኮንን ላይ ሂስ አለኝ ስላሉ ነው፡፡

"እኒህኛው መኮንን ሻምበል ብሩ ፈይሳ ይባላሉ፡፡ የማስተናገጃ አንዱ ደመወዝ ከፋይ ነበሩ፡፡ ሆለታ ለሶስት ቀናት ያህል ከቆዩ በኋላ ጠፍተው አዲስ አበባ ካደፈጡበት ሲያዙ ችለዋል፡፡ አሁን በቀጥታ ወደ ሂሱ እንገባለን፤ በንቃት ተከታተሉ" አለንና ተቀመጠ፡፡ ወዲያው መቶ አለቃ ለሜሳ ፈቀቅ ብሎ እንዲቆም ሆነና ሀያሲው መኮንን ማስታወሻውን ይዞ ከፊትለፊታችን ከሻምበል ብሩ ጎን ቆመ፡፡ ማእረጉ መቶ አለቃ ነው፡፡ ሂሳብ ተቆጣጣሪ የነበረ ነው፡፡ ጉሮሮውን ሞረደና፡-

"ጓዶች! ሁላችሁም እንደምታውቁት እኔ ለመሂስ የምፈልጋቸው መኮንኖች ጠፍተዋል፡፡ ያሉትም ያው ባለፈው አጋልጫቸው ታስረዋል፡፡ እንግዲህ ከጠፉት መካከል አንዱ ሻምበል ብሩ ነበሩ፡፡ የዛሬውን ሂሴን የማቀርበው በሳቸው ላይ ነው" አለና ገልመጥ ብሎ አየው፡፡ እጆቹን አጣምሮ ከደረቱ ላይ በማድረግ ፍርሃትና ድንጋጤ ወሮት ቆሟል፡፡ ቦርጩም ትርሽትሽት ብሎ ትል የወጋው ዱባ መስሏል፡፡

ሀያሲው መኮንን ማስታወሻውን ገልበጥ አድርጎ አይቶ "ጓዶች! ከሁሉ አስቀድሜ ለመግለፅ የምፈልገው ለግል ጥቅም ብዬ አለመነሳቴን ነው፡፡ ጥቅም ብፈልግ ኖሮማ ሆለታ ሳለን 'አርፈህ ተቀመጥ፤ ሀያ ሺ ብር እንስጥህ' ሲሉኝ አርፌ በተቀመጥኩ ነበር፡፡ የኔ አላማ ሀቅ እንድትወጣ ነው፡፡

"ጓዶች! ምድር ጦር ማስተናገጃን የምታውቁ ታውቁታላችሁ፡፡ ማስተናገጃ ሳይሆን ማሳበጃ ነበር፡፡ በርግጥም በሺ የሚቆጠሩ አብደውበታል፡፡ የማስተናገጃ ደመወዝ ከፋዮች ሀያ ሶስት ሲሆኑ አዲት በምናደርግበት ወቅት ትንሹ ደመወዝ ከፋይ በካዝናው ውስጥ ሰማኒያ ሺ ብር ሲገኝበት ትልቁ ደግሞ መቶ ሃያ ሺ ብር ነበር፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ሻምበል ብሩ ናቸው፡፡ በዚህ ስሌት ተነስተን በየወሩ ይህን ያህል ገንዘብ ተመላሽ ቢያደርጉ ኖሮ በትንሹ ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ ሺ ብር ይሆን ነበር፡፡ የአንዱ ዓመት ደግሞ ሰላሣ ሶስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር ይሆን ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ መስሪያ ቤት እብዮት ከፈነዳ ጀምሮ አዲት ተደርጎ ስለማያውቅ ምን ያህል ገንዘብ እንደተዘረፈና ግለሰቦች እንደበለፀጉበት በቀላሉ መገመት ይቻላል፡፡ 'ታዲያ አብዮት ከፈነዳ ጀምሮ አዲት ካልተደረገ አንተ እንዴት አዲት ልታደርግ ቻልክ?' የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ መልሱ፡-

"የማስተናገጃ አንዱ ንኡስ ክፍል በ1983 ዓ.ም. በመስከረም ወር የሰው ሀይል ሰላሳ አራት ሺ ሆኖ ሳለ አርባ ሺ ሰው ተብሎ ደመወዝ ይጠየቅና ወጭ ሆኖ የስድስት ሺ ሰው ደመወዝ በነፃ ይበላል፡፡ ይህንን ጉድ መከላከያ ሚኒስቴር ይደርስበትና የማስተናገጃ ደመወዝ ከፋዮች ካዝናቸው ታሽጎ አዲት እንዲደረጉ ትእዛዝ ለምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያ ይሰጣል፡፡ በትእዛዙ መሰረትም ባንድ ሻለቃ የሚመራ ሶስት አባላት ያሉት ኮሚቴ ተቋቋመና የምርመራው ተግባር ተጀመረ፡፡ ከነዚህ መርማሪዎች መካከል አንዱ እኔ ነበርኩኝ፡፡ የሚገርማችሁ ነገር ታዲያ ሆለታ ሳለን ሀያ ሺ ብር እንስጥህ ያሉኝ ያኔ ሀያ ሳንቲም አላሉኝም ነበር፡፡ እንዲያውም 'አርፈህ ብትቀመጥ ይሻልሃል' ይሉኝ ነበር፡፡ ይህን ከሚሉኝ መካከል አንዱ ሻምበል ብሩ ነበሩ፡፡ በርግጥም የተወሰደ እርምጃ

አልነበረም። የእዲቱ ተግባርም እኛ በማናውቀው ሁኔታ ቀም እኛ እንድንበተን ተደርጓል።

"የምድር ጦር ማስተናገጃ ጉድ እንዲህ በቀላሉ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። ያበላሉ ስልት ሰፊና የረቀቀ ነው። ከየር ሀይል፣ ከባህር ሀይል፣ ከፖሊስ ሰራዊት በስተቀር ባራቱም ማእዘናት ወደዚህ መስሪያ ቤት በየቀኑ የሚጎርፈው ቁጥሩ እጅግ ብዙ ነው። በመቁሰል፣ በህመም፣ በጡረታ፣ አዲስ በመቀጠርና በልዩ ልዩ ምክንያት የምድር ጦር አባል የሆነ ሁሉ ማስተናገጃን የግድ ይረግጣል። ለነገሩማ የንግዳ ማረፊያ ነበር። ታዲያ ይኸ ሁሉ ይዘረፋል። የሚገባው ሁሉ ሲመዘገብ ሲወጣ ግን ሄዷል ተብሎ ከሰው ሀይል አይቀነስም። በሚሞቱት፣ በሚከዱት፣ ቡበዶቹ ሁሉ ደመወዝ እየተጠየቀ ይበላል። ለምሳሌ አንድ ኮለኔል ሶስት ወራት ተስተናግደው ወደ ክፍላቸው ከተመለሱ በኋላ በስማቸው ደመወዝ ወጭ እየሆነ ሶስት አመት ተበልቶበታል። ስምንት ወታደሮች ደግሞ ጡረታ ከወጡ በኋላ እንደ ገና አዲስ ከግንባር እንደ መጡ ተደርገው ስማቸውን በማስተከል ለሁለት አመት ደመወዝ ተከፍሏቸዋል። ችግር የለም፣ ከፀሀፊዎች ጋር መሻረክ ነው። 'ፔሮል ተፍቶሀል፣ ስምህ ሰነድ ላይ የለም' እየተባለ የሚዘረፈው የዋህ ሰራዊት ቁጥሩ ብዙ ነው።

"ሌላው ትርኢት ከየግንባሩ በጠና ቆስለው ይመጡና በየሆስፒታሉ ይሞታሉ። በቀን ቢያንስ ቢያንስ ኳምስት እስከ አስር ድረስ ይሞታሉ። የነዚህ ሁሉ ያንገት ሀብል፣ የጣት ወርቅ፣ ቴፕ፣ ሬዲዮ፣ የጅ ሰአት፣ ጥሬ ገንዘብ፣ ልብስ ለቤተሰብ አይሰጥም። ተሸጦ ገንዘቡን ይከፋፈሉታል።" በማለት እየዘረዘረ እንዳለ አንድ ሻምበል እጁን አወጣና:-

"ስለሚሞቱ የጦሩ አባላት ንብረት መዘረፍ ጉዳይ የማቀው ነገር ስላለ ለጓዱ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲሆን መናገር ፈልጌ ነበር፤ ይቻላል?" አለ ከተቀመጠበት ተነስቶ።

"ይቻላል! ይቻላል! ይናገሩ" አለ ሀንስ። እንዲህ አይነት ማጠናከሪያ ይወዳል።

"ቀደም ሲል መከንኑ እንደ ገለፀው የማስተናገጃ ጉድ እንዲህ በቀላሉ በግል ሂስና በሂስ የሚያልቅ አይደለም። ገና መመርመር ያለበት መስሪያ ቤት ነው። ለነገሩ 'ያሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ' እንዲሉ ከላይ ነው የተግማሙብንና የተጨማለቁብን። እኔ ከዚሁ መስሪያ ቤት ለሁለት አመት ተቀምጫለሁ። እያሌ የሚዘገንኑ ነገሮች ሲፈፀሙ አይቻለሁ። ከነዚህ ዘግናኝ ደባዎች ውስጥም የሙታን ንብረት መዘረፍ ነው። ጓዶች! ለቤተሰብ ንብረት ማስረከብ ይቅርና ሙተውላችኋል ተብለው የሚረዱት በጣም ጥቂቶች ናቸው። ያውም የሟቾቹ ቤተሰቦች ጠንካሮች ከሆኑ ነው። ደርግ የሞቱትን ለቤተሰቦቻቸው ማርዳት የማይፈልገው በሁለት ምክንያቶች ይመስለኛል። አንደኛው በየቀኑ እንደ ቅጠል የሚረግፈው ሰራዊት ቁጥሩ እጅግ ብዙ ስለሆነ የጡረታ መብቱን ለመጠበቅ ካቅሙ በላይ ስለሆነበት፣ ሁለተኛው የሟቾቹን ንብረት ለመውረስ ነው። ንብረቱ ደግሞ ቀላል አይደለም።

ግምቱ እንዲህ ነው። አንድ ጓደኛዬ ከሰሜን ጦር ግንባር ይቆስልና ለከፍተኛ ህክምና አዲስ አበባ መጥቶ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል እንዲተኛ ተደረገ። ያኔ እኔ ታምሜ ከዚሁ ሆስፒታል ተኝቼ ነበር። የጣት ቀለበቱን፣ ያንገት ሀብሉን፣ የጁን ሰአት፣ ቴፑን፣ አራት ሺ ብርና አንድ ሙሉ ሳጥን ልብስ አሳካሚ ተብየዎች ሲረከቡት አይ ነበር።

"ከጥቂት ቀናት በኋላ ሻምበሉ ሞተ። እኔ ድኘ እንደ ወጣሁ አገር ቤት ልኬ ባለቤቱ እንድትረዳ አደረኩኝ። የወራሽነት መብቷን ለማስከበር አዲስ አበባ ስትመጣ 'ንብረቱ ሆስፒታል አለና ነይ ተረከቢ' ብዬ ይገርት ሄድሁ። አሳካሚ የተባሉት የሰጡን መልስ 'እኛ ማሳከም እንጅ ስለ ሟቾች ንብረት የምናውቀው ነገር የለም' አሉን። 'ታዲያ ማንን እንጠይቅ?' ስንላቸው 'የቀብር ስነስርአት አስፈፃሚዎችን ጠይቁ' አሉን። እነርሱን ስንጠይቃቸው የሰጡንን መልስ እራሳቸው ይግለፁት። ጓድ ሻምበል አንድ ጊዜ ይንሱልኝ" ሲላቸው አመዳቸው ቡን አለ። ደግሞ ሽማግሌ ናቸው። ነጭ መነፅር ሰክተዋል። ቁሽሽ ብለው ተነሱና:-

"ነገሩ እውነት ነው። የሚቹ ባለቤትና ጓድ ሻምበል በወቅቱ ጠይቀውኝ ስለሟቾች ንብረት እኔ የማውቀው ነገር እንደሌለ ገልጨላቸው ነበር። የኔ ስራ ከየሆስፒታሉ የሚታከሙትን የጦሩን አባላት ሲሞቱ አሳካሚዎች ሲነግሩን ሄደን አስከሬኑን አምጥተን እንቀብራለን። የኔ ስራ መቅበር ነው" ሲሉ ዋ! ብለን ሳቅን።

"ታዲያ ንብረትን በተመለከተ ማነው ተጠያቂው?" ሲል ሀንስ አፋጠጣቸው።

"አንድ የጦር አባል ከግንባር ቆስሎም ሆነ ታሞ ሲመጣ ንብረቱን በመጀመሪያ የሚረከቡት በየሆስፒታሉ የተመደቡ አሳካሚዎች ናቸው። በሞት ሲለይ ከነሱ ላይ ድርጅት ይረከባል። ከዚያ በኋላ ግን የት እንደሚደርስ አላውቅም" ሲሉ መለሱ።

"የማስተናገጃ የድርጅት መኮንን አሉ?" ሲል ሀንስ ጠየቀ።

"የሉም" የሚል መልስ ከቤቱ ተሰጠ።

"የራሳ ሳጥንስ አልሸጡም?" ብሎ ሲጠይቃቸው እኛ ሳቅን።

"አልሸጥኩም" አሉ።

"ይቀመጡ" ሲላቸው ሹክክ ብለው ተቀመጡ።

"እንግዲህ ጓዶች፣ አይኔ እያየ የተረከቡትን ንብረት በልተውት ቀርተዋል፤ ጨርሻለሁ" ብሎ ሻምበሉ ሲቀመጥ ሲሄስ የነበረው መቶ አለቃ ደግሞ ቀጠለ።

"የማስተናገጃ የገቢ ምንጩም ማለቂያ የለውም፤ ከከቡብ፣ ከዐጉር፣ ከሺዲዮ፣ ለስፖርት እየተባለ ከወታደሮች ላይ ሁለት ብር፣ ከመኮንኖች ላይ አራት ብር ይቆረጣል። ይኸ ሁሉ ደረሰኝ የለውም። የሚገርማችሁ ነገር ለሽንት ቤት እየተባለ ሃያ አምስት ሳንቲም ከደመወዙ ላይ ይቆረጥበታል። ፍረዱ እንግዲህ፤ ጦሩ ደሙን እያፈሰሰ እሱ ሽንቱን የሚያፈስበት አጥቶ ስሙኒ ይቆርጡበታል። ይኸ ሁሉ ገንዘብ ተጋፎ ለልማት ሲውል አላየንም። ግለሰቦች ሲለሙበት እንጅ።

"እንግዲህ እጠቃላይ ስለማስተናገጃ ያለኝ ሂስ ይህን ሲመስል ሻምበል ብሩን ግን በወቅቱ በመቶ ሀያ ሺ ብር አስፈርሚአቸዋለሁ። ጨርሻለሁ" ሲል ሞቅ ያለ ጭብጨባ አጨበጨብንለት።

ሀጎስ ከተቀመጠበት ተነሳና "እናመሰግናለን መቶ አለቃ" ካለው በኋላ "ስለማስተናገጃ ጉድ የሰማችሁ መሰለኝ:: ሰው ተጠብሶ የተበላበት ነው ማለት ይቻላል:: እስቲ ደግሞ መቶ አለቃ ለሚሳ የሚሉትን እንስማ:: ይቀዕሉ" ብሎት ተቀመጠ::

ለሚሳ ወጣ ብሎ በመቆም "ጓዶች፣ ቀድም እንደተገለፀው ባሁኑ ወቅት እኔ እስር ቤት እገኛለሁ:: ለስር ካበቃኝ አንዱ ሻምበል ብሩ ፈይሳ ነው:: የማስተናገጃ እባላት እንደምታወቁት እሱና እኔ ጓደኛሞች ነበርን:: ሀቅ እንድትወጣ ብየ አንድ እሱን ለመወንጀል ፈልጌ አይደለም:: ይኸ ጎደለብህ የተባልኩት ሰማኒያ ሺ. ብር በሙሉ እጥፍቼው አይደለም:: አንድ ጊዜ አምስት ሺ. ብር፣ አንድ ጊዜ ደግሞ አስር ሺ. ብር በሱ አስተባባሪነት ለበላይ ጠባቂዎች ተብሎ አዋጥቻለሁ:: ቀሪውን ስልሳ ሺ. ብርም ቢሆን ከሱው ጋር ነው ያጠፋሁት:: እንደሱ እንኳን ንብረት አላፈራሁም::

"ሻምበል ብሩ ፈይሳ ባለ ቀለም ቴሌቪዥን ገዝቶ ለወዳጁ ገፀ በረከት የሚያቀርብ መከንን ነው:: አሁን በቅርብ ጊዜ ደግሞ በዚችው በወዳጁ ስም እንዲት ሚኒባስ ገዝቷል:: ከዚህ ሌላ እንኳን እኔ እሱም ቁጥሩን በትክክል የማያውቀው ገንዘብ ዘርፍዋል" ብሎ ሂሱን ሲጨርስ:-

"የሻምበል ብሩ የወዳጅ ስም ማን ይባላል መቶ አለቃ?" አለው ሀጎስ ስሟን ለመመዝገብ ማስታወሻ እያወጣ::

"የኔነሽ አሰፋ ትባላለች" ሲለው ልቤ በድንጋጤ ዘለለች::

"ድራማውን እየተከታተላችሁት መሰለኝ:: እስቲ ደግሞ ሻምበል ብሩ የሚሉትን እንስማ" አለ ሀጎስ የየኔነሽን ስም በማስታወሻው ከመዘገበ በኋላ:: ሻምበል ብሩ ላብ በላብ ሆኖ ነበር:: ያንገቱን ዙሪያ ሁሉ ጠራረገና ወደኛ ቀና ብሎ ለማየት ብዙ ተቅለሰለሰ:: ሳውቀው ትቢተኛና ጉረኛ ነበር:: ዛሬ ግን ሙትት ብሏል::

"መቶ ሀያ ሺ. ብር አለብህ ለተባልኩት እውነት ነው:: በመተማመኛው ላይ ፈርሜለት ነበር:: ከዚህ ውስጥም አሁን ስያዝ መቶ ሺ. ብሩን አስረክቤአለሁ" ሲል አዲተሩ አቋረጠውና:-

"ሀሰት ነው ጓዶች:: መቶ ሀያ ሺ ብሩ በመስከረም አዲት ስናደርግ ከካዝናቸው ውስጥ የተገኘ ተመላሽ ማድረግ የሚገባቸው ነው:: አሁን ሲያዙ የተገኘባቸው መቶ ሺ ብር ግን ኢህአዲግ አዲስ አበባ ለመግባት ሲገሰግስ የግንቦትን ወር ደመወዝ ለጦሩ ከፊሉ ተብሎ የተሰጣቸው ነው:: ይኸውም ቢሆን እሳቸው እንደ ሚሉት መቶ ሺ ብር ብቻ አይደለም፤ የዚህን አራት እጅ ይሆናል" በማለት አስተባበለበት::

"አይዋሹ ሻምበል ብሩ:: ካሁን በኋላ ውሸት አያዋጣዎትም::"

"እንዲህ ከሆነ ስለገንዘቡ ጉዳይ ወደፊት የሚጣራ ይሆናል:: አሁን የምለው የለኝም:: ቴሌቪዥን ለተባለው አሁን የተያዙ እለት ታጋዮች ወስደውታል::" ብሎ ዝም ሲል:-

"በወዳጅዎት ስም የገዟት ሚኒ ባስስ?" አለው ሀጎስ::

"ባለቤቴ እንጅ ወዳጅ አይደለችም:: ይህ አባባል ይታረምልኝ" አለ ኩስተር ብሎ::

"ይቅርታ እርማለሁ:: ስለሚኒባሷ ይቀፅሉ" አለው::

"በርግጥ በባለቤቴ ስም እንዲት የሰራች ሚኒባስ ገዝቻለሁ::"

"ገንዘብ ከየት አምጥተው ገዟት?" ሲለው:-

"በደመወዙ" ሲል እኛ ሳቅን::

"ለቤቱ ግልፅ መሰለኝ:: ካሁን በኋላ ጥያቄና መልስ የሚያስፈልግ አልመሰለኝም" አለ ሀጎስ:: በዚህ ጊዜ ብሩ:-

"እኔም በመቶ አለቃው ላይ ሂስ አለኝ" አለ::

"ይቀፅሉ" አለው::

"መቶ አለቃው ችሎታ የሌለው ደካማ ነው:: እንኳን ደመወዝ ከፋይ ሊሆን ይቅርና ተራኛ ዘብ ማውጣትም አይችልም:: ደመወዝ ከፋይ ለመሆን የቻለው አምስት ሺ. ብር ቅድሚያ ጉቦ በመክፈሉ ነው:: ከዚህ ሌላ ደግሞ ምንም ነገር የለኝም ደላል እንጅ በናቴ ስም አገር ቤት ጠጅ ቤት መክፈቱን አጫውቶኛል" በማለት የራሱን ሂስ አቀረበ:: ለሚሳ ደግሞ በመጠራጨት:-

"ሀሰት ነው ጓዶች! 'እናቴ ጠጅ ቤት አላት 'አልኩት እንጅ 'በናቴ ስም ጠጅ ቤት ከፈትኩ' አላልኩትም" በማለት መለሰ:: ሻምበል ብሩ በበኩሉ ለመናገር ሲቃጣ ሀጎስ ከለከለውና:-

"ቤቱን ሳየው ድካም የተሰማው ይመስላል:: በይህ ላይም ሰአት ደርሷል:: ስለዚህ ለዛሬው በዚህ ቢበቃንስ?" ሲል ሀሳብ አቀረበ:: በመስማማት አጨበጨብን:: በዚሁ ውይይቱ አበቃ:: እኛ ከመውጣታችን በፊት ሻምበል ብሩና መቶ አለቃ ለሚሳን ጧት ያመጣቸው ታጋይ ይዟቸው ሄደ::

"እየ የኔነሽ! ለካ የብሩ ሆነሽ ነው የጠፋሽኝ" አልኩኝ ካዳራሹ ስወጣ:: የት አግኝታ ጠለፈችው? የፍቅር ቀበኛ:: ቅናት በገበገኝ!

36

እኛን ደስታ እራቀን እንጅ እለቱስ ብሩህ ቅዳሜ ነበር:: ምሳ በልተን እንዳበቃን ከካምፓችን ጀርባ ካለው አንድ ዘርፋፋ ግራር ስር ሄደን ተቀመጥን:: ጥላው ደስ ይላል:: እኛ ግን ጥላ የለንም:: መስከረም ከጠባ ጀምሮ ከዚህ ዛፍ ስር መቀመጥ አዘውትረናል:: ሲከፋን መተከዣ፣ ደስ ሲለን መጫወቻ፣ ሲደክመን ማረፊያ አድርገነዋል::

ሂሱ ከተጀመረ ወዲህ በየግላችን ማሰብ ይዘናል:: አንድነት እጥተናል:: መተዛዘን ጠፍቷል:: አንዱን ጥሎ ሌላው ለማለፍ እሩጫ ተይዟል:: ሁኔታዎች ሁሉ አሳሳቢ እየሆኑ መጥተዋል:: በተዛድሶ ማእከሉ ውስጥ ትኩዜ ነግሷል:: ወያኔዎች በስንጥር እንጨት ቁስላችንን እየመነቀሩ በማነፍረቅ እስበሳችንን እስተናነቁን:: በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በአስተዳደሩ ሲናቆር የኖረው መከንን ዛሬ ጉርቦ ለጉርቦ ተናንቋል:: ይሉኝታ፣ ትህትና፣ መቻቻል የሚባል ነገር የለም:: እራስን አድኖ ሌላውን ለመቀበር እሽቅድድም ተይዟል::

ከዛፉ ስር ሶስታችንም እንደተቀመጥን ከወደታች በኩል ኮሎኔል ዘርጋው መጡ:: ስናያቸው ፈገግ አልን:: ካጠገባችን ሲደርሱ ከተቀመጥንበት በመነሳት አክብሮታችንን ገለፅንላቸው::

"እረ በግዜር ተቀመጡ" ብለው ቀልጠፍ በማለት ካጠገባችን ተቀመጡ::

"የነሸምበል ብሩ ነገር አላስገረመዎትም ጌታዬ?" አላቸው አዱኛ::

"ሁላችንም እናስገርማለን አዱኛ:: በመንጋ ተመርተን መንጋ ሁነን የቀረን:: እረ ዛሬስ ሳንዋረድ ከዚህ በተገላገልን:: ምነው የምስራቁ ጦርነት ጊዜ ሙቸ ቢሆን ኖሮ" አሉ የድምፃቸው ቃና እንደ መሰበር ብሎ:: እንደዚህ ሲሉ አሳዘኑን:: ጀግናና ምሁር እንደ ዲሪቶ የተናቀበት ዘመን:: እረ ዲሪቶስ ተጠቅም ይጠቅማል::

"በዚህ አይነትማ ምኑን እንገላገለዋለን? በየምክንያቱ ያስሩናል እንጅ" አላቸው:: ይህን ሰምን አዱኛ ክፉኛ ትካዜ ውጦታል:: ጮክ ብሎ መናገር አቁሟል:: ተጠቅልሎ መተኛትም ይዟል:: በተለይ ሂሉ ከተጀመረ ወዲህ ስጋት ገብቶታል::

"ልክ ነህ:: እናር ባይ እንስቶ ይለጥፍብናል:: ጎበዝ! ክፉ ጊዜ ነው የመጣብን:: አብረን የበላነውን፣ አብረን የጠጣነውን፣ ባንድ የጦር አውድማ አብረን የተሰለፍነውን እንደዚህ ክፍልፍል አድርገው አስበሳችን ያናክሱን! ህዝቡ እንዴት አድርጎ አንድነት ኖሮት እንደሚችላቸው እግዚአብሄር ይወቅ:: ትንሿን ጥፋት ንቀን በመተው ትልቁን ጥፋት በመመከት እኛ አንድነታችንን አጠንክረን ያልተቋቋምናቸው ህብረተሰቡ እንዴት አድርጎ ይቋቋማቸዋል? ይኸ ጎሳ የተረሳ፣ይኸ ዘር የተጨቆነ፣ ይኸ ዘር ደግሞ ጨቋኝ እያሉ በመከፋፈል እንደ ፈለጉ በዚች አገር ላይ ይፈነጩባታል:: እረ እግዚአብሄር ፍርዱን ይስጠን:: እረ ይችን አገር ይቅር ይበላት" አሉ ምርር ባለ አነጋገር::

"መቶ አለቃ ዘከሪምኮ ነገር እያመጣ ነው ጌታዬ" አላቸው አዱኛ:: ከስጋቱ ጋር ነው የሚጫወተው::

"እሱ ደግሞ ምን ልሁን ነው የሚለው? ታስሮ የለም እንዴ?" አሉ ግንባራቸውን ኩፍትር እያደረጉ::

"ቢታሰር መቼ አረፈ:: 'እስመጋቢ መኮንኖች፣ የክብብ ሃላፊዎች፣ ተቆጣጣሪዎች፣ የደመወዝ ትኬት ቆራጮች የነበራችሁ ሁሉ አንዳንድ ሺ ብር አዋጥታችሁ ለሚስቴ ካልሰጣችኋት አጋልጣችኋለሁ:: እኔ ብቻ ታስሬ አልቀርም' ብሎ ይኸውና ውስጥ ለውስጥ በመላክ ማስቦካት ይዟል" ሲላቸው ብልጭ አላቸውና:-

"እምስት ሳንቲም እንዳታዋጣ! ይህ ሌባ! የዘረፈው አልበቃው ብሎ እንደገና ግለሰቦችን እያስፈራራ መዝረፍ ይፈልጋል?! እረ ከምን አይነቱ ጊዜ ደረስን? ምነው እናንተ በሽተኛ ውሻ ይመስል ዛበሩ!" አሉ በቁርቱ ተቆጥተው::

"ከኋላክ ግፊትና ቅስቀሳ አለ ጌታዬ:: እነሀጎስ 'ሌሎችን ከጠቆማችሁና ካጋለጣችሁ እናንተን እንፈታችኋለን' እያሉ ይሉበኳቸዋል" አለ በድሉ::

"የነሀጎስ ቅስቀሳና ሴራ መሆኑንማ መቼ አጣሁት በድሉ:: እንዴት መሰሪነታቸውን መገንዘብ ያቅተናል ብዬ እንጅ:: ጎበዝ አንደየ፣

ሁለትየ እንታለል:: ከዚህ ወዲያ እንዴት ስንታለል እንኖራለን? አእምሮ ቢኖረንማ የደርግም ድርጊት ትምህርት ሊሰጠን ይገባ ነበር::"

"ቆይ ታያላችሁ ያልተጫወቱባቸው እንደ ሆነ፣ አላምጠው፣ አላምጠው ነው እንደ አገዳ የሚተፍዋቸው" አለ በድሉ::

"በቀር ሲሾሟቸው፣ ሊሽልሟቸው ኖሯል:: በደርግ ጊዜ አንድ የተለመደ ነገር ነበር:: አንዱ የፖለቲካ ድርጅት ሲመታ ወደ ደርግ ልጥፍ እየተባለ ከቀን ተደርሶ ነበር:: እነሀጎስ ግን በዚህ መንገድ የሚጓዙ አይደሉም:: ዘር ለማንገስ ነው ጥረታቸው:: መመሪያቸው ከዘር ጋር የተቆራኘ ነው" አሉ ኮሎኔል:: እኔ ደግሞ እሳቸው ዘርን ሲያነሱ በእአምሮየ አንድ ነገር ተጫረብኝ:-

ዘረኞች በወቅቱ ዘርተው አበቀሉ፣
ምቀኞች ቀራችሁ አረም ስትነቅሉ::
የኑግ ፍሬ መስሎኝ አንስቼ ብቀምሰው፣
መጭ ሆኖ አገኘሁት እረግ የዛሬ ሰው::

ለጥቂት ጊዜ በመካከላችን ዝምታ ሰፍኖ ሳለ በድሉ ትንሽ በቀልድ ሊያዝናናን ፈልጎ አስቀድሞ እሱ ፈገግ በማለት "ጌታዬ ሊላምኮ አስገራሚ ነገር አለ" አላቸው::

"ምንድን ነው ደግሞ?" አሉ ወደሱ አፍጥጠው እያዩ::

"የሸምበል ብሩ ሚስት የተባለችው የጎርፉ ወዳጅ ሆና ተገኘች" ሲላቸው:-

"አትለኝም! እውነት ነው ጎርፉ?" አሉ ወደኔ በመዞር::

"ስመ ሞክሸም ልትሆን ትችላለች ጌታዬ::"

"የሰው ሚስት አባልገሃላ! እኔኮ እንደዚህ ያለህ አትመስለኝም ነበር:: የሚነዲድ አባል ሆንክ እንዴ?" ሲሉ ቀልድ ጨመሩበት::

"የለም ጌታዬ፤ የሰው ሚስት አላባለኩም:: የተባለችው ሴት የኔ ወዳጅ ከሆነች እሱ ነው የነጠቀኝ:: ከኔ ጋር ግንኙነታችን የቆየ ነው:: እሷ ከሆነችም ወዳጄ ትሆናለች እንጅ ሚስቱ አትሆንም:: ባል አግብታ በሰማኒያ መታሰር አትፈልግም::"

"ኤዲያ! ጅል፣ የሚስማማትን ስታገኝ ለምን አታገባም:: የጦሩ ብር ያለቀው ባንተ ወዳጅ ነዋ! በዚህ አይነትስ አንተም ከተጠያቂነት አታመልጥም:: በተዘዋዋሪም ቢሆን ሳይደርስህ አይቀርም::"

"በሚገባ ደርሶታል:: ጥርጥር የለውም" አለ በድሉ::

"ታዲያ ምን ትጠብቃለህ በድሉ? ይህን ጉድ ለሀጎስ ጠቁመህ ከዚህ አትገላገልም" ሲሉ ተሳሳቅን::

"ሁለተኛ ክፍለ ጦር ባንዱ የሻለቃ አዳራሽ ውስጥ የተካሄደ ሂስ ልንገራችሁ" አለ በድሉ አስቀድሞ ፈገግታውን በማድመቅ::

"እስቲ ንገረን፤ መቼም ጉዳችን ማለቂያ የለው" አሉ ኮሎኔል::

"ከዚያው አዳራሽ ውስጥ የሚወያይ ወዳጂ ነው ያጫወተኝ:: መቶ አለቃው የክበብ ሀላፊ ነው:: ሻለቃው ደግሞ የብርጌድ አዛዥ ነበሩ:: መቶ አለቃው ሻለቃውን ሲሄስ 'በየጊዜው የክበብ ገንዘብ አምጣ እያሉኝ እንቢ እንዳልላቸው ደግሞ አለቃየ ስለሆኑ በመፍራት የሚጠይቁኝን ገንዘብ እሰጣቸው ነበር:: ስለዚህ በማስታወሻየ እይዝ

ስለነበረ ጠቅላላ የወሰዱት ገንዘብ ሀያ ሺ. ብር ነው' ይልና ይሄሳል:: ሻለቃው በበኩላቸው መልስ ሲሰጡ:-

'ያለው ሁሉ ትክክል ነው:: አምጣ ስለው ይሰጠኝ ነበር:: ነገር ግን አንድ የቀረው ሂሳብ አለ:: አረስቶት ከሆነ እኔ አስታውሰዋለሁ:: ገንዘብ አምጣ እያልኩ እንደ ተጠቀምኩ ሁሉ ሚስትህንም አምጣልኝ እያልኩ ተጠቅሜባታለሁ:: ለሱ የማትገባ ቆንጆ ሚስት አለችው:: በግለ ሂሱ ወቅት ይህን ነስዛ ባለማውረዱ ቤቱን ይቅርታ እጠይቃለሁ' ብለው አርፍ" ሲሉን አዱኛና እኔ ስንስቅ ኮለኔል በሁለት እጆቻቸው እራሳቸውን ያዙና:-

"ሙተናል ጎበዝ! አለን ትላላችሁ! ለመሆኑ መጨረሻቸው ምን ሆነ በድሉ?" ሲሉ ጠየቁት::

"መጨረሻቸውማ ሁለቱም እስር ቤት ገቡ::"

"እንግዲህ ሚስቱ ለሆለቱም ስንቅ ታቀብላ!" ሲሉ እንደገና ሳቅን::

"በሉ ጎበዝ ልግባና ልተኛ" አሉና ተነስተው ሄዱ:: እራስ ምታት ሳይነሳባቸው አልቀረም:: እኛም ሻሂ ለመጠጣት ተነስተን ሄድን::

እራት ላይ ነበር ኮለኔልን ያየናቸው:: ተኝተው ሳይውሉ አልቀሩም:: ፊታቸው ክብድብድ ብሎ አይኖቻቸውም ቀልተዋል:: አላነጋገሩንም:: እራታቸውንም የረባ አልበሉ:: ትተውት ነው የወጡት:: አዱኛም ነክቶ ነው ትቶት የወጣው:: ያውም አጅሬ የሆዱ ነገር አይሆንለትም ነበር:: እኛም ስለነሱ ተጨነቅን::

እኔና በድሉ አረጋ ብለን እራታችንን በልተን ስንሄድ አዱኛ ከዘረንዳው ብቻውን ፊንጠር ብሎ ተቀምጦ ሲተክዝ አገኘነው:: ሄደን ከጎኑ ተቀመጥን:: ቀዝቃዛ ንፋስ በርጋታ ሽው እያለ ያልፋል:: ሁለታችን ስንነጋገር እሱ ዝግት እንዳለ ነበር:: ለማበረታታትም ተቸገርን:: ህመሙ የውስጥ ሆነ:: ወይ ግልፅ አድርጎ ምስጢሩን ቢነግረን ኖሮ ችግሩን በተጋራን ነበር:: ለመጠየቅ ደግሞ ከበደን:: በርግጥ አንድ ሰሞን እስመጋቢ መኮንን መሆኑን እናውቃለን:: ገንዘብ ያባክን አያባክን ግን የምናውቀው ነገር የለም:: ከሰሞኑ ሁኔታው ስናየው ግን ሳይባክንበት አልቀረም:: ሂሱን እንደ ጦር ነው የፈራው::

ቢጨንቀን አንዳንድ ጊዜ ወደ ሰማይ እናንጋጥጣለን:: ከተወለደች አራት ቀናት የሚሆናት ጨረቃ ማጭድ መስላ ከጠራው ሰማይ ላይ ተለጥፋ ትታያለች:: ጊዜውም ማጭድ ነው:: ጠማማ! አጭዶ የሚጥል፣ ከዋክብት ፍንጥቅጥቅ ብለው ፈክተዋል፣ እንደ ፈንዲሻ:: የኛ ፊት ግን አልፈካም:: ፍዝዝ ቅዝዝ ብሏል:: ጆሮዎቻችንን ብቻ አልፎ አልፎ ለድምፅ ማጉሊያው እንሰጣለን:: እለቱ ቅዳሜ በመሆኑ ካዲስ አበባ ጠያቂ ዘመድ የሚመጣላቸው መኮንኖች ይጠራሉ:: ከድምፅ ማጉሊያው አጠገብ አገርግረው ጥሪ የሚጠባበቁ መኮንኖች በርካታ ናቸው:: የሚጠሩት ደግሞ እየተጣደፉ ይሄዳሉ::

"ሙቶ አለቃ ጎርፉ እንደሻው! ባህል አዳራሽ ድረስ ዘመድ ይፈልግዎታል" ሲለኝ የደስታ ድንጋጤ ከተቀመጥኩበት አነጠረኝ::

"ዕጌ ነች!" አለ በድሉ ቀልጠፍ ብሎ::

"እንኳን ደስ አለህ" አለኝ አዱኛ ቀጥሎ:: ለሁለቱም መልስ ሳልሰጣቸው ፈጥኜ በመነሳት ተጣድፌ ሄድኩ::

"ከእንግዳ ማረፊያዋ መኝታ አዘጋጅለት:: እኔ አብሬው ልሂድ" በማለት በድሉ እሩጦ ደረሰብኝና "በፍቅር ተርበህ ነበር፤ ዛሬ ይለፍልህ" አለኝ በመንገድ ላይ እንዳለን::

"ተው አስቀድመህ ስሜቴን አታነሳሳው:: አክስቴም ልትሆን ትችላለች" አልኩት::

"በኔ ይሁንብህ ዕጌ ነች::"

ካዳራሹ ስደርስ አውቶቢሶቹ መቱን ተደርድረው ቁመዋል:: መርካቶ አውቶብስ መናኸሪያ ሆኗል:: ህዝብ ይንጫጫል:: ትርምሱ ሌላ ነው:: ታጋዮች ከግቢው በር ላይ በመቆም ያልተጠራ ወደ ውስጥ እንዳይገባ ይከላከላሉ:: እነ ኪዳዲድ፣ ሚነዲድ፣ እመዲድ ሰርገው እንዳይገቡ ነው:: ከውጭ እንዳይገቡ የተከለከሉት መኮንኖች ጭፍቅ ብለው ቁመው ወደ ውስጥ ይመለከታሉ:: ከውስጥ ደግሞ ካዲስ አበባ የመጡት እንግዶች ካዳራሹ በር ፈሰው ወደ ውጭ አፍጥጠው ያያሉ:: በመሀል አገናኞቹ ወደ ላይ ወደ ታች ሽርጉድ እያሉ:-

"እረጋ በሉ፤ እንዳትንቀሳቀሱ፤ ተጠርተውላችኋል፤ ካላችሁበት ድረስ እየመጡ ይወስዷችኋል" በማለት እንግዶቹን ያስተናብራሉ:: ጫጫታው ጆሮ ይጠልዛል::

"ሙቶ አለቃ ጎርፉ እንዳሻው መጥቻለሁ" አልኩት ከበሩ ላይ እንዳንገባ የሚከላከለውን ታጋይ:: የስም ዝርዝር የያዘበትን ወረቀት አየና በርሳስ ምልክት አድርጎ አስገባኝ:: በድሉ ከበሩ ቁሞ ቀረ:: ከነኪዳዲድ ጋር::

ካዳራሹ በር ላይ ያለው ትልቁ ፍሎረሰንት መብራት ግቢውን አድምቆታል:: የሳት እራቶች እሱን ከበው ይርገበገባሉ:: ብርሃን ፍለጋ ... እኛስ የሳት እራት ሆነን ቀርተን የለ ...

አይኖቼ በጉጉት ቃበዙ:: የልብ ምቴም ጨመረ:: እምር እምር ይልብኝ ጀመር:: አየኋት:: እንደ መብረክረክ አልኩ:: ያልጠበኳትና ያላሰብኳት በመሆኗ ይሆን የተብረከረኩት? የኔነሽ እስፋ ነች:: በመገረም ቁማለች:: ግርግሩ እንግዳ ነገር ሳይሆንባት አልቀረም:: ደግሞ ነጠል ብላ ብቻዋን ነው የቆመችው:: ካጠገቧ ልደርስ ስል እሷም አየችኝ:: ጥርሶቿ ተፈለቀቁ:: እኔም ፈገግ አልኩ:: ወዲያው:-

"የኔ ጎርፍ" ብላ እቅፍ ስታደርገኝ የሽቶዋ መአዛ እውድ አደተገኝ::

"ጎርፍዬ ደህና ነህ?" አለችኝ ተሳስመን ካበቃን በኋላ:: የለበሰችው ቀይ የባህር ማዶ ቀሚስ እንድኛዋን የበረሃ እንቁ አስመስሏታል:: በዚህ ላይ ልስልስ ብላ ለምጭታለች:: ድንገት ቅናት ወረረኝ:: ተሽቀርቅራ ሳያት አንዳች ነገር በአእምሮዬ መጣ:: ሻምበል ብሩ በመካከላችን እንደ ጋሬጣ ሲሳግ ታየኝ::

"ደህና ነኝ" አልኳት ጆነን ብዬ::

"እማዬ ትሙት፤ እውነትም ደህና ነህ:: የታሰርክም አትመስል:: አምሮብሃል" አለችኝ ያን ዘንቢል ቦርሳዋን ወደ ትከሻዋ ከፍ እያደረገች:: አትኩሬ ባየኋት ቁጥር ቅናት ደረጃውን ጨመረብኝ:: ሻምበል ብሩን ልትጠይቅ እንደመጣች ገባኝ:: እሱን ስታጣ ነው እኔን ያስጠራችኝ:: "ነይ እንሂድ" ለማለት ከበደኝ:: ዝም ብያት ቆምኩ:: ከግሯ ስር ዲብ የሚያክል አገልግል ጉብ ብሏል:: ለብሩ የመጣ ፍትፍት መሆን አለበት::

ፊቴ ጨርሶ ፈገግታ አጣ። እሷም ግራ እንደመጋባት ብላ አይናይኔን እየችኝ።

ከኔ በኋላ እየመጡ ቤተሰቦቻቸውን እየያዙ ይወጣሉ። እኔ ግን የኔ ያልሆኑትን ይገፉ ለመሄድ ከፋኝ ከበደኝ። ደግሞስ የተገናኘነው ድንገት ቢሆንስ? እኔን ያስጠራችኝ ፅጌ ብትሆንስ? እንደ ገና መንገደኞቹን አስተዋልኳቸው! የለችም። ወደሷ መለስ አልኩና:-

"አንቺ ነሽ እንዴ ያስጠራሽኝ?" አልኳት። ድንገት ነበር ካፌ ያመለጠኝ።

"ሌላ የምታስጠራህ አለች እንዴ?" አለች ፊቷ ስብስብ ብሎ።

"ማለቴ... " ብዬ ለመናገር ያሰብኩትን ሳልጨርስ አቋረጠችኝና:-

"እማዩ ትሙት እንዳታስቀይመኝ። ምን ለማለት እንደፈለክ ገብቶኛል። ደግሞ የመጣሁት አንተንም ለመጠየቅ ነው። ለሁሉም በኋላ እንደርስበታለን። አሁን ደክሞኛል! ወደምትወስድበት ውሰደኝ" አለችኝ በትዛዝ መልክ። ከግሯ ስር ያለውን አገልግል አንስቼ በመሸከም:-

"በይ ነይ" ብያት ቀደም አልኩ። በርሳዋን ወደ ትከሻዋ ከፍ አድርጋ ተከተለችኝ። ከውጭው በር ስንደርስ:-

"ምነካህ? ዋልክሳ?" አለኝ በድሉ የኔነሽን ሰረቅ አድርጎ እያየ።

"ከውስጥ ያለው ትርምስ የወግ መሰለህ እንዴ? 'አልኩትና' 'የኔነሽ አስፋ' ብዬ ሳስተዋውቀው ደንገጥ አለና እጇን ጨበጣት። ከዚያም አገልግሉን ተቀበለኝና:-

"እናንተ ቀስ ብላችሁ ኑ! እኔ ልሂድ" ብሎን ነጠቅ ነጠቅ እያለ ተራመደ።

"ይህን ሻምበል አውቀዋለሁ" አለችኝ።

"የት በታ?" አልኳት።

"ከመቶ አለቃ ለሜሳ ሰርግ ላይ።"

"መቶ አለቃ ለሜሳ የባልሽ ጓደኛ?" ድንገት ቅናት ብልጭ አለብኝ።

"እማዩ ትሙት! እንደዚህ እንድትለኝ አልፈልግም 'ባለቤትሽ' የምትለኝ ድረኸኛል እንዴ?"

"አዳራሽ ሙሉ ህዝብ በተሰበሰበት ነው 'ሚስቴ ነች' ብሎ የወሸከተልሽ። ደግሞስ ከተጋባችሁ ምን አሳፈረሽ? ይኸው ልትጠይቂው መጥተሽ የለም እንዴ?"

"በቃ ዝጋ" አለችኝና "አዛባ! እሱም ብሎ ባለሚስት!" አለችው። እንዲህ ስትለው ደግሞ ደስ አለኝ። ንቃዋለች ማለት ነው።

ዝም ተባብለን ትንሽ እንደ ሄድን ቆም አልኩና "አንድ ስህተት ሰርተናል!" ስላት:-

"ምንድን ነው?" አለችኝ።

"ሻምበል ብሩ የታሰረው ወደ ኋላችን ነው። አገልግሉን እንኳን አቀብለነው የምንመጣውን" አልኳት። ሆንብዬ ነበር ደህን ጥያቄ ያነሳሁት።

"ለሱ አይደለም ያመጣሁት። ላንተ ነው። ደግሞ አንድ ከረጢት በሶ ሰጥቼዋለሁ። ያን እየበጠበጠ ይጠጣ" አለችው በንቀትና በግዴለሽነት አነጋገር።

"አይተሽዋል እንዴ?" አልኳት እንደገና ንዴት እየመጣብኝ።

"አዎን" ስትለኝ:-

"እሱ እስረኛ ስለሆነ እንደ ማታገኝው ስታውቂ ነዋ እኔን ያስጠራሽኝ?" ስላት ቆም አለችና:-

"እማዩ ትሙት ጎርፉ! በምን ተጣለችኝ እንዳትል! መኝታ አጥቼ እንዳይመስልህ እንተን ያስጠራሁህ። ለእስረኞች ቤተሰቦች ተብሎ አዳራሽ ውስጥ ተዘጋጅቶ ነበር። ከዚያ ማደር እችል ነበር" አለችኝ። የድምፅዋ ቃና እንደ መሰበር አለ።

"በይ አሁን እንሂድ" አልኳት እንደ ገና ለዘብ ብዬ! አሳዘነችኝ። ካባቴ የሸምብራ ማሳ ያገኘኋት አደረኳት።

ወደ መኝታ ክፍል ይገፕት ልገባ ስል "ወደዚህ ይዘሃት ና" አለኝ በድሉ ከንግዳ ማረፊያዋ በር ላይ ቆሞ። አጠፍ ብለን ሄድን። ገና ክበሩ ስንደርስ የሰንደሉ ሽታ ተቀበለን። አዱኛ ደቻሳ ተፍ ተፍ ይላል። ወደ ውስጥ ስንገባ ደግሞ የኔ ፍራሽ መጥቶ በሚገባ ተነጥፍዋል። ግሩም ጫጉላ!

ካዱኛ ደቻሳ ጋር አስተዋወኳትና ከፍራሹ ላይ አስቀመጥኳት። ድካም ስለያዛት ነው መሰል ፍዝዝ ብላለች። እኔም ሳላስቀይማት አልቀረሁም። ምን ላድርግ! ቅናት አቃጠለኝ።

"አይዞሽ" አልኳትና ከጎኗ ተቀመጥኩ።

"ውሃ ጠማኝ" አለችኝ! ቀልጠፍ ብዬ በመነሳት ከመኝታ ክፍሌ ሄጄ ቀዝቀዝ ያለች የኮዳ ውሃ አምጥቼ ሰጠኋት። ሽምጥጥ አድርጋ ጠጣችና:-

"አሁ! ተቃጥየ ነበር" አለችኝ።

"እኔ ልቃጠልልሽ" ስላት:-

"ምን በወጣህ! እኔው ልቃጠልልህ እንጂ" ስትለኝ አቅፍ አድርጌ ከንፈሮቿን ሳምኳቸው።

"እማዩ ትሙት ባለጌ ነህ" አለችኝና ቶሎ ብላ ወደ በሩ አቅጣጫ አየች። እነበድሉ እንዳያዩን ብላ ነበር። እነሱ ደግሞ ቡና ለማፍላት ይጣደፋሉ። ወጣ አልኩና:-

"በድሉ! ሂድና ኮለኔልን ይዘሀቸው ና! ቡናም እንዲጠጡ" ብዬው ተመልሼ በመግባት ከጎኗ ተቀመጥኩ። ኩርትም ብላ በንግዳ ወግ ነበር የተቀመጠችው።

"ዘና ብለሽ ተቀመጭ" አልኩና ጋቢየን አለበስኳት።

አዱኛ ደቻሳ ከውጭ ቡናውን እደው እደው እያደረገ ሲወቅጥ የኔም ልብ አብሮ እድው እድው ማለት ያዘ። ትክ ብዬ እየኋት። ፈገግ አለችልኝ። እቅፍ አድርጌ ልስማት ስል ኮለኔልና በድሉ እየተነጋገሩ ገቡ። እሷም እኔም ቁመታችንን ሙሉ ተነሳንላቸው።

"እረ በግዜር! እንደምን ዋልሽ" በማለት ቀልጠፍ ብለው እጇን ጨበጧትና ተቀመጡ።

"አዲስ አበባ እንዴት ነው? ስለኛ ምን ይወራል?" አሏት ከተረጋጋን በኋላ።

"መስከረም ከጠባ እንኳን ስለናንተ ብዙም አይወራም" አለቻቸው።

"መረሳታችን ነዋ" አሉ ራሳቸውን ነቅንቀው::

እየተጫወትን አዱኛ ያፈላውን ቡና ከጠጣን በኋላ አጃችንን ተጣጥበን ያን የጤፍ ቂጣ የሚያክል እንጀራ ከፈትኩት::

"ሙቀቱ አበላሽቶት ይሆን?" አለች ሲጋ በማለት::

"ደህና ነው:: ምንም አልሆነ" አልኳት:: እንጀራውን ከላይ በፊያው አነሳሁለትና በማንኪያ ገመስመስ ሳደርገው እንቁላሉና መላላጫው ዝክንትሉ ወጣ::

"በሉ አንግዲህ" አልኩ አመቻችቼ ከመሀከላችን እያስቀመጥኩ::

"ጎርፉ! ይኸ ነገር እንዴት ነው?" አሉኝ ኮለኔል የኛ ድርሻ ብቻ ነወይ በሚል ያሸሙር ጥያቄ::

"ይጉረሱ ጌታዬ፤ ከዚህ የሚተርፍ የለም::"

"እኔማ ይገርለሁ:: ብይስቱ የኔመቤት፤ ጎርፉ አጉርሳት እስቲ፤ አልበላችምኮ" አሉኝ:: ከመላላጫው ልጩ በፍትፍት አጎረስኳት:: ልደግማት ስል:-

"እማዬ ትሙት በጄ አበላሁኝ" ስትል ተከላከለችኝ::

"ይችን ብቻ" ብዬ አስገድጄ አጎረስኳት::

ቆንጆ እሩት ነበር የበላነው:: ኮለኔል መራርቀው ሲወጡ ልንሸኛቸው እኔና በድሉ አብረናቸው ወጣን::

"አንተ ጎርፉ፤ ይችን እንክይ የመሰለች ልጅ አሳልፈህ ለብሩ ትሰጥ? የማትረባ!" አሉ በሽቀው::

"ጌታዬ፤ እሷም ባል ማግባት አትፈልግ:: እኔም ሚስት የሚባል ነገር አልፈልግ:: ሁለታችንም አስበንበትም እናውቅ::"

"ኢዲያ ጅል! ባል ማግባት ካልፈለገች ብሩን ለምን አገባችው? የሆነ ሆኖ ጠይቃዋለች?"

"አዎን፤ ጠይቃዋለች::"

"ባል የዛሬን መቼም የክብር እንግዳህ ነች:: ውሸን ያነሳ ውሸ፤ ነገ በሚት አሳፍረህ መላክ አለብህ:: ይኸ ነገር ይሰማና ደግሞ የሰረኛ ሚስት ይዞ አደረ ተብለህ እንዳትዋረድ:: በሉ አሁን ተመለሱ" ብለውን ሄዱ::

ተመልሰን ስንገባ ካዱኛ ጋር እረጋ ያለ ጨዋታ ይዘው ነበር:: "አዱኛ! እኛ እንሂድ፤ መንገደኛ ነች፤ ትረፍበት" አለ በድሉ እንደ ቆመ::

ሁለቱ ሲወጡ ተከትያቸው በመውጣት ሸኘት አድርጊያቸው ተመለስኩ:: ስገባ ደመና ገልባ የወጣች የምሽት ጨረቃ መስላ ጠበቀችኝ:: ልብሷን አውልቃ በውስጥ ልብስ ብቻ ነበረች:: በሩን ቀረቀርኩትና እኔም ተጣድፌ ልብሴን አወለኩና ተስገብግቤ ጥምጥም አልኩባት::

"እስቲ ቀስበል፤ በመጀመሪያ ሳመኝ" አለችኝ፤ ከንፈሮችዋን ሳም አደረኳቸው:: ትንሿ አንገቷል ከጣራው ተንጠልጥላ ዘቅዝቃ ታየናለች::

"ቅድም አስቀየምኩኝ አይደል::"

"ምን ብዬ?"

"ብሩን ነው ልትጠይቂ የመጣሽው ብለህ::"

"ይህን ተይውና እስቲ እንዴት እንደ ተገናኛችሁ ንገሪኝ:: እውነት ተጋብታችኋል?"

"ሚስቴ ነች አለ እንዴ?"

"አዎን:: መከንኖቹ በተሰበሰቡበት 'በባለቤቱ ስም ሚኒባስ ገዝቻለሁኝ' አለ ስላት:-

"ከርሳም! ይህን ሁሉ ምን አስለፈለፈው!" አለች ተቆጥታ:: ቀጠል አድርጋ "እኔ ደግሞ ሰው መስሎኝ ድንገት እኔን 'ገንዘብ ከየት አምጥተሽ ገዛሽ?' ብለው የጠየቁኝ እንደ ሆን አልኩልህና ድሬዳዋ ሄጄ አክስቴን አማከርኳት:: 'ምንም ችግር የለበት፤ እኔ ገንዘብ ሰጥቸሽ እንደገዛሻት ማስረዳት ነው' ብላኝ ይህን ሁሉ ጨርሼ እመጣልሃለሁ አጅሬ አምኗል:: እማየ ትሙት ወንድ አይደለም!

"መቼ መሰለህ የሱን ወንድነት የታዘብኩት? ኢህአዲግ አዲስ አበባ በገባ ማግስት 'መሳሪያችሁን አስገቡ' ብሎ በሬዲዮ ጥሪ ሲያደርግ ለምን ጧት ክላሹንና ሽጉጡን ይዞ አይነሳልህም:: 'እረ በፈጠረህ! ሲሆን ሁሉቱንም አታስረክብ፤ አስረክባለሁ ካልክም ባይሆን ሽጉጥህን አስቀር' ብዬ ለመንኩት:: እማየ ሳትቀር 'እረ ነውር ነው ልጄ! ወንድ ልጅ መሳሪያውን ተሸክሞ ወስዶ እንክ አይልም::' ብትለው ሰምቶን ነው! ወስዶ አስረክቦ መጣ::

"ይገርምሃል፤ በፊት 'አንቺን ቀና ብሎ የሚያይ ወንድ ባፉ ነው የማጎርሰው! አንቺን ደግሞ ከቂጥሽ ላይ ነው የማቀምስሽ!' እያለ በሽጉጡ ያስፈራራኝ ነበር:: ለካ ቡካቲያም ኖሯል" ስትል ብሽቅ ብሏት ተናገረች::

"ሰማኒያ አስራችሁ ኖሯል?" ስል ነካ አደረኳት::

"የምን ሰማኒያ? እረ እባክህ ተወኝ" ብላ ከተኛችበት እንደ መገላበጥ ስትል የጡቶቿን መሀል እየሁት::የጧት ሙራ የፈነጠቀበት መስሏል::

"መቼስ ከመሬት ተነስቶ ሚስቴ ነች አይል::"

"ባጋጣሚ ተገናኘን፤ ከዚህ በኋላ በጉልበቱ ገብቶ ጉብ አለ:: ግንኙነታችን ይኸው ነው::"

"እስቲ ከመጀመሪያው ስለግንኙነታችሁ ንገሪኝ?"

"ምን ያደርግልሃል?"

"ባውቀው ደስ ይለኛል:: አንቺ የፍቅር ሰው እንጅ የትዳር ሰው አይደለሽም:: እንዴት ሊያጠምድሽ ቻለ? በፍቅር አንበርክኮሽ ነበር ማለት ነው?" ስላት:-

"ድንቄም ማንበርከክ!" ብላ የታች ከንፈሯን ለጠጥ ስታደርገው በከንፈሮቼ እንቅ አድርጌ ምጥጥ አደረኳት:: ወደ ሰውነቱ ጥብቅ አለችልኝ::

"ምናለ የኔ ሆነሽ ብትቀሪ!"

"አሁንስ ያንተ አይደለሁ:: የማን ሆንኩብህ?"

"የብሩ ሆነሻል::"

"አይት ይብረር ስሙን አትጥራብኝ!"

"ውሸትሽን ነው:: ትወጅዋለሽ::"

"እማየ ትሙት ካንተ አላደርሰውም:: ከሱ አብልጬ እንደምወድህ ማረጋገጫ ልስጥህ"

"እስቲ ስጭኝ::"

"ኢህአዲግ የገባ ጊዜ እኔና አንተ አሊቤርጎ ለሶስት ቀናት አልቆየንም? እየውልህ፤ ያኔ ብሩ ከቤት ትራስ አቅፎ ያድር ነበር:: እስከዚህ ነው የማፈቅርህ:: አሁን ሳመኝ" አለችኝ:: ጉንጮቿን ሳምኳቸው::

ባክነን ባክነን ክንፋ እንደተመታ እሞራ ተዘረርነው:: ላብ በላብ ሆነን ነበር:: በጀርባየ ጋደም ብያለሁ:: እሷ ከጎኔ ለጠፍ እንዳለች ነው:: ድንገት አይኖቿን ሳይ ዕጌ ጥርሶቿን ብልጭ አድርጋ በአእምሮየ ሽው ብላ አለፈች::

"ሆለታ እንኳን መጥተሽ ሳትጠይቂኝ ቀረሽ:: ለነገሩ እኔም ጠያቂ አላጣሁም" አልኳት ኮራ ብዬ::

"ማነች የጠየቀችህ?" ስትል ከወደራሷ ቀና አለች::

"ዕጌ ነች::"

"የማናት ዕጌ?" ስትል ግንባሯን ሰበሰበችው::

"አታውቂያትም:: ፍቅረኛየ ነች::"

"እማየ ትሙት ቅሌታም ነህ" በማለት ኩርፍ ብላ ፊቷን በማዞር ተጠቅልላ ተኛች:: ስለቀናችልኝ ደስ አለኝ::

"ተቀየምሽ እንዴ የኔ?" ብዬ ከወደ ፊቷ ገለጥ አደረኳት::

"በቃ ዝጋ! እማየ ትሙት አበሸከኝ:: የማናባቷ ዕጌ ነች? ዕጊረዳዋ ይርገፍና!"

"አትስደቢያት::"

"አፍቅረሃታል ማለት ነው?"

"በሚገባ እንጂ" ስላት ለትንሽ ጊዜ በዝምታ አስተዋለችኝና:-

"እማየ ትሙት እንዴት ሞኝ ኖሬአለሁ:: ከኔ ሌላኮ ሴት የምታፈቅር አይመስለኝም ነበር::" አለች በመገረም::

"አንቺ ከኔ ሌላ አፍቅረሽ የለ እንዴ?"

"በቃ ዝጋ!" ብላ እንደ ገና ተጠቅልላ ልትተኛ ስትል እቅፍ አድርጌ አስቀረኳትና ሳም አድርጌ አባበልኳት::

"ኃርፋዬ ለምንድነው ግን የምታስቀይመኝ?"

"እይዞሽ:: ስለማፈቅርሽኮ ነው::"

"አሁንማ ከኔ የበለጠች አግኝተሃል:: እማየ ትሙት አትደልለኝ::"

"የኔ ሙች አልደልልሽም::"

"ለመሆኑ ስራዋ ምንድን ነው?" ስትል ጠየቀችኝ::

"ቡና ቤት ነው የምትሰራው" ስላት ከት ብላ የንቀት ሳቅ ሳቀችና:-

"ቅልስልስ! ቡና ልትጠጣ ገብተህ ስትቅለሰለስ አግኝታሃለች ማለት ነዋ? እማየ ትሙት ኤድስ አስያዝከኝ" አለችኝ ፊቷን በመጠየፍ አይነት አኮፍታ::

"አንቺ እንደ ምታስቢው የቡና ቤት ሴቶች ብቻ የኤድስ በሽታ አስተላላፊዎች አይደሉም:: አንቺም፤ እኔም ባንድ እስካልተወሰን ድረስ

የበሽታው አስተላላፊዎች ነን" ስላት ዝም አለችኝ:: እኔም ለትንሽ ጊዜ ዝም ብዬ ቆየሁና:-

"ከብሩ ጋር እንዴት እንደተገናኛችሁ ንገሪኝ ብየሽ ነበር?" አልኳት ቀስ ብዬ::

"አንተ በመጀመሪያ ዕጌን እንዴት እንዳገኘሀት ንገረኝና?"

"እኔማ አንቺኑ ፍለጋ ከሆለታ ተነስቼ አዲስ አበባ ሄጄ ስልክ ብደውል 'የለችም ሆለታ ሄዳለች' ተባልኩ:: ለካ ብሩን ጥየቃ ኖሯል የሄድሽው:: በዚህ ተናድጄ ካንድ ቡና ቤት ጎራ አልኩኝ:: ከዚያ ዕጌን አገኘሁኝ:: አብረን አደርን:: በሳምንቱ ሆለታ መጥታ ጠየቀችኝ:: ባጭሩ የግንኙነታችን ሁኔታ ይኸው ነው::"

"እሽ ማደሩንስ ይዘሃት አደር፤ እንዴት ታፈቅራታለህ?"

"ይኸ ከባድ ጥያቄ ነው:: ቢደንቅሽ ገና ሳያት ነው ያፈቀርኳት::"

"አሁን ከኔ አብልጠህ ታፈቅራታለህ?"

"ይኸም ከባድ ጥያቄ ነው:: አልመልሰውም:: ልዋሽሽ ደግሞ አልፈልግም::"

"እማየ ትሙት ጠልተሽኛል:: ገና ስታገኘኝ ጀምረህ ነው በነገር የጠዘጠዝከኝ:: ከድሮው የተለየ ፀባይ ነው ያየሁብህ:: በፊት ብትቀናብኝም እኔን ማስቀየም አትፈልግም ነበር:: ዛሬ ግን ሆን ብለህ ነው የምታበሽቀኝ::"

"የኔ ሙቺ:: አንቺን ሆን ብዬ ለማብሸቅ አላማ የለኝም::"

"አሁን ከዚህ ስትሄድ ከዕጌ ትሄዳለህ?"

"ብሄድም እንደማትቀየሚ ተስፋ አለኝ:: ምክንያቱም አንቺ ባለባል ነሽ::"

"ዝጋ! ደግሰህ ድረሽኛል!" ኩርፍ አለች::

"የኔና የዕጌን ግንኙነት ነገርኩሽ:: በይስቲ ደግሞ ያንቺና የብሩን ግንኙነት ንገሪኝ::" አልኳት:: ትንሽ ዝም ብላ ቆየችና:-

"እየውልህ፤ የተገናኘነው ከመቶ አለቃ ለሜሳ ሰርግ ላይ ነው:: ባይኖቹ ነው የማረከኝ:: በእለቱ አድራሻ ተለዋውጠን ከሶስት ቀናት በኋላ ተገናኘን:: እኔ እንኳን ይህን ያህል አልነበርኩም:: እሱ ነው ሞትኩልሽ ያለው:: መቶ መቶ ብሩን ሲመዘው ያንድ ብር ያህል እንኳን አይቆጥረውም ነበር:: ከሽቶ ጀምሮ ከባህር ማዶ ከሚመጡ ምርጥ ልብሶች ባይነት አንዳንድ መሉ ልብስ ገዝቶልኛል:: ይኸ ሁሉ ሆኖ በፍቅር አላንበረከከኝም ነበር:: እማየ ትሙት፤ አንዳንድ ጊዜ የምሰራው ስራ ልክ አልነበረም:: እሱ ገንዘቡን እያፈሰሰ እኔ ሌላ ወንድ አማርጥ ነበረ" ብላ ፈገግ አለችና:-

"አንድ ጊዜ ታዲያ ስንዝናና አምሽተን 'ወደ ቤቴ ልሂድ' ስለው 'ካላደርሽ' ብሎ ችክ አለብኝ:: 'እናቴን አሚታል፤ አልሞክረውም'' ስለው 'እንግዲያው አብሬሽ ሄጄ እያቸዋለሁ:: አንቺንም አደርስሻለሁ' ብሎ በመኪና ይዞኝ ሄደ:: በርግጥም እማየን እሚት ስለነበር ጠይቋት ተመለሰ::

"በማግስቱ ከረፋዱ ላይ ብሩ ሆየ ሸንጥ ስጋ፤ ታናሽ ታላቅ፤ ፍራፍሬ ካይነት በመኪናው ጭኖ ከተፍ አይልልህም:: ደነገጥኩ:: ትንሽ

ሲያነጋግረን ቆይቶ ከሄደ በኋላ እማየ እንኳን ደንቋት 'ኖረሽ ኖረሽ ባሬ ገና ከትልቅ ሰው ወደቅሽ' አለችኝ። ከዚህ በኋላ እማየን ልጠይቅ እያለ ጧት ማታ ይመላለስልህ ጀመር። ከማየ ጋር ለምን ሰምና ወርቅ አይሆኑልህም መሰለህ። ቢሞት ባዶ እጁን አይመጣም።

"አንድ ቀን ምሽት ታዲያ እሱ እንደ ተቀመጠ ለምን ሀይለኛ ዝናብ አይዘንብልህም። ብሩ ሆየ ከዚያው እድር አለልህ። እየውልህ! ቤትን ለወንድ ልጅ ማሳየት ትርፉ ይኸው ነው።

"ሰንበትልህና 'ካልተጋባን' ብሎ ለምን ሙዝዝ አይልልህም። 'አርፈህ ተቀመጥ! እኔ ባል የሚባል ነገር አልፈልግም' አልኩት። እማየን መቆሚያ መቀመጫ አሳጣት። እማየ ደግሞ እኔን 'ብሩን ካላገባሽ' ብላ ጭቅጭቅ አደረገችኝ። አንድ ቀን ምርር ብዬ ስናገራት 'የጤናሽ አይደለም ልጄ ባል የሚያስጠላ ነገር' ብላ ጠብ እርግፍ አድርጋ ተወችኝ። እጅሬ ግን መች ተስፋ ቆርጦልህ። ጭቅጭቅ ሲያደርገኝ ጊዜ ከመስሪያ ቤቴ ያስር ቀን ፈቃድ ተቀበልኩልህና ድሬዳዋየ ጭልጥ። እሱን ሽሽት።

"ፈቃዴን ጨርሸ ስመለስልህ ለምን ተነፋፍቶ አይጠብቀኝም መሰለህ።

'የት ሄደሽ ነው?' አለኝ።

'የትስ ብሄድ አንተን ምን ያገባሃል!' አልኩት። ለምን በጥፊ አያጮለኝም መሰለህ። እማየ ትሙት ዘልየ ነው እንደድመት ፊቱን የቧጠጥኩት። ጉሮሮውን ደሞ ላንቀው ስል መንጫጫቀኝና ወጥቶ ሲሄድ ከበሩ ድረስ ተከትየ 'ዳግመኛ ከዚች ቤት ብትመጣ ትዋረዳለህ' ብዬ አስጠነቀቅኩት።

"ዳግመኛ ብቅ አይልም ስል በማግስቱ ከመስሪያ ቤት ስመጣልህ ባለቀለም ቴሌቪዥን ለምን ጉብ ብሎ አይጠብቀኝም መሰለህ። 'የማነው?' ስላት እማየን 'ሻምበል ብሩ ነው ያመጣው። ትናንት የኔነሽን አስቀይሜያታለሁ። ካሳ ነው የገዛሁላት ብሏል። ልጁ አሁን ይመጣል! ፊት እንዳትነሺው። የወንድ ልጅ ጡር መጥፎ ነው።' ብላ ተማፀነችኝ።

"እየውልህ! ማታ ሲመጣ ፈገግ ብዬ ተቀበልኩት። በይቅርታ መልክም ተሳሳምን። ከዚህ በኋላ ብሩ ሆየ ቀስ እያለ በመለሳለስ ጓዙን አንድ ባንድ እያንጠለጠለ በመምጣት ተጠቃሎ ቁጭ አለልህ። እንዲህ ሲል ቆየልህና ባለፈው አመት በኔ ስም ሚኒባሷን ገዛልህ። ከዚህ በኋላስ እኔም ስከን አልኩና ከሱው ጋር ለጠኩኝ። ታዲያ ምን ይሆናል! ኢህአዴግ ገብቶ ነገሩን ሁሉ ፍርስርስ አደረገው! እንጀቱ ይፍረስና!

"ብሩ ሆየ አድፍጦ ቆይቶ ለሶስት ቀናት ያህል ሆስታ ገብቶ ነበር። ልጠይቀው ብሄድ ወደ አዲስ አበባ ሊመጣ መኪና ሲጠባበቅ አገኘሁት። 'ምነው?' ብለው፦

'መጥፋት አለብኝ' አለኝ።

'ነፍስ አጥፍተሃል እንዴ?' ስለው፦

'ከነፍስ የበለጠ የመንግስት ገንዘብ አጥፍቻለሁ። ይህንን ያህል ልልሽ አልችልም' አለኝ። እንደ ፈረደብኝ ከሱው ጋር ተመለስኩ።

"እንዲት አክስት አሉት፤ ከሳቸው ጋር ለትንሽ ቀን ደህና አድፍጦልህ ሳለ ጨለም ሲልለት እየመጣ ማደር ያዘልህ። 'ተው

ካክስትህ ቤት ተቀመጥ' ብለው አልሰማኝ አለ። ማን እንደ ጠቆመበት አላውቅም ከሌሊቱ ስድስት ሰአት ሲሆን የቤቱን በር እንኳኩተው በማስከፈት አንጠልጥለው ይዘውት ሄዱ። ጧት እሱን ይዘው መጥተው ቴሌቪዥኑንና አስቀምጭ ያለኝ መቶ ሺ ብር ነበር እሱን አስረከበ። ቤቱን በፍተሻ ምንቅርቅር አደረጉት። እንጀቴን ነው ቁርጥ ያደረጉት። ኧረ እነዚህን ኢህአዴጎችስ ይንቀላቸው! በሰው ጉሮሮ ሳንጃ የሚሰኩ! ከዚያ ወደዚህ አንጠልጥለው አመጡት እልሃለሁ። ከዚህ ሌላ የምትፈልገው ነገር አለ?" አለችኝ።

"ባክነሽ ባክነሽ ከብሩ እጅ ላይ በመውደቅሽ በጣም አዝንልሻለሁ። እንቺን ተጋራኝ ብዬ ሳይሆን እቅድ የሌለው ዝፍጥ ነው። መኪናና ቴሌቪዥን የገዛልሽ ስላፈቀረሽ ከጁ እንዳትወጭበት እንጅ እንደ ሰው ለመሆን ብሎ አይደለም" አልኳት።

"በል አሁን ልተኛበት! ደክሞኛል" አለችኝ አይኖቿ ግርብብ እያሉ።

እኔ ድክም ልበልላት። ጧት መነሳት አቅቷት ነበር። ላሳፍራት ወደ መኪናው ይገኑት ስሄድም እግሮቿ እስርስር ብለው ስትራመድ እንደ እግረ ተከል ልጅ ፍንግል ፍንግል እያለች ነበር። ተስፋም ሳትቆርጥ አልቀረችም። እኔም እንዲህ ሁና ሳያት አሳዘነችኝ። ቢጨንቀኝ፦

"አይዞሽ! አንድ ብለሽ አትበሳጪ። እኔ በቅርብ ቀን ስለምመጣ ለሁሉም እንመካከራለን" ስላት ፈጠን ብላ፦

"አንተን ነጥለው ይለቁሃል እንዴ?" አለችኝ።

"አዎን፤ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ትሄዳላችሁ ብለውናል" ስላት የከበዳት ነገር ትንሽ የቀለላት መሰላት።

"በል እሺ፤ እንደ መጣህ ደውልልኝ። ይች ዕኔ ከምትላት ብትሄድ ወዮልህ። እማየ ትሙት እንዳንጣላ"

"ግዴለሽም አንጣላም" አልኳት ፈገግ ብዬ።

አሳፍሬያት ተመለስኩ። ከንግዲህ የኔነሽ የኔ ትሆን ይሆን? ዕኔንስ እንዴት አደርጋታለሁ? ወደ ካምፕ ስመለስ አስብ የነበረው ይህንኑ ነበር።

የኔነሽ ... ዕኔ ... የኔነሽ ዕኔ ...

ምእራፍ አስራ አራት

«አልሆን ብሎ ነገሩ ሲጠጥር፣
ውጥረቱ እንዲላላ የላላውን ወጥር!»

37

እለቱ ሰኞ ነው:: ወደ አዳራሽ ስንገባ ፊታችን እንደ ጨፈገገ ነበር:: ይህን ሂስ ተሳቀነዋል:: ከዚህ ማት በሰላም የተገላገለ ትልቅ ሰው ነው::

ሀጎስ ሲጋራውን እያጨሰ ገባና ሰላምታ ከሰጠን በኋላ "የዛሬውን ሂሳችንን የምንጀምረው በምድር ጦር ጥገና ይሆናል:: በጥሞና ተከታተሉ" አለንና ሀያሲው እንዲነሱ ተደረገ:: ማአረጋቸው ሻለቃ ነው:: አጠር ያሉና ጥቁር ናቸው::

"ጓዶች፣ እኔ ለመሄስ የምፈልጋቸው መከንኖች የሉም:: ጠፍተዋል:: ነገር ግን ደባውን ለናንተ ለማሳወቅ ነው" አሉና ማስታዎሻቸውን ገለጥለጥ አድርገው አይተው:-

"የጥገና መምሪያ የወር የስራ ማስኬጃ መቶ ሺ. ብር፣ ፒቲ ካሽ አስር ሺ. ብር፣ የውሎ አበል አስር ሺ. ብር ሲሆን በድምሩ መቶ ሀያ ሺ. ብር ነው:: እንድም ቀን ግን በተገቢው ሁኔታ ተሰርቶበት አያውቅም:: ገንዘቡን ግን ባለስልጣኖች ይከፋፈሉታል:: አዛዡን፣ ፖለቲካ ሀላፊን፣ ደህንነትን ማን ይናገራል? ማንስ ሌቦች ናቸው ይላል? እነሱኮ ኮሚኒስቶች ናቸው::

"ሌላው ድራማ በምድር ጦር ጥገና እውቅ ጠጋኞች እያሉን ለሙብላት ሲባል በክፍሉ ቢጠገኑም ከሰስትና ካራት ሺ. ብር በላይ የማያስወጡትን ወደ አምቼ እየተላኩ ሰላሳና አርባ ሺ. ብር ተበልቶባቸዋል:: ይኸም ባልከፋ ነበር:: በዚያው ሰጥመው የሚቀሩት ብዙ ናቸው:: የማውቀው እስከዚህ ድረስ ነው» ብለው ተቀመጡ::

ቀጥሎ የቀረበው ሂስ በምድር ጦር ድርጅት መምሪያ ላይ ነበር:: እንድ ሻምበል ናቸው ሀያሲው::

"እንደሚታወቀው በ66 ዓ.ም. ጦሩን ካስቆጣውና ላመፅ ካነሳሳው አንዱ የቀለብ አቅርቦት ጉዳይ ነበር:: ደርግ ስልጣኑን እስኪያደላድል ድረስ የጦሩን ጥያቄ የመለሰ በማስመሰል ያዳ ነጭ ጤፍ፣ ንፁህ ምስር፣ ምጥን በርበሬ ... ለጦሩ እንዲቀርብ ተብሎ ከፍተኛ በጀት ይመደባል:: ነገር ግን በነጭ ጤፍ ፈንታ አበቁ የበዛበት ጥቁር ጤፍ፣ በምጥን በርበሬ ምትክ እርድና ሰጋቱራ ወይንም የንጨት ፍቅፋቂ ተቀላቅሎ እስከነ እግሩ እየተፈጨ ይቀርብለት ጀመር:: ነበዝ፣ ደርግና ከጎኑ ያሰለፋቸው ባለስልጣኖች ሀሊና የሚባል የላቸውም:: ከላይ የዘረዘርኩት ትርፍ የባለስልጣኖችን እንጀት ባለማጥገቡ ሌላ ዘዴ መጠቀም ነበረባቸው:: ይኸውም:-

"ለጦሩ የተዘጋጀው ቀለብ ወደ ተለያዩ ክፍሎች ሲላክ አንዱ ኩንታል መቶ ኪሎ መሆን ሲገባው እነ አጅሬ ግን ከያንዳንዱ ኩንታል

ላይ ሀያና ሰላሳ ኪሎ እየቀነሱ ጆንያውን እያጠፉ በመስፋት ግንባር ያለው ጦር በሙቶ ኪሎ ሂሳብ እንዲረከብ ይደረጋል:: የተቀነሰው ይሟላና እየተሰፋ ለመርካቶ ነጋዴ ይሸጣል:: በዚህ መልኩ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተዘርፍዋል::

"ይህ በእንዲህ እንዳለ በ77 ዓ.ም. ይህን ምስጢር የሚያውቁ በቅጣት መልክ ወደ ኤርትራ ይዛወራሉ:: ይህን ጉድም ከዚያ ላለው ጦር ይነግራሉ:: እስራሩንም ያሳያሉ:: በዚህ መሰረት ወደ ሰሜን የሚላክ ቀለብ እየተራገፈ እንድ ባንድ ሲመዘን በእጥፍ ጉድለት ያሳያል:: በዚህ የተነሳ ለመከላከያ ሚኒስቴር ሪፖርት ይደረጋል:: ሀገር መከላከያ ሚኒስቴርም ለምድር ጦር ደብዳቤ ፅፎ ድርጅት መምሪያ ኦዲት እንዲደረግ ያዛል:: ኦዲት ሲደረግም ከ69 ዓ.ም. እስከ 77 ዓ.ም. ድረስ ወደ ሌሎች የጦር ክፍሎች የተላከውን ሳይጨምር ወደ ሰሜን ጦር ግንባር ከሚላከው የተበላው እስራ አምስት ሚሊዮን ብር ነበር:: የሚገርመው ግን ተበላ ተባለ እንጅ የተወሰደ እርምጃ የለም::

"እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ነው ጦሩ በቁሙ ቆዳው ተገፎ ሲጋው የተበላው:: እንዲህ አይነት ግፍና በደል እየፈፀሙበት ነው 'አብዮታዊ ጦር ግንባሩን እያጥፍም!' ይሉት የነበረው:: እሱ ግን እንጀቱ ታጥፍዋል:: ጨርሻለሁ" ብለው ተቀመጡ::

ምድር ጦር ሙዚቀኛ ሻለቃም ከኛው ጋር ነበር የሚወያየው:: ነገር ግን መሰንቆ ወይንም ሳክስፎን ሸጧል ተብሎ አልተሄሰም:: ንፁህነቱን አድንቀናል:: ምድር ጦር መሃንዲስም ፍንክች አላለም:: ሌላው ለነህሳስ ያልተበገረው ሰላማዊ ፖሊስ ነው:: የግለሂሱንም ሆነ የሂሱን በር ክርችም አድርጎ ዘግቶ "እኛ የስራችን ፀባይ ከህዝቡ ጋር ስለሆነ ህዝቡ ያጋልጠን" ብሎ ቁጭ::

ባህር ሀይልም በመጀመሪያ ደህና ነበር:: በመጨረሻው ግን እነህሳስ ሞገድ ለቀቁበትና ተበሻቅጦ ቁጭ አለ:: ባህር ሀይላችን ከቀይ ባህር ማእበል ቢያመልጥም ከግቤ ጎርፍ አላመለጠም::

አየር ሀይላችንም በመጀመሪያ በሩን አልከፈተም ነበር:: ኋላ ግን ነፋስ በረገደበት:: እሱም ያው ቢራቢሮ ሆኖ አረፈው:: ብቻ ሁሉም ዝርጥርጡ ወጥቷል::

በዚሁ ሰአት ደረሰና ተበተነ:: መቼ እንሰባሰብ ይሆን? የነገው ሂስ ደግሞ በጣም ነው የተፈራው:: ገና ከማታው ጀምረን ነበር ወሬ ሽው ያለን:: መቶ አለቃ ዘከረ በበርካታ መከንኖች ላይ የሂስ በትሩን ለመሰንዘር ዝቷል አሉ:: ኦዲኛ ደቻሳ አዳር አላደረም፣ እንደ እቃሰተ ነው ያነጋው:: እኛም ቢሆን ስለሱ አምጠናል::

ቁርሳችንን በልተን ወደ አዳራሹ ስናመራ ልክ ጭር እንዳለች ዶሮ ተንክርፍፈን ነበር:: ገብተን ቦታ ቦታችንን ይዘን ተቀመጥን::

"ሰምታችኋል? ሂሱ ዛሬ ነው እሱ የሚያልቀው:: ያ-ጉድቢላ ፊት ዘከረም ይመጣል እሉ:: ሳያዋርደን አይቀርም" እሉን ኮለኔል ዘርጋው በሹክሹክታ አነጋገሩ::

"እሱ ከመጣማ ምኑን ተረፍነው ጌታዬ? እሱኮ ሰው ይገዞ ልሙት ያለ ሰው ነው" አላቸው በድሉ::

ባዳራሹ ውስጥ የሹክሹክታ ድምፅ ይሰማል:: ሁሉም አፍላፍ ገጥሞ ያቀኩቱካል:: ከመስንበቻው ለየት ያለ ሁኔታ ነው የሚታየው:: የሁሉም ፊት በርግጓል...

ሀጎስ ትንሽ ዘግየት ብሎ ነበር የገባው:: እሱ ከመቀመጡ መቶ አለቃ ዘከረ ባንድ ታጋይ እየተነዳ ገባ:: ልክ ከጫካ ውስጥ ድንገት ብቅ እንዳለ አስፈሪ አውሬ በደነበረ አስተያየት አየነው:: እውነትም ኮሎኔል እንዳሉት "ጉድቢላ ፊት ነው!" ፍልጉድጉድ ያለ ጉድ ፍጥረት:: ከሀጎስ ፊትለፊት ካግዳሚ ወንበር ላይ እንዲቀመጥ ተደረገ:: ከዚያም ሀጎስ ከተቀመጠበት ተነሳና:-

"በዛሬው እለት ሂሱን እናጠናቅቃለን:: ስለዚህ አንዳንድ በስነምግባር ብልሹነት የታወቁ መኮንኖች አድፍጠው ስላሉ እነሱን በማጋለጡ በኩል እርብርብ ማድረግ አለባችሁ:: ትምህርቱን በዚህ ሳምንት ውስጥ ስለምንጀምር ከዚሁ ነፅታችሁ መሄድ አለባችሁ:: አብሮ መብላትና መጠጣት ወይንም በጓደኛነት በይሉኝታ መታፈን የለባችሁም:: አሁን ወደ ሂሱ እንገባለን:: በቅድሚያ መቶ አለቃ ዘከረ በመኮንኖች ላይ ሂስ አለኝ ስላሉ በመካከላችን ይገኛሉ:: መድረኩን ለሳቸው እለቃለሁ" ብሎ ሲቀመጥ ሲል:-

"ከዚያ በፊት ማሳሰቢያ አለኝ" በማለት አንድ ሻምበል ተነስቶ "በማጋለጡ በኩል 'እርብርብ ማድረግ አለባችሁ' ሳልከው በበኩላችን የተረባረብን ይመስለናል:: በምዝበራ፣ በነፍስ ግድያ፣ በስልጣን ያላግባብ የባለጉትን ከሞላ ጎደል አጋልጠን ሰጥተናል:: ተሸፋፍነው ያሉም ካሉ ወደፊት ቀስ እያልን እናወጣቸዋለን:: አንድ ነገር ግን መታወቅ ያለበት ይመስለኛል:: በዘመነ ደርግ ይኑሩም ይብዛ፣ ለመኖር ሲባልም አብሮ ያልበላና አብሮ ያልጠጣ የለም":: ተነካክቷል:: ባይዘርፍም ሲዘርፍ አያየ ዝም ብሏል:: ባይገድልም ሲገደል አይቷል:: ባያምንበትም ሲያጨበጭቡ አጨብጭቧል:: የደርግን አላማ ደግፎ ግራዱን በማውጣት መፈክር ያላሰማ፣ ይውደም፣ ያላለ የለም":: ታዲያ ይህን ሁሉ እንሰር ካላችሁ ቀለብም፣ የማሰሪያ ቦታም አታገኙም:: ይህን ነገር ልታስቡበት ይገባል::

"ደርግ በመጀመሪያ ስልጣን እንደ ያዘ አንድ አይና ኢትዮጵያ ስሎ 'እስር ቤቶች ሁሉ ትምህርት ቤቶች ይሆናሉ' ብሎን ነበር:: ዋል አደር ብሎ ግን የወረሰውን ቤት ሁሉ እስር ቤት አድርጎት ነበር:: እናንተም ስትገቡ 'ሰላምና መረጋጋት' ብላችሁ ነበር:: መልሳችሁ እራሳችሁ በማደፍረስ ይችን አንዲት አይና ኢትዮጵያ ጨርሳችሁ እንዳታጠፋዋት:: ግለሰቦች ስህተት ላይ እንዳይጥሏችሁ መጠንቀቅ አለባችሁ:: ደርግን መቀመቅ ያገቡት ግለሰቦች ናቸው:: የግለሰቦችን ጥቆማ ብቻ ይዛችሁ ሰው ያላግባብ ባታስሩ ጥሩ ነው:: ለማንኛውም ማሰር መፍትሄ አይሆንም:: ማሰርና መግደል መፍትሄ ቢሆን ኖሮ ደርግ አይወድቅም ነበር:: ከሱም ውድቀት መማር አለባችሁ:: ጨርሻለሁ" ብሎ ሲቀመጥ ሀጎስ ቀበል ብሎ:-

"ተገቢ ማሳሰቢያ ነው:: ተቀብየዋለሁ:: በዚህ ነገር ላይ አሳብ አይግባችሁ:: ተጠቁሞበት ወይንም ሂስ ተካሂዶበት ቢታሰርም መኮንኑ የሚሆነው ነገር የለም:: እኛ ማጣራት እናደርጋለን:: አሁን ጊዜ ሳናባክን ወደ ሂሱ እንግባ:: መቶ አለቃ ዘከረ ይነሱ" አለው:: የቸኮለ ይመስላል:: ዘከረም ቀልጠፍ ብሎ በመነሳት ፊቱን ወደኛ አዙሮ በመቆም ከኪሱ

ወረቀት አወጣና:- "ጓዶች! እንደ ምታስታውሱት እኔ የታሰርኩት በቅፅ መሙላት ወቅት ነበር:: ከኔ የበለጠ የመዘበሩ ግን እስካሁን አድፍጠው ተቀምጠዋል:: ግለሂስም ያወርዳሉ ብዬ ጠብቄያቸው ነበር፤ አላወረዱም:: በሂሱ ወቅትም እስበሳቸው ይገላለጣሉ ብዬ ነበር፤ ተሸፋፍነው ፀጥ አሉ:: ዛሬ እኔ አወጣቸዋለሁ" አለና አይኖቹን ዘወርወር አድርጎ አዳራሹን ቃኘው:: ፀጥ ብለን ወደሱ አፍጥጠናል:: ጎንበስ ብሎ የያዘውን ወረቀት አየና:-

"ከዚህ ቀጥየ ስማችሁን የምጠራው ወደዚህ ትወጣላችሁ" አለ በትእዛዝ መልክ:: ተስፋ የቆረጠ ይመስላል:: ሀጎስ ደግሞ ለማስተናበር ተነስቶ ቆመ:: ወዲያው መጥራት ያዘ:: የተጠሩት እየሄዱ አገርግሬው ቆሙ:: ሁሉም ዘለው ሲያንቁት የከጀሉ ይመስላሉ:: በመጨረሻው:-

"ሻምበል አዱኛ ደቻሳ!" ሲለው ጠረጴዛውን በቡጢ ደልቆ ብድግ ብሎ ሄደ:: አምሳ ሰባት መኮንኖችን እየጠራ አወጣቸው:: ኋላማ ጠቅላላችን እራድን::

ከዚህ በኋላ ተጋፊው ከጀርባ ካለችው ክፍል ታጎሩ:: ክፍሏ ጠባቸው ፀጉራቸውን እየነጩ ይንጫጩ ጀመር::

"ይበሉ መቶ አለቃ ዘከረ በያንዳንዳቸው ላይ የሚያውቁትን ሂስ ያቅርቡ" አለው ሀጎስ::

"ጠሩን የሚያስመግቡ መኮንኖች ዱቄትም፣ ስኳርም፣ ጨውና ሽንኩርት ሸጠው ተጠቅመዋል:: የክበብ ሀላፊ መኮንኖች ደግሞ ስኳር፣ ሻሂ ቅጠል፣ ቢራና አልኮል መጠጥ ከማከፋፈያ እያወጡ አየር ባየር ሸጠው ተጠቅመዋል:: ጠሩን የሚቆጣጠሩ መኮንኖችም ጉቦ እየተቀበሉ ድሬዳዋ በመላክ ሳልባጅ ሳይቀር እያስነገዱ ትርፍ ሲጋራ ይጠቀሙ ነበር:: የደመወዝ ትኬት ሰጭ መኮንኖች ከወታደር ላይ ከ10-20 ብር፣ ከመኮንኖች ላይ ደግሞ እስከ 50 ብር ድረስ ጉቦ ሳይቀበሉ የደመወዝ ትኬት አይሰጡም" እያለ ሲተነትን ከመሀል አንድ መቶ አለቃ ብድግ ብሎ:-

"እውነቱን ነው፤ እኔን ሰላሳ ብር በልተውኛል!" ሲል እኛ አውክተን ሳቅን:: እስካሁን ሌላው ሌላው ሲያልቅብን ጭብጨባና ሳቅ አላለቀብንም:: ጭብጨባው ልማድ ሆኖ ነው:: ሳቁ ግን የብሽቀትም፣ የመገረምም ነው::

ዘከረ ዘክዝኮ ሲጨርስ ከጀርባ የተዘከዘከባቸው፣ "እኛም በሱ ላይ ሂስ አለን" እያሉ ተንጫጩ:: ሀጎስ ወደነሱ መለስ ብሎ እያየ:-

"ለጠቅላላችሁ እድል መስጠት አልችልም:: ለሁለት መኮንኖች ብቻ እንዲናገሩ እፈቅዳለሁ" አለና ሻዱኛ ደቻሳና ላንድ ሻምበል ፈቀደላቸው:: ወዲያው እየተወራጩ ከጉሬኖዋ ወጡና በቅድሚያ አዱኛ እንዲናገር ተፈቀደለት::

"ጓዶች፤ መቶ አለቃ ዘከረን የምታውቁ ታውቁታላችሁ:: እልም ያለ ሌባና ዘራፊ ነው!" በማለት እጁን ወደኛ እወናጭፎ ሲናገር ሀጎስ አቋረጠውና:-

"ዋእ! ሻምበል፤ መሳደብ አይችሉም! ባግባቡ ነው መሄስ ያለብዎት!" በማለት ሲያስጠነቅቀው::

"እኔን ዘርፍዋል ብሎም አይደል ክዚህ የገተረኝ! ማእረግ የሰጠኝ መሰለህ? ሌባ ነው! ጠብደል ሌባ!" አለ ወደ ሀጎስ ዞሮ ጥርሶቹ እየተንገጫገጩ! ከዘከረ ላይም ዘሎ ለመከመር ከጅሎት ነበር።

"ዋእ! በቃሥት" ብሎ አቋረጠውና ያኛው ሻምበል እንዲናገር ተደረገ።

"ጓዶች! መኮንኑ ባካፋ ዝቆ በማንኪያ ጨልፎ በመስጠት የራሱን ጉድ የተገላገለ መስሎት እንጂ እኔ በበኩሌ አምስት ሳንቲም አልተጠቀምኩም። እሱ ግን ቀደም ሲል በታጠቅ ብሄራዊ ማስተናገጃ የድርጅት መኮንን ሆኖ ሲዘርፍ ለበርካታ አመታት ቆይቷል። በዚህም አብልቶ በመብላቱ ስንት ብስለት ያላቸው መኮንኖች እያሉ ማስተናገጃው ባዷስ ሲዋቀር ሹመት በሹመት ሆነ። ያውም የሚሰራበት ሳይሆን የሚበላበት እየተመረጠ።

"የስአሰ የድርጅት መኮንን፣ የክበብ ሀላፊ፣ የሚገስ ቤት አስመጋቢ፣ ግዥ ክፍሉንና ሂሳብ ክፍሉን አጣምሮ ይሰራ ነበር። እንደ ገና ለበላዮቹ ቅን አገልጋይ በመሆኑ እሱ የውስጥ የደህንነት አባል ሲሆን ሚስቱ ደግሞ የደህንነት በሀፊ ነበረች። እኔን ያለ ስራዩ የላከኩብኝ ላንድ ወር ያህል የክበብ ሀላፊ ሆኘ በመስራቴ ነው። እና ለሚስቱ አንዳንድ ሺ ብር አዋጥታችሁ ስጡልኝ ሲል እኔ ባለመስማማቴ ይህን ቂም አድርጎ ነው። ሌላው የነጩ ወርቅ ጥቅም ተካፋይም ነበር። ይህን እሱ እራሱ ይዘረዝረው" ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ።

"መልካም፤ በመጀመሪያ ደረጃ የጥቅም ተካፋይ አለመሆኔን እንድታውቁልኝ እፈልጋለሁ። በተረፈ ግን ስለ ነጩ ወርቅ ምስጢር የማውቀውን ያህል ለማብራራት እሞክራለሁ። ነጩ ወርቅ ማለት ስኳር፣ ጨው፣ ፍርኖ ዱቄት ማለት ነው። በዋናው ማስተናገጃ፣ ታጠቅ ትልቅ የስንቅ ዴፖ ነበር። ስምንት መጋዘኖች ነበሩት። ከነዚህ ውስጥ የነበረው ዱቄት፣ ስኳርና ጨው ወደ አዲስ አበባ ተገዞ መሸጡንና ባለስልጣኖች እንደ ተካፈሉት አውቃለሁ። የገንዘቡን ልክ ግን በትክክል አላውቅም። በወሬ ደረጃ ግን ካንድ ሚሊዮን ብር በላይ ነው ይባላል። ይህንን ነው የማውቀው" ብሎ በግዴለሽነት ዘና ብሎ ቆመ።

ከዚህ በኋላ አምሳ ሰባቱን መኮንኖች ሁለት ኢህአዲጎች ከተረኛዋ አውጥተው እንደ መንጋ በግ እያንጋጉ ወደ እስር ቤት ይዘዋቸው ሄዱ። ለጥቂት ደቂቃዎች ያለ ንግግር እረጭ ብለን ቆየን።

ሀጎስም በዝምታ ሲጋራውን ምግ ከጨረሰ በኋላ፣ "አሁን ደግሞ በኮሎኔል ዘርጋው ላይ ሂስ አለኝ ያሉ ሻምበል አሉና አሳቸውን እናዳምጥ" ሲለን ቤቱ በጠቅላላ ያለ ድምፅ ተንቀሳቀሰ። ቶሎ ብዬ ኮሎኔልን ሳያቸው አይኖቻቸው ከመቅዕበት ደም ለብሰዋል። ወዲያው የሚሄሳቸው ሻንበል ከተቀመጡበት ቀስ ብሎ ተነሳና፦

"ጓድ ኮሎኔል! አንድ ጊዜ ወደዚህ ቢወጡልኝ" አላቸው በቀስስተኛ አነጋገር። ኮሎኔል ደንብረው በመነሳት፦

"ጉዳጓድ ግቦና! እኔን ነው አንተ ጓድ የምትለኝ" ፊታቸው ይንቀጠቀጥ ነበር። ሻምበሉ ቀልቡ ግፍፍ አለ።

"ዋእ! ምን ማለትሥት ነው ኮሎኔል፤ እስሥ ከማን ይበልጣሉ? ወደዚህ ይምጡና ሂስሥትን ይቀበሉ" አላቸው ሀጎስ ከተቀመጡበት ተፈናጥሮ በመነሳት።

"ትሰማኛለህ ሀጎስ" አሉ ጣታቸውን ወደሱ በመቀሰር ከቆሙበት ሳይንቀሳቀሱ፤ "እኔ ዘርጋው ቁሜ እየሄድኩኝ በጀብሎ አልሄስም! ታስሬ ለፍርድ ስታቀርቡኝ ያኔ ይኸ የተገተረው ሲጋራ አፂሪ ይመስክርብኝ፤ ቃሌ ይኸው ነው!" አሉ እንደ ተሚጋች ክንዳቸውን አወራጭተው።

"መታሰሩማ አይቀርልዎትም። ይበሉ ወደዚህ ይምጡ" ሲላቸው ቀልጠፍ ብለው ሄዱ። በዚህ ጊዜ በድሉ ከተቀመጠበት በመነሳት፦

"ኮሎኔል ወደ እስር ቤት ከመወሰዳቸው በፊት ሻምበሉ በሳቸው ላይ አለኝ የሚለውን ሂስ ቢያቀርብና ብንሰማው ጥሩ ነበር። ምናልባት ከግል ቂም ተነሳስቶ ሊሆን ይችላል። በተደጋጋሚ ሁኔታ ከስራ ገበታው ላይ ባለመገኘቱ አንድ ጊዜ አምሳ ብር አንድ ጊዜ ሀያ ብር ከደመወዙ ላይ ቀጥተውት ነበር። ይህን እኔ አውቃለሁ። ከዚህ ሌላ ሂስ አለኝ የሚል ከሆን ያቅርበውና እንስማው" ብሎ ሲቀመጥ እኔ ደግሞ "ተጨማሪ" ብዬ ተነሳሁና፦

"አንተ እኛን አታውቀንም። እኛ ግን እስበሳችን እንተዋወቃለን። በተለይ ካንድ ክፍል የመጣነው ማን ምን እንደነበረ እናውቀዋለን። በመሰረቱ አንድ ሰው ባንድ ሰው ላይ ሂስ አለኝ ሲል በመጀመሪያ ደረጃ ያ ሰው ሰው ሆኖ ሲገኝ ነው። አለበለዚያ ግን እርካሽ ሰው ሰው ያረክሳል።

"መቼም ሰው ለማያውቀው ሰው ነው የሚመሰክረው። ኮሎኔል ዘርጋው ቀደም ሲል አለቃየ ነበሩ። ከሶማሌ ጋር በተካሄደው ጦርነት ታላቅ ጀግንነት ያስመዘገቡ ነበሩ። አገሪቱ ትኩራባቸው የነበሩ መኮንን ናቸው። በስነምግባርም ቢሆን ኮሎኔል ዘርጋው የተከበሩ ናቸው። እርግጥ እንደ ነውር ከተቆጠረባቸው ሲበዛ ሀይለኛ ናቸው። ዋዛ ፈዛዘ አይወዱም። በዚህ የተነሳ ስነምግባር የጎደላቸው መኮንኖች አይወዷቸውም። ከዚህ ውጭ ግን ኮሎኔል ዘርጋው እንከን አይገኝባቸውም።

"እኔ እንኳ አሁንስ እየሰጋሁ ነው። ይች አገር ጨርሳ ታረክ እንዳታጣ። ምናልባትምኮ አንድ ቀን የጋራ ችግር ይገጥመንና ጀግና የሚፈለግበት ወቅት ይመጣ ይሆናል። ስለዚህ ጥሩ ስም ያላቸውን አባውንቶች በረባ ባረባው ባናንገላታቸው ጥሩ ነው። እና ሻምበል በድሉ እንዳለው መኮንኑ ሂሱን ያቅርብና እንስማው። ከዚያ በኋላ አስተያየት ለመስጠት ያመቸናል" ብዬ ተቀመጥኩ። ሀጎስ ባነጋገሬ ያልተደሰተ መሆኑን ፊቱ ያስታውቅበት ነበር።

"እስሩን የመረጡት እራሳቸው ናቸው። የናንተን የምስክርነት ቃል እሳቸው የሚመርጡት ፍርድ ቤት ሲቋቋም የዚያን ጊዜ ቀርባችሁ ልትመሰክሩላቸው ትችላላችሁ" በማለት የምፀት መልስ ሰጠን። ወዲያው አንድ ታጋይ ይዟቸው ሄደ። ወደ እስር ቤት። አዳራሹ ጭርታ ዋጠው። አድባራችን ነበሩ። ልብሳችንን የተገፈፍን ያህል ነው ርቃናችንን የቀረነው።

ሀጎስ ሲጋራውን አጭሶ ከጨረሰ በኋላ ከተቀመጠበት ተነስቶ "እንግዲህ ሂሱን ጨርሰናል። አሁንም ቢሆን አድፍጠው የተቀመጡ ካሉ ወደፊት ልታጋልጧቸው ይገባል። እስካሁን ላደረጋችሁት ተሳትፎ አመሰግናለሁ። በዚሁ ግባበት።

"ከሂሱ ቀጥሎ የሚኖረን ፕሮግራም ትምህርቱን በቀጥታ መጀመር ነው:: በርግጥ ከትምህርቱ ጋር ጎን ለጎን የምናካሂዳቸው ተግባሮች ይኖሩናል::

"ሌላው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ስለሚሄዱ ለነሱ አሸኛኘት የሚያደርጉ ከየሻለቃው አምስት አምስት መኮንኖች ይመረጡ ስለተባለ እኛም እንመርጣለን" በማለት እንደ ቆመ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መርጠን ጨረስን::

"መልካም፤ በሚቀጥለው እስክምንገናኝ በሰላም ያቆየን" ብሎ አሰናበተን::

ካዳራሹ ስንወጣ ልክ አውራ እንደ ሌለው ንብ ብትንትን አልን:: በተለይ እኔና በድሉ ጫንቃ ቀሎን ነበር::

ጓዛቸውን ጠቅልለን ከታሰሩበት ወስደን አስረከብናቸው:: አዱኛ ደቻሳ ገና ንዴቱ አልበረደለትም:: ኮለኔል ግን ስክን ብለዋል:: እንዲያውም ለኔ በመጨነቅ:-

"ጎርፋ፤ ከዙን በኋላ እኛን ልጠይቅ ብለህ እንዳትመጣ:: ከትምህርትህ እንዳትስተጓጎል:: ሀጎስ መሄዳው አይታወቅም:: እኔን በምን እንዳጠመደኝ ታውቃላችሁ? ያኔ 'የበደልነውን ህዝብ መልሰን እንክሳለን' ብሎ ያሉን ጊዜ በተናገርኳት ቃል ነው ቂም ይዞ ይህንን ነፈዝ ያስነሳብኝ" አሉ::

"ምንም አይደል ጌታዬ፤ አይናደዱ:: ጀግና ምንጊዜም ቢሆን እንደ ታሰረና እንደ ተገደለ ነው::"

"ኧረ እንደዚህ መሆኔን ባውቀውስ ለስርም አልበቃ ነበር:: 'ሰላምና መረጋጋት፤ ዲሞክራሲ' እየተባለ ነው ጉድ የሆንኩት" አሉ በብርቱ እየበገቻቸው::

እነሱን ተሰናብተን ወደ ካምፕ ስንመለስ ያዲስ አበባ ጉዞ ደግሞ ስንቅር አለብኝ:: እውን ይሆን?

38

እኛን ለመሸኘት ከሁሉቱም ክፍለ ጦሮች የተመረጡት መኮንኖች ቀድመው ቦታቸውን ይዘዋል:: የክብር እንግዶች መሆናቸው ነው:: እኛም በደስታ ፈንደቅደቅ ብለን ከነሱ ጎን ተቀምጠናል:: ከፊትለፊታችን የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማና የኢህአዴግ አርማ ተሰቅሏል:: ከግድግዳው ላይ የተለጠፉ መፈክሮች እንዲህ የሚሉ ናቸው::

-ኢህአዴግ ለትምህርት ያለው አመለካከት ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ነው!

-እውቀታችንን ለሀገር ግንባታ እናውላለን!

የማእከሉ ሀላፊ መጥተው ቦታቸውን እንደ ያዙ የተማሪዎች ተወካይ የመግቢያ ንግግር ካደረገ በኋላ ለሁለት ቀናት ያጠናነውን መዝሙር ዘመርን::

«ድንቅ ህይወት ይምጣ በኢትዮጵያ፣
የሰላም ህይወት በኢትዮጵያ፣
ጦርነቱ ጠፍቶ ሰላም ይስፈንበት፣
መረገጡ ቀርቶ ፍትህ ይስፈንበት፣
ረሃብ ተወግዶ ጎተራው ይሙላበት፣
ድንቁርና ይጥፋ እውቀት ይፍለቅበት፣
ጅምርህ ድንቅ ነው ኢህአዴግ ግፋበት::»

ከዚህ በኋላ የመኮንኖች ተወካይ ንግግር አድርጎ ሲጨርስ የማእከሉ ሀላፊ የመዝጊያ ንግግር አድርገው ያሸኛኘቱ ፍጻሜ ሆነ::

በማግስቱ እነኮለኔልን እስር ቤት ሄጄ በመሰናበት ጉዞየን ወደ አዲስ አበባ አደረኩ:: በድሉ ጫኔ ብቻውን ያለ ጓደኛ ቀረ:: አሳዘነኝ:: እኔ ግን ከጦላይ ተገላገልኩ::

ምእራፍ አስራ አምስት

ሌባስ የሚሰርቀው ካለው ቤት ገብቶ ነው፣
ኢትዮጵያን ያጠፋት ወሮ በላው ነው!

39

የግቤን ወንዝ እስክምንሻገር ድረስ በፍፁም አላመናቸውም ነበር:: «ተመለሱ» ይሉናል እያልን ስጋት አድሮብን ነበር:: ኧረ ምናቸው ይታመናል?

ጫኔ ያለ ገንዘብ የነበራቸው የእጥፍ እጥፍ እየከፈሉ በሁለት ላንድሮቨር በመሳፈር በተነሱበት እለት አዲስ አበባ ገብተው አድረዋል:: ከአለት ጉርስ የማያልፍ ገንዘብ ያለን ግን ባንድ የእርዳታ መኪና ታጭቀን ሲጎተት ውሎ ምሽት ላይ ወልቂጤ ደዞን ገባ:: ለመጀመሪያ ጊዜ ከታጎርንበት በረሃ ወጥተን የወገን ጠረን ሸተተን:: ደስ አለን::

ወልቂጤ አድረን ጧት ለየራሳችን መኪና እየፈለግን በመንጠልጠል ወደ አዲስ አበባ እግሬ አውጭኝ ሆነ:: እኔ እንደ አጋጣሚ አንድ መለስተኛ አውቶብስ አግኝቼ ተሳፈርኩ:: ዋጋው ግን እጥፍ ነበር:: ወድጄ የገባሁበት ስለነበረ ቅር አልተሰኘሁም:: ብቻ አክተፍትፎ አዲስ አበባ ያድርሰኝ::

አዲስ አበባ የገባሁት ልክ ስድስት ሰአት ሲሆን ነው:: ከጃንሜዳ ስነሳ ይዤት የነበረችውን የጉዞ ቦርሳየን አንጠልጥየ ብቅ ስል እማማ ልኬ:-

"እልል!" አሉ:: በዚህ ወቅት ደግሞ የሰፈር ሴቶችና ልጆች ከያሉበት ብቅ ብቅ አሉ:: ወዲያው ካንገቴ ላይ ተጠምጥመው ይስሙኝ ጀመር:: እሻቸው እንደ ለቀቁኝ ደግሞ የመንደሩ ሴቶችና ህፃናት ሰፈሩብኝ:: ሁሉንም ተራ እያገባሁ ሳምኳቸው::

"መቶ አለቃ ጎርፋ፤ ግባስቲ ልጄ" አሉ እማማ ልኬ በደስታ ድብርክ ድብርክ እያሉ:: ሙቶ የተቀበረ ማእረግ "መቶ አለቃ" ይሉኛል::

ከግዞት መጣሁ እንጅ በድል አድራጊነት ምርኮ ይዤ አልመጣሁኝ። የሆነ ሆኖ በንቀት አልታየሁም። ሁሉም በሀዘንና በርህራኄ ነው የሳሙኝ። ይህ የመከበርና የመወደድ ምልክት ነው።

የእንኳን ደህና መጣህ ግርግሩ ጋብ ሲል የምበላው አቀረቡልኝ። በችኮላ የተንተከተከ የሽሮ ወጥ ነበር። ፊርዶብኝ የሽሮ ወጥና ወተት አልወድም። ወተትን እንኳን ጠልቸው የቀረሁት በልጅነቴ በብርጭቆ ስጠጣ እንዲት ባለማርዳ ጠንቋይ ወግታኝ ነው። በትውከት የወጋችኝ መርዟ ባይወጣልኝ ኖሮ እሞት ነበር አሉ። እናቴ ነች የነገረችኝ። በዚያው ወተትን ጠልቼው ቀረሁ። ሽሮ ወጥን ግን በምን እንደጠላሁት ምክንያቱን አላውቅም። ብቻ አልወድም። እማማ ልኬም አለመውደዴን ደህና አድርገው ያውቃሉ። ምርጫ እንዳጡ ገባኝ። ሁለት ጊዜ ያህል ጎራርሼ ተውኩት።

"ተውከው? አንተ ሽሮ ወጥ አትወድ" አሉ እንደ መጨነቅ ብለው።

"ከመንገድ ምሳ ስለበላሁ ነው" አልኳቸው። እንዳያስቡ ብዬ እንጅ ከነጋ ምንም ነገር አልቀመስኩም። ግን ደግሞ አዲስ አበባ በመግባቴ ተደስቼ ነው መሰል ርሀብ የሚባል ነገር አልተሰማኝም።

ውሃ እሞቁልኝና የጠላይን እድፍ ተለቃለኩት። አእምሮየ ጠላይ ሆኖ እንዳይቀር እንጅ እድፉንስ ውብ አድርጌ ታጠብኩት።

እኔ ሰውነቴን ስታጠብ እሳቸው ደግሞ መኝታ ቤቴን ጠራርገው ዝንቡን፣ ትንኙን፣ ሽረሪቱን ለማጥፋት ጭሳጭሱን አግፈጠፈጡበት። የሰንደሉ፣ የእጣኑ ሽታ ሌላ ነበር። ጫጉላ አስመስለውታል። ጫጉላ ብል ፅጌና የኔነሽ ትዝ አሉኝ። ኪሴ ባዶ ሆኖ እንጅ ዛሬ ካንዷ ጋር መሞሸር ነበረብኝ። እንግዲህ ገንዘብ እስከማገኝ ድረስ አድፍጩ የፍቅርን ርሃብ መራብ ነው።

አስር ሰአት ላይ ወዳክስቴ ለመሄድ ስነሳ፡-

"የት ትሄድ ጎርፉ?" አሉኝ አንጋጠው እያዩኝ።

"አክስቴጋ መሄዴ ነው፤ እንዳይሰጉ" አልኳቸው ወደ በሩ እያመራሁ።

"ካክስትህጋ ከሆነስ ደግ" አሉኝ ከተል እያሉኝ። እኔም ፈጠን እያልኩ ሄድኩኝ። ካክስቴ ቤት ድርስ ስል፡-

"ጎርፉ! እንኳን ደህና መጣህ!" አለችኝና ለመሳሳም ተቃቀፍን። "ዛሬ ነገ ስል መጥቼ ሳልጠይቅህ መጣህ! መጨነቄ ግን አልቀረልኝም" አለችኝ ተሳስመን ካበቃን በኋላ።

"ከዚሁ ሁነሽ ከተጨነቅሽልኝ ይበቃኛል።"

"ትምህርቱን ጨርሰህ መጣህ?"

"ጨርሽ መጣሁ። የዲሞክራሲ ዲግሪ ጭኘ" ስላት ሳቅ አለችና የሚበላውን፣ የሚጠጣውን አቀረበችልኝ። እርቦኝ ስለነበር እየተጣደፍኩ ነበር የጎረስኩት። ደግሞ የምወደውን የስጋ ወጥ ነበር ያገኘሁት። ስጋን ማን ይጠላል። እርጉም ካልሆነ በስተቀር ...

"ቡቴሌቪዥኑን አንተን አላየሁህም" አለችኝ በልቼ ካበቃሁ በኋላ የረጋ ጨዋታ ስንጀምር።

"አልተነሳሁም" አልኳት።

"ለምን?"

"ምን የሚያስደስት ነገር ሆኖ ነው በቴሌቪዥን የምቀረፀው።"

"ማስደሰትስ አታስደስቱም ልጄ! ምነው እንደዚህ ፍርክስክሳችሁ ወጣ? ለጥቂት ጊዜ እንኳን አንድ መሆን አቃታችሁ?"

"ተይኝ እባክሽን እትየ ሰናይት" አልኳት ቁስሌን የነካችብኝ ያህል ተሰምቶኝ። ፊቴንም አጨፈገኩት።

"ያለም መሳቂያ ነው የሆናችሁት" ስትል ደገመችኝ።

"እኛም በኛ ስቀናል" አልኳት።

"ለመሆኑ አላማቸው ምንድን ነው?"

"ኢትዮጵያን በኃላ ከፋፍሎ መግዛት።"

"በዚህ ጉዳይ ላይ ያሏችሁ ነገር አለ?"

"አዎን። 'ብሄር፣ ብሄረሰቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው መወሰን አለባቸው። እስከ መገንጠል ድረስ' ነው የሚሉት።"

"አሁን ሁሉም ብሄረሰብ መገንጠል ነው የምንፈልገው ቢሉ ሊፈቅዱላቸው ነው?"

"ወኔው ካላቸው።"

"ወኔውማ ኖሯቸው እናንተን በታትነዋችኋል" አለችኝ በሽሙጥ አነጋገር።

"ኢትዮጵያንም መበታተን አያቅታቸውም።"

"ግን ለዚች አገር መፈራረስ የደርግ ድርሻ የለበትም ትላለህ?"

"በሚገባ አለበት እንጅ። እሽሁን ጠርጎ፣ እንቅፋቱን ከልቶ፣ ሁሉን ነገር አምቻችቶ ነው የጠበቃቸው።

"ልጆቻችንን ሁሉ ጨፍጭፎ ጨርሶ፣
ሀብታችንን ሁሉ አንድ ሳይቀር ወርሶ፣
ደርግ ፈረጠጠ አገርን አፍርሶ!" ተብሏልኮ እትየ ሰናይት።"

"አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ከደርግ እነዚህ ይሻላሉ ይላሉ። አንተ እንዳየሃቸው ይሽ አባባል እውነት ይመስልሃል?"

"ከወያኔዎች ተለጥፈው የሚመጡ እነዚህ ይሻላሉ ቢሉ እግባብ አላቸው። 'ውሻ በበላበት ይጮሃልና!' ከደርግ ተጣግተው የኖሩም ደርግን ቢያሞግሱ አይፈረድባቸውም። ለህዝቡ ግን ሁለቱም ገዣነሞች ናቸው። እናበላልጥ ከተባለ ግን በበኩሌ ደርግ ይሻላል ባይ ነኝ። ምክንያቱም ደርግ እራሱ ይዘርፋል፣ ይጨፈጭፋል እንጅ በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት ከፋፍሎ አላጨፋጨፈም። እነዚህ ግን የጎሳ መርዝ እየዘሩ ናቸው። ለኢትዮጵያ ቀርቶ ላፍሪካም የሚተርፍ። በዘረፋውና በጭፍጨፋውም ቢሆን ከደርግ አይተናነሱም። ሁለቱም ግን ያው ካንድ ኩሬ የተቀዱ በመሆናቸው በቅርፅ የተለያዩ ይምሰሉ እንጅ በይዘት አንድ ናቸው።"

አነጋገሬ ካንጀቷ ገባ መሰለኝ ለትንሽ ጊዜ ትክዝ ብላ ቆይታ "እድሜ ስጥቶን እንደ ደርግ የነዚህንም ውድቀት ለማየት ያብቃን። ፈጣሪየ እባክህን ኢትዮጵያን ጠብቃት!" አለች በመጨረሻ በመማፀን።

ካክስቴ አድራ ጧት ቁርሴን በልቼ ለመሄድ ስነሳ "በል እንካ ወዲህ ወዲያ ስትል ለታክሲ መሳፈሪያ እንኳን እንዳይቸግርህ" ብላ

ድፍን ሙቶ ብር ሰጠችኝ። እግዜር ይስጣት። እንግዲህ ዛሬ የፍቅር ቀን ነች።

እሷን ተሰናብቼ እንደ ወጣሁ ቀጠሮ ለመያዝና ወዲያውም መምጣቴን ለማብሰር ለየኔነሽ ደወልኩላት። ለጊዜው «የለችም» ተባልኩ። ትንፋሿን እስከምሰማው ቸኩየ ነበር። አልሆነም። ከቤቴ ወጥቼ ወደየትም ሳልሄድ ዋልኩ።

አስር ሰአት ላይ ሸክ ብዬ ለብሼ ወጣሁና ለየኔነሽ ደወልኩላት። አሁንም «የለችም» አሉኝ። ብሽቅ አለኝ። መቼ ይሆን ከቤቷ አረግታ የምትቀመጠው? ቅብጥብጥ። ከጣላይ መምጣቴንና የስልክ ቁጥሬን ሰጥቼ ስልኩን በመዝጋት ጉዞየን ወደ መርካቶ አደረኩ። ከፅጌጋ።

በጣና የገበያ አዳራሽ በኩል አድርጌ ሽቅብ አቀናሁ። አለባበሴ ከተሜ ልምሰል እንጅ እርምጃየና አስተያየቴስ እንግዳ ደራሽ ገጠሬ እመስላለሁ። ሁሉም ነገር ድንግርግር አለብኝ። ሰዉ ሲያዩት ያስፈራል። ጨርሶ ተስፋ የሚነበብበት ፊት የለም። የሁሉም ፊት የመከራ ፊት ነው። ደግሞ ሁሉም ወራሪ እንደመጣበት ግራ የተጋባና መሄጃው የጠፋው ይመስላል። በርግጥም በታታኝ ወራሪ መጥቶበታል ...

በልማዱ መርካቶ አካባቢ ሞቅ ደመቅ ያለ ነበር። ጫጫታው እራሱ ህይወት ነበረው። አሁን ሳየው ግን ህይወት አልባ በድን ባንዳች ሀይል እየተገፋ የሚንቀሳቀስ ይመስላል። እግዚአ ነው ሰው እያዩ ህይወት ማጣት ... ቢጨንቀኝ ከዚያ ግድም ፈትለክ አልኩኝ።

ከሆቴሉ ስደርስ አረጋ ብዬ እርምጃየን እየቆጠርኩ ገባሁና ጥግ ይገኙ ተቀመጥኩ። ወዲያው ደግሞ አይኖቼ ወዲያና ወዲህ ቃበዙ። ፅጌን ፍለጋ። ለምን እንደ ሆነ እንጃ የልብ ምቴም ኖር ኖር ማለት ይዞ ነበር። አየኋት። ከወዲያ ጥግ በኩል ብቸዋን ቂጭ ብላ በትካዜ ተውጣለች። እኔ ልተክዝላት። እንዴት ወጣት አስተናጋጅ መጥታ "ምን ልታዘዝዎት?" አለችኝ።

"ሻሂ" አልኳት። መለስ ብላ ልትሄድ ስትል "ፅጌን ጥሪልኝ" አልኳት። ሄዳ ስትነግራት ቀና ስትል አየችኝ። ክው ብላ ደነገጠች። የደስታ ድንጋጤ። ከሰማይ የወረድኩ ነው የመሰላት። ወደኔ ስትመጣ ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ጠበኳት። ከቅሬ ስትገባልኝ ጉንጮቿን አገላብጬ ሳምኳቸው። ተስመው አላለቁም። እሷም እያገላበጠች ሳመችኝ።

"ደህና ነህ" አለችኝ ተሳስመን ከበቃን በኋላ ከፊትለፊቴ እየተቀመጠች።

"ደህና ነኝ" አልኳት በፈገግታ ተውጬ።

"እውነትም ደህና ነህ። ትንሽ ጠቁረሃል እንጅ።"

"መጥቆርማ በታው በረሃ አይደል።"

"መጥቼ ሳልጠይቅህ! መቸስ ታዝበኸኛል።"

"አልታዘብኩሽም። ሆስታ የጠየቅሽኝ ይበቃኛል" አልኳት።

ሻሂው መጣልኝ። ፉት ሳደርገው ትኩስ ነው። ፅጌም ትኩስ ነች። ዛሬ ስንገመው ማደራችን ነው። ስለጠላይ ቆይታየ እያወራን እያለን "እጮኛህ መጥታ አልጠየቀችህም?" አለችኝ።

"የሚገርምሽ ነገር አንድ ሻምበል አፍቅራ ኖሮ እሱኑ ልትጠይቅ ስትመጣ እግረመንገዷን ጠየቀችኝ" ስላት:-

"ቅሌታም ነች!" ስትል አንጓጠጠቻት።

ካስር ሰአት ጀምሬ መንስቴ ስለ ከበደኝ አልጋ እንድትይዝ ብር ሰጥቻት ወጣ አልኩ። ከዚያው መርካቶ አካባቢ አራኩም! አሁንም የማየው የተንከላወሰ ህይወት ነው። አዲስ አበባ የናፈቀችኝን ያህል ባንድ ጊዜ አስጠላችኝ።

አስራ አንድ ተኩል ላይ ወደ ፅጌ ተመለስኩ። መጠጥ ቤቱ በመሽተኞች ታፍኗል። መቀመጫ በማጣቴ ወደ ባንኮኒው ጠጋ ብዬ በመቆም ድራፍት አዘዝኩ። ገልመጥ ብዬ ፅጌን አየኋት። እሷም አይታኝ ኖሮ ጥርሶቿን ገለጥ አድርጋ ወደኔ መጣች።

"መቀመጫ አጣህ አይደል?" ብላ በጎኔ ሻጥ አለች። በክንዴ እቅፍ አደረኳትና:-

"ድራፍት እዘዥ" አልኳት። ሁለታችንም እየተጎነጨን ጨዋታችንን ቀጠልን።

መሽተኛው ሁሉ እየተጣደፈ ከጠጣ በኋላ አንድ ሰአት ላይ ውልቅ አለ። መጠጥ ቤቱ ባዶውን ቀረ። ያውም ከ ሰአት እላፊ እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ተራዝሞ ነበር። ህይወት ነው መራዘም ያልቻለው። እኔና ፅጌ ግን ዘና ብለን ቆይተን ልክ በሰአቱ ሂሳቧን አስረክባ ወደ መኝታ ክፍላችን ገባን። አቤት ችኮላችን! ጋደም ከማለታችን ተናነቅነው። ጎምጆቼ ነው መሰል የዶሮ ያህል እንኳን አልቆየሁም። ደግሞ ያመመኝ ለመምሰል እንደ ማቃሰት አልኩኝ። አፍሬ ነበር።

"ምን ሆንክ?" አለችኝ። አጠያየቋ ሌላ ትርጉም ያዘለ ነበር። እሷም አምሮቷን ሳትወጣ ነው የተናጠበችው።

"ጣላይ በረሃ ስለሆነ ሰውነቴ ሙቀቱን ተላምዶት ቆይቶ አሁን ደግሞ ያዲስ አበባን ቀዝቃዛ አየር መለማመድ እቃተኝ መሰል ተዝለፈለፍኩ" አልኳት።

"አይዞህ! አሁን ትለማመደዋለህ" አለችና እቅፍ አድርጋ ከንፈሮቼን ሳም በማድረግ "እስቲ አንተ ደግሞ ሳመኝ። አልናፈኩህም?" አለችኝ።

"እረ ናፍቀሽኛል" አልኩና ጉንጮቿን! ከንፈሮቿን ተራ በተራ ሳምኳቸው። የፍቅር ስሜቴ ወዲያው ተነሳ። አሁንም ተስገብግቤ ኖሯል:-

"ቀስ በል" አለችኝ ትንፋሿ እየሮጠ። እንዳለችኝ አረጋ አልኩ። እውነትም ስከንት ብዙ ምስጢር አለው። ከዚህ በኋላ ምን እንደ ወሽከትን አላስታውሰውም። ደግሞ የስቅስቅታ ድምፅ ታሰማ ነበር። እኔ ደግሞ አጠቃኋት እያልኩ ብከን አልኩት።

"እሁ! ከንፈሬ ቆሰለ" አለች የታችኛውን ከንፈሯን ሳብ አድርጋ ይዛ።

"እንኳን ቆሰለ" ስላት እንገቴን እቅፍ አድርጋ በመያዝ ከንፈሮቼን ቅርጥጥ አደረገቻቸው።

"እንዴ! ምነካሽ?" አልኩና መነጬኳት።

"እስቲ አለማመሙን ቅመሰው"

"ጅል! እኔ ታዲያ ሳምኩሽ እንጅ ነከስኩሽ እንዴ።"

"እንደ ሸንኮራ አገዳ አልመጠጥከኝም!" አለችኝ።

የፍቅር ተሃድሶ ይሏል እንዲህ ነው:: በሚገባ ታደስኳት:: የኔ ጥንቅሽ ባንቺ ላይ ይኸ ጠማማ ጊዜ አይዳምን ...

ጧት ቁርሳችንን በልተን እሷም ወደ ቤቷ፣ እኔም ወደ ቤቴ ...

40

"ጋሽ ጎርፉ" አለችኝ የማማ ልኬ ጎረቤት ልጅ ወደ ቤቴ ልገባ ስል::

"አቤት" አልኳት ቆም እያልኩ::

"ትናንት ማታ ሁለት ጊዜ ስልክ ተደውሎልህ ነበር:: 'እንደ መጣህ ደውልልኝ.. የኔነሽ ነኝ' ተብለሃል" በማለት መልእክቷን አድርሳ መለስ አለች:: እኔም መልእክቱን ተቀብዬ ወደ ቤት ገባሁ:: ወዲያው ወጣ ብዬ ልደውልላት አልፈለኩም:: እስቲ እኔ ደውየ ሳጣት የሚሰማኝ ስሜት ይሰማት፣ እርር እንደምል እሷም እርር ትበል አልኩና መኝታ ቤት ገብቼ ለጥ አልኩ::

አስር ሰአት ተኩል ላይ ጧት መልእክት የነገረችኝ ልጅ "ስልክ" አለችኝ:: ተጣድፌ ወጣሁ:: የኔነሽ እንደሆነች አልተጠራጠርኩም:: ስልኩን አንስቼ:-

"ሀሎ!" ከማለቴ በስድብ አጣደፈችኝ:: ትግስቷን አስጨርሻት ኖሯል:: እሰይ! እኔም እንደዚህ ነው ድብን የምለው::

"ዕጌረዳዋ ይርገፍና! ዕጌ አለቅህ አለች! ከነጋ እስካሁን ያልደወልክልኝ? ወይንስ መልእክቱ አልደረሰህም ማለት ነው?"

"መልእክትሽ ደርሶኛል:: ልደውልልሽ ስል ነው ለትንሽ የቀደምሽኝ::"

"እማየ ትሙት አትረባም! በጣም ነው ያበሸከኝ!"

"እኔ እንኳን አልበሸኩም እንደ መጣሁ ሁለት ጊዜ ደውየ ያጣሁሽ::"

"ዝጋ! እንተማ ምን ትበሽቃለህ፣ ተለዋጭ አግኝተሃል! እማየ ትሙት ተጫወትህብኝ የምትቀር እንዳይመስልህ!"

"እሽ አሁን የት እንገናኝ?" ስላት:-

"ብሄራዊ ቲያትር አጠገብ ጠብቀኝ" ብላ ስልኩን ዘጋች::

ጊዮርጊስ አስፍ ብዬ ባንደ ቁጥር አውቶብስ ተጋብቼ ብሄራዊ ቲያትር አጠገብ ዱብ አልኩና አይኖቼን ወዲያና ወዲህ አቅበዘበዝኳቸው፣ የለችም:: ቀ..ሚያታለሁ ማለት ነው:: ቆም ብዬ ስቅበጠበጥ በፊት ለፊቴ እየተውረገረገች መጣች:: ዛሬስ ያን ዘንቢል ቦርሳዋን አልያዘችም:: በሱ ምትክ አነስተኛ ጥቁር ቦርሳ አንግታለች:: ቡና አይነት ጉርድ ቀሚስ ለብሳለች:: ሽንሽናቴ እንክት ብሎ ዳሌዋን አሳምሮታል:: በላይ የለበሰቻት ነጭ ሸሚዝ ደግሞ የበለጠ አስውባታለች:: ስትቀርበኝ ፈገግ አልኩኝ:: እሷም ፈገግ አለች::

"የኔ ጎርፍ እንኳን ደህና መጣህ!" ብላኝ ለመሳሳም ተቃቀፍን:: ተሸምቼ ጉንጮችዋን ሳምኳቸው::

"አንተ ደህና ተገላገልክ፣ ጎሽ" አለችኝ ተሳስመን ስናበቃ::

"እንብሩም ይለቀቃሉ:: ይዘገያሉ እንጅ ምንም አይመጣባቸውም" አልኳት:: ሆን ብዬ የተናገርኩት ሳይሆን እሷን ያፅናናሁ መስሎኝ ነበር:: እሷ ግን ወረፈችኝ::

"አይኑ ይብረርና! እሱን አልጠየኩህም!" ስትለኝ ደነገጥኩ::

ጎን ለጎን እያወራን አግድም አለፍንና እስፖርት ኮሚሽን ፊት ለፊት በውይይት ተሳፍረን ወደ አስመራ መንገድ ሄድን::

ላም በረት ስንደርስ ደግሞ በሌላ ታክሲ ተሳፍረን ካንድ መናፈሻ ሆቴል ገባን:: ይህ ሁሉ ሲሆን በሷ መሪነት ነው:: እኔ ዛሬ የሷ እንግዳ ነኝ:: ሆቴሉን ግን ከዚያ በፊት ከሷው ጋር ተዝናንተንበታል:: የቆየ ትዝታ ውልብ አለብኝ::

ወደ ሆቴል ሳንገባ በቀጥታ ወደ መኝታ ክፍል ነበር ያመራነው:: አስተናጋጁ ገና ሲያየን በፈገግታ ተሽቆጠቆጠ:: ገና ሳንጠይቀው:-

"ይኸኛው ይሻላችኋል:: አንሶላው አሁን ነው የተለወጠው" አለንና ቀደም ብሎ በሩን ከፍቶ ሲገባ ተከትለነው ገባን:: እውነትም የተሻለ ክፍል ነው:: ጥሩ ጠረን አለው:: እኔ ከወንበር ላይ ተቀመጥኩ:: የኔነሽ ደግሞ ካልጋው ጫፍ ቁጭ ብላ ጣራ ግድግዳውን ቃኘችው:: አስተናጋጁ ደግሞ እጆቹን አጣምሮ በመቆም:-

"እሽ ምን ልታዘዛችሁ?" አለን:: የኔነሽ ተሽቀዳደማ:-

"የሚበላ ጥብስ ታመጣልናለህ:: ጮማ እንዳይበዛበት:: የሚጠጣ ደግሞ ቀዝቃዛ የጠርሙስ ቢራ" ስትለው ተጣድፎ ወጥቶ ሄደ::

ከተቀመጠችበት ተነስታ በክፍሉ ውስጥ እንደ መንጎራደድ አለችና ጫማዋን አውልቃ ካልጋው ላይ ጋደም አለች:: አልጋው አረገረገ:: ይህንየ የእኔ አይኖች ደግሞ እንደ መቅበዝበዝ አሉ:: ወዲያው ቀልጠፍ ብዬ ተነሳሁና ካልጋው ጫፍ በመቀመጥ በክንዴ እቅፍ ሳደርጋት:-

"እማየ ትሙት! ዛሬ ከኔና ከዕጌ ማንን እንደምታፈቅር ሳትነግረኝ አንድ የፍቅር ጨዋታ የለም" አለችኝ ኮስተር ብላ::

"አንዳንድ ጊዜኮ ታስገርሚኛለሽ! የማታውቂያትን ሴት ለምንድን ነው አምርረሽ የምትጠያት?"

"ባውቃትማ ኖሮ አንቀ አድርጌ ይዠ ግብ ነበር የማደርጋት" አለችኝ አይኖቿን አፍጥጣ:: ጠጋ አልኩና ከንፈሮቿን ሳም ሳደርጋቸው:-

"እማየ ትሙት እረፍ ብየሃለሁ" ብላ በጄ ገፋ ስታደርገኝ አስተናጋጁ በሩን አንኳኩቶ ገባ:: የጠርሙስ ቢራ ይዞልን፣ ትንሿን ጠረጴዛ ወዳልጋው ቀረብ አድርጎ ከፊቱና ከዚያ ላይ አስቀምጦልን ሊወጣ ሲል:-

"እንዳትመላለስ አራት ጠርሙሶች ጨምር" አልኩት::

"እሽ" ብሎ ውልቅ አለ:: ብዙም ሳይቆይ ተመልሶ መጣ:: ጥብሱም፣ ቢራውም መጣልን:: አቀራርቦልን ሲወጣ በሩን ቀረቀርኩት:: ከንግዲህ ወዲያ ኮሽታ መስማት አንፈልግም:: መብላት ስንጀምር አከታትላ አጎረሰችኝ:: እኔም አጎረስኳት:: የፍቅር ምልክት ይሆን እንዴ?

ግን ከማውቃት ለየት ብላብኛለች። ቅብጥብጥ ሆናለች። ፅጌ አመል ሳታስወጣት አልቀረችም።

በልተን ካበቃን በኋላ ተጣጥበን በቢራ አወራርደን ካልጋው ወጥተን ጋደም አልን። ወዲያው እቅፍ አድርጌ ከንፈሮቿን ምጥጥ ሳደርጋቸው አይኖቿ ስልምልም እያሉ፦

"እስቲ እባክህን ልቀቀኝና በወጉ እንተኛ" አለችኝ። ለቀኳትና ልብሳችንን አወላልቀን ካንሶላው ውስጥ ገባን...

"እማየ ትሙት ጎርፉዬ ከዚያች ፅጌ ከምትባል ላትደርስ ቃል ግባልኝ።"

"ምን አይነት ቃል?"

"ማልልኝ።"

"መሃላ መጥፎ ነው።"

"በራስህ ስለማትተማመን ነው አይደል መሀላውን የፈራኸው?"

"አሁን እንችን ከሌላ ወንድ ላትደርሽ ማይ ብልሽ ትምያለሽ?"

"እማየ ትሙት በፈለከው መንገድ እስምለኝ፤ እምልልሃለሁ"

"ከመቸ ወዲህ ነው ግን ባንድ ቆራቢ የሆንሽው?"

"ኢህአዴግ አዲስ አበባ ከገባ ወዲህ" ስትለኝ ሳኩኝና፦

"ኢህአዴግ ሲበታትንና የቀረቡትን ሁሉ ሲያፋታ እንጂ አንድ ሲያደርግ አላየሁም" አልኳት።

"ይልቅ ቀልዱን ተወውና ከፅጌ ላትሄድ ቃል ግባልኝ።"

"እቅጩን እንድነግርሽ ትፈልጊያለሽ?"

"እሽ ንገረኝ"

"አንቼንም፣ ፅጌንም አልተውም። ሁለታችሁንም በእኩል አፈቅራችኋለሁ።"

"ዝጋ! ሁለታችንን ባንድ ጊዜ ማፍቀር አትችልም። ወይ እሷን ወይ እኔን መምረጥ አለብህ።"

"በሷና ባንቺ መካከል ምርጫ የሚባል ነገር የለም። ስትፈልጊ አንቺ ጥይኝ። ያኔ ካጠገብሽ አልደርስም። እሷም ብትሆን ከጠላችኝ ዞሬ አላያትም።"

"እስከዚህ ድረስ ካንጀትህ ገብታለች ማለት ነው?"

"በሚገባ እንጂ።"

"እኔስ?" አለችኝ።

"አንችማ በደምስሬም ትራወጫለሽ። ያንች ነገር አይሆንልኝም።" ስላት እቅፍ አድርጋ ሳመችኝ። እኔም ሳምኳት። በዚህ ነገር ላይ ዳግመኛ አልተመለሰችም። የፍቅርን ነገር ታውቀዋለችና።

የወያኔ መንግሥት ብቻ ነው የሕዝብ ፍቅር የማይገባው። ተጠልቶ፣ ተተፍቶ፣ በራሱ ነቅዞ በራሱ ካልበነነ በስተቀር መካርም የለው።

ከምሽቱ አንድ ሰአት ላይ ነበር ወደ ቤታችን የተመለስነው። አብረን ማደር አልቻልንም። ተጣድፋለች፣ ማን ያውቃል፣ አዳር ቀጠሮ የያዘችለት ወንድ ሊኖራት ይችላል። እሷ መቼም ባንድ አትወሰን። እኔም ብሆን በጥንድ ማስኬዱን ተያይዤዋለሁ...

41

ቀንን ቀን ሲወልደው፣ ሳምንትን ሳምንት ሲተካው፣ ለጓደኛየ፣ ለሻምበል በድሉ ሜኔ ደብዳቤ ሳልፅፍለት አንድ ወር አለፈ። እንዴት ይታዘበኝ? ምን ላድርግ፣ ላይ ታች እባክናለሁኝ። ማህበራዊ ኑሮውም አልተስመደኝም። ምስቅልቅል ነው ያለብኝ። ምናልባት ዲሞክራሲ ሳይሰርፀኝ ቀርቶ ይሆን? እስቲ ለማንኛውም የኔን ችግር ወደ ጎን ልተውና ደብዳቤ ልፃፍለት።

"ለውድ ጓደኛዬ ለሻምበል በድሉ ሜኔ! ለጤናህ እንደምን አለህልኝ? እኔ በጣም ደህና ነኝ። በድሉ እስካሁን ደብዳቤ ያልፃፍኩልህ የተደላደለ ህይወት ባለመጀመሬ ነው። ዛሬም ቢሆን የተሳካልኝ ነገር የለም። ትምህርቱንም አልጀመርኩ። ወደ ፊትም ተሳክቶልኝ የምማር አይመስለኝም። ጣላይ የነበረኝ ተስፋ አዲስ አበባ ስገባ ጨርሶ ተሟጠጠ።

"እየውልህ፣ አዲስ አበባ የብዶች ከተማ መስላለች። ጉስቁልቁል ብላ ለዛዋን አጥታለች። እንኳን አዲስ አበባ ልትሆን ቀርቶ አርጌ አበባም አትመስል። አርጌ አበባስ ክሽል ቢልም በውስጡ እንቡጥ ስለሚቋጥር ተስፋ አለው። አዲስ አበባ ግን ፍሬ አልቋጠረችም። በባዶው አበባዋ እየረገፈ ነው።...

"ስርአት የለም። ለምን ብሎ የሚጠይቅም የለም። ዘመኑ ዲሞክራሲ ነው። መንገዶች ሁሉ መገበያያ ሆነዋል። ድልድዮች ሳይቀሩ ጉልት ገበያ ተመስርቶባቸዋል። የሚገርምህ ደግሞ ሁሉም ሻጭ እንጅ ገዥ የለም ... የሻጭ ዘመን ...

"ለኛ የታደለን፣ የህበረ ብሄሩ ጦር ትራፊ ምግብ በየሄድኩበት ሁሉ ተዘርግቶ እየዋለሁ። እንዲም አዲስ አበባን ያቆሸሻት እሱ ነው። ለካ ለኛ መስጠቱ የተቋረጠው አዲስ አበባ ሰጥሞ በመቅረቱ ኖሯል። እንግዲህ ይኸ ሁሉ ተጠራቅሞ ዲሞክራሲ ነው።

"የቆሻሻ መፍሰሻ ቦዮች ተደፍነው ከፋት በማጣታቸው የተነሳ በየጎዳናው ዳር ለዳር ቆሻሻው ስለሚፈስ ሽታው አፍንጫን ይሰንጋል። ውስጥ ለውስጥ ባሉ የሰፈር መንገዶችማ ማለፍ አይቻልም። ሽንት ቤቶች ስለማይመጠጡ ሞልተው በመፍሰስ፣ አንዳንዶቹም ከስር በመፈንዳት ካትራሚ የመሰለ ምልግልግ ነገር ቦይ ሰርቶ ይፈሳል። አንዳንድ ቦታ ያለምንም ማጋነን እናቶች ካልተጠነቀቁ በስተቀር ህፃናትን ውጦ ያስቀራል። ረግረግ አበጅቷል። በዚህ የተነሳ ዛሬ ያዲስ አበባ ህዝብ ያስምና የጉንፋን ምሽግ ሆኗል። የማይስል አታገኝም። ኑሮውም ያስላል። ባጠቃላይ አዲስ አበባ ጠንብታለች። ማህበራዊ ኑሮው ራሱ የተግማማና የተጨማለቀ ነው።

"በድሉ! ዛሬ አዲስ አበባ ውስጥ ስራ የሚባል ነገር የለም። ባንዳንድ ቢሮዎች አካባቢ ጎራ ብዬ ነበር። ምንም አይነት የስራ እንቅስቃሴ አላየሁም። አለቆች ወይንም የስራ ሀላፊዎች ጥሻ ውስጥ አድፍጣ እንደተቀመጠች ጥንቸል አይኖቻቸውን እያቁለጨለጩ አንድ

ነገር የሚጠባበቁ ይመስላሉ:: ሁሉም የሰጉ ናቸው:: 'ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ' የሚባል በየመስሪያ ቤቱ ተቋቁሞ የስራ ሀላፊዎችን ያተራምሳል:: ያገልግሎት ዘመን፣ የዜግነት መብት ከግምት ውስጥ የሚገቡ አይደሉም!

"በዚሁ ልክ የለማኙ ጋጋታ አያላውስህም:: የለማኙን ብዛት ስታይ የኢትዮጵያ ህዝብ በጠቅላላው ልመና ተሰማራ ወይ ያሰኝሃል:: ባጠቃላይ የጠወለገና የጠነዛ ህይወት ነው የምታየው:: ከሰው ፊት ላይ ፈገግታ አታይም:: የሁሉም ፊት የጨለመ ነው:: የህፃናት ፊት እንኳን አይበዳሽ ሆኗል:: የሚተዋወቁም እንደ ተኳረፉ ሁሉ ተጋፍተው ይተላለፋሉ::

"የሚገርምህ ደግሞ ነጋ ጠባ ሰልፍ ነው:: መደበኛ ስራ ሰልፍ ነው ማለት ይቻላል:: ሰልፈኞቹ ጨኸው ጨኸው ሲደክማቸው ይበተናሉ:: ከሁሉም ያስደነቀኝ ሰልፍ ታዲያ የምእራብ አዲስ አበባ ህዝብ ተሰልፎ ያቀረበው ጥያቄ ነበር:: ጥያቄውም «መቀበሪያ ቦታ አጣን፣ ይሰጠን» የሚል ነበር:: እየውልህ፣ እንግዲህ ሁሉም ሞቱን አውቆ ላስከሬኑ ማስቀመጫ ቦታ ይጠይቃል:: እኔ ላንተቴ ማስገቢያ ጎጆ የምቀልስበት ቦታ አጣሁ ብዬ ስበሳጭ ለካ ላስከሬን መጣያም ሶስት ክንድ መሬት ይቸግራል:: ዛሬ ገና ነው የገባኝ:: ዋናው ነገር ሰው በቁሙ የሞተ መሆኑን ተረዳልኝ:: ህይወት ትርጉም አጥታለች::

"ከተጨናነቀ ህዝብ መሀከል ሆነህ ብቸኝነት ይሰማሃል፤ ፍርሃት ይውጥሃል:: ዛሬ አዲስ አበባ ውስጥ ጎሰኝነት ነግሶ ዘውድ ጭኗል:: በሰፈር፣ በጎዳና ስትሄድ ጎሳ ጎሳ ይሸትሃል:: ሳትወድ በግድ ጎሳ ፍለጋ ታነፈንፋለህ:: አለበለዚያ እርቃንህን መቅረትህ ነው:: ዛሬ ኢትዮጵያዊ ባህል፣ ኢትዮጵያዊ ወግ የለም:: ካነሳኸውም 'ነፍጠኛ፣ ትምክህተኛ!' ይሉሃል:: የማይሰጡህ ስም የለም::

"የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያም ዋነኛ ስራው የጎሳዎችን የስብሰባ ጥሪ ማስተላለፍ ነው:: ጎሳዎች ተደራጅተው የት እንደ ሚደርሱ አላውቅም:: በመብራት እየተፈለጉ የፖለቲካ ድርጅት እንዲመሰርቱ እየተደረገ ነው:: ጋፋት ብቻ ሊገኝ አልቻለም::

"በድሉ! ታዲያ ያዲስ አበባ ህዝብ ትስስር እንዲህ እንዳይመስልህ:: ልንኩራበት የሚገባን ህዝብ ነው:: ይህን ሁሉ ውዥንብር ተቋቁሞታል:: ዘረፋና ውንብድና ፈፅመው የሉም ማለት እችላለሁ:: ይህን ስልህ ግን ተራ ኪስ አውላቂዎች የሉም ማለቴ አይደለም:: ነገር ግን ህዝቡ ያለ ፀጥታ አስከባሪ እረጭ ብሎ የእለት ተግባሩን ይነስም ይብዛ ሲያከናውን ውሎ ሲመሽ ወደ ቤቱ ይገባል:: ዛሬ ያዲስ አበባ ህዝብ ብቻ ሳይሆን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለራሱ ዳኛ፣ ለራሱ ፀጥታ አስከባሪ ሆኖ ሲታይ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ምን ያህል ታላቅነት እንደሆነ ያኮራል:: የጎሳ መሪዎች ነን የሚሉ ከዚህ ህዝብ ምን እንደሚማሩ አላውቅም:: ህዝቡ የሆዱን በሆዱ አምቆ በመያዝ ይሳለቅባቸዋል:: ግን የሚገባቸው አይመስለኝም::

"አባቶቻችን በባዶ እግራቸው ላይ ወጥተው ታች ወርደው፣ ያህያ ሽንት እየጠጡ ከቅኝ ገዥዎች ጋር ተናንቀው ዛሬ የምንመካበትን አገር ቢያቆዩን የስድብ ናዳ ይወርድባቸዋል:: ይባስ ተብሎ 'መሬት ፍለጋ ነው የሄዱት' ተባለልህ:: እውነት አጋዱን ወርደው ከኢጣሊያን ጋር

የተናነቁት የነዳጅ መሬት ፍለጋ ነበር? አደዋ ድረስ ዘልቀው የተፋለሙትስ የክበረ ድንጋይ ፍለጋ ነው? እሩቅ ምን አስኬደን፣ ትናንት 69 ዓ.ም. ከሶማሌ ጋር በተካሄደው ጦርነት ከጎንደር፣ ከጎጃም፣ ከወሎ፣ ከሸዋ ሞፈር ቀንበሩን ስቅሎ የዘመተው ሚሊሺያ ሰራዊት መሬት ፍለጋ ይሆን? ይኸ ሰራዊትም ነፍጠኛ ይሆን እንዴ? የዛሬው ሰራዊትስ ከትግራይ ተነቅንቆ የመጣው የመሃል ኢትዮጵያንና የደቡብ ኢትዮጵያን ህዝብ ከማራ ቅኝ ተገዥነት ነፃ ለማውጣት ይሆን? ሁሉንም ታሪክ ይፍረደው!

"እይውልህ! ከትግራይ፣ ከወለጋ፣ ከሲዳሞ፣ ከጋሞጎፋ... የዘመቱትን ሚሊሻዎች ያልጠቀስኳቸው ነፍጠኛ ስላልሆኑ ነው:: ነፍጠኛ ማለት መሳሪያ ያነገበ የጥንት ሰራዊት እንዳይመስልህ:: አማራ ማለት ነው:: ነጋዴም ይሁን ገበሬ እዋሽና ግቤን ከተሻገረ ነፍጠኛ ነው:: ታዲያ አማራ ከሆነ ነው::

"የጀግኖች ስምማ እንዳይነሳ ውግዘት የተደረገ ይመስላል:: መጥፎውን በመጥፎነቱ መውቀስ፣ ጥሩውን በጥሩነቱ ማሞገስ የለም:: የጤፍ ቅንጣት የምታክል ስህተት እየፈለጉ መሳደብና ማራከስ ብቻ ነው::

"እንግዲህ ስለ አዲስ አበባ ይህን ያህል ካልኩህ ይበቃሃል:: የቀረውን ስትመጣ ትደርስበታለህ:: ያው እንገናኘን ደፍተህ ለመኖር ነው:: የምትሰራው ስራ የለህም:: በጎልማሳነትህ እጆችህንና እግሮችህን አጣጥፈህ መጎለት ነው:: እኔን ጭንቅላቴን እየበጠበጠው ያለው አንዱ ይኸ ነው:: ወንዞች፣ ሀይቆች፣ ለም መሬት እያለን ስራ ፈት ሆነን እንራባለን:: ዘር መቁጠሩን ትተን ወንዞችን ገድበን፣ በመስኖ ተጠቅመን ዘር ብንዘራ ከምዕዋት እንገላገል ነበር:: ወገንንም ከርሃብ ስቆቃ ከመገላገል የበለጠ ታላቅ ስራ አልነበረም:: አለበለዚያ ግን ጊዜው ያለፈበትን ቋንቋና ዘር እየቆጠሩ ለስልጣን መቆያ ሲባል ወገንን እስበሱ ማባላት ከወንጀል ሁሉ የከፋ ወንጀል ነው:: ይህን በጦርነትና በርሃብ የደቀቀ ህዝብ እንደ ወንበ ቅማል ተጣብቆ በጎሳ ተጠቃቅሶ መመጥመጥ ጭራቅነት ነው::

"በድሉ እኔ እንጃ፤ ጭንቅ ጭንቅ እያለኝ ነው:: እሰር ጊዜ በአእምሮየ ውስጥ የሚመላለሰው ደርግ በ67 ዓ.ም. ባፍላው እንደ ጨሌ አህያ ሲያናፋ ይለው የነበረው ነው:-

የማትረባ ፍየል ዘጠኝ ትወልዳለች፤
ልጆቿም ያልቃሉ እሷም ትሞታለች!'

"እውነትምኮ የማትረባ እናት ነች:: ማህፀኗ ያልተባረከ:: በድርቁ፣ በጦርነቱ፣ በርሃቡ ልጆቿ እንደ ቅጠል እረግፈዋል:: ዛሬም እየረገፉ ናቸው:: ይባስ ተብሎ በጎሳ የሚከፋፍሏትንና የሚበታትኗትን አፈራች:: ኧረ የማይነጥፍ ደም እንዳይተከል ያሰጋል! የመቶ አመት ታሪክ እየተተረከ አልቂት መጋበዝ በጅት ከብደኛል:: የጎሳ መሪዎች ምን ያስቡ ይሆን? ወንበር ወይንስ ሰው? አገር ወይንስ መንደር? የትኛው ነው መቅደም ያለበት?

"አንዳንድ ጊዜማ የሌለ ታሪክ እየተፈጠረ ህዝብን ለማጨፋጨፍ ቤንዚን አርከፍክፈው ለመጫር የሚጣደፉትን የጎሳ የፖለቲካ ድርጅቶች

ላይ ይደንቀኛል:: ህዝቡ ተላልቆ መሬቷ ባዶዋን ብትቀር ምን ይጠቀማሉ? አባቶች እንኳን የሚሉት 'ሰዉ ዋሽቶ ያስታርቃል እንጅ ዋሽቶ አያጣላም' ነው:: ኧረ በኋላ ደም ማድረቁ ይቸግራል! ለትውልድ ጠንቅ አይተክሉ::

"መታወቅ ያለበት ግን የሰው ልጅ የቋጥኝ ድንጋይ አለመሆኑ ነው፤ ካንድ ቦታ ተጎልቶ አይኖርም:: ከቦታ ወደ ቦታ፣ ካገር ወደ አገር በፍልሰት፣ በንግድ፣ በጦርነት ይንቀሳቀሳል:: የኢትዮጵያ ሁኔታም ከዚህ ውጭ አይደለም:: ደግሞ፥ የሰሜኑ ወደ ደቡብ፣ የምስራቁ ወደ ምዕራብ፣ የመሀሉ ወደ ዳር፣ የዳሩ ወደ መሃል በታሪክ አጋጣሚዎች ተቀላቅሎ በፍቅርና በሰላም ተጋብቶ የሚኖር ህዝብ እንጅ፤ ከሩቅ ምስራቅ ወይንም ካውሮፓ መጥቶ የሰፈረ ህዝብ አይደለም:: ለምን መበጫጨቁን እንደ መረጡት አልገባኝም? ለጊዜው በወረቀት ላይ ካርታ ስሎ ቋንቋን መስፈርት በማድረግ 'ይኸ የኔ ክልል ነው' ማለት ይቻል ይሆናል:: የህዝቦችን የረጅም ጊዜ የታሪክ ትስስር ፈፅሞ መበጣጠስ ግን አይቻልም:: ይልቁንም የማይጠፋ እሳት እየተጫረ መሆኑ መታወቅ አለበት:: በመሰረቱ ቋንቋ ብቻውን የክልል መስፈርት ሊሆን አይችልም፤ ከዘር አይወረስም፤ ከማህበራዊ ግንኙነት እንጅ::

"እየውልህ! የዘመኑ ሊቃውንት በዲሞክራሲ ሽፋን ይዘውልን የመጡት ፍልስፍና ቋንቋን መስፈርት በማድረግ አገርን መበታተን ነው:: እንደ ቡትቶ ጨርቅ ሊቦጫጭቁን ሸርጉድ እያሉ ናቸው::

"በድሉ ባገር ጉዳይ ላይ ብቻ እንዳስለቸሁህ ይገባኛል:: ከዚህ ውጭ የምዕፍልህ ነገር ስላጣሁ ነው:: ከየኔነሽና ከፅጌ ጋር ጥሩ ግንኙነት አለኝ:: በርግጥ የኔነሽ ከፅጌ እንዳልደርስ ደጋግማ አስጠንቅቃኛለች:: እኔ ግን ፅጌን የምተውበት አንጀት አላገኘሁም:: ፀባየ ሸጋ ወለላ ማርነች::

"በል በድሉ፣ ለኮሎኔል ዘርጋውና ለሻምበል አዱኛ ደቻሳ የጠበቀ ሰላምታ አቅርብልኝ:: ከባንዳ መኮንኖች በስተቀር ለመላው መኮንንም የከበረ ሰላምታ አድርስልኝ:: ባንዶችን ግን አሁንም ቢሆን ተዋጓቸው:: ባንዶች የታሪክ ጠላቶቻችን ናቸው::

"መልካም ተሃድሶ! ያንተው መ/አ ጎርፉ እንደሻው፣ አዲስ አበባ::"

ምእራፍ አስራ ስድስት

እነዚህ በልጎኞች አዩት ሲቀናጡ፣
አማራን እድኑት ብለው ትእዛዝ ሰጡ::

42

ሁሉም እንገቱን ደፍቶ ይቆዝማል:: የማይተክዝ፣ የማያዝን የለም:: እኔም ከቆዛሚዎቹ ቆዛሚ፣ ከተካዦቹ ተካዥ ሆኛለሁ:: ከፖለቲካው ትኩሳት ሌላ ኑሮውም ከብዶኛል:: ልወጣው አልቻልኩም::

ከደርግ የሰቆቃ አገዛዝ ማክተም በኋላ ሌላ ቅስም የሚሰብር፣ ጀርባ የሚያጎብጥ አገዛዝ ይመጣል ብሎ ማንም ዜጋ አልገመተም ነበር:: ግን መጣ፤ ያውም በጎሳ፣ በብሔር፣ በቋንቋ ከፋፍሎ የሚያፋልም::

ዛሬ አዲስ አበባ ውስጥ እያነጋገረ ያለው የበደኖ እልቂት፣ ያርባ ጉጉ ጭፍጨፋ ነው:: ህዝቡ በቁጣ ገንፍሏል:: በኢህአዲግ ላይ ቅንጣት እምነቱን አጥቷል:: በተለይም ያማራው ህዝብ ጠሩ የሚሰበቀው፣ ጎራዴው የሚሰላው፣ ጠመንጃው የሚወለወለው ለሱ እንደሆነ በውል ተገንዝቦታል:: አማራ የዘመኑ ታዳኝ አውሬ ሆኗል...

በየቀኑ ግን «በደርግ የተጨፈጨፉ ሰማዕታት» እየተባሉ አፅማቸው ተቆፍሮ እየወጣ ህዝቡን ያስለቅሱታል:: ጉድጓዶቹ ግን አፋቸውን ከፍተው አያድሩም፤ ያኑ ለሊት ይዳፈንባቸዋል:: እነዚህም አንድ ቀን በፈንታቸው አፅማቸው ወጥቶ ይለቀስላቸው ይሆናል:: የኢትዮጵያ ህዝብ መቼም ሲያለቅስ እንዲኖር ተፈርዶበታል...

የታሰረ አይፈታም፤ የተያዘ አይለቀቅም፤ ጥፍርፍር ያለ ጊዜ ሆኗል:: የጦላይ መኮንኖችም ወሬ ደብዛዝ እያለ መጥቷል:: የሻምበል በድሉ ጫኔ ደብዳቤ ገና ዛሬ ነው የደረሰኝ:: እጅግ ዘግይቶ ነው የዛፈልኝ:: ምን ያድርግ! የማጋለጡ ዘመቻ የደብዳቤ መዛፊያ ጊዜ አሳጥቶት ነው:: አገራቱስ ሁለመናዋ ተጋልጦ እርቃኗን ሆና ታሪካዊ ጠላቶቿ እየሳቁባት አይደል:: ያልታደለች እናት፤ ክብሯን በልጆቿ የተገፈፈች...

"ለውድ ጓደኛዬ ለሙቶ አለቃ ጎርፋ እንደሻው! ለጤናህ እንደምን አለህልኝ:: እኔ ከነሀጎስ ንዝንዝ በስተቀር በጣም ደህና ነኝ::

"ጎርፋ፣ የተሃድሶ ትምህርታችንን አጠናቀናል:: የቀረን ጊዜ በጣም አጭር ነው:: አንድ ዙር ግምገማ ካካሄድን በኋላ ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ነው:: እነ ሀጎስ ነግረውናል:: እንግዲህ ተቀላጥፈን ለመጨረስ የበቃነው ከነሀጎስ ጋር በመግባባታችን ነው:: መጨቃጨቁና መነታረኩ እርባና እንደሌለው ተረድተናል:: የመቶ አመቱ ታሪክም ከማስገረም አልፎ አስቆናል:: ኢትዮጵያም ብቸኛዋ አፍሪካዊት ቅኝ ገዢ ሀገር መሆኗን ነግረውናል:: ታዲያ መሳቅ ይነሰን? በእውነት ነው የምልህ በዚህ ይዞታቸው የሚቀፅሉ ከሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ መከራ ነው የወደቀበት...

"ጎርፋ፣ አጋጣሚ የነበሩ መከንኖች ባንዳ መባላቸው ቀርቶ ኮንደሞች ተብለዋል። እነሆንስ በነሱ ተጠቅመው ተጠቅመው ተጋላጮቹ ሲያበቁ ዘወር በሉ አሏቸው። በዚህስ እንጀታችንን እርሰውናል። ኮንዳንደቹ ከነሆንስ እግር ላይ ወድቀው በማልቀሳቸው አዲስ አበባ ከንመለስ ለኛ የሚታደል የርዳታ ስንዴ አለ አሉ፤ እሱን 'ትሸከማላችሁ' ብለው ቃል ገብተውላቸዋል። እንግዲህ ጎርፋ አንድ ምክር ልምክርህና ልሰናበትህ፦

"ሁለት ማፍቀር አደገኛ ነውና ከሁለት አንዷን መምረጥ ይኖርብሃል። ይህን ከነገርኩህ ይበቃሀል። ከለኔልና አዱኛ ሰላም ብለውሃል። ያንተንም ሰላምታ አድርሻለሁኝ። በል እስከምንገናኝ ድረስ በሰላም ያቆየን። ኢትዮጵያንም ከዘረኞችና ከከፋፋዮች እግዚአብሔር ይጠብቃት። ያንተው በድሉ ጫኔ፤ ጠላይ"

* * *

የበድሉን ደብዳቤ አንብቤ እንደጨረስኩ ወዲያውኑ ላንድየና ለመጨረሻ ጊዜ ፃፍኩለት።

"ለውድ ጓደኛዬ ለሻምበል በድሉ ጫኔ፣ ከተጋዛችሁበት በረሃ እንድትወጡ መልካም ምኞቴን ስገልፅልህ የኔንም ደህንነት ጨምሬ እየገለፅኩኝ ነው።

"በድሉ፣ የፃፍክልኝ ደብዳቤ ደርሶኛል። እውነትም ሆነ ውሸት፣ ታሪክም ሆነ ተረት፣ ነፍጠኛም ሆነ ትምክህተኛ፣ ከነሆንስ ጋር ተግባብታችሁ የተሃድሶ ትምህርታችሁን በመጨረሳችሁ እንኳን ደስ አላችሁ። ቱም ነገሩ ከታጎራችሁበት በረሃ የምትወጡበት ቀዳዳ መፈጠሩ እንጂ የታሪክን ነገርማ ተወው፤ ታሪክ ይፍረደው...

"የሙቶ አሙቱ ታሪክ ይልቅ ከዚህ አዲስ አበባ ሊቃውንትን እያወያየ ነው። ቢደንቅህ የሰስት ሺህ ዘመን ታሪካችን ወደ ሰባት ሺህ ከፍ ብሏል። ደግሞ የሙቶ አሙቱ ታሪክ በፕሮፓጋንዲስቶች የሚነፋ እንዳይመስልህ። በማስረጃ የተደገፈ ነው። የነሉሲ አፅም ሁሉ እያንጋገረ ነው። ወያኔዎች ማጥፊያው አጥሯቸዋል።

"ባለፈው ደብዳቤዬ እንደ ገለፅኩልህ ዛሬም አዲስ አበባ መደበኛ ስራ ስልፍ ነው። ዛሬስ የፈራሁት ሴቶችም ተሰልፈው 'ኧረ የወንድ ያለህ!' ያሉ እንደሆነ ብዬ ነው። ታዲያ በዚህ ሳምንት ውስጥ ከተካሄዱት ሰልፎች ሁሉ ደመቅ ያለውና የሽግግር መንግስቱም ከፍተኛ ትኩረት የሰጠው የምኒልክ ሀውልት እንዲፈርስ ብሎ የጠየቀውን ሰልፈኛ ነው።

"የዘንጀሮ ጎፈር ባጠለቁ የፈረሰኛ ሰልፈኞች አዲስ አበባ ተጥለቀለቀች። ሰልፉን የጠራውና ያቀናበረው ኦህዴድ-ኢህአዲግ የተባለው የፖለቲካ ድርጅት ነው ይባላል። ሰልፈኞቹ በፈረሶቻቸው ላይ ሆነው እየፎከሩና እየጨፈሩ የምኒልክን ሀውልት ክፉኛ ገላምጠውት አለፉ። ከመደረማመስ ያራዳው ጊዮርጊስ አዳነው። በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉትን ኦሮሞዎች ሰብስበው ነው መፈክር አሸክመው ያዞሯቸው።

"በማግስቱ ታዲያ ምን ተደረገ መሰለህ፤ የምኒልክ ሀውልት የብር ቀለም እንዲቀባ ተደረገ። ጅንኑ ምኒልክ ዛሬ ተንቆጥቁጦ ባንዲራውን ይዞ ተጀንኗል።

"አንዳንድ ፖለቲከኞች እንደሚሉት ከሆነ ኢህአዲግ በየቦታው የሚጭራቸው የጎሳ ግጭቶች ብልጭ እያሉ ድርግም በማለታቸው አንጀቱ ሳይቆስል አልቀረም ባይ ናቸው። እና የምኒልክ ሀውልት ይፍረስ መባሉ ሌላው ሙከራው ነው። ምክንያቱም ኦሮሞው አፈርሳለሁ ሲል አማራው አላስፈርስም ብሎ ይነሳል። በዚህ ወቅት አምባጓሮ መፈጠሩ ስለማይቀር ደም መፋሰስ ይከተላል። ከዚህ በኋላ ባማራውና በኦሮሞው መካከል የማይጠፋ እሳት ተቀጣጠለ ማለት ነው ይላሉ። ነገር ግን አማራው እንኳንስ አይፍረስ ብሎ ሊነሳ ይቅርና ለሰልፉም ቁም ነገር አልሰጠው። በዚህ ሲከሽፍ ደግሞ በሌላ መጡ፦

"በማግስቱ የብር ቀለም እንዲቀባ የተደረገው ኦሮሞው 'ይፍረስ እያልን እንዴት እንደገና ታስጌጡታላችሁ' ብሎ ረብሻ ያነሳል ተብሎ ተጠብቆ ነበር አሉ። ብቅም ያለ የለ። አየህ የህዝባችንን ጥንካሬ። ይኸ ሁሉ የታላቅነቱና ያስተዋይነቱ ውጤት ነው። ሴረኞች ሴራቸውን ታቅፈው ቀሩ።

"አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎች ደግሞ የሚሉት ከፖለቲከኞቹ አስተያየት የተለየ ነው። በዘመነ ደርግ 'አብዮት ልጇን ትበላለች' እየተባለ ኢትዮጵያ ልጆቿን እንደ እራስ ድመት ቆረጣጥማ የበላች ስለሆነ ፍዳዋ ገና ነው ባይ ናቸው። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ዛሬም ቢሆን የአብዮት ስም አይነሳ እንጂ ሌሊት ሌሊት የጠፋ አፈና አለ...

"በድሉ፣ የሰሞኑ ሌላው አዲስ ነገር ደግሞ ኢህዲን-ኢህአዲግ የተባለው የፖለቲካ ድርጅት በባህርዳር ላይ ጉባኤ ከፍቶ 'የማራው ብቸኛ ተጠሪ ድርጅት እኔ ነኝ' ብሎ ብቅ ብሏል። ዛሬ አዲስ አበባ ውስጥ ዋና የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኗል። አብዛኛው ህዝብ 'ሁሉም ነገር እቃቃ ጨዋታ እየሆነ ነው' በማለት ይስቃል። ፈዙ፣ ሽሙጡ ስጉድ ነው።

እኛ የምናውቀው አህያ በጭነት ጀረባው ተገጣጥቦ ወገቡ ሲደቅ፣
እንዲህ የደለበስ ያማረ አህያ አይተንም አናውቅ።

"እንደ ምታስታውስው በ83 ዓ.ም. በሰኔ 24 ኮንፈረንስ ኢህዲን ተወክሎ ነበር። አማራን ወክሎ ግን አልቀረበም፤ እራሱን እንጅ። እንዲያውም በወቅቱ አማራን የሚወክል ድርጅት ባለመቅረቡ የተነሳ 'ወደ ፊት እራሱን አደራጅቶ ይቀርባል' ተብሎ ነበር የታለፈው። ታዲያ ዛሬ ያቶ ኢህአዲግ ልጅ ኢህዲን ምን አሳሰበውና ነው 'ብቸኛ ተወካይ' ሆኖ የቀረበው? ይህ አድራጎቱ አማራዎችን አስቋቸዋል። 'ጌታ የሌላትን አህያ ሁሉ ይጭናታል' እያሉ የሚቆጩ ደግሞ ጥቂቶች አይደሉም። አንዳንዶቹ ደግሞ ባማራው ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ስላሳዛነው ለነፍሴ ብሎ ነው እያሉ ያሽሟጥጣሉ። የውስጥ አዋቂዎች እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ ኢህዲን ቀደም ሲል ፋኖ በነበረበት ወቅት ፋከራው 'ዘራፍ አማራ ገዳይ' ስለነበረ ለዚህ ማካካሻ ቢሆነኝ ብሎ ነው ይላሉ። ያማራ አዛውንቶች ደግሞ 'ዶሮን ሲቀጣጠቧት በመጫኛ ጣሏት' በማለት

አስተያየታቸውን በምሳሌ ይደመድማሉ:: የሚገርመው ደግሞ ይኸው ድርጅት ኢህአፓንም እወክላለሁ፤የዙፋኑ ወራሽ እኔ ነኝ ይላል::

ሶሌው ሶሉ ቀጥሮ ሲያስፎክር ሲያቅራራ፣ ሲያስጨፍር ሰምቼ፣
ጀግና አገኘሁ ብዬ ዘልዬ ልገባ እኔም ተሳስቼ::

"በዚህ በባህር ዳሩ ጉባኤ ላይ አዲስ የታሪክ ግኝትም ተከስቷል:: ከዚህ በፊት ስንት የታሪክ ሊቃውንት ተመራምረው ያልደረሱበት፣ እውቁ የጂኦግራፊ ምሁር ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም እንኳን 'አማራ የሚባል ዘረኛ ብሔር የለም:: ወደ ፊት መፍጠር ይቻል እንደሆነ እንጃ....' እያሉ ሲከራከሩ ብቸኛው ያማራ ተጠሪ ድርጅት ግን ሶስት ያማራ ዝርያዎች እንዳሉ በጉባኤው በይፋ አስታወቀ:: እነሱም:-

1ኛ. ጭቁኑ አማራ፣

2ኛ. ትምክህተኛ አማራ፣

3ኛ. ነፍጠኛ አማራ ናቸው:: እንግዲህ ኢህዴን-ኢህአዴግ የሚወክለው ብሄር ጭቁኑን አማራ ነው::

"ትምክህተኛ አማራ የተባለው ደግሞ ፕሮፌሰሩ፣ ደክተሩ፣ ባለማስተርሱና ትንሽ ነቃ ነቃ ያለውን ሁሉ ያጠቃልላል:: 'የትምክህተኞች ጎራ ይደረመሳል' እየተባለም መፈክር እየተስተጋባበት ነው:: 'ጎራ' የሚባለው የትምክህተኞች መሰብሰቢያ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መሆኑ ነው:: በቅርብ ቀን ወረራ ሳይካሄድበት አይቀርም ተብሎ ተፈርቷል::

"ነፍጠኛ አማራ ደግሞ ከቁጥር ሶስት ክልል ውጭ በሌሎች ክፍላተ ሀገር ተሰባጥሮ የሚኖረው ነው:: ይህ ብሔር 'መሬት ፍለጋ የሄደ ነው...' ተብሎ ቅስቀሳ የሚደረግበት ነው:: ወደፊት ተደራጅቶ እራሱን ከእልቂት ካልተከላከለ በስተቀር የቆንጨራ እራት ከመሆን አይድንም የሚሉ ብዙዎች ናቸው::

አርሲን ምነካው በስሜት ተነዳ፣
እህል ሳይቸግረው ገባ የስጋዳ::
በሀረርጌም በኩል ጨኸቱ በርክቷል፣
ሰው እየታፈሰ እስር ቤት ተከቷል፣
የሌላውን እንጃ አማራስ ተፈቷል::

"ሌላው ያዲስ አበባ አሳዛኝ ገፅታ የቀድሞ ጦር አባላት የጀግናና የቁስለኛ ሜዳያቸውን ዘርግተው ሲለምኑ ጉድ ያሰኘውን ያህል አሁን ደግሞ ዲግሪያቸውን እንጥፈው የሚለምኑ ወጣቶች መታየት ይዘዋል:: ዲሞክራሲ ቢትረፈረፍም ተምሮ ስራ የማግኘት ነገር የማይታሰብ ሆኗል:: በኬሚስትሪም ይመረቅ በባይኦሎጂ ምድብ ስራ 'ቤጌኦሎጂ' ሆኗል:: ዛሬ ሁሉም እየተዘጋጀ ያለው ለስራ ሳይሆን ስልቻውን ሰፍቶ ለልመና ነው:: ይልቅ ትልቅ ስጋት የፈጠረው ወደ ፊት ልመናም በጎሳ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ ነው:: እንግዲህ ይህን ሁሉ ስትመጡ ትደርሱበታላችሁ:: ያው እናንተም የጥይት ኮረጆችሁን ይዛችሁ ለቁራሽ ልመና መዘጋጀት ነው...

"ከሁለት አንዷን ምረጥ፤ ሁለት ማፍቀር አደገኛ ነው፤ ብለህ ላልከኝ የኔነሽም 'ወይ እኔን ወይ ዕጌን ምረጥ' ብላኝ ነበር:: እኔ ግን ሁለቱንም አልተው፤ ሁለቱንም በእኩል አፈቅራቸዋለሁ:: አንዷን አፍቅሬ ሌላዋን በግድ ጠልቻለሁ፤ ካንች አልደርስም የምልበት ሀሊና የለኝም:: ከሁለት እነሱው አንቅረው ይትፉኝ:: ያኔ ለመቁረጡ እውቅበታለሁ:: በተረፈ ግን የኔነሽንም ሆነ ዕጌን ከአቅሌ ማውጣት አልሻም:: የፈለገ ደግሞ እንደኔ ሲያፈቅራቸው ይችላል:: ለማንኛውም በዚህ ጉዳይ ላይ ስትመጣ እንመካከርበታለን::

"ከዚህ በተረፈ ከጠላይ መጥታችሁ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ለመቀላቀል ያብቃችሁ:: እነ ኮሎኔልንም 'እግዚአብሔር ያስፈታችሁ' በልልኝ:: እንግዲህ በቅርብ ቀን መምጣታችሁ ስለማይቀር ደብዳቤ አልፅፍልህም:: በል ቻው፤ ያንተው መ/አ ጎርፉ እንደሻው፤ ክልል 14፤ አዲስ አበባ::"

43

በንትዘትና በልዩ ልዩ ምክንያት የተጋለጡ መኮንኖች ተለይተው ሲቀሩ ታህሳስ ማለቂያ ላይ ሌሎቹ የጠላይ መኮንኖች አዲስ አበባ ገቡ:: የሞቱት ያሳዝናሉ እንጅ ያሉትስ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ተቀላቀሉ:: ጠላይ የቀሩትም ቢሆን ይዘገያሉ እንጂ የሚሆኑት ነገር የለም:: አንድ ቀን ከዘመዶቻቸው ጋር ይቀላቀላሉ:: እንጀት የሚበሉት ካፊር ጋር ተቀላቅለው የቀሩት ናቸው:: እንዲህ ሲያልፍ ቀን መ/አ ሀይለሚካኤል ሀይወቱን አሳለፈ:: ዛሬ የሱ ቤተሰቦች ሀዘንና ረሃብ እንደ እሳት ይጠብሳቸዋል:: ልጆቹ ቂም አርግዘው ቂም ነው የሚወልዱት:: ኢትዮጵያም የልጅ ጠላት አላጣችም፤ ለእድገትም አልታደለችም...

ኢትዮጵያ በየጊዜው በስልጣን ጥመኞች እጅ እየወደቀች ልጆቿ ያላግባብ ሲጨፈጨፉባት ኖረዋል:: ዛሬም እየተጨፈጨፉ ነው:: ማህፀኗ ሁል ጊዜ ቂም ፀንሶ በቀል እንደወለደ ነው:: ያልተባረከች አገር...

ከበድሉ ጫኔ ጋር አንድ ምሽት ተገናኝተን ድራፍት እየጠጣን በጥሩ ሁኔታ አሳለፍን:: ኮሎኔል ዘርጋውና ሻምበል አዱኛ ደቻሳንም አስታወስናቸዋል:: ስለ የኔነሽና ስለ ዕጌ ጉዳይም አንስተን ተጫውተናል::

"የኔነሽን ትተህ ዕጌን ብታፈቅር አይሻልህም?" አለኝ::

"ለምን?" አልኩት::

"የኔነሽ ሃጂ ናት" አለኝ::

"ለመሄድማ ዕጌንስ ምን የሚያግዳት ነገር አለ?"

"እሱስ ልክ ነህ::"

"ይልቅ ኢትዮጵያን ከጎሳ ደዌ ይገላግላት አትልም!" ስለው:-

"ይገላግላት! ይህን የዘር በሽታ ከምድረ ገፅዋ ያጥፋላት!" አለ::

"ልብ ያለው ልብ ይበል:: ልብ የሌለው ግን ቅሌቱን ታቅፎ ይቀራታል እንጃ. ኢትዮጵያ የምትሆነው ነገር የለም" ስለው:-

"ልክ ነው፤ እግዚአብሔር ይጠብቃታል!" አለኝ። ከዚያም "ለጤናችን" ብለን የድራፍት ብርጭቆዎቻችንን አንስተን በማጋጨት ተጎነጨን።

"እንዲያውቅ ጎርፉ! ያለፍነበትን ሂደት መለስ ብዬ ሳስበው ይደንቀኛል፤ እጣብቂኝ የበዛበት፤ ሰው በሰው ላይ ተራምዶ፤ ጓደኛውን አሳልፎ በመስጠት ራሱን ለማስነበት የተፍጨረጨረበት የከፋ ፈተና ጊዜ ነውኮ ያሳለፍነው" አለ በድሉ ተከዝ ብሎ።

"መቼም ከስነበትን የወደፊቱንም በጊዜው እናየዋለን፤ ተስፋ የማደርገው ግን ከኛ ውድቀት አዲሱ ትውልድ ትምህርት ያገኛል ብዬ ነው" ስለው ቀበል አደረገና፡-

"ከኛ ውድቀት ካልተማረማ እንደኛው ወይም በባሰ ሁኔታ ጊዜ ያስተምረዋል።" አለኝና ድራፍታችንን እየጨለጥን በየባእታችን ተጓዝን...



ካሁን ቀደም ያሳተማቸው መጻሕፍት:-
1. ዳር እስከዳር፣
2. ጥቁር ደም፣
3. ጥልፍልፍ።

ደራሲው መ/አ አንዳርጌ መስፍን

«... አገር እናት ነች፤ አገር ሚስት ነች፤ አገር ልጅ ነች፤ አገር ሀብት ነች፤ ሲያገኙ መደሰቻ፣ ሲያጡ መተከዣ፣ ሲሞቱ መቀበሪያ። ያለአገር ምንም ነገር የለም...»

«... ለመሆኑ የጎሳ መሪዎች ምን ያስቡ ይሆን? ሰው ወይስ ወንበር? አገር ወይስ መንደር? የትኛው ነው መቅደም ያለበት?...»

«... ሆዳም ሰው ከሆዱ ሌላ አገርም፣ ዘመድም የለው... በሆዱ ብቻ እየተገዛ ውርደትን ክብሩ አድርጎ ይኖራል!...»

«... እኔ ባባቴ ጎንደሬ፣ በናቴ ትግሬ ነኝ፤ ባለቤቴ ግማሽ ኦሮሞ፣ ግማሽ ደግሞ አደሬ ናት። የኛ ልጆች የየትኛው ብሔረሰብ አባል ሊሆኑ ነው?...

«... እንዲያው ይኸ ሠራዊት ሲመለመል ባፈሳ፣ ሲረሸን ባፈሳ፣ በርድ ሲወጣ በመንጋ፣ ሲሸሽ በጅምላ፣ በመጨረሻም እጅ ሲሰጥ እየተሻማ በጠቅላላ ሆነ!...»

ዋጋው 6.50